እያንዳንዱ የWashington ነዋሪ እንዲኖር፣ እንዲሠራ፣
መኪና እንዲነዳ እና እንዲበለጽግ መርዳት።

# የWASHINGTON
# የአሽከርካሪ መመሪያ







ለሁሉም አገልግሎቶች!

ስካን ያድርጉኝ

WASHINGTON STATE DEPARTMENT OF
LICENSING

dol.wa.gov

# መታወቂያዎ በአየር ማረፊያ የሚጠየቁ መስፈርቶችን ያሟላል?

# REAL ID







REAL ID መንጃ ፈቃዶች እና መታወቂያዎችለአገር ውስጥ የአየር ጉዞ ተቀባይነት እንዲያገኙወይም ወደ አንዳንድ የፌዴራል ተቋማት ውስጥ እንዲገቡ ለማስቻል የተወሰኑ የደህንነት ደረጃዎችን እንዲያሟሉ የሚጠይቅ ሕግ ነው። የተሻሳሉ ፍቃዶች እና መታወቂያዎች የREAL ID- መስፈቶችን ከሚያሟሉ በርካታ አማራጮች መካከል ናቸው።

የተሻሻሉ ፍቃዶች እና መታወቂያዎች REAL ID ተገዢነትን ከሚያሟሉ በርካታ አማራጮቭ መካከል ናቸው። የሚያስፈልጉዎትን ነገር ይዘዋል?

ተጨማሪ ለማወቅ QR ኮዱን ይቃኙ ወይም dol.wa.gov/real-id ይጎብኙ።




# ሁሉም ሰው ወደየቤቱ በሰላም ይገባል።




**ወደ ቦታ ከመድረስዎ በፊት እና ከደረሱ በኋላ 200 ጫማ ያህል ርቀት ወደ ጎን ዞር ይበሉ።**



**ከተለጠፈው የፍጥነት ገደብ በታች በሰዓት 10 ማይል ፍጥነት ያህል ይቀንሱ።**

## የመኪና አደጋዎች በአሜሪካ ውስጥ ላሉ ወጣት አሽከርካሪዎች ዋነኛ የሞት እና የአካል ጉዳት መንስኤዎች ናቸው።

# ሰዎች የግጭት አደጋዎችን ይወቁ

እድሜያቸው **16** እስከ **25** ለሆኑ

እርጥበታማ መንገዶች

**ልምድ አለመኖር**

የደህንነት ቀበቶ አለማሰር

**በምሽት መንዳት**

ፍጥነት | ድካም

**አደንዛዥ ዕጾች እና አልኮሆል**

ታዳጊ ተሳፋሪዎች

# ትኩረት ሳይሰጡ ማሽከርከር

- **በየአመቱ በአሜሪካ መንገዶች ላይ ስንት ሰዎች ይሞታሉ?**
- **የWashington በትራፊክ አደጋ የሚከሰት ሞት ግብ ምን ያህል መሆን አለበት?**

TARGET ZERO

Washington Driver Guide | 520-392 | እንግሊዝኛ (Amharic) | (N/6/25)

# ማውጫ

## እኛ Washington ነን

**መግቢያ**
ይዘቶች
እኩልነት ለሁሉም ደንበኞች
የእውቂያ መረጃ

## 1 | ፍቃዶች

**ለመንዳት መወሰን ..................1.0**

**የሚሰጥ የWA ቁጥር (WDL ቁጥር) ..................1.1**

**License Express ..................1.2**

**የፍቃድ መስጫ እና የተሽከርካሪ ጽህፈት ቤቶች ..................1.3**

**የWashington ስቴት ነዋሪዎች ..................1.4**

**አዲስ ነዋሪዎች ..................1.5**
18+ ዓመት የሆናቸው አዲስ ነዋሪዎች ..................1.5
አዲስ ነዋሪዎች፦ ከ16-17 አመት..................1.5
የእርስዎ ማንነት ..................1.5
መኖሪያ ቤት ለሌላቸው የሚደረግ ድጋፍ ..................1.5

**መታወቂያ እና መንጃ ፍቃዶች ..................1.6**

**REAL ID ..................1.7**

**የግል መንጃ ፍቃድ ስለማውጣት ..................1.8**
የመመሪያ ፍቃድ ..................1.8
የግል መንጃ ፍቃድ ስለማውጣት፦ ከ16 እስከ 17 እድሜ ..................1.8
የግል መንጃ ፍቃድ ስለማውጣት፦ እድሜ 18+..................1.8
መካከለኛ መንጃ ፍቃድ ..................1.8
የግብርና መንጃ ፍቃዶች ..................1.8
የቅድመ ማስጠንቀቂያ ደብዳቤዎች ..................1.8

**ጤና** ............ **1.9**
የአይን ምርመራ ............ 1.9
የአካል ክፍል ለጋሽ ............ 1.9
የህክምና ስያሜዎች ............ 1.9

**የድጋፍ እውቅናዎች** ............ **1.10**

**በእድሜ ገፋ ያሉ አሽከርካሪዎች** ............ **1.11**

**የግል መንጃ ፍቃድ ፈተናዎች** ............ **1.12**
ሁለት ፈተናዎች ............ 1.12
ፈተናዎቹን መፈተን ............ 1.12

**የአሽከርካሪዎች ስልጠና ትምህርት** ............ **1.13**
ከ18 በላይ ............ 1.13

**የአዲስ አሽከርካሪዎች አሳዳጊዎችን የሚመለከት** ............ **1.14**

**መንጃ ፍቃድዎን ማቆየት** ............ **1.15**
መንጃ ፈቃድዎን መተካት ............ 1.15
መንጃ ፈቃድዎን ማሳደስ ............ 1.15
ጊዜው ያለፈበት መንጃ ፍቃድ ............ 1.15
የመንዳት መብቶችዎን ማጣት ............ 1.15
የአልኮል፣ የአደንዛዥ ዕጽ እና የጦር መሳርያዎች ጥሰቶች ............ 1.15
በተጽዕኖ ስር ሆነው መንዳት (DUI) ............ 1.15
መጠጥ/ካናቢስ ጥቅም ላይ የዋለበትን ማስቀመጫ
የመያዝ ህግ ............ 1.15

**ተጨማሪ አገልግሎቶች** ............ **1.16**
የአድራሻ ወይም የስም ለውጥ ............ 1.16
የመራጮች ምዝገባ ............ 1.16
አስገዳጅ የወታደራዊ አገልግሎት ምዝገባ ............ 1.16
የመንትዮች ምዝገባ ............ 1.16

# 2 | ተሽከርካሪዎች

**የተሽከርካሪዎች አገልግሎት ........................................................2.0**
የባለቤትነት የምስክር ወረቀት (የመብት ማረጋገጫ) ..............................2.0
ምዝገባ ........................................................................................2.0
የተሽከርካሪ አድራሻ..........................................................................2.0

**የሽያጭ ሪፖርት ...............................................................................2.1**
ከግለሰብ ወደ ግለሰብ ............................................................................2.1
ከሻጭ ድርጅት ወደ ግለሰብ ........................................................................2.1

**የተሽከርካሪ ታርጋ ሰሌዳዎች .......................................................2.2**

**መድን ያስፈልጋል .........................................................................2.3**

**ተሽከርካሪዎን ይወቁ .....................................................................2.4**
ተግባራት ........................................................................................2.4
ማስተካከያዎች ..................................................................................2.4
የተሽከርካሪ ደህንነት ቴክኖሎጂ .............................................................2.4

**የተሽከርካሪ ጥገና ........................................................................2.5**
ጎማዎች ..........................................................................................2.5
የመስታወት ወለሎች ...........................................................................2.5
የግንባር መብራቶች ..........................................................................2.5
የፍሬን መብራቶች ............................................................................2.5
የፍሬቻ መብራቶች (አቅጣጫን የሚያመለክቱ መብራቶች) ..........................2.5
የእጅ ምልክቶች ...............................................................................2.5
የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያ መብራቶች ....................................................2.5
የአሽከርካሪ ወንበር ..........................................................................2.5

**የተሳፋሪ ደህንነት ጥበቃ ...............................................................2.6**
የደህንነት ቀበቶዎች እና የተሳፋሪ ደህንነት ጥበቃ ....................................2.6
የህጻናት መቀመጫዎች .........................................................................2.6
ኤርባጎች .........................................................................................2.6

**መሪ ማሽከርከር ............................................................................2.7**
ከእጅ-ወደ-እጅ መሪን ማሽከርከር ..........................................................2.7

አንድ እጅ ከሌላኛው እጅ ከላይ በማድረግ መሪን ማሽከርከር .............2.7
በአንድ እጅ ብቻ መሪን ማሽከርከር .............2.7

**ፍሬን መያዝ .............2.8**
የፍሬን ግፊት .............2.8
የማይቆልፉ የፍሬን ሲስተሞች .............2.8

**መፍጠን .............2.9**

**ሚዛኑ የጠበቀ ክብደት .............2.10**
ተሽከርካሪ ወደ ፊት/ኋላ ማዘንበል .............2.10
ተሽከርካሪ ወደ ጎን ማዘንበል .............2.10
ተሽከርካሪ በቁመቱ ዙሪያ መዞር .............2.10

**የተሽከርካሪ ማመሳከሪያ ነጥቦች .............2.11**

**ለእርስዎ የማይታዩ ቦታዎች .............2.12**

**ለሌሎች ተሽከርካሪዎች የማይታዩ ቦታዎች .............2.13**
በአይን መቃኘት .............2.13

**ከመሄድዎ በፊት .............2.13**

## 3 | አሽከርካሪዎች

**እርስዎ ተሽከርካሪ ሲነዱ .............3.0**
ጤንነት .............3.0
አካላዊ ጤንነት .............3.0
እይታ .............3.0
በምሽት ማየት .............3.0
መስማት .............3.0

**በተዳከመ ሁኔታ መንዳት .............3.1**
አልኮል እና መንዳት .............3.1
ካናቢስ እና መንዳት .............3.1
መድሃኒቶች እና መንዳት .............3.1
ብዙ መድሃኒቶችን መጠቀም እና መንዳት .............3.1
በድካም እና በእንቅልፍ ስሜት ውስጥ ሆነው መንዳት .............3.1

የአእምሮ ጤንነት ....... 3.1
ግልፍተኛ ማሽከርከር ....... 3.1
መሽቀዳደም እና የመንገድ ላይ ትዕይንቶች ....... 3.1
በቁጣ ስሜት ማሽከርከር ....... 3.1
በቁጣ ስሜት እያሽከረከሩ ከሆነ ....... 3.1
በቁጣ ስሜት የሚያሽከረክር ሰው ካጋጠመዎት ....... 3.1
በቁጣ ስሜት የሚያሽከረክር ሰውን ሪፖርት ማድረግ ....... 3.1

**በመንገድ ላይ በመረጃ ላይ የተመሰረቱ ውሳኔዎች መወሰን ....... 3.2**
በመንገድ ላይ በመረጃ ላይ የተመሰረቱ ውሳኔዎች
የመወሰን አስፈላጊነት ....... 3.2
ጥሩ ውሳኔዎችን መወሰን ....... 3.2

**መንገድ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፍታት ....... 3.3**

**ትኩረት የጎደለው ማሽከርከርን ማስወገድ ....... 3.4**
የWashington ትኩረት የጎደለው ማሽከርከር ሕጎች ....... 3.4

**ብልህ አሽከርካሪዎች ....... 3.5**
ትኩረት ይስጡ ....... 3.5
በእይታ መፈለግ እና መቃኘት ....... 3.5

**አክብሮት እና ሃላፊነት ....... 3.6**
የትራፊክ ማስጠንቀቂያዎች ....... 3.6
ቆሻሻ ....... 3.6
አካባቢ ....... 3.6
ራስን መገምገም ....... 3.6

## 4 | መንገዶች

**ንቃት እና ትብብር ....... 4.0**

**ከሰዎች ጋር መጋራት ....... 4.1**

**ከትምህርት ቤት አውቶቡሶች ጋር መጋራት ....... 4.2**
ከአውቶቡሶች ጀርባ ሲሆኑ ....... 4.2
ከአውቶቡሶች ፊት ሲሆኑ....... 4.2

**ከህዝብ ማመላለሻ አውቶቡሶች ጋር መጋራት ....... 4.3**

**ከትላልቅ ተሽከርካሪዎች ጋር መጋራት .................................. 4.4**
የበረዶ ማረሻዎች ..................................................................4.4

**ከሞተር ብስክሌቶች ጋር መጋራት .................................. 4.5**
መከተል ..................................................................4.5
የመንገድ መስመሮች ..................................................................4.5
መታጠፍ ..................................................................4.5
የመንገድ ወለል ..................................................................4.5
መብራቶች ..................................................................4.5

**ከብስክሌተኞች ጋር መጋራት .................................. 4.6**
አጠቃላይ መምርያ ..................................................................4.6
ብስክሌተኛን ማለፍ ..................................................................4.6
የብስክሌተኞች የመንገድ መስመር ..................................................................4.6

**መንገድን ከባቡሮች ጋር መጋራት .................................. 4.7**
አስፈላጊ የደህንነት ማሳሰቢያዎች ..................................................................4.7
ለእርዳታ መቼ እንደሚደውሉ ..................................................................4.7
ቀላል የባቡር ሃዲድ ..................................................................4.7

**ከግብርና ተሽከርካሪዎች ጋር መጋራት .................................. 4.8**

**ከአደጋ ጊዜ ተሽከርካሪዎች ጋር መጋራት .................................. 4.9**

## የመንገድ ህጎች

**የትራፊክ ህጎች .................................. 4.10**
አጠቃላይ የመንዳት መምርያ ..................................................................4.10
የትራፊክ ቁጥጥር መሳሪያዎች ..................................................................4.10
የተበላሹ መብራቶች ወይም ምልክቶች ..................................................................4.10

**የትራፊክ መብራት ምልክቶች .................................. 4.11**
የፍጥነት መንገድ መግቢያ መቆጣጠሪያ መብራቶች ..................................................................4.11

**ምልክቶች .................................. 4.12**
የተለመዱ ምልክቶች ..................................................................4.12
የስራ ቀጠና ምልክቶች ..................................................................4.12
የአገልግሎት ምልክቶች ..................................................................4.12

የመዝናኛ ምልክቶች ........ 4.12
የመዳረሻ ምልክቶች ........ 4.12
ሌሎች የትራፊክ ምልክቶች ........ 4.12

**የተለመዱ መገናኛ/መስቀለኛ መንገዶች ........ 4.13**

**መታጠፍ ........ 4.14**
U-መታጠፎች ........ 4.14

**ሌላ አይነት መገናኛ/መስቀለኛ መንገዶች ........ 4.15**
አደባባዮች ........ 4.15
የሚለያዩ የአልማዝ መገናኛዎች ........ 4.15
የትራፊክ መቆጣጠርያ መሳርያዎች የሌለው መገናኛ/መስቀለኛ መንገድ ........ 4.15

**የመንገድ ላይ ምልክቶች ........ 4.16**
የመንገድ መስመሮች ........ 4.16
HOV / ካርፑል ........ 4.16
የሚቀያየሩ የትራፊክ መስመሮች ........ 4.16
የተመደቡ የመንገድ መስመሮች ........ 4.16
የሚከፈልባቸው የመንገድ መስመሮች ........ 4.16
ሌላ የመንገድ ላይ ምልክቶች ........ 4.16

**ቀጠናዎች ........ 4.17**
የትምህርት ቤት ቀጠና ........ 4.17
የስራ ቀጠና ........ 4.17
የአደጋ ጊዜ ቀጠና ........ 4.17

**መኪና ማቆሚያ ........ 4.18**
አጠቃላይ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ህጎች ........ 4.18
ቀጥ ያለ እና አንግል ያለው የተሽከርካሪ ማቆሚያ ........ 4.18
በትይዩ ማቆም ........ 4.18
ኮረብታማ ቦታ ላይ ተሽከርካሪ ማቆም ........ 4.18
የተያዘ የአካል ጉዳተኞች መኪና ማቆሚያ ........ 4.18
የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ሃይል መሙያ ጣብያ መኪና ማቆሚያ ........ 4.18

**ማጓጓዝ ........ 4.19**
መጎተት ........ 4.19

ጭነትዎን ደህንነቱን ይጠብቁ ....................................................................4.19
እንስሳቶች ....................................................................................................4.19

**ባህርን የሚመለከት .................................................................4.20**
የማጓጓዣ ጀልባዎች ............................................................................................4.20
የባህር ዳርቻዎች ................................................................................................4.20

## 5 | ስጋቶች

**የመንዳት አደጋዎች ......................................................................5.0**
የስጋት ግንዛቤ ....................................................................................................5.0
የአደጋ ግንዛቤ ....................................................................................................5.0
ሁኔታዊ ግንዛቤ ..................................................................................................5.0
አደጋን መቆጣጠር ...............................................................................................5.0

**ፍጥነት .........................................................................................5.1**
ከልክ ያለፉ ከፍተኛ ፍጥነቶች ...........................................................................5.1
የፍጥነት ገደቦች ..................................................................................................5.1
ለሁኔታዎች ፍጥነትን ማስተካከል .....................................................................5.1

**ቦታ .............................................................................................5.2**

**ወደ ትራፊክ ፍሰት መቀላልቀል (Merging) ..............................5.3**
ወደ አነስ ያለ የመንገድ መስመሮች መግባት .....................................................5.3

**ጊዜ ...............................................................................................5.4**
ሰከንዶችን ይቁጠሩ ..........................................................................................5.4
እየተቃረቡ ካሉ ተሽከርካሪዎች ፊት መታጠፍ ...............................................5.4

**ትኩረት ..........................................................................................5.5**
ትኩረት መስጠት .................................................................................................5.5
የእይታ መስክ .....................................................................................................5.5
የጉዞ መንገድ .....................................................................................................5.5
የእይታ መስመር ..................................................................................................5.5
መረጃ መሰብሰብ .................................................................................................5.5

**የመንገድ እና የመንዳት ሁኔታዎች ..............................................5.6**
በምሽት መንዳት ................................................................................................5.6
ኩርባዎች ..........................................................................................................5.6

የሚያንሸራትቱ መንገዶች ..... 5.6
መንሸራተት ..... 5.6
በውሃ ምክንያት የጎማዎች መላላት ..... 5.6

**የተሽከርካሪ ብልሽቶች ..... 5.7**
ጎማዎች ..... 5.7
ኃይል ..... 5.7
የግንባር መብራቶች ..... 5.7
ማፍጠኛ ..... 5.7

**ስጋቶችን ማሳወቅ ..... 5.8**

**ግጭቶች ..... 5.9**
ተሽከርካሪን ማጋጨት ..... 5.9
ግጭትን ሪፖርት ማድረግ ..... 5.9
ጉዳትን ሪፖርት ማድረግ ..... 5.9
911 መደወል ..... 5.9
የሀይል መስመሮች ጋር ስለመገናኘት ..... 5.9
ግጭትን መመስከር ..... 5.9
የአደጋ ጊዜ መሳሪያ ..... 5.9

**ህግ ማስከበር ..... 5.10**
የህግ አስከባሪዎች ሲያስቆሙዎት ..... 5.10
የቅጣት ትኬት ስለመቀበል ..... 5.10

## ምንጮች

**ማጠቃለያ**
ሙዳየ ቃላት
ተደራሽነት እና መስተንግዶዎች
ማስተባበያ

# እኛ Washington ነን

ይህ መምሪያ የሚከተሉትን የWashington የጋራ እሴቶችን የሚያንጸባርቅ ነው፡፡

- የመንገድ ሕጎችን በመከተል ራሳችንን እና ሌሎችን እንጠብቃለን፡፡
- ለአደጋ ተጋላጭ ለሆኑ የመንገድ ተጠቃሚዎች እንጠነቀቅላቸዋለን፡፡
- ተሽከርካሪ በምንነዳበት ወቅት ትኩረት የምንሰጥ፣ ሆን ብለን የምናደርግ እና ማገናዘብ የምንችል ነን፡፡
- ሁሉም በደህና ወደ መድረሻቸው እንዲደርሱ የምንሻ ነን፡፡



## ይዘቶች

የWashington ግዛት Department of Licensing (DOL) ይፋዊ የWashington ግዛት የአሽከርካሪ መመሪያ ያዘጋጃል፡፡ ይህ መምርያ ብዙ የWashington ህጎችን ያወሳል፤ ከዚህም በተጨማሪም በህጎች ውስጥ ላይገኙ የሚችሉ የደህንነት ምክሮችን ይሰጣል፡፡ ሁሉም መረጃዎች በሚታተሙበት ወቅት በተቻለ መጠን ትክክለኛ ናቸው፡፡ ሆኖም ግን መመሪያው በWashington ህግ አውጪ አካል የተደረጉትን የቅርብ ጊዜ ለውጦች ላያንጸባርቅ ይችላል፡፡ የዚህን መምርያ የቅርብ ጊዜውን ዕትም በDOL ደረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይችላሉ፡ dol.wa.gov፡፡

## ፍትሃዊነት ለሁሉም ደንበኞች

Department of Licensing (DOL) የእኛን እሴቶች ማለትም ብዝሃነት፣ ፍትሃዊነት፣ አካታችነት፣ እምነት እንዲሁም አክብሮትን በመጠቀም የአብሮነት ባህልን ለመገንባት ቁርጠኛ ነው። በተቻለ መጠን፣ ለደንበኞቻችን ፍትሃዊ ተደራሽነት እናቀርባለን እንዲሁም ዕንቅፋቶችን እናስወግዳለን። ተቋሞቻችንን እና አገልግሎቶቻችንን ለመጠቀም ለሚፈልጉ ደንበኞች ጥያቄ በሚያቀርቡበት ወቅት ተገቢ የሆነ መስተንግዶ ሁሉ እንሰጣለን። ዋናው ቋንቋቸው እንግሊዝኛ ላልሆኑ ደንበኞች የቋንቋ አገልግሎቶችን እናቀርባለን። DOL የPEAR (Pro-Equity Anti-Racism፣ የፍታሃዊነት እና ጸረ-ዘረኝነት) መርሆችን ይተገብራል። ኤጀንሲው ለማህበረሰቡ ግብረመልስ ትኩረት ሰጥቶ ምላሽ የሚሰጥ የአገልግሎት አከባቢን ለመፍጠር የሚሰሩ የማህበርሰብ አጋሮች፣ ሰራተኞች እና መሪዎች ያሉት የPEAR ቡድን አለው። ስለመስተንግዶዎች እና ተደራሽነት ተጨማሪ መርጃ ለማግኘት እባክዎን የመምርያውን የመጨረሻ ገጽ ይመልከቱ።

## የእውቂያ መረጃ | DOL.WA.GOV



**የመንጃ ፈቃድ የደንበኞች አገልግሎት:-**
360-902-3900

**የተሽከርካሪ ፈቃድ አሰጣጥ የደንበኞች አገልግሎት:-**
360-902-3770

Facebook.com/WashingtonDOL

Instagram.com/wa_licensing

LinkedIn.com/company/Washington-state-department-of-licensing

Threads.net/@wa_licensing

X.com/WA_DOL

Youtube.com/WALicensing


1
ምዕራፍ /
ፍቃዶች
SPEED
LIMIT
25

አሽከርካሪ መሆን ልዩ መብትም ኃላፊነትም ነው። ለአብዛኛው የህይወት ዘመንዎ ከእርስዎ ጋር የሚዘልቅ ነገር ነው። የመንዳት እውቀትዎን እና ችሎታዎን ለማዳበር በደንብ ጊዜ ይውሰዱ። ጤናማ የሆኑ ልምዶችን እንዲያዳብሩ እና ለቀጣይ የመንዳት ህይወትዎ ዘላቂ የሆነ መሰረት እንዲኖርዎት ይረዱዎታል።

## 1.1 | የሚሰጥ የWA ቁጥር WDL (WASHINGTON DRIVER LICENSE NUMBER, የዋሽንግተን የመንጃ ፍቃድ ቁጥር)

ሁሉም የWashington መንጃ ፈቃዶች፣ ፈቃዶች እና መታወቂያ ካርዶች የሚሰጣቸው የWashington ቁጥር ይኖራቸዋል። ይህ ቁጥር ለእርስዎ ብቻ የሚሰጥ ነው። አብዛኛውን ጊዜ የሚጀምረው WDL (Washington Driver License number, የዋሽንግተን የመንጃ ፍቃድ ቁጥር) በሚሉ ፊደላት ነው።

## 1.2 | LICENSE EXPRESS

የWDL ቁጥር ከሌለዎት ከመንጃ ፈቃድ መስጫ ጽ/ቤት (driver licensing office) ወይም በLicense Express ላይ አዲስ የደንበኛ መለያ በመፍጠር ማግኘት ይችላሉ። License Express በርካታ የDOL አገልግሎቶችን ማግኘት የሚችሉበት ደህንነቱ የተጠበቀ ድረ-ገጽ ነው። የLicense Express አገናኝ dol.wa.gov መነሻ ገጽ ላይ ማግኘት ይችላሉ። በቀላሉ በሚያስታውሱት የተጠቃሚ ስም እና የይለፍ ቃል ይመዝገቡ። አዲስ አሽከርካሪዎች የራሳቸውን መለያ መክፈት አለባቸው። ለራስዎ አገልግሎቶች የሌላ ሰው መለያ በመጠቀም አገልግሎቶችን ማግኘት አይችሉም። መለያው የእርስዎ መሆን አለበት።

**በLicense Express ውስጥ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፦**

- በመንጃ ፈቃድ መስጫ ጽህፈት ቤት ቀጠሮ ማስያዝ።
- ለተማሪ ፈቃድ አስቀድመው ማመልከት።
- የመንዳት ክህሎት መመዘኛ ፈተናዎን ቀጠሮ ማስያዝ።
- መንጃ ፈቃድዎን ማሳደስ።
- የተሽከርካሪዎን መርጃዎች ማስተዳደር።
- አድራሻዎን ማዘመን።

WDL ቁጥርዎን የማያስታውሱ ከሆነ ወይም ስለ License Express መለያዎ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ለDOL የአሽከርካሪዎች ፍቃድ ሰጪ ጽህፈት ቤት የደንበኞች አገልግሎት በ 360-902-3900 ይደውሉ።

## 1.3 | የፈቃድ መስጫ እና የተሽከርካሪ ጽህፈት ቤቶች

በመንጃ ፈቃድ መስጫ ጽህፈት ቤቶች የሚሰሩ ሰራተኞች መንጃ ፍቃድዎን ወይም መታወቂያ ካርድዎን እንዲያገኙ ይረዱዎታል። የተሽከርካሪ ፍቃድ አሰጣጥ እና ምዝገባ የሚመለከት መረጃ ለማግኘት የተሽከርካሪ ፍቃድ መስጫ ጽህፈት ቤትን (vehicle licensing office) ይጎብኙ። የሚፈልጉትን አገልግሎት ለማግኘት ትክክለኛውን ጽህፈት ቤት ማነጋገርዎን ያረጋግጡ።




## 1.4 | የWASHINGTON ግዛት ነዋሪዎች

ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ትክክል ከሆነ የWashington ነዋሪ ነዎት ማለት ነው፦

- በWashington የግል መኖሪያ ቤት ካለዎት።
- Washington ውስጥ ለመምረጥ ከተመዘገቡ።
- ለፌደራል ወይም ለክልል ግብሮች የWashington አድራሻ የሚጠቀሙ ከሆነ።
- ከWashington የህዝብ ድጋፍ ፕሮግራሞች ከአንዱ ጥቅማ ጥቅም የሚያገኙ ከሆነ።
- በዚህ ግዛት ውስጥ በሚገኝ ትምህርት ቤት እየተማሩ እና እንደ የWashington ነዋሪ ክፍያ እየከፈሉ ከሆነ ወይም በዚህ ግዛት ውስጥ በሚገኝ የህዝብ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማር ልጅ ካለዎት።
- ከየትኛውም ንብረት ጋር በቋሚነት ባልተያያዘ ተንቀሳቃሽ ቤት ወይም መርከብ ውስጥ ከዚህ ቀደም በWashington ይኖሩ የነበረ እና በማንኛውም ሌላ ግዛት ውስጥ ቋሚ መኖሪያ ከሌለዎት።

# 1.5 | አዲስ ነዋሪዎች




## 18+ ዓመት የሆናቸው አዲስ ነዋሪዎች

በሌላ ግዛት መንጃ ፍቃድ ያላቸው አዲስ ነዋሪዎች የWashington ግዛት መንጃ ፍቃድ ለማውጣት 30 ቀናት አላቸው። ከሌላ ግዛት ያገኙት መንጃ ፍቃድ ጊዜው ያለፈበት ከሆነ፣ የWashington ግዛት መንጃ ፍቃድ ከማውጣትዎ በፊት ሁለቱንም ማለትም የእውቀት መመዘኛ ፈተና እና የክህሎት መመዘኛ ፈተና ማለፍ ይኖርብዎታል። አንዳንድ ፈቃዶች ፈተናዎችን እንደገና መፈተን ሳይኖርብዎት ሊተላለፉ ይችላሉ። እርስዎን ስለሚመለከቱ ፈተናዎች መረጃ ለማግኘት dol.wa.gov ድረ ጽ ላይ ገብተው የአሽከርካሪዎች **training (ስልጠና)** እና **testing (ፈተና)** ብለው ይፈልጉ።

## አዲስ ነዋሪዎች፡- ከ16 እስከ 17 ዓመት የሆናቸው

ዕድሜዎ ከ18 ዓመት በታች ከሆነ እና መንጃ ፈቃድዎ የሌላ ግዛት ከሆነ፣ ለWashington መካከለኛ መንጃ ፈቃድ (Intermediate Driver License) ማመልከት ይኖርብዎታል። DOL ከሌላ ግዛት ያገኙትን የአሽከርካሪ ትምህርት ማረጋገጥ እና ቢያንስ ለ6 ወራት ያህል የተማሪ ፈቃድ እንደነበርዎት ማረጋገጥ ይኖርበታል። የአሽከርካሪ ስልጠና ኮርስዎን ወደ Washington ስለማዛዋወር ጥያቄዎች ካሉዎት እባክዎን ለአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ፕሮግራም tse@dol.wa.gov ላይ ኢሜይል ያድርጉ።

## የእርስዎ ማንነት

የተማሪ ፈቃድ፣ መንጃ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ካርድ ለማግኘት የእርስዎን ማንነት የሚያረጋግጡ ሰነዶችን ማቅረብ ይኖርብዎታል።

- የሚያስፈልግዎትን የሰነድ አይነት ለማወቅ dol.wa.gov ድረ-ገጽ ላይ **identification requirements brochure (የማንነት መስፈርቶች ብሮሹር)** ብለው ይፈልጉ።
- ሁሉንም አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ዋና ቅጂዎች ይዘው ወደ የመንጃ ፈቃድ መስጫ ጽህፈት ቤት ይምጡ።

## አገልግሎቶች

- የተሻሻለውን ጨምሮ ለመጀመርያ ግዜ የWashington መንጃ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ማውጣት
- የሌላ ግዛት ዝውውሮች
- የመንጃ ፈቃድ፣ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ካርድን ማሳደስ
- የአሽከርካሪ መዝገብ
- መንጃ ፍቃዶችን መልሶ አገልግሎት ላይ የማዋል ደብዳቤዎች
- ማንነትን ለማረጋገጥ የሚደረግ የሰነድ ማጣራት




## መኖሪያ ቤት ለሌላቸው የሚደርግ ድጋፍ

የመኖሪያ ቤት እጦት እያጋጠመዎ ከሆነ ያለ ምንም ወጪ መታወቂያ ወይም በቅናሽ ክፍያ መታወቂያ ለማግኘት ብቁ ነዎት። የመንግስት እርዳታ የሚቀበሉ ሰዎችም በቅናሽ ዋጋ መታወቂያ ካርድ ማግኘት ይችላሉ። እርዳታ ለማግኘት በአከባቢዎ የሚገኝ የDSHS (Department of Social and Health Services፣ የማህበራዊ እና የጤና አገልግሎቶች መምርያ) የማህበረሰብ አገልግሎት ጽህፈት ቤትን ያነጋግሩ። በአቅራቢያዎ ያሉ አገልግሎቶችን ለማግኘት ወደ dshs.wa.gov ድረ-ገጽ በመሄድ የጽህፈት ቤት ማግኛውን ይጠቀሙ።

# መደበኛ መንጃ ፍቃድ እና መታወቂያ




- ✔ መታወቂያ
- ✔ የሞተር ተሽከርካሪን ማሽከርከር (በመንጃ ፈቃድ ብቻ)
- ✘ የአገር ውስጥ የአየር ጉዞ
- ✘ ዓለም አቀፍ የአየር ጉዞ
- ✘ በመሬት ወይም በባህር ዓለም አቀፍ ደንበር ማቋረጥ
- ✘ የፌደራል ተቋማትን ለመድረስ
- ✘ Real ID መስፈርቶችን ማሟላት

# የተሻሻለ የመንጃ ፈቃድ እና መታወቂያ




- ✔ መታወቂያ
- ✔ የሞተር ተሽከርካሪን ማሽከርከር (በመንጃ ፈቃድ ብቻ)
- ✔ የአገር ውስጥ የአየር ጉዞ
- ✘ ዓለም አቀፍ የአየር ጉዞ
- ✔ በመሬት ወይም በባህር ዓለም አቀፍ ደንበር ማቋረጥ (ካናዳ፣ ሜክሲኮ፣ ካረቢያን)
- ✔ የፌደራል ተቋማትን ለመድረስ
- ✔ REAL ID መስፈርቶችን ማሟላት

## 1.7 | REAL ID

REAL ID ሕግ እንጂ መታወቂያ ካርዱን ማለት አይደለም።

የተሻሻለ መንጃ ፍቃድ (Enhanced driver license) ወይም መታወቂያ የREAL ID መስፈርቶችን ከሚያሟሉ በርካታ አማራጮች መካከል ናቸው። መደበኛ መንጃ ፍቃዶች ከአሁን በኋላ ለአየር ማረፊያ የደህንነት ኬላዎችን ለማለፍ፣ የአሜሪካ ድንበር ማቋረጫዎች ለማለፍ ወይም ደህንነታቸው ወደ የተጠበቁ የፌደራል ህንጻዎች ውስጥ ለመግባት ተቀባይነት ያለው የመታወቂያ ዓይነት አይሆንም።

የመረጃ ቪድዮዎችን ለመመልከት፣ የትኛው የመታወቂያ ዓይነት እንደሚያስፈልግዎ ለመወሰን ፈተና ለመውሰድ እና ስለ REAL ID ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት REALIDwa.com ይጎብኙ።






## 1.8 | የግል መንጃ ፈቃድ ማውጣት

### የተማሪ ፈቃድ

ለተማሪ ፈቃድ ከማመልከትዎ በፊት የWDL ቁጥር ሊኖርዎት ይገባል።

**ለአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ ኮርስ እየተመዘገቡ ከሆነ**

ለፈቃድዎ ከ15 ዓመትዎ ጀምረው ማመልከት ይችላሉ። ኮርስዎ ከመጀመሩ በፊት ከ1 እስከ 10 ቀናት ውስጥ በመንጃ ፈቃድ መስጫ ጽህፈት ቤት ወይም በበይነመረብ ላይ ያመልክቱ። ለመመዝገብ የWDL ቁጥርዎን ለአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤትዎ ለመስጠት ዝግጁ ይሁኑ።

**ለአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ ኮርስ የማይመዘገቡ ከሆነ**

የእውቀት መመዘኛ ፈተናውን 15½ ከሞላዎት በኋላ መውሰድ ይችላሉ። ፈተናውን ካለፉ በኋላ ፈቃድዎን ያገኛሉ። ሆኖም ግን፣ የክህሎት መመዘኛ ፈተናውን ለመውሰድ እና መንጃ ፈቃድዎን ለማግኘት 18 ዓመት እስኪሞላዎት ድረስ መጠበቅ ይኖርብዎታል።

ፈቃድዎ ለ1 አመት የሚሰራ ነው (በክፍያ መታደስ ይችላል)። የእውቀት መመዘኛ ፈተና ውጤትዎ ለ2 ዓመታት ያገለግላል። የክህሎት መመዘኛ ፈተናውን ለመውሰድ ረጅም ጊዜ ከቆዩ የእውቀት መመዘኛ ፈተናውን እንደገና መውሰድ ሊኖርብዎ ይችላል።

ለWashington ነዋሪዎች የተለያዩ የመታወቂያ ዓይነቶች፣ ፈቃዶች እና ድጋፎች አሉ።

## የግል መንጃ ፍቃድ ማግኘት፦እድሜ ከ16 እስከ 17

**የመጀመርያ መንጃ ፈቃድዎን ለማውጣት የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፦**

- ቢያንስ ለ6 ወራት የቆየ የተማሪ ፈቃድ ሊኖርዎ ይገባል።
- ቢያንስ 16 ዓመት መሆን እና የWashington ነዋሪ መሆን አለብዎት።
- ፈቃድ ባለው የአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ውስጥ የትራፊክ ደህንነት ኮርስ ማጠናቀቅ አለብዎት።
- ሌላ ግዛት ላይ የወሰዱት የትራፊክ ደህንነት ኮርስ የWashington ዝቅተኛ መስፈርቶችን (የ30 ሰዓታት የክፍል ውስጥ ትምህርት እና የ6 ሰዓታት የተግባር ትምህርት) ማሟላቱን ማረጋገጥ አለብዎት።
- የእውቀት መመዘኛ ፈተናውን እና የክህሎት መመዘኛ ፈተናውን ማለፍ አለብዎት።
- ከ3 ዓመታት በላይ የማሽከርከር ልምድ ካለው አሽከርካሪ ጋር በመሆን ቢያንስ በቀን 40 ሰዓታት መንዳት እና በምሽት 10 ሰዓታት መንዳት ማጠናቀቅ አለብዎት። (ወላጆች፣ አሳዳጊዎች፣ ወይም ሃላፊነት ያላቸው አዋቂዎች ይህን ማረጋገጥ አለባቸው።)
- ፈቃዱን ለማግኘት ከማመልከትዎ በፊት ባሉት 6 ወራት ውስጥ ምንም ዓይነት የትራፊክ ጥሰት ወይም የጥፋተኝነት ውሳኔ ሊኖርዎ አይገባም።
- በተማሪ ፈቃድዎ በሚያሽከረክሩበት ወቅት የአልኮል ወይም አደንዛዥ ዕጽ ጥፋቶች ሊኖርዎት አይገባም።
- የአካል ክፍል፣ የአይን እና የህብረ-ህዋስ ለጋሽ ሆነው መመዝገብ ይፈልጉ እንደሆነ ይወስኑ።

**መንጃ ፈቃድዎን በአካል ለማግኘት የሚከትሉት ነገሮች ማድረግ አለብዎት፦**

- በመንጃ ፈቃድ መስጫ ጽህፈት ቤት ቀጠሮ ማስያዝ። ይህን በLicense Express በኩል ወይም ለDOL ፈቃድ መስጫ የደንበኞች አገልግሎት 360-902-3900 ላይ በመደወል ማድረግ ይችላሉ።
- የወላጅ ፈቃድ ቅጽ (parental authorization form) ለመፈረም ወላጅዎን ወይም አሳዳጊዎን ወደ ፈቃድ መስጫ ጽህፈት ቤት ይዘው መምጣት። ይህ ቅጽ እንዲያመለክቱ ፈቃድ ይሰጥዎታል፤ ቢያንስ 50 ሰዓታት የመንዳት ልምድ እንዳልዎት ያረጋግጣል እንዲሁም ባለፉት 6 ወራት ውስጥ ምንም አይነት የትራፊክ ጥሰት እንዳልፈጸሙ ያረጋግጣል። ወላጅዎ ወይም አሳዳጊዎ ማንነታቸውን እና ከእርስዎ ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው። የአባት ስምዎ የሚለይ ከሆነ ግንኙነታችሁን የሚያረጋግጡ ሰነዶች ይዘው መምጣት።

- የአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ ትምህርት ቤትዎ ኮርሱን ማጠናቀቅዎትን እና የፈተና ውጤዎን እስኪያስገባ መጠበቅ። የአሽከርካሪዎች ማስልጠኛ ትምህርት ቤትዎ እያንዳንዱን ፈተና ካለፉ በኋላ ውጤቶችዎን በስርዓቱ ውስጥ ለማስገባት 24 ሰዓታት አለው። የአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ ትምህርት ቤትዎ በቋሚነት ከተዘጋ እና እርዳታ ከፈለጉ ወደ የአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ፕሮግራም tse@dol.wa.gov በኩል ኢሜይል ማድረግ።
- የማህበራዊ ዋስትና ቁጥርዎን ማቅረብ ወይም ከሌለዎት መግለጫ መፈረም።
- የማንነት ማረጋገጫውን ማሳየት።
- የአይን የማየት ችሎታ ምርመራ ማለፍ።
- ፎቶ መነሳት።
- ማንኛውንም የፈቃድ ክፍያዎችን ይፈርሙ።

**ከቢሮው ከመውጣትዎ በፊት ለ45 ቀናት የሚያገለግል ጊዚያዊ መንጃ ፈቃድ ይሰጥዎታል። ይፋዊ መንጃ ፈቃድዎ በፖስታ ይላክልዎታል።**

**መንጃ ፈቃድዎን መስመር ላይ ለማግኘት የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ አለብዎት፡-**

- የWashington ፎቶ የመመሪያ ፍቃድ ሊኖርዎት ይገባል።
- ከወላጅዎ ወይም ከአሳዳጊዎ ፈቃድ ማግኘት።
- የአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ ትምህርት ቤትዎ ኮርሱን ማጠናቀቅዎን እና የፈተና ውጤትዎን ስርዓቱ ውስጥ ማስገባቱን ማረጋገጥ።
- ማናቸውንም የፈቃድ ክፍያዎች መፈረም።
- ደረሰኙን ማሳተም። (ይህ ጊዜያዊ መንጃ ፈቃድዎ ነው። ፎቶዎን አያካትትም፤ ስለዚህ እንደ መታወቂያ ሊጠቀሙበት አይችሉም።)

ይፋዊ መንጃ ፈቃድዎ ከተማሪ ፍቃድዎ ወይም ከWashington መታወቂያ ካርድዎ ጋር ተመሳሳይ ፎቶ ሊኖረው ይገባል።

## የግል መንጃ ፈቃድ ለማውጣት፦ እድሜ 18+

እድሜዎ 18 ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ የመጀመርያ የWashington መንጃ ፈቃድዎን ለማግኘት አራት አማራጮች አሉዎት። የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፦

1. የሌላ ግዛት መንጃ ፈቃድዎን ማስተላለፍ።
2. የእውቀት እና የክህሎት መመዘኛ ፈተናዎችን ማለፍ።
3. የእውቀት መመዘኛ ፈተናውን ማለፍ፣ ፍቃድ ማግኘት፣ ከ5 ወይም ከዚያ በላይ ዓመታት ልምድ እንዲሁም ፈቃድ ካለው አሽከርካሪ ጋር ማሽከርከር መለማመድ፤ ከዚያም የክህሎት መመዘኛ ፈተናውን ማለፍ።
4. ፍቃድዎን ለማግኘት ፈተና ያለመፈተን ፍቃድ ማግኘት፣ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ትምህርት መውሰድ፣ ከዚያም ትምህርቱን ካጠናቀቁ በኋላ የእውቀት መመዘኛ እና የክህሎት መመዘኛ ፈተናውን ማለፍ።

## መካከለኛ መንጃ ፍቃድ

በWashington የሚገኙ ከ16 እስከ 17 ዓመት የሆናቸው ታዳጊዎች ያልተገደበ የአሽከርካሪዎች መንጃ ፍቃድ ከማግኘታቸው በፊት በሁለት የተገደቡ የፍቃድ ደረጃዎች ውስጥ የሚያልፉ ሲሆን እነዚህም፦ 1) የተማሪ ፍቃድ እና 2) መካከለኛ መንጃ ፈቃድ ናቸው። በመካከለኛ መንጃ ፍቃድ የሚያሽከረክሩ ከሆነ ከዚህ በታች ያሉትን ህጎች መከተል አለብዎት።

| ገደቦች | ከተሰጠበት ቀን እስከ 6 ወራት | ከ6 ወራት እስከ 18 ዓመት እስኪሞላዎ ወይም አንድ ዓመት እስኪሞላ ድረስ (ቀድሞ በመጣው መሠረት) |
|---|---|---|
| ተሳፋሪዎች | ከቅርብ የቤተሰብ አባላት በስተቀር ከ20 ዓመት በታች የሆኑ ተሳፋሪዎች እንዲያሳፍሩ አይፈቀድም | ከቅርብ የቤተሰብ አባላት በስተቀር ዕድሜያቸው ከ20 አመት በታች የሆኑ ተሳፋሪዎች ከ3 በላይ እንዲያሳፍሩ አይፈቀድም |
| የመንዳት ሰዓታት | ወላጅ፣ አሳዳጊ ወይም ቢያንስ 25 አመት የሞላው መንጃ ፈቃድ ያለው አዋቂ አብሮዎት ከሌለ በስተቀር ከጠዋት 1 ሰአት እስከ ከሰዓት 5 ሰዓት ማሽከርከር አይችሉም። | የምሽት ገደቦች ከአንድ ዓመት ደህንነቱ የተጠበቀ የማሽከርከር ጊዜያት በኋላ ያበቃል። |

መካከለኛ መንጃ ፍቃድ ህጎች በተጨማሪ በሚነዱበት ወቅት ሞባይል ስልክ እና ተንቀሳቃሽ የመገናኛ መሳሪያዎችን ከእጅ ንክኪ ነጻ ቴክኖሎጂ ጭምር መጠቀምን ይከለክላል። ስልክዎን መጠቀም የሚችሉት ድንገተኛ አደጋ ሪፖርት ለማድረግ ብቻ ነው።

የትራፊክ ጥሰቶች እና በእርስዎ ጥፋት ለሚከሰቱ ግጭቶች የሚጣሉ ቅጣቶች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

| ጥሰት | ቅጣት |
|---|---|
| 1ኛ | አሁን ላይ ያሉት ገደቦች 18 አመት እስኪሞላዎ ደረስ ተፈጻሚ ይሆናሉ። |
| 2ኛ | ፍቃድዎ ለ6 ወራት ወይም 18 አመት እስኪሞላዎት ድረስ ይታገዳል፤ ይህም አስቀድሞ በተከሰተው መሠረት ነው። |
| 3ኛ | መንጃ ፈቃዱ 18 አመት እስኪሞላዎት ድረስ ይታገዳል። |

**ልዩ ሁኔታዎች**

- ***ለግብርና ዓላማዎች።*** መካከለኛ መንጃ ፈቃድ ያላቸው አሽከርካሪዎች ከግብርና ጋር ለተያያዙ ዓላማዎች በማንኛውም ሰዓት ተሳፋሪዎችን ይዘው መንዳት ይችላሉ።
- ***ለአንድ ዓመት ያህል ደህንነቱ የተጠበቀ ማሽከርከር።*** መካከለኛ መንጃ ፈቃድ ያላቸው ሰዎች የትራፊክ አደጋ ካላጋጠማቸው ወይም የትራፊክ ጥሰት ካልፈጸሙ በማንኛውም ሰዓት ተሳፋሪዎችን ይዘው መንዳት ይችላሉ።

18 ዓመት ሲሞላዎ አዲስ መንጃ ፍቃድ ማውጣት አያስፈልግዎትም። የመካከለኛ መንጃ ፍቃድ ገደቦች በቀጥታ በራስ ሰር ይነሳሉ። የመንጃ ፍቃድዎን አካላዊ ቅጂ ለማግኘት ፈቃድዎን እስኪያድሱ ድረስ መጠበቅ ይችላሉ።

## የግብርና መንጃ ፈቃዶች

የግብርና ፍቃዶች ከ18 ዓመት በታች የሆኑ አሽከርካሪዎች የእርሻ ስራ ለመስራት በተወሰኑ አከባቢዎች እንዲያሽከረክሩ ያስችላቸዋል። ለታዳጊ የግብርና ፈቃድ ዝቅተኛ የዕድሜ መስፈርት የለም።

የግብርና ፈቃድ የተማሪ ፈቃድ ምትክ አይደለም። የመጀመርያውን መንጃ ፈቃድዎን ከማግኘትዎ በፊት አሁንም የመመሪያ ፍቃድ ማግኘት እና ሁሉንም የመንዳት ልምምድ መስፈርቶች ማሟላት አለብዎት። የግብርና ፈቃድ የመጀመርያውን የWashington መንጃ ፈቃድዎን ለማግኘት የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን አያስቀርም።

## የመጀመርያ ደረጃ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤዎች

DOL የመጀመርያ የትራፊክ እንቅስቃሴ ጥሰት ለሚፈጽሙ ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 21 ዓመት ለሆነ አሽከርካሪዎች ደብዳቤዎችን ይልካል። አንድ አሽከርካሪ የመጀመርያ ጥሰታቸውን ከፈጸሙ በኋላ የመጋጨት እድላቸው በእጥፍ ይጨምራል። መካከለኛ መንጃ ፈቃድ ያላቸው አሽከርካሪዎች ጥሰት ሲፈጽሙ ወይም ግጭቶች ሲያጋጥማቸው ለወላጆቻቸው ወይም ለአሳዳጊዎቻቸው ተመሳሳይ ደብዳቤዎች ይላክላቸዋል። የደብዳቤው ዓላማ ታዳጊ አሽከርካሪዎች ቀጣይነት ካላቸው ጥሰቶች ጋር ተያይዘው የሚመጡትን አደጋዎች እንዲገነዘቡ እና ተደጋጋሚ እንዲቀንሱ ለመርዳት ነው።

# 1.9 | ጤና

## የአይን የማየት ችሎታ ምርመራ

DOL መንጃ ፈቃድዎ ከመስጠቱ በፊት የአይንዎን የማየት ችሎታ ይፈትሻል። የማስተካከያ መነጽሮችን ወይም ኮንታክት ሌንሶችን ከተጠቀሙ ይህ በፍቃድዎ ላይ ይመዘገባል።

- በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ሁሉ መነጽርዎን ወይም ኮንታክት ሌንሶችዎን ማድረግዎን ልብ ይበሉ።
- አይንዎን በአይን ሐኪም በየጊዜው ይመርመሩ።

## የአካል ክፍል ለጋሽ

መንጃ ፍቃድዎን በሚያወጡበት ወቅት የአካል ክፍል ለጋሽ መሆን ይፈልጉ እንደሆነ ይጠየቃሉ። የአካል ክፍል ለጋሽ ለመሆን ከወሰኑ፣ የለጋሽ ልብ ምልክት ♥ በመንጃ ፍቃድዎ ላይ ይታያል እንዲሁም መረጃዎ ለለጋሾች መዝገብ ይሰጣል።

DONATE LIFE TODAY!

**ለተጨማሪ መረጃ LifeCenter Northwest lcnw.org ያነጋግሩ፤ ወይም donatelifetoday.com፤ የሚገኘውን የመመዝገብያ ድረ-ገጽ ይጎብኙ።**

## የህክምና ስያሜዎች

በመንጃ ፍቃድዎ ወይም በመታወቂያ ካርድዎ ላይ የአካል ጉዳት እና የህክምና ስያሜዎችዎን ማከል ወይም ማስወገድ ይችላሉ። ድንገተኛ አደጋ ሲከሰት፣ እነዚህ ስያሜዎች ለመጀመሪያ ምላሽ ሰጪዎች እርስዎ እንዴት እንደሚግባቡ መረጃ ይሰጣሉ ወይም በጤና ድንገተኛ ሁኔታ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ሁኔታዎች እንዳሉ ያሳውቋቸዋል።

ከዚህ በታች ካሉት ስያሜዎች ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ወደ መዝገብዎ ላይ ማከል ይችላሉ።




| የአእምሮ እድገት እክል | መስማት የተሳናቸው ወይም የመስማት ችግር ያለባቸው | የሕክምና ማስጠንቀቂያ |
| --- | --- | --- |





## 1.10 | ድጋፎች

ሞተር ሳይክሎችን ወይም የንግድ ሞተር ተሽከርካሪዎችን ለማሽከርከር በግል መንጃ ፈቃድዎ ላይ ተጨማሪ ድጋፍ ማግኘት ያስፈልግዎታል። dol.wa.gov ላይ **ድጋፎች (endorsement)** ብለው በመፈለግ ወደሚፈልጉት ፈቃድ በመሸብለል ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

## 1.11 | በእድሜ ገፋ ያሉ አሽከርካሪዎች

የመንዳት ችሎታዎችዎን የሚመለከቱ ውሳኔዎች በእድሜ ብቻ መወሰን የለባቸውም። ሆኖም ግን በአይን እይታዎ፣ በአካል ብቃት እና በፍጥነት የመመለስ አቅምዎ ላይ የሚያጋጥሙ ለውጦች የደህንነት ስጋቶችን ሊያስከትሉ ይችላሉ። ከእድሜ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ለውጦች በትክክል በመገምገም በሚያሽከረክሩበት ወቅት ደህንነትዎ ለመጠበቅ የመንዳት ልምዶችዎን መለወጥ ወይም ሌሎች የመጓጓዣ ዓይነቶችን መምረጥ ይችላሉ።

በእይታዎ፣ በአካል ብቃትዎ፣ በትኩረትዎ ወይም ለድንገተኛ ለውጦች በፍጥነት ምላሽ የመስጠት ችሎታ ላይ ለውጦችን ካስተዋሉ፣ እነዚህ ለውጦች ደህንነትዎ በተጠበቀ ሁኔታ የመንዳት ችሎታዎት ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚፈጥሩ መገንዘብ አስፈላጊ ነው። ደህንነትዎ በተጠበቀ ሁኔታ እያሽከረከሩ በጥሩ ሁኔታ ማርጀት (Driving Safely While Aging Gracefully) የሚለው ጽሁፍ በ USAA (United Services Automobile Association educational foundation, የተባበሩት አገልግሎቶች አውቶሞቢል ማህበር የትምህርት ፋውንዴሽን)፣ በብሄራዊ አውራ ጎዳና ትራፊክ ደህንነት አስተዳደር (National Highway Traffic Safety Administration) እና በ AARP (American Association of Retired Persons, የ የአሜሪካዊ የጡረተኞች ማህበር) የተዘጋጀ ነው። የጥንቃቄ ምልክቶችን ቀድሞውኑ እንዲያውቁ እና ደህንነቱ የተጠበቀ አሽከርካሪ ለመሆን ምን ማድረግ እንደሚችሉ ጠቃሚ ምክሮችን እንዲያገኙ ይረዳዎታል። መምሪያውን፣ ለማውረድ ወደ nhtsa.gov በመሄድ መነሻ ገጹ ላይ ባለው መፈለጊያ ሳጽን **driving safely (ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ማሽከርከር)** ብለው ይፈልጉ።

## 1.12 | የግል መንጃ ፈቃድ ፈተናዎች

### ሁለት ፈተናዎች

መንጃ ፍቃድ ያለው አሽከርካሪ ከመሆንዎ በፊት፣ ሁለት ፈተናዎችን ማለፍ ይኖርብዎታል።

**የእውቀት መመዘኛ ፈተና**

- የእውቀት መመዘኛ ፈተናው ስለ Washington የመንገድ ህጎች ያልዎትን ግንዛቤን የሚገመግም ነው።
- የመንዳት ክህሎት መመዘኛ ፈተና ከመፈተንዎ በፊት የእውቀት መመዘኛ ፈተናውን ማለፍ አለብዎት።
- የእውቀት መመዘኛ ፈተናውን ካለፉ በኋላ የክህሎት ፈተናውን ለማጠናቀቅ ሁለት ዓመታት አሉዎት።

**የመንዳት ክህሎት መመዘኛ ፈተና**

- የመንዳት ክህሎት መመዘኛ ፈተና የWashington የመንገድ ህጎችን የመተግበር ችሎታዎን የሚገመግም ነው።
- በፈተናው ወቅት በተሽከርካሪው ውስጥ መሆን የሚፈቀድላችሁ እርስዎ እና ፈታኙ ብቻ ናችሁ። ለአገልግሎት እንስሳቶች እና ለምልክት ቋንቋ አስተርጓሚዎች ብቻ በልዩ ሁኔታ እንፈቅዳለን።
- የመንዳት የክህሎት መመዘኛ ፈተና የሚፈተኑበት ተሽከርካሪ ፍቃድ ያለው እና የተመዘገበ መሆን አለበት። ተሽከርካሪው የአሁን የተጠያቂነት ኢንሹራንስ ሽፋን ያለው መሆን (መድን የገባው ሰው ስም የሚያሳይ እና የተሽከርካሪው መግለጫ ያካተተ መሆን አለበት) እና ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ላይ ያለ መሆን አለበት። የፍሬን መብራቶች፣ የምልክት መብራቶች እንዲሁም የደህንነት ቀበቶዎች የሚሰሩ መሆን አለባቸው። ፈታኝዎ ፈተናውን ከመጀመርዎ በፊት ሁሉንም መስፈቶች ያረጋግጣል።




## ፈተናውን መፈተን

የመንጃ ፍቃድ ፈተናዎችዎን የሚወስዱባቸው ሁለት መንገዶች አሉ።

- dol.wa.gov ድረ ገጽ ላይ **approved driver training school (ፍቃድ ያለው የአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት)** በማለት የአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት መፈተኛ ቦታን ይፈልጉ።
- በLicense Express ውስጥ በአሽከርካሪ ፍቃድ መስጫ ጽህፈት ቤት ቀጠሮ ያስይዙ።




## 1.13 | የአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ ትምህርት

ከ18 በታች ለሆኑ አዲስ አሽከርካሪዎች ኮርሶች እንዲሰጡ የተፈቀደላቸው የአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶች **የክፍል ውስጥ ትምህርት** እና **የመንዳት የተግባር ትምህርት** ኮርሶችን ለመስጠት ፈቃድ ያላቸው ናቸው።

የትምህርት ቤት አማራጮች የግል የአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶችን እና የትምህርት ቤት ቅርንጫፎችን መምረጥን ያካትታሉ። ፍቃድ ያላቸው የትምህርት ቤቶች ካርታ እና አገልግሎቶቻቸው dol.wa.gov ላይ **driver training school (የአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶች)** ብለው በመፈለግ ማግኘት ይችላሉ።

### ከ18 ዓመት በላይ

የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ኮርስ ያላጠናቀቁ ከ18 አመት በላይ የሆናቸው አሽከርካሪዎች ለአደጋ የመጋለጥ እድላቸው ይጨምራል። ይህን ችግር ለመፍታት፣ አንዳንድ የአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶች ከ18 ዓመት በላይ ለሆኑ አዲስ አሽከርካሪዎች የአዋቂዎች የትራፊክ ደህንነት ትምህርቶችን ይሰጣሉ። እነዚህ ትምህርቶችን እንደ ጀማሪ አሽከርካሪ፣ ወደ አሜሪካ አዲስ እንደመጣ ሰው ወይም እንደ ማደሻ መውሰድ ይችላሉ። ትክክለኛ ስልጠና እና የክህሎት ግምገማ ለማንኛውም እድሜ ጥሩ ነው።

## 1.14 | የአዲስ አሽከርካሪዎች አሳዳጊዎችን የሚመለከት

ልምድ ያካበቱ የመንዳት አማካሪዎች ለአዳዲስ አሽከርካሪዎች ትልቅ ግብዓት ሊሆኑ ይችላሉ። ደህንነቱ የተጠበቀ የማሽከርከር ባህሪን ማሳየት እና ግልጽ የሆነ የሃሳብ ልውውጥ አማካሪዎች ታዳጊ አሽከርካሪዎችን ማስተማር የሚችሉባቸው ሁለት መንገዶች ናቸው።

ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ተማሪዎች የአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ ኮርሶች የወላጅ ትውውቅ ክፍለ ጊዜ መስጠት አለባቸው። በእነዚህ ክፍለ ጊዜያት መገኘት አማካሪዎች ከፕሮግራሙ ጋር እንዲተዋወቁ እና የ40 ሰዓታት የቀን ፈረቃ ማሽከርከር እና የ10 ሰዓታት በምሽት የማሽከርከር መስፈርቶችን የበለጠ እንዲብራራላቸው እድል ይሰጣል።

dol.wa.gov ላይ **teen safe driving agreement (የታዳጊዎች ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ የመንዳት ስምምነት)** ብለው በመፈለግ ተጨማሪ መረጃዎችን ማግኘት ይችላሉ።

## 1.15 | መንጃ ፍቃድዎን ማቆየት

### መንጃ ፈቃድዎን መተካት።

መንጃ ፍቃድዎ ከጠፋ፣ ከተሰረቀ፣ ከተበላሸ ወይም ብቁ ካልሆነ ለመተካት በመስመር ላይ dol.wa.gov በኩል ማመልከት ይችላሉ። እንዲሁም በማንኛውም የአሽከርካሪ ፍቃድ መስጫ ጽህፈት ቤት በአካል በመገኘት ቅጂ መጠየቅ ይችላሉ።

### መንጃ ፈቃድዎን ማሳደስ

- የመንጃ ፍቃድዎ ማብቂያ ቀን በመንጃ ፈቃድ ካርድዎ ታችኛው ክፍል ላይ ይገኛል። ፈቃድዎ ከመጠናቀቁ በፊት እስከ አንድ ዓመት ድረስ ማደስ ይችላሉ።
- በመስመር ላይ በLicense Express በኩል ወይም በመንጃ ፈቃድ መስጫ ጽህፈት ቤት በመገኘት ማሳደስ ይችላሉ።

### ጊዜው ያለፈበት መንጃ ፍቃድ

- መንጃ ፍቃድዎን ጊዜው ካለፈበት በኋላ ካሳደሱ ተጨማሪ ክፍያ መክፈል ሊያስፈልግዎ ይችላል።
- መንጃ ፍቃድዎ 8 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ጊዜ ካለፈው፣ የእውቀት መመዘኛ እና የክህሎት መመዘኛ ፈተናዎችን እንደገና መፈተን ይኖርብዎታል።

## የመንዳት መብቶችን ማጣት

መንዳት ትልቅ ኃላፊነት ነው። ሁልጊዜ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ መንዳት አለብዎት። አሽከርካሪዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጨምሮ በተለያዩ ምክንያቶች የመንዳት ልዩ መብቶቻቸውን ሊያጡ ይችላሉ።

- የመካከለኛ መንጃ ፍቃድ ገደቦችን መጣስ
- ታዳጊ ሆነው አልኮል፣ አንደንዛዥ ዕጽ ወይም የጦር መሳርያ ይዞ መገኘት
- ተደራራቢ የእንቅስቃሴ ጥሰቶችን መፈጸም
- የታገድ ወይም የተሰረዘ መንጃ ፍቃድ ይዞ ማሽከርከር
- ከህግ አስከባሪ አካላት ማምለጥ
- በተጽዕኖ ስር ሆነው መንዳት
- በከፍተኛ ፍጥነት ማሽከርከር ወይም በግዴለሽነት ማሽከርከር
- የግንባታ ሰራተኛን ወይም የአደጋ ጊዜ ሰራተኛን አደጋ ላይ መጣል
- ያልተፈቱ የትራፊክ ክሶችን ማከማቸት
- በተሽከርካሪ ጥቃት መፈጸም፣ በተሽከርካሪ ግድያ መፈጸም ወይም ገጭቶ ማምለጥ
- ከሞተር ተሽከርካሪ ጋር የተያያዘ ወንጀል መፈጸም
- ኢንሹራንስ ሳይኖርዎት ማሽከርከር
- የብቃት ማረጋገጫ ግምገማን ማለፍ አለመቻል

ለተጨማሪ መረጃ dol.wa.gov ላይ **license suspensions (የመንጃ ፍቃድ መታገድ)** ብለው ይፈልጉ።

## የአልኮል፣ የአደንዛዥ ዕጽ እና የጦር መሳርያዎች ጥሰቶች

የአልኮል፣ የአደንዛዥ ዕጽ ወይም የጦር መሳርያዎች ጥሰቶች የፈጸሙ ታዳጊዎች መንጃ ፍቃዳቸው 17 እስኪሞላቸው ድረስ ሊዘገይ ይችላል።

የመንጃ ፍቃድዎን እንደገና ለመውሰድ ብቁ ሲሆኑ የመንዳት የእውቀት መመዘኛ እና የክህሎት መመዘኛ ፈተናዎችን እንደገና መውሰድ ይኖርብዎታል (ምንም እንኳን ከዚህ ቀደም ፈተናዎቹን ቢወስዱም)። ከተለመዱት የፈተና እና የመንጃ ፍቃድ ክፍያዎች በተጨማሪ እንደገና የማውጣት ክፍያ መክፈል ያስፈልግዎታል። እንዲሁም ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ የወላጅ ወይም የአሳዳጊ ፈቃድ ሊያገኙ ይገባል።

## በተጽዕኖ ስር ሆኖ መንዳት (DUI)



Washington ውስጥ በአልኮል ወይም በአደንዛዥ ዕጽ ተጽዕኖ ስር ሆነው መንዳት በህግ የተከለከለ ነው (RCW (Revised Code of Washington, የተሻሻለው የWashington ኮድ) 46.61.502)። በተጽዕኖ ስር ሆኖ መንዳት ለህይወት አስጊ እና የህግ ቅጣቶች ያስከትላል።

እንዲሁም DUI (Driving under the influence, በተጽዕኖ ስር ሆነው መንዳት) ምንም እንኳን የቆመ ቢሆን፣ተሽከርካሪን ለመቆጣጠር ይሠራል (RCW 46.61.503)። የሚችሉበት ሁኔታ ውስጥ ካሉ ተሽከርካሪውን በአካል ይቆጣጠራሉ ተብሎ ይታሰባል። **በተተገበረው የስምምነት ህግ (Implied Consent Law)** (RCW 46.20.308) መሰረት በWashington የሚነዳ ማንኛውም አሽከርካሪ በአልኮል ወይም አደንዛዥ ዕጽ ተጽዕኖ ስር እያሽከረከሩ ነው ብሎ የጠረጠረ የህግ አካል ምርመራ እንዲያደርግባቸው ፈቃድ ይሰጣቸዋል።

### በደም ውስጥ ያለ የአልኮል መጠን (BAC)

የBAC (Blood Alcohol Concentration, በደም ውስጥ ያለ የአልኮል መጠን) ምርመራ በሰውነትዎ ውስጥ ምን ያህል አልኮል እንዳለ ይለካል። እድሜያቸው 21 እና ከዚያ በላይ ለሆነ አሽከርካሪዎች በሰውነታቸው ያለው የአልኮል መጠን BAC .08% ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ እንደ DUI ይቆጠራል እና ህጋዊ ቅጣቶችን ሊያስከትልም ይችላል። እድሜያቸው ከ21 በታች የሆኑ አሽከርካሪዎች በደማቸው ያለው የአልኮል መጠን BAC 0.02% ሲገኝባቸው ተመሳሳይ ቅጣቶች ሊጣልባቸው ይችላል።

### የቴትራሃይድሮካናቢኖል የካናቢስ መጠን (THC)

የTHC (Tetrahydrocannabinol, የቴትራሃይድሮካናቢኖል) ምርመራ በሰውነትዎ ውስጥ ምን ያህል የTHC መጠን እንዳለ ይለካል። እድሜያቸው 21 አመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ አሽከርካሪዎች በአንድ ሚሊ ሊትር ደም ውስጥ ከ5 ናኖ ግራም በላይ THC ካለባቸው DUI እንደሆነ ይቆጠራል እና ህጋዊ ቅጣቶችን ሊያስከትልም ይችላል። እድሜያቸው ከ21 በታች የሆኑ አሽከርካሪዎች በስርዓታቸው ውስጥ በአንድ ሚሊ ሊትር ደም ውስጥ ከ0 ናኖግራም በላይ THC ሲገኝባቸው ተመሳሳይ ቅጣቶች ሊጣልባቸው ይችላል።

ምርመራ ለማድረግ ፈቃደኛ ካልሆኑ፣ ከ90 እስከ 730 ቀናት ወይም 21 እድሜ እስኪሞላዎት ድረስ መንጃ ፍቃድዎን ሊነጠቁ ይችላሉ። ምን ያህል ጥሰቶችን እንደፈጸሙ ጨምሮ የእገዳዎ ጊዜ ርዝማኔ በብዙ ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ነው።

| አዋቂዎች (21 ዓመት እና ከዚያ በላይ) | ታዳጊዎች (ከ 21 ዓመት በታች) |
|---|---|
| 0.08% ወይም ከዚያ በላይ የBAC መጠን<br>5.00 ናኖግራም ወይም ከዚያ በላይ የTHC መጠን | 0.02% ወይም ከዚያ በላይ የBAC መጠን<br>ከ0.00 ናኖግራም በላይ የTHC መጠን |

**የረጅም ጊዜ ልምድ ያካበቱ አሽከርካሪዎች እንኳን አልኮል ከጠጡ በኋላ እና/ወይም አደንዛዥ ዕጽ ከተጠቀሙ በኋላ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ማሽከርከር አይችሉም። በተጽዕኖ ስር ሆነው በጭራሽ ላለመንዳት በመወሰን ህይወትን ያድኑ!**

ከአልኮል እና አደንዛዥ ዕጽ ጋር የተያያዙ ጥፋቶች በመንጃ ፈቃድ መዝገብዎ ላይ በህይወት ዘመንዎ በሙሉ የሚታዩ ይሆናል። በአልኮል ወይም አደንዛዥ እጽ ተጽዕኖ ስር ሆነው ሲያሽከረክሩ ከተያዙ ቅጣቶቹ ከባድ ናቸው፦ መንጃ ፍቃድዎን ማጣት፣ ከፍተኛ የገንዘብ መቀጮ፣ የወንጀል ቅጣቶች እና ከፍተኛ የሆኑ የመድን ክፍያዎች።

የጥፋተኝነት ውሳኔዎች የሚከተሉትን ጥምረቶችን ሊያካትቱ ይችላሉ፦

- የመንዳት መብቶችን ከ90 እስከ 4 ዓመታት ያህል መታገድ
- የሙከራ ፈቃድ
- ተሽከርካሪዎን ለመንዳት ኢግኒሽን ኢንተርሎክ መሳርያ እንዲጠቀሙ ሊገደዱ ይችላሉ
- የገንዘብ ሃላፊነት ማረጋገጫ እንዲያቀርቡ መጠየቅ
- የአልኮል ምርመራ እና የሕክምና ሪፖርት
- ለመንጃ ፍቃድ እንደገና ማመልከት፣ የእውቀት እና የክህሎት መመዘኛ ፈተናዎችን እንደገና መውሰድ እና ክፍያዎችን እንደገና እንዲፈጽሙ መጠየቅ

## መጠጥ/ካናቢስ ጥቅም ላይ የዋለበትን ዕቃ የመያዝ ህግ (OPEN CONTAINER LAW)

መጠጥ/ካናቢስ ጥቅም ላይ የዋለበትን ዕቃ በመያዝ ህግ መሰረት በመንገድ ላይ ባለ ተሽከርካሪው ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን ነገሮች ካደረገ እንደ ትራፊክ ህግ ጥሰት ይቆጠራል፦

- አልኮል መጠጣት ወይም ካናቢስ መጠቀም።
- የተከፈቱ ወይም ማሸጊያቸው የተሰበረ ወይም በከፊል የተጠጡ የአልኮል ጠርሞዞችን ወይም የካናቢስ ምርቶችን ይዞ መገኘት።
- አልኮል ወይም ካናቢስን መለያ በሌላቸው ወይም የተሳሳተ መለያ በተደረገባቸው እቃዎች ውስጥ መደበቅ።

የተከፈቱ የአልኮል እና የካናቢስ ምርቶች ማጓጓዝ የሚቻለው የጭነት መኪና አልጋ ላይ ብቻ ነው። የአልኮል ወይም የካናቢስ እቃዎች አሽከርካሪው ሊደርስባቸው በሚችልባቸው የማከማቻ ቦታዎች ውስጥ መቀመጥ የለባቸውም።

## 1.16 | ተጨማሪ አገልግሎቶች

### የአድራሻ ወይም የስም ለውጥ

አድራሻዎ ከተለወጠ ለውጡ በተደረገ በ10 ቀናት ውስጥ መረጃውን በLicense Express ውስጥ ያዘምኑ። የስም ለውጦች በአሽከርካሪ ፈቃድ መስጫ ጽህፈት ቤት ውስጥ መደረግ አለባቸው።

### የመራጮች ምዝገባ (VOTER REGISTRATION)

በውጪ ጉዳይ ሚኒስተር (Secretary of State) ድረ-ገጽ sos.wa.gov ላይ ወይም መንጃ ፍቃድዎን ሲቀበሉ በአሽከርካሪ ፍቃድ መስጫ ጽህፈት ቤት ውስጥ ለመራጭነት መመዝገብ ይችላሉ። እድሜያቸው 16 እና 17 አመት የሆናቸው ነዋሪዎች መንጃ ፍቃድ ወይም መታወቂያ ካርድ ሲያወጡ ለመራጭነት ቅድመ-ምዝገባ ማድረግ ይችላሉ።

### አስገዳጅ የወታደራዊ አገልግሎት ምዝገባ (SELECTIVE SERVICE REGISTRATION)

ለመንጃ ፍቃድ ወይም መታወቂያ ካርድ ሲያመለክቱ ለUnited States አስገዳጅ ወታደራዊ አገልግሎት ስርዓት (United States Selective Service System) መመዝገብ ይችላሉ። በWashington ግዛት ጠቅላይ አቃቢ ሕግ ጽህፈት ቤት (Washington State Office of the Attorney General) ደረ-ገጽ ላይ ተጨማሪ መረጃዎች አሉ፦ atg.wa.gov።

### የመንትዮች መዝገብ

ለመንጃ ፍቃድ በሚያመለክቱበት ወቅት መንትያ እንዳለዎት ይጠየቃሉ። የWashington ግዛት የመንትዮች መዝገብ (Washington State Twin Registry) በምርምር እና ጥናቶች ውስጥ መሳተፍ ለሚፈልጉ መንትዮች ነው። ዩኒቨርስቲዎች በDepartment of Licensing ውስጥ እንደ መንትዮች የተመዘቡ ግለሰቦችን ሊያነጋግሩ ይችላሉ። ጥያቄዎች ካሉዎት እባክዎ wstwinregistry.org ይጎብኙ።



# ምዕራፍ 2

# ተሽከርካሪዎች



ፈቃድ ያለው አሽከርካሪ እንደመሆንዎ የመንገድ ሕጎችን መከተል ይጠበቅብዎታል። ከዚህም በተጨማሪም እየነዱት ያለውን ተሽከርካሪ ምን እንደሚያስፈልገው ማወቅ አለብዎት። ተሽከርካሪዎን በጥሩ ሁኔታ ለማቆየት የሚያስፈልጉ ብዙ አገልግሎቶች በLicense Express ውስጥ ይገኛሉ። ወደ License Express የሚወስድዎት አገናኝ በdol.wa.gov መነሻ ገጽ ከላይ በቀኝ በኩል ጥግ ላይ ማግኘት ይችላሉ። (ቀጥተኛው አድራሻ secure.dol.wa.gov/home ነው።) እንዲሁም ጉዳይ ለማስፈጸም የተሽከርካሪ ፈቃድ መስጫ ጽህፈት ቤትን በአካል መጎብኘት ይችላሉ።

## የባለቤትነት የምስክር ወረቀት (የባለቤትነት ማረጋገጫ)

Department of Licensing ለአብዛኛዎቹ ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት የምስክር ወረቀት (Certificate of ownership) (እንዲሁም የባለቤትነት ማረጋገጫ በመባል የሚታወቅ) ይሰጣል። የባለቤትነት የምስክር ወረቀቱ የተሽከርካሪውን የተመዘገበ እና ህጋዊ ባለቤት(ቶች)፣ VIN (Vehicle Identification Number፣ የተሽከርካሪው መለያ ቁጥር) እና የባንክ መረጃን (ብድር ያለው እንደሆነ) ያሳያል። ይህ አስፈላጊ ሰነድ ነው! ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ያስቀምጡት ነገር ግን በተሽከርካሪው ውስጥ አይደለም።

## ምዝገባ

ሁሉም ተሽከርካሪዎች Department of Licensing ውስጥ መመዝገብ አለባቸው። Washington ውስጥ አንድን ተሽከርካሪ ከማስመዝገብዎ በፊት መጀመርያ መንጃ ፍቃድ ሊኖርዎት ይገባል (በህግ በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደልዎት በስተቀር)። በልዩ ሁኔታ የተሽከርካሪ ምዝገባ ተፈቅዶልናል የሚሉ ደንበኞች ከተሽከርካሪ ምዝገባ መንጃ ፈቃድ ነፃ የመሆን ቅጽ (Vehicle Registration Driver License Exemption form) መሙላት ይችላሉ። አዲስ ነዋሪዎች የተሽከርካሪያቸውን ምዝገባ ለማጠናቀቅ 30 ቀናት አላቸው። ከሌላ ግዛት የተገዙ ተሽከርካሪዎች ወዲያውኑ Washington ውስጥ መመዝገብ አለባቸው።

ተሽከርካሪዎን ለማስመዝገብ የሚከተሉት ነገሮች ያስፈልጉዎታል፦

- የአሁን የባለቤትነት የምስክር ወረቀት (የባለቤትነት ማረጋገጫ)። (የተሽከርካሪዎ የባለቤትነት ማረጋገጫ ከጠፋብዎት፣ ወደ ያወጡበት ግዛት በመሄድ ምትክ እንዲሰጥዎት ይጠይቁ።)
- ለሁሉም የተመዘገቡ ባለቤቶች የWashington መንጃ ፈቃድ።

የተሽከርካሪዎን ምዝገባ ሲያሳድሱ በየዓመቱ አዲስ የምዝገባ ሰነድ ይሰጥዎታል። እያንዳንዱን አዲስ ምዝገባ ላይ ይፈርሙ እንዲሁም በተሽከርካሪዎ ውስጥ ያስቀምጡ።

### የተሽከርካሪ አድራሻ

መንጃ ፈቃድዎ ላይ ያለውን አድራሻ መቀየር የተሽከርካሪዎን አድራሻ አይለውጠውም። አድራሻዎን መስመር ላይ በLicense Express በኩል ወይም በተሽከርካሪ ፍቃድ መስጫ ጽህፈት ቤት በአካል በመቅረብ አድራሻዎን መቀየር ይችላሉ።

## 2.1 | የሽያጭ ሪፖርት

### ከግለሰብ ወደ ግለሰብ

ተሽከርካሪዎን ከሸጡ፣ ከለወጡ፣ በስጦታነት ካበረከቱ ወይም ካስወገዱ በ5 ቀናት ውስጥ የተሽከርካሪ ሽያጭ ሪፖርት ቅጽ (Vehicle Report of Sale) ማስገባት ይኖርብዎታል። ታርጋዉን ከተሽከርካሪው ያንሱ፣ ክፍያውን ይክፈሉ እና የሽያጭ ሪፖርት ለተሽከርካሪ ፍቃድ መስጫ ጽህፈት ቤት ያስገቡ ወይም dol.wa.gov ላይ **report of sale** (የሽያጭ ሪፖርት) ብለው ይፈልጉ። የሽያጭ ሪፖርት ባለቤትነትን አያዘዋውርም። ተሽከርካሪን ሲሸጡ የባለቤትነት የምስክር ወረቀቱ በባለቤቱ(ቶቹ) የተፈረመበት እና የተመዘገበ መሆን እና ለገዢው መሰጠት አለበት። የባለቤትነት ስም ለማዘዋወር ገዢው የቅጣት ክፍያዎችን እንዳይከፍል በ15 ቀናት ውስጥ የተፈረመበት የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ይዞ ወደ ፈቃድ መስጫ ጽህፈት ቤት መምጣት አለበት።

### ከሻጭ ድርጅት ወደ ግለሰብ

ተሽከርካሪው በሻጭ ድርጅት የተሸጠ ከሆነ፣ ድርጅቱ በእርስዎ ስም የሽያጭ ሪፖርት ሊያስገባ ይችላል፣ ነገር ግን የማስገባት ግዴታ የለበትም። የሽያጭ ሪፖርት ራስዎ ማስገባትዎ ለእርስዎ የተሻለ ነው።




## 2.2 | የተሽከርካሪ ታርጋዎች

በWashington የተመዘገቡ የሞተር ተሽከርካሪዎች የተሽከርካሪ ታርጋዎች ከፊትና ከኋላ በግልጽ በሚታይ መልኩ መቀመጥ አለባቸው። ንጹህና ለማንበብ ቀላል መሆን አለባቸው። የተሽከርካሪዎ የታርጋ አቃፊ ማድረግ ይችላሉ፣ ነገር ግን በታርጋው ላይ ያሉ ፊደሎችን፣ ቁጥሮችን ወይም ትሮችን መሸፈን በህገ-ወጥ ተግባር ነው።

## 2.3 | የኢንሹራንስ ያስፈልጋል

የኢንሹራንስ ማስረጃዎን ከእርስዎ ጋር ወይም በተሽከርካሪዎ ውስጥ መያዝ አለብዎት። የWashington ግዛት የተጠያቂነት ኢንሹራንስ እንዲኖርዎት እና ማስረጃውን ይዘው እንዲንቀሳቀሱ ያስገድዳል። የተጠያቂነት ኢንሹራንሱ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፦

- በአንድ ግጭት ውስጥ አንድ ሰው ብቻ ተጎድቶ ወይም ተገድሎ ከሆነ ለደረሰበት የአካል ጉዳት ወይም ሞት የሚከፈል $25,000 ወይም ከዚያ በላይ
- በአንድ ግጭት ውስጥ ሁለት ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ወይም ሞት ከደረሰ ለደረሰባቸው የአካል ጉዳት ወይም ሞት የሚከፈል $50,000 ወይም ከዚያ በላይ
- በማንኛውም አንድ ግጭት በሌሎች ንብረት ላይ ለሚደርስ ጉዳት ወይም ውድመት የሚከፈል $10,000 ወይም ከዚያ በላይ

## 2.4 | ተሽከርካሪዎን ይወቁ




እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የራሱ የሆኑ ባህሪያት አሉት። በመጠን፣ በሞተር፣ በደህንነት መሳሪያዎች፣ በመለዋወጫ ዕቃዎች፣ በቴክኖሎጂ፣ እና በአነዳድ ባህሪያት ይለያያሉ። የሚነዱትን የእያንዳንዱን ተሽከርካሪ መመሪያ ማንበብ አስፈላጊ ነው። የተሽከርካሪውን መሰረታዊ አካላት ለማወቅ ጊዜ ይውሰዱ።

### ተግባራት

ወደ ተሽከርካሪ በገቡበት ቅጽበት፣ ተሽከርካሪው አውቶማቲክ ወይም ማንዋል ማስተላለፊያ እንዳለው ማወቅ ይችላሉ። እያንዳንዱን መንዳት ጠንቅቆ ማወቅ እና ልምምድ ማድረግን ይጠይቃል። በተሽከርካሪው ብቻ የሚገኙ ስርዓቶችን፣ መሳርያዎችን፣ መለኪያዎችን እና መሳርያዎችን ለማወቅ የባለቤቱን መምሪያ (owner's manual) ያንብቡ። ትኩረትዎ በመንገዱ ላይ እንዲሆን፣ ከመንዳትዎ በፊት የተሽከርካሪዎን ዝርዝር ነገሮች በደንብ ይወቁ።

### ማስተካከያዎች

ወደ ተሽከርካሪዎ በገቡ ቁጥር ለደህንነትዎ፣ ለቁጥጥርዎ እና ምቾትዎን ለማረጋገጥ በየግዜው ማስተካከያዎችን ማድረግ ያስፈልግዎታል። ጥሩ እይታ እንዲኖርዎት መሪውን፣ መቀመጫውን እና መስተዋቶቹን ያስተካክሉ። ፔዳሎቹን እና መሳርያዎቹን በቀላሉ መድረስ መቻል አለብዎት።

## የተሽከርካሪ ደህንነት ቴክኖሎጂ (VEHICLE SAFETY TECHNOLOGY)

በበተሽከርካሪ ኢንዱስትሪ ውስጥ ፈጠራ እና እድገት የሰው ስህተት እና ደህንነቱ ያልተጠበቀ ባህሪ አሉታዊ ውጤቶችን ለመቀነስ የሚረዱ የደህንነት ስርዓቶች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል። VST (Vehicle Safety Technology፣ የተሽከርካሪ የደህንነት ስርዓት) እና ADAS (Advanced Driver Assistance Systems፣ የላቁ የአሽከርካሪ አጋዥ ስርዓቶች) አደጋው እንዳይከሰት በመከላከል የአደጋውን ተጽዕኖ ይቀንሳሉ። ምላሽ የመስጠት ግዜዎን የሚያሻሽሉ የላቁ ወይም ተጨማሪ ማስጠንቀቂያዎችን ሊሰጡዎ ይችላሉ። ቀድሞውኑ ያልዎትን ጤናማ የማሽከርከር ልምዶቹዎን ለመደገፍ የታሰቡ ናቸው እንጂ እነሱን ለመተካት የታሰቡ አይደሉም። ለተሽከርካሪዎ መንቀሳቀስ ሙሉ ኃላፊነት የሚወስዱት እርስዎ ነዎት።

VST እና ADAS ያልዎት ቢሆንም እንኳን፣ እነዚህ ስርዓቶች ውስንነትዎች ስላሏቸው አሁንም የአደጋ ስጋት ግንዛቤ ክህሎትዎን እና የመንገድ ሕጎችን እውቀት መጠቀም ይኖርብዎታል። ለምሳሌ፣ እነዚህ ስርዓቶች ለእርስዎ ለማየት በሚያዳግቱ ቦታዎች ተሽከርካሪዎች ካሉ ሊያሳውቆት ይችላል፤ ሆኖም ግን ሁለት የመንገድ መስመር ጋር ያለ ወደ እርስዎ ለመጠጋት ያሰበ ተሽከርካሪ ላይለዩ ይችላል። እንዲሁም የተሽከርካሪዎ የነገሮች መለያ ቴክኖሎጂዎች ከተሽከርካሪዎ አቅራቢያ የሚራመዱ፣ የሚሽከረከሩ ወይም የሚነዱ ሰዎችን ለይተው ላያውቁ ይችላል። በግዛቱ ህግ መሰረት ቅድሚያ መስጠት የእርስዎ ኃላፊነት ነው። በተጨማሪም፣ ዳሳሾች ሊቆሸሹ ወይም የመንገድ ላይ ምልክቶች ሊደበዝዙ ይችላሉ፤ ይህም ቴክኖሎጂው በአግባቡ እንዳይሰራ ሊያደርጉ ይችላሉ።

የሚነዱትን ማንኛውንም ተሽከርካሪ ባህሪያት እና ቴክኖሎጂዎች ማወቅዎ አስፈላጊ ነው። የአየር ሁኔታ በጣም ከባድ ከመሆኑ የተነሳ የሚላኩልዎት ማሳወቂያዎች ትኩረትዎን እየከፋፈሉት ካልሆነ በስተቀረ እንደበራ ይተዉት። እነዚህን ባህሪያት በአግባቡ መጠቀም እንደሚችሉ ያረጋግጡ። ተሽከርካሪዎ ስላሉት የደህንነት ቴክኖሎጂዎች የበለጠ ለማወቅ የተሽከርካሪዎን መምርያ ያንብቡ፣ የተሽከርካሪ ሻጭ ድርጅትን ይጠይቁ ወይም mycardoeswhat.org ይጎብኙ።

የVST እና ADAS የተወሰኑ ቁልፍ ክፍሎች እና ባህሪያት እነሆ፦

1. **ግጭትን የማስቀረት ስርዓት፡፡** መሰናክሎችን በመለየት አደጋ እንዳይፈጠር አስቀድሞ ያስጠነቅቃል፡፡ እነዚህም እንደ AEB (Automatic emergency braking፣ ራስ-ሰር ድንገተኛ ፍሬን)፣ ከፊት ሊፈጠር የሚችል ግጭት ማስጠንቀቂያ እና ከመንገድ መስመር የመውጣት ማስጠንቀቂያ ያሉ ባህሪያትን ያካትታሉ፡፡
2. **ACC (Adaptive cruise control፣ ተለዋዋጭ የጉዞ መቆጣጠሪያ)፡፡** የተወሰነ ፍጥነት ጠብቆ ይሄዳል ነገር ግን ከፊቱ ካለው ተሽከርካሪ ያለውን ርቀት በመመስረት ፍጥነቱን ያስተካክላል፣ ይህም ደህንነቱ የጠበቀ የመከተያ ርቀት እንዲኖር ያረጋል፡፡ ACC በረጅም ጉዞዎች ላይ ብዙ ግዜ ፍጥነትን የመቀያየር አስፈላጊነት በማስቀረት ምቾትን ያሳድጋል፡፡
3. **የመንገድ መስመር ጥብቆ መቆያ ረዳት፡፡** የመንገድ መስመር ምልክቶችን ይቆጣጠራል እንዲሁም ተሽከርካሪው ከመንገዱ ሲወጣ የማሽከርከር ግብአት ወይም ማስጠንቀቂያዎችን ይሰጣል፡፡ እንዲሁም ይህ ባህሪ ያልታሰቡ ከመንገድ መስመር መውጣቶችን በመከላከል ደህንነትን ያሻሽላል፡፡
4. **የማይታዩ ቦታዎች ማወቂያ፡፡** ዳሳሾችን በመጠቀም ለአሽከርካሪው የማይታዩ ቦታዎችን ይቆጣጠራል እና በጎን ባለው የመንገድ መስመር ተሽከርካሪ ካለ አሽከርካሪዉን ያስጠነቅቃል፡፡ እንዲሁም ይህ ባህሪ የመንገድ መስመር በሚቀይሩበት ወቅት ሊደርስ የሚችል የግጭት አደጋን ለመቀነስ ያለመ ነው፡፡
5. **የማቆሚያ ረዳት፡፡** በእይታ እና/ወይም በድምፅ መመሪያ በመስጠት በመኪና ማቆም ጊዜ ለመርዳት ዳሳሾችን እና ካሜራዎችን ይጠቀማል፡፡ ይህም እንደ ራስ ሰር የትይዩ ማቆሚያ ያሉ ባህሪያትን ሊያካትት ይችላል፡፡
6. **የትራፊክ ምልክት ማወቂያ፡፡** ካሜራዎችን በመጠቀም የትራፊክ ምልክቶችን በመለየት እና በመተርጎም ለአሽከርካሪው አስፈላጊ መረጃዎችን ያቀርባል፡፡ ይህ ባህሪ የፍጥነት ገደቦችን እና ሌሎች የመንገድ ህጎችን ግንዛቤን ለመጠበቅ ይረዳል፡፡
7. **የአሽከርካሪ መቆጣጠርያ ስርዓት፡፡** የአሽከርካሪውን ባህር ይቆጣጠራል እና የእንቅልፍ ስሜት ወይም ትኩረት ማጣት ምልክቶች ከታዩ ያስጠነቅቃቸዋል፡፡ ይህ ባህሪ የአሽከርካሪዉን ንቁነት በማረጋገጥ ደህንነትን ያሻሽላል፡፡

8. **የጎን ትራፊክ ፍሰት ማሳወቂያ።** እንደ ተሽከርካሪዎች ከማቆሚያ ቦታዎች ሲወጡ ከጎን በኩል እየተቃረበ ያለን ተሽከርካሪ ለአሽከርካሪው ያሳውቃል። ይህ ባህሪ የታይነት ሁኔታው የተገደበ በሚሆንበት ወቅት የመጋጨትን አደጋ ይቀንሳል።
9. **ራስ ሰር የከፍተኛ ጨረር መቆጣጠርያ።** ከተቃራኒ አቅጣጫ የሚመጣ የትራፊክ ፍሰት እና በአከባቢያዊ ሁኔታዎች ላይ በመመስረት የፊት መብራቶች የብርሃን ድምቀት ያስተካክላል። ይህ ባህሪ የሌሎች ተሽከርካሪዎችን ምቾት ሳይነሳ ታይነትን ይጨምራል።
10. **ግጭት መቆጣጠርያ ስርዓቶች።** ግጭትን ማስቀረት የማይቻል ሲሆን የግጭቱ ተጽዕኖ እንዲቀንስ ያደርጋል። ይህ ክፍል ግጭትን ከማስቀረት ባሻገር እንደ ቅድመ-ግጭት የደህንነት ቀበቶ ማጥበቅ እና ድህረ-ግጭት ፍሬን መያዝ የመሳሰሉ ባህሪያትን ሊያካትት ይችላል።

ቴክኖሎጂ ሊረዳዎት ይችላል፣ ነገር ግን በትኩረት መንዳትን ሊተካ አይችልም። የሚያሽከረክሩትን ማንኛውንም ተሽከርካሪ የVST እና ADAS ባህሪያትን ማወቅ ያስፈልግዎታል ነገርግን አሁንም በትኩረት የመንዳት ልማዶችዎ ላይ መተማመን ይችላሉ።



## 2.5 | የተሽከርካሪ ጥገና

ተሽከርካሪዎ ለማሽከርከር አስተማማኝ መሆኑን ማረጋገጥ የእርስዎ ኃላፊነት ነው። አንድ ትንሽ ችግር ወደ እጅግ ትልቅ (በጣም ውድ፣ በጣም አደገኛ) ችግር ለመቀየር ብዙ ግዜ አይፈጅም፣ ስለዚህ ለተሽከርካሪዎ ማስጠንቀቂያዎች ትኩረት ይስጡ። የተጠቆመው መደበኛ ጥገናን በተመለከተ የተሽከርካሪዎ የባለቤትነት መምርያ ይመልከቱ፣ እንዲሁም ጠቋሚ መብራቶችዎ ከበሩ አስፈላጊዉን እርምጃ ይውሰዱ።

### ጎማዎች

| | |
|---|---|
| **የጎማ መርገጫ** | ያረጁ መርገጫ ማዳለጥን እና መንሸራተትን ሊያስከትሉ ይችላሉ፣ በተለይም መንገዱ እርጥብ ሲሆን። የጎማ ትሬድ ጥልቀት ከ2/32 ኢንች ያነሰ መሆን የለበትም። |
| **የጎማ ግፊት** | ዝቅተኛ የጎማ ግፊት መኪናዎን የመቆጣጠር አቅም እና ፍጥነት ሊጎዳ ይችላል።<br><br>ለጎማዎችዎ ትክክለኛው የአየር ግፊት በአሽከርካሪው ጎን በር ጠርዝ ላይ ባለው የጎማ እና የመጫኛ መረጃ መለያ ላይ ወይም በተሽከርካሪዎ ባለቤት መመሪያ ውስጥ ይገኛል። |

### የተሽከርካሪ መስታወቶች

- የፊት መስታወቱን እና መስኮቶቹን ንጽህና ይጠብቁ — ከውስጥም ከውጭም።
- የመስኮት ማጠቢያ ፈሳሽዎን ይሙሉ።
- ከመንዳትዎ በፊት የበረዶ ብናኝ፣ በረዶ ወይም ቀጭን የበረዶ ግግር ከሁሉም መስኮቶችዎ ያስወግዱ።
- ከዕቃዎችን መስታዎትዎ ላይ አያንጠልጥሉ ወይም መስኮቶችዎን እይታዎን ሊጋርዱ በሚችሉ ነገሮች አይሸፍኑ።
- ማጽጃዎችዎን ለመተካት የተሽከርካሪዎን አምራች ምክሮችን ይከተሉ።




ከኋላህ ያለው ሰው በማይጠብቀው ቦታ እየቆሙ ወይም ፍጥነት እየቀነሱ ከሆነ እሱን ለማሳወቅ የፍሬን ፔዳልዎን በፍጥነት ሦስት ጊዜ ወይም አራት ግዜ ይጫኑት።

## የፊት መብራቶች (HEADLIGHTS)

የWashington ህግ የፊት መብራቶችዎን ፀሃይ ከጠለቀች ከግማሽ ሰዓት በኋላ እስከ ፀሃይ ከመውጣትዋ ከግማሽ ሰዓት በፊት ማብራት እንዳለብዎት ይደነግጋል። ሆኖም ግን የፊት መብራቶችዎን በሚከተሉት ሁኔታዎች እንዲበሩ ማድረግ ለማስታወስ ቀላል ሊሆን ይችላል፦

- ሁል ግዜ።
- ጨለማ ሲሆን።
- ዝናባማ፣ በረዷማ፣ ጭጋጋማ ወይም ጉም በሚሸፍንበት ወቅጥ

**የፊት መብራቶች እርስዎ እንዲያዩ ከመርዳት በተጨማሪ ሌሎች ሰዎች እርስዎን እንዲያዩም ይረዳሉ።**

አንዳንድ ተሽከርካሪዎች ተሽከርካሪዉን በሚያስነሱበት ወቅት በቀን የሚበሩ መብራቶች አሏቸው። ሆኖም ግን በቀን የሚበሩ መብራቶች እንደ የፊት መብራቶች ደማቅ አይደሉም፤ እንዲሁም የኋላ መብራቶችዎን አያበሩም።

ሁሉም መብራቶች ንጹህ፣ ደማቅ፣ ወደ ትክክለኛ አቅጣጫ የሚያመላክቱ እና በትክክል የሚሰሩ መሆናቸውን ያረጋግጡ። ዳሽቦርድዎ “lamp out (የአምፖል ብልሽት አለ)” የሚል ምልክት ካሳየ አምፖሎችዎን መቀየር አለብዎት ማለት ነው።

የመንገድ መብራት በሌሉባቸው ክፍት መንገዶች ከፍተኛ ጨረሮችን መጠቀም ይችላሉ፣ ነገር ግን በሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ በሚሆኑበት ወቅት ወደ የፊት መብራቶችን መልሰው ማብራትዎን ልብ ይበሉ፦

- ከተቃራኒ አቅጣጫ ከሚመጣ ተሽከርካሪ በ500 ጫማ ርቀት ውስጥ ሲሆኑ።
- ከኋላ ሲከተሉ ደግሞ በ300 ጫማ ርቀት ውስጥ ሲሆኑ።

## የፍሬን መብራቶች

የፍሬን መብራቶች ከኋላዎ ያለውን ሰው ፍጥነት እንዲቀንስ እና ለማቆም እንዲዘጋጅ ያስጠነቅቃሉ። የፍሬን መብራቶችዎ ቀይ ሲሆኑ ከ100 ጫማ ርቀት በግልጽ ሊታዩ ይገባል።

የፍሬን መብራቶችዎ እየሰሩ ካልሆነ፣ የእጅ ምልክቶችን ያሳዩ። የግራ እጅዎን በአሽከርካሪው በኩል ባለው መስኮት በማስወጣት በጣቶችዎ ወደ መሬት ይጠቁሙ። ይህም ከኋላዎ ያለው ተሽከርካሪ ፍጥነት እንዲቀንስ እና ለማቆም እንዲዘጋጅ ያሳውቀዋል።

## የፍሬቻ መብራቶች

ምንም እንኳን ሌላ ሰው በዙርያዎ እንዳለ ባያዩም፣ አቅጣጫ ከመቀየርዎ በፊት ሁልግዜ ምልክት መስጠትን ልምድ ያድርጉ።

- እንቅስቃሴዎን ከመጀመርዎ በፊት 100 ጫማ ርቀት ሲቀርዎት ምልክት ይስጡ።
- ታጥፈው ሲጨርሱ ምልክትዎ ብልጭ ድርግም ማለቱን ማቆሙን ያረጋግጡ።



## የእጅ ምልክቶች

አንዱ ወይም ሁለቱም ምልክቶች ካልሰሩ፣ ምን እያደረጉ እንደሆነ ለሌሎች አሽከርካሪዎች ለማሳወቅ የእጅ ምልክቶችን ይጠቀሙ።

**ቁም**

የግራ እጅዎን በአሽከርካሪው መስኮት በኩል ያውጡ። በጣቶችዎ ወደ መሬት ይጠቁሙ። ይህም ከኋላዎ ያለው ሰው ፍጥነት እንዲቀንስ እና ለማቆም እንዲዘጋጅ ያሳውቀዋል።

**ወደ ግራ መታጠፍ**

የግራ እጅዎን በመስኮቱ ያውጡ። ጣቶችዎ በቀጥታ ወደ ግራ አቅጣጫ እንዲጠቁሙ ያድርጉ።

**ወደ ቀኝ መታጠፍ**

የግራ እጅዎን በመስኮቱ ያውጡ። እጅዎን በማጠፍ ጣቶችዎ ወደ ሰማይ እንዲያመለክቱ ያድርጉ።

## የአደጋ ግዜ ማስጠንቀቂያ መብራቶች

መኪናዎ በድንገት መስራት ቢያቆም ወይም በድንገት ማቆም ቢኖርብዎት፣ ብልጭ ድርግም የሚሉ የአደጋ ግዜ ማስጠንቀቂያ መብራቶችዎን ያብሩ። ይህም ሌሎች አሽከርካሪዎች ሁኔታዎን እንዲያውቁ እና በጥንቃቄ እርስዎን አልፈው እንዲሄዱ ይረዳቸዋል።

## የአሽከርካሪ ወንበር

- የንፋስ መከላከያ መስታወቱን በግልጽ ማየትና እና ፔዳሎቹን በቀላሉ መድረስ እንዲችሉ አድርገው መቀመጫዎን ያስተካክሉ።
- ቀጥ ብለው በምቾት እንዲቀመጡ የመቀመጫዎን ጀርባ ያስተካክሉ። ለአየር ከረጢት ክፍት ቦታ ለመተው ደረትዎ ከመሪው ቢያንስ 10 ኢንች መራቅ አለበት።
- ክርናችዎ በጥሩ ሁኔታ ታጥፈው መሪዉን በቀላሉ ለመያዝ እንዲችሉ መሪዉን ያስተካክሉ።
- የጭንቅላት ማስደገፍያው ከጆሮዎ ጋር ቀጥ ያለ መሆኑን በማረጋገጥ ራስዎን ከድንገተኛ ጉዳት ይጠብቁ።

በማንኛውም ጊዜ ሌላ ሰው ካሽከረከረ በኋላ ለመንዳት ከመሪው ጀርባ ሲቀመጡ፣ ምቾትዎን እንዲሁም ደህንነትዎን የሚጠብቁ ማስተካከያዎችን ያድርጉ።

# 2.6 | የተሳፋሪ ደህንነት

## የደህንነት ቀበቶዎች እና የተሳፋሪ ደህንነት ጥበቃ

ራስዎን ለመጠበቅ ሊያደርጉት የሚችሉት በጣም ቀላሉ ነገር በትክክል የደህንነት ቀበቶ ማድረግ ነው። የደህንነት ቀበቶ ማድረግ በሚገርም ሁኔታ በአደጋ ወቅት ሊደርስቦት የሚችል የሞት አደጋን በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሰዋል። ሁልጊዜ የደህንነት ቀበቶዎን ያድርጉ እንዲሁም ሁሉም ተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶዎችን፣ የህጻናት የደህንነት መጠበቂያዎች ወይም የህጻናት የመኪና ወንበሮችን እየተጠቀሙ መሆናቸውን ያረጋግጡ።



**ይጫኑት**



የደህንነት ቀብቶዎ በደረትዎ መሃል ማለፍ አለበት። ከጀርባዎ ወይም ከእጅዎ በታች በፍጹም እንዳያደርጉት። ትከሻዎን የሚሸፍነው ቀበቶ በቀጥታ በትከሻዎ አድርጎ በደረትዎ መሃል ማለፍ እንጂ አንገትዎ ላይ ወይም ፊትዎ ላይ መሆን የለበትም። ጭንዎ ላይ የሚያርፈው ቀበቶ ከሆድዎ በታች ያለውን ወገብዎን በአስተማማኝ እና በተስተካከለ ሁኔታ መያዝ አለበት።

በሚንቀሳቀስ ተሽከርካሪ ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው የደህንነት ቀበቶ ማሰር ወይም ፍቃድ ያለው የህጻናት የደህንነት መጠበቂያ መሳርያዎችን ማድረግ አለበት።

**የደህንነት ቀበቶ ወይም የህጻናት የደህንነት መጠበቂያዎችን ሳያደርጉ ተሽከርካሪን መንዳት ወይም መሳፈር ህገ-ወጥ ነው። RCW (Revised Code of Washington፣ የተሻሻለው የWashington ኮድ) 46.61.687 እና RCW 46.61.688**

የደህንነት ቀበቶዎ እንዳልተዘበራረቀ ያረጋግጡ፤ የጭን ቀበቶ የሚያርፈው የጭንዎ ላይኛው ክፍል ላይ ሲሆን በደረትዎ የሚያልፈው ቀበቶ ደግሞ ትከሻዎ መሃል ላይ ማረፍ አለበት። የእግሮችዎ መታጠፍያዎች በመቀመጫው ጫፍ ላይ መታጠፍ አለባቸው፤ እግሮችዎም ወለሉን መንካት አለባቸው፤ እንዲሁም የጭንቅላትዎ መደገፊያ ከጆሮዎ ጋር በተመሳሳይ መስመር ላይ መሆን አለበት።

## የልጆች መቀመጫዎች



እርስዎ (ወይም ሌሎች) ከልጅ ጋር በሚጓዙበት ጊዜ ሁሉ ለእድሚያቸው እና ለመጠናቸው የሚሆን ትክክለኛ መቀመጫ በመጠቀም የተሳፋሪ ህጻናት ደህንነት ይጠብቁ።

የልጆች ደህንነት መጠበቂያ ስርዓት የፌደራል የሞተር ተሽከርካሪ ደህንነት መስፈርቶችን (Federal Motor Vehicle Safety Standards) ማክበር እና በልጆች ደህንነት መጠበቂያ መቀመጫዎች ስርዓት አምራች መመሪያዎች መሰረት በተሽከርካሪ ውስጥ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ መቀመጥ አለበት።

የልጆች ደህንነት መጠበቂያ መቀመጫዎች ስርዓት አገጣጠም የምስክር ወረቀት ባለው የተሳፋሪ ልጅ ደህንነት ባለሙያ እንዲታይ ማድረግ ይችላሉ።

ለተጨማሪ መረጃዎች እና የድህንነት ፍተሻ ቦታዎችን በተመለከተ wacarseats.com ይጎብኙ።

አንድ ልጅ መቀመጫው የተሻለውን ጥበቃ እስካደረገ ድረስ በእያንዳንዱ የልጅ ደህንነት መጠበቅያ ስርዓት ደረጃ ላይ መቆየት አለበት።



**ወደ ኋላ አቅጣጫ የሚመለከት የልጆች መቀመጫ**

**እድሚያቸው እስከ 2 ዓመት የሆኑ ህጻናት ወደ ኋላ አቅጣጫ የሚመለከት ወንበር ላይ መቀመጥ አለባቸው።**

**እድሜ: ከውልደት - 2 ዓመት**



**ወደ ፊት አቅጣጫ የሚመለከት የልጆች መቀመጫ**

**እድሚያቸው ከ2 እስከ 4 ዓመት የሆኑ ልጆች ወደ ኋላ ወይም ወደ ፊት አቅጣጫ የሚመለከት የደህንነት ወንበር ላይ መቀመጥ ይችላሉ።**

**እድሜ: ከ2 እስክ 4 ዓመት**



**የልጆች የመኪና ወንበር**

**እድሚያቸው 4 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆናቸው ልጆች የተሽከርካሪዎች የጭን ቀበቶ እና በደረት ላይ የሚያልፍ ቀበቶ በትክክል ይዟቸው መታጠቅ እስኪጀምሩ ድረስ በልጆች የመኪና ወንበር ላይ መቀመጥ አለባቸው— የደህንነት ቀበቶ በተለምዶ መታጠቅ የሚጀምሩት ከ8 እስከ 12 አመት ባለው እድሜ ላይ ነው።**

**እድሜ እና ቁመት: 4 ዓመት እስከ 4’9”**



**የደህንነት ቀበቶ**

**የደህንነት ቀበቶ ለማድረግ እድሜያቸው እና ቁመታቸው የደረሰ ተሳፋሪዎች በሙሉ የደህንነት ቀበቶ ማድረግ አለባቸው።**

**ቁመት: ከ4’9” በላይ**

## አየር ከረጢቶች

የአየር ከረጢቶች እና የደህንነት ቀበቶዎች በአደጋ ጊዜ ደህንነትዎን ለመጠበቅ በጋራ ይሰራሉ። የአየር ከረጢቱ በሚፈነዳበት ወቅት የደህንነት ቀበቶዎን ካልታጠቁ ለከባድ ጉዳት ወይም ለሞት አደጋ ሊዳረጉ ይችላሉ። እንዲሁም ዕድሚያቸው ከ13 አመት በታች የሆኑ ህጻናት ከፊት ወንበር የማይቀመጡበት ምክያንት አየር ከረጢቶች ናቸው። አየር ከረጢት ከፈነዳ ከባድ ጎዳት ሊደርስባቸው ወይም ሊሞቱ ይችላሉ።




እጆችዎን ከመሪው በውጪ በኩሉ ከላይኛው ክፍል ላይ ያድርጉ። ይህ የተሻለ የመቆጣጠር አቅም ይሰጥዎታል።




መሪው ሰዓት ነው ብለው ያስቡ። እያንዳንዱ ሰዓት መሪዉን የሚይዙበትን ቦታ ይወክላል። ከላይ ባለው ምስል የአሽከርካሪው እጆች በ 9:00 እና 3:00 ላይ ናቸው።

ቀላል እና ቀጣይነት ያለው መሪን መቆጣጠርን የሚያቀርቡ ሦስት የማዞሪያ ዘዴዎች አሉ።

# ከእጅ ወደ እጅ መሪን ማዞር (መሳብ/መግፋት)



ይህን ዘዴ ሲጠቀሙ፣ እጆችዎ 9 እና 3 ላይ ወይም 10 እና 2 ላይ መሆን አለባቸው።



ሲታጠፉ እጆችዎን በእነዚህ ቦታዎች ላይ ያድርጉ። በዚህ ምስል ላይ አሽከርካሪው በግራ እጃቸው እየሳቡ፣ በቀኝ እጃቸው ደግሞ እየገፉ ነው።



እጆችዎ መሪው ላይ እርስ በርስ ስለማይተላለፉ፣ የአየር ከረጢቱ ከፈነዳ ፊትዎት፣ እጆችዎ ወይም ክንዶችዎ ላይ ጉዳት የመድረስ እድል በጣም አነስተኛ ነው።



እጆችዎ ከመሪው ላይ በፍጹም አይነሱም እንዲሁም እያንዳንዱ እጅ በየራሱ ጎን ላይ ይቆያል። አንድ እጅ መሪዉን ይይዛል እና ያዞራል። ሌላኛው እጅ መሪው ላይ እየተንሸራተተ መሪውን ከሚያዞረው እጅ በተቃራኒ አቅጣጫ ላይ ይቆያል።



ከእጅ ወደ እጅ የማዞር ዘዴ ሁለቱም እጆች መሪ ላይ እንዲቆዩ ያደርጋል፣ አስፈላጊ የሆኑ ለውጦችን ወዲያውኑ እንዲያደርጉ ያስችልዎታል እንዲሁም ክንዶችዎን ከአየር ከረጢት አካባቢ ያርቃል።

## አንድ በእጅ ላይ እጅ በማድረግ መሪን ማዞር



ይህን የመሪ የማዞር ዘዴ በዝቅተኛ ፍጥነት ላይ ሆነው ሲዞሩ፣ የተገደበ ታይነት ሁኔታ ላይ፣ በመስቀለኛ መንገድ ላይ፣ ተሽከርካሪ ሲያቆሙ ወይም ተሽከርካሪዎ በሚንሸራተትበት ወቅት ለመቆጣጠር በሚሞክሩበት ወቅት ይጠቀሙ።



ይህን ዘዴ ሲጠቀሙ፣ እጆችዎ 9 እና 3 ወይም 10 እና 2 ላይ መሆን አለባቸው።



ሲታጠፉ መሪዉን ለመጨበጥ አንዱን እጅዎ በሌላኛው እጅ ላይ በማሳለፍ እንደአስፈላጊነቱ መሪውን ያዙሩ።



የመሪው ሌላ ቦታ ላይ ለመያዝ እንዲያስችሉ ከስር ያለው እጅዎን ከመሪው ያስቀቁት።



መታጠፉን በተረጋጋ ሁኔታ ሲያጠናቅቁ መሪዉን ቀጥ ያድርጉት።



### በአንድ እጅ ብቻ መሪን ማዞር

ተሽከርካሪዎን ወደ ኋላ ሲያሽከረክሩ ወይም ከመሪው ሆነው ሌሎች ለመጠቀም የሚፈልጓቸውን የተሽከርካሪ መቆጣጠሪያዎች (ማጽጃዎች፣ የድንገተኛ አደጋ መብራቶችን፣ መብራቶች ወዘተ) ለመድረስ በአንድ እጅ ብቻ መሪ ማዞርን ይጠቀሙ።

አንድ እጅዎን መሪው ላይ ማስቀመጥ ለተሽከርካሪዎ ሚዛን መጠበቅ እና ወደ ኋላ በሚነዱበት ወቅት ደግሞ መሪዉን ለመቆጣጠር በጣም ወሳኝ ነው።

የ12 ሰዓት አቀማመጥ የሚመከረው ወደ ኋላ ሲነዱ ብቻ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ፣ ከኋላዎ ያለውን የጉዞ መንገድ ለመመልከት ሰውነትዎን ያዙሩ።

## 2.8 | ፍሬን መያዝ

ጥሩ የተሽከርካሪ አያያዝ በማንኛውም ጊዜ ፍጥነትን እና ቦታን በትክክል እና በተቀላጠፈ ሁኔታ የመቆጣጠር ችሎታዎ ላይ የተመሠረተ ነው።

### የፍሬን ግፊት

ምን ያህል የፍሬን ግፊት ማሳረፍ እንዳለብዎት ማወቅ እጅግ ወሳኝ ክህሎት ነው። ይህም በብዙ ልምምድ እና የሚነዱት ተሽከርካሪ በደንብ እያወቁት ሲሄዱ ያድጋል። አራት የፍሬን አያያዝ ደረጃዎች አሉ፦

1. ቀላል
2. መካከለኛ
3. ጠንካራ
4. ድንገተኛ

በሃሳብ ደረጃ፣ መጠቀም ያለብዎት ቀላል እና መካከለኛ የፍሬን አያያዞችን ብቻ ነው፣ ሆኖም ግን ሁልጊዜ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጠንካራ ወይም ድንገተኛ የፍሬን አያያዝ መጠቀም ይችላሉ። እንደ የፍሬን አያያዝ ዘዴ፣ በምናብዎ አንድ እንዲደፋ የማይፈልጉት የኩባያ ወሃ በጭንዎ ላይ እንዳለ ያስቡ።

እንዲሁም ከኋላዎት ያሉትን ሰዎችንም ከግምት ውስጥ ያስገቧቸው። አላስፈላጊ ያልሆኑ ጠንካራ ወይም ድንገተኛ የፍሬን መያዝ በተረጋጋ ሁኔታ እንደሚቆሙ ሲጠብቁ የነበሩ ከኋላዎ ያሉ ሰዎችን ሊያስደነግጥ ይችላል።

## አንቲሎክ የፍሬን አያያዝ ስርዓቶች (ANTILOCK BRAKING SYSTEMS)

የተሽከርካሪዎች ABS (Antilock Brake System፣ አንቲሎክ የፍሬን አያያዝ ስርዓት) አሽከርካሪዎች በአስቸኳይ ፍሬን በሚይዙበት ወቅት መሪውን እንዲያዞሩ በማስቻል ትልቅ የደህንነት ጠቀሜታ ይሰጣል። ABS የማቆሚያ ርቀትዎን አያሳጥርም፣ ነገር ግን የተሻለ የመሪ ቁጥጥር እንዲኖርዎት ያስችላል። በሚበራበት ወቅት፣ ተሽክርካሪዎ ትንሽ ሲንቀጠቀጥ ሊሰማዎት ይችላል።

ጠንካራ ወይም ድንገተኛ የፍሬን አያያዝን በትልቅ፣ ክፍት እና በተስተካከሉ ቦታዎች ላይ ይለማመዱ። ፍሬኑን በደንብ ይጫኑት እና ABS ጎማዎቹ እንዳይቆልፉ ሲከላከል ይመልከቱ።

## 2.9 | ፍጥነት መጨመር

በተረጋጋ ሁኔታ ለመንዳት፣ ከተለያዩ የፍጥነት ደረጃዎች ጋር በደንብ መተዋወቅ እና ምቾት ሊሰማዎት ይገባል። አንዳንድ ጊዜ የሚያስፈልጎት የፍጥነት መጨመር የፍሬን ፔዳሉን መልቀቅ ብቻ የሆነበት ቁም እና ሂድ የትራፊክ ፍሰት ውስጥ የሚሆኑበት ጊዜ ሊኖር ይችላል። አደጋን ለማስወገድ ቶሎ ፍጥነት መጨመር የሚያስፈልግዎ ጊዜያት ሊኖሩ ይችላሉ። ፍጥነት የሚጨምሩበት ዘዴ ልክ እንደ ፍሬን አያይዝ መሆን አለበት — በጭንዎት ላይ የኩባያ ወሃ እንዳለ እና ፍጥነት ሲጨምሩ ማፍሰስ እንደማይፈልጉ ያስቡ።

## 2.10 | ሚዛኑን የጠበቀ ክብደት



ተሽከርካሪዎ መንቀሳቀስ ሲጀምር ሚዛኑ ትንሽ መዛባቱ የተለመደ ነው። የተሽከርካሪዎ ሚዛን ለመጠበቅ ክብደቱ በሁሉም ጎማዎች ላይ በእኩል መጠን መሰራጨቱን ያረጋግጡ። መደበኛ የሆነ ጥገና፣ ትክክለኛ የጎማ ግፊት እና የጎማ አቀማመጥ ፍተሻዎች ይህን እንዲያደርጉ ያስችሉዎታል።



### ጥርቀት (PITCH)

እጅዎን ጠረጴዛ ላይ ሙሉ በሙሉ ይዘርጉ። ጣቶችዎን ያንሱ እና የእጅዎ አንጓ ላይ ግፊት ሲጨምር ይሰማዎታል። አሁን ደግሞ ጣቶችዎን ጠርጴዛው ላይ አስቀምጠው የእጅ አንጓዎን ያንሱ። ይህ የወደፊት እና ወደኋላ የሚደረግ እንቅስቃሴ ጥርቀት(ፒች) ይባላል (እዚህ በቀስቶች ይታያል)።

ፍጥነት ሲጨምሩ፣ የተሽከርካሪው ክብደት ወደኋላ የሚያዘነብል ሲሆን ይህም በተሽከርካሪው ከኋላ በኩል ያለውን ግፊት ይጨምረዋል። በድንገት ሲያቆሙ፣ ክብደቱ ወደ ፊት ያዘነብል እና በተሽከርካሪው ፊትኛ ክፍል ግፊት ይጨምራል።



## ሮል (ROLL)

እጅዎን ጠረጴዛ ላይ ይዘርጉ። ትንሽ ጣትዎ ከጠረጴዛው ጋር እንደተጣበቀ ነገር ግን አውራ ጣትዎ ወደ ሰማይ እንዲያመለክት እጅዎን ያሽከርክሩ። አሁን በተቃራኒው አውራ ጣትዎ በጠረጴዛው ላይ እንዲሆን ያድርጉት። ይህ ከጎን ወደ ጎን የሚደረግ የተሽከርካሪ እንቅስቃሴ ሮል ይባላል (ከላይ በቀስቶች ይታያል)።

ወደ ግራ ሲታጠፉ፣ ሴትሪፉጋል ኃይል ክብደቱን ውጭ ወይም ወደ ተሽከርካሪዎ ቀኝ በኩል ያዛውረዋል። የተሽከርካሪው አካል ወደ አንድ ጎን ያዘነብላል።



## ዮ'ው (YAW)

እጅዎን ጠረጴዛ ላይ ዘርግተው ያቆዩ። ጣቶችዎን ወደ ግራ ያንቀሳቅሱና የእጅ አንጓዎን ደግሞ ወደ ቀኝ ያንቀሳቅሱ። አሁን ጠረጴዛውን እንደምትሰናበቱ በማስመሰል ወደ ኋላ እና ወደ ፊት ያወዛውዙት። ይህ ዮ'ው ይባላል (ከላይ በቀስቶች ይታያል)።

መሪዉን ከጎን ወደ ጎን በፍጥነት ሲያዞሩት፣ የተሽከርካሪዎ ፊት እና ጀርባ በትክክል አንድ ላይ ቀጥ አይሉም። የፊት ጎማዎች መሪዉን ወዳዞሩበት አቅጣጫ የሚዞሩ ሲሆን የኋላዎቹ ደግሞ ትንሽ ሊንሸራተቱ ይችላሉ፤ ይህም የዚግ-ዛግ እንቅስቃሴ ይፈጥራል።

## 2.11 | የተሽከርካሪ ዋቢ ነጥቦች

የተሽከርካሪ ዋቢ ነጥቦች በሚያሽከረክሩት ተሽከርካሪ እና በሚጓዙበት መንገድ ላይ በመመስረት ይወሰናሉ። የተሽከርካሪ ዋቢ ነጥቦችን በደንብ ማወቅ ተሽከርካሪዎን ሲያቆሙ፣ ሲታጠፉ፣ ወደኋላ ሲሄዱ እና ሲቆሙ ርቀትን ለመገመት ይረዳዎታል።

**የተሽከርካሪ ዋቢ ነጥቦች ምሳሌዎች:-**

- የግራ የፊት መብራት
- የኮፈን መሃል
- የጎን ማያ መስታወቶች
- የኋላ መከላከያ




በመስቀለኛ መንገድ ላይ ሲደርሱ የማቆሚያ መስመር ከጎን መስታወትዎ ስር ሲሆን ከመስመሩ ከ3 እስከ 6 ኢንች ርቀት ላይ ነዎት ማለት ነው። ይህ የዋቢ ነጥብ የተሽከርካሪዎ የፊትኛ ጫፍ ክፍል አቀማመጥ ለመወሰን ይረዳዎታል።




የመንገድ መስመር አቀማመጥዎን ለመወሰን፣ የኮፈንዎ መሃል ከመንገድ መስመር ቅቦች ጋር የተስተካከለ መሆኑን ያረጋግጡ። ከተስተካከሉ ከመንገድ መስመሩ ጠርዝ በግምት ከ3 እስከ 6 ኢንች ርቀት ላይ ነዎት።

## 2.12 | ለእርስዎ የማይታዩ ቦታዎች

የማይታዩ ቦታዎች ማለት ከአሽከርካው ወንበር ሆነው ማየት የማይችሏቸው ቦታዎች ናቸው። እነዚህ ቦታዎች ሌላ ተሽከርካሪ፣ ሞተር ሳይክል ነጂን ወይም ብስክሌት ነጂን ሊደብቁ የሚችሉ ስለሆኑ እጅግ አደገኛ ናቸው። ለእርስዎ የማይታዩ ቦታዎች ውስጥ ስላሉ ነገሮች በሙሉ ማወቅ የእርስዎ ሃላፊነት ነው።

ለእርስዎ የማይታዩ ቦታዎችን መቀነስ የሚችሉበት አንዱ መንገድ መስተዋቶችዎን ማስተካከል ነው።

1. መነሳት ሳያስፈልግዎት ከጀርባ መስታወት በኩል ለማየት እንዲችሉ የኋላ መመልከቻ መስታወትዎን ያስተካክሉ።
2. ለእርስዎ የማይታዩ ቦታዎች ለመቀነስ የጎን መስታወቶችዎን ማስተካከል የሚችሉባቸው ሁለት ዘዴዎች አሉ፦ ባህላዊ ወይም የተሻሻለ። በሁለቱም መንገድ በተሽከርካሪዎ ዙሪያ ያለውን ቦታ በአይንዎ መፈለግ አለብዎት። ለእርስዎ የማይታዩ ቦታዎች ክፍት መሆናቸው ለማረጋገጥ ጭንቅላትዎን፣ አንገትዎን እና ሰውነትዎን እስኪታይዎት ድረስ ያንቀሳቅሱ። ማስታወሻ፦ ለመመልከት ጭንቅላትዎን ሲያዞሩ መሪውን ቀጥ አድርገው ይያዙ።
3. አንዳንድ የተሽከርካሪ ደህንነት ቴክኖሎጂ ስርዓቶች የማይታዩ ቦታዎች ላይ ሰው ካለ የሚያስጠነቅቁ ልዩ ባህሪያት አላቸው። ይህ ረዳት መሳሪያ ጠቃሚ ነው፣ ነገር ግን በራስዎ ለማረጋገጥ አይኖችዎን መጠቀምን ልምድ ያድርጉ።

በዙርያዎ ያለውን ሁኔታ ለማወቅ በየጊዜው የሚከተሉትን ነገሮች ያረጋግጡ፦

1. ከፊት ለፊትዎ ያለው ቦታ

2. የኋላ ማያ መስታወት ይመልከቱ

3+4. የጎን ማያ መስታወቶችዎ

5+6. ከትከሻዊ ጀርባ ይመልከቱ




## የእይታ ቅኝቶች

ለሌሎች ተሽከርካሪዎች የማይታዩ ቦታዎችንም ልብ ሊሉ ይገባል። ከእነዚህ ቦታዎች ለመራቅ የተቻልዎትን ያድርጉ። አሽከርካሪው በግልጽ እንዲያይዎት ፍጥነት መጨመር ወይም መቀነስ ይችላሉ።

እንደ አውቶብሶች፣ ተንቀሳቃሽ የመኪና ቤቶች እና የንግድ ሞተር ተሽከርካሪዎች ላሉ ትላልቅ ተሽከርካሪዎች ልዩ ትኩረት ይስጡ። ትልቅ የማይታዩ ቦታዎች አሏቸው አንዳንድ ጊዜም “ምንም የማይታዩ ቦታዎች (no zones)” ተብለው ይጠራሉ። ይህም በዚያ ዞን ውስጥ የሚጓዙ ተሽከርካሪዎች መኖር ስለሌለባቸው ነው።

በትላልቅ ተሽከርካሪዎች ዙሪያ በሚጓዙበት ወቅት አስተዋይ እና ንቁ ይሁኑ። ልብ ይበሉ፦ መስታወቶቻቸውን ማየት የማይችሉ ከሆነ፣ አሽከርካሪው እርስዎን ማየት አይችሉም ማለት ነው።



**ያሻሽሉ**
ለእርስዎ የማይታዩ ቦታዎችን በተቻለ መጠን ለመቀነስ መስተዋቶችዎን ያስተካክሉ። ለመንዳት በተቀመጡ ቁጥር መስታወቶችዎን እንደገና ያረጋግጡ።

**ንቁ ይሁኑ**
በእርስዎ ዙርያ ስለሚሆነው ነገር ሁሉ ማወቅ አለብዎት። ሊከሰቱ የሚችሉ የመንዳት ሁኔታ ለውጦችን ለማወቅ በየጊዜው መስታወቶችዎን ይመልከቱ።

## 2.14 | መንዳት ከመጀመርዎ በፊት

ለመንዳት ሲዘጋጁ ማድረግ ያለብዎት ጥሩ ልምዶች የሚከተሉት ናቸው፦

1. **ከተሽከርካሪዎ ውጪ ያለውን ነገር ይመልከቱ።** በጎማዎች ውስጥ እንግዳ ነገሮች፣ በአከባቢው የተሰበረ መስታወት፣ ወይም ከተሽከርካሪው ስር የፈሳሽ መፍሰስ አለ? ሌሎች እንቅፋቶች፣ ልጆች፣ የቤት እንስሳዎች ወይም ከአየር ሁኔታ ጋር የተገናኙ እንቅፋቶች አሉ?
2. **የተሽከርካሪዎ ውስጥ ይፈትሹ።** በመሳሪያው ፓነል ላይ ማስጠንቀቂያዎች አሉ? ሁሉም መስኮቶች እይታን ከሚጋርዱ ነገሮች የጸዱ ናቸው? ያልታሰሩ ንብረቶች በጥንቃቄ ተይዘዋል?
3. **ሁሉንም የውስጥ መስተካከሎች ትክክል መሆናቸውን ያረጋግጡ።** መስታወቶችዎ ተስተካክለዋል? መቀመጫው እና መሪው ትክክለኛ ቦታ ላይ ናቸው? የደህንነት ቀበቶዎ ታስሯል? ስልክዎ ደምጸ ከል ሆኗል እና ከእርስዎ ርቆ ተቀምጧል?
4. **ራስዎን ይፈትሹ።** ጤናማ እና ጥሩ ስሜት እየተሰማዎት ነው? ትኩረትዎን መንዳት ላይ ሙሉ በሙሉ ለማድረግ ዝግጁ ነዎት? ብልህ ውሳኔዎች ለመወሰን የሚያስችል የተረጋጋ ስሜት ውስጥ ነዎት?

# ምዕራፍ 3
# አሽከርካሪዎች



## 3.0 | ከመሪው በስተጀርባ ነዎት

እንደ አሽከርካሪ፣ የተለያዩ ተሽከርካሪዎችን፣ መንገዶችን እና ሰዎችን ያካተተ የማህበረሰብ አካል ነዎት። የዚህ ማህበረሰብ ስምምነት አሽከርካሪዎች ከአካባቢያቸው ጋር እና እርስ በርስ በደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እና ኃላፊነት ባለው መስተጋብር ላይ የተመሰረተ ነው። በማሽከርከርዎ ላይ ተጽዕኖ የሚያደርጉ ብዙ የግል ምክንያቶች አሉ፣ ነገር ግን አብዛኛዎቹ ሰዎች ዓላማቸው አንድ ነው፦ ወደሚሄዱበት ቦታ በሰላም መድረስ።

**ጥሩ አሽከርካሪ ለመሆን የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፦**

1. ስለራስዎ፣ ስለሌሎች እና በማህበረሰቡ ላይ ያለዎትን ተፅእኖ ከግምት ውስጥ ማስገባት።
2. ለመንገድ ደንቦች ያለብዎትን ኃላፊነት መወጣት።
3. ተሽከርካሪዎ እንዴት እንደሚሰራ እና ቦታ እንደሚይዝ ማወቅ።
4. ታጋሽ እና የተረጋጋ ስብዕና መያዝ።

እንደ አሽከርካሪ የረጅም ጊዜ ስኬትዎ የሚወሰነው በሚማሩበት ጊዜ በሚፈጥሯቸው ልማዶች ላይ ነው። ሲለማመዱ ሆን ብለው ይለማመዱ። ብልህ እና አስተማማኝ ልማዶችን ያዳብሩ፣ ለምሳሌ ሁልጊዜ ከትከሻዎ በላይ በመመልከት ለእርስዎ የማይታዩ ቦታዎች ለመፈተሽ መፈተሽ፣ ይህም ልምድ ይሆናል። ይህ በየጊዜው በሚለዋወጡ የመንዳት ሁኔታዎች ላይ የበለጠ እንዲያተኩሩ ያስችልዎታል። መጀመሪያ ላይ ከባድ ሊመስልዎ ይችላል፣ ነገር ግን ከመሪ በስተጀርባ የበለጠ ልምድ ባዳበሩ ቁጥር የተሻለ አሽከርካሪ ይሆናሉ።

## ጤና

ማሽከርከር በአካል እና በአእምሮ ጤናማ እንዲሆኑ ይጠይቃል።

ዕለታዊ ጭንቀቶች በጤንነትዎ ላይ በቀላሉ ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላሉ። መጥፎ የሆነ ጉንፋን የአዕምሮ ሂደቶችን ሊያዘገይ እና የሰውነት ህመም ያስከትላል። ራስ ምታት ወይም በትከሻዎ ላይ ያለው ውጥረት ተሽከርካሪውን የመቆጣጠር ችሎታዎን ሊቀንስ ይችላል። ውጥረት ከመሪው በስተጀርባ ጥበብ የተሞላበት ውሳኔ የማድረግ ችሎታዎ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። በርካታ የጤና ተግዳሮቶች ማሽከርከርዎ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ። የማሽከርከር ችሎታዎ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ስለሚችሉ ሁኔታዎች ስጋት ካለዎት ሐኪምዎን ያነጋግሩ።

ሞተር ከማስነሳትዎ በፊት ራስዎን ለመፈተሽ ትንሽ ጊዜ ይውሰዱ። ጥበብ የተሞላበት ውሳኔ ለመወሰን፣ ስን የመግዛት ባሕርይ ለማዳበርና ሁኔታውን በሚገባ ለመረዳት የሚያስችል ጤንነት አለዎት? በጥቂቱ በጥልቀት ይተንፍሱ እና በማሽከርከር ላይ ያተኩሩ። ጥሩ ስሜት ካልተሰማዎት ነገር ግን የሆነ ቦታ መሄድ ካለብዎት፣ እባክዎን ሌላ ሰው እንዲያሽከረክር ያድርጉ።

## አካላዊ ጤንነት

አካላዊ ጤንነትዎ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። ደህንነቱ የተጠበቀ እና ውጤታማ አሽከርካሪ የመሆን ችሎታዎ ላይ በቀጥታ ተጽዕኖ ያሳድራል። ከመሪው በስተጀርባ ከመሆንዎ በፊት በጥሩ ጤንነት ላይ እንደሆኑ እና **በአልኮል ወይም በሌሎች አደንዛዥ ዕጾች ተጽዕኖ ስር አለመሆንዎን** ያረጋግጡ።

## እይታ

ጥሩ እይታ ደህንነቱ ለተጠበቀ ማሽከርከር በጣም አስፈላጊ ስለሆነ መንጃ ፈቃድ ከማግኘትዎ በፊት ሕጉ የአይን የማየት ችሎታ ምርመራ እንዲያልፉ ያስገድዳል። በግልጽ ማየት ካልቻሉ የትራፊክ አደጋዎችን የመለየት እና ለችግሮች ምላሽ የመስጠት ችግር ያጋጥምዎታል። በደንብ ማየት ደህንነቱ ለተጠበቀ ማሽከርከር አስፈላጊ ነው።

**የማስተካከያ ሌንሶችን ለማድረግ ከተገደዱ:-**

- በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ሁልጊዜ ያድርጓቸው።
- ምሽት ላይ ጨለማ ወይም ባለቀለም የማስተካከያ ሌንሶችን ከመጠቀም ይቆጠቡ።

**የእይታ አስፈላጊ ገጽታዎች:-**

- **የጎን እይታ።** ወደፊት እየተመለከቱ ሳሉ ተሽከርካሪዎችን እና ሌሎች ችግሮችን ከዓይንዎ ጥግ ላይ ማየት ይችላሉ።
- **ርቀትን እና ፍጥነትን መገመት።** በደንብ ማየት መቻል ከሌሎች ተሽከርካሪዎች፣ እግረኞች እና ሌሎች አደጋዎች ምን ያህል ርቀው እንዳሉ ለማወቅ ይረዳዎታል።

## በምሽት ማየት

አንዳንድ አሽከርካሪዎች በጨለማ ውስጥ በሚያሽከረክሩበት ወቅት ከፊት ለፊት በሚመጣው የፊት መብራቶች ነጸብራቅ ይረበሻሉ። በምሽት የማየት ችግር ካለብዎት፣ ከሚያስፈልገው በላይ አያሽከርክሩ እና በሚያሽከረክሩበት ጊዜ በጣም ይጠንቀቁ።

- የፊት መብራቶችዎ መብራታቸውን ያረጋግጡ።
- የመንገዱን ቀኝ ጠርዝ በመመልከት እና እንደ የማሽከርከር መመሪያ በመጠቀም የሚመጡትን የመብራቶች ነጸብራቅ ያስወግዱ።
- የፊት መብራቶች በትክክል ማነጣጠራቸውን ያረጋግጡ። በትክክል ያላነጣጠሩ የፊት መብራቶች ለሌሎች አሽከርካሪዎች ማየትን አስቸጋሪ ያደርጋሉ እና መንገዱን የማየት ችሎታቸውን ይቀንሳሉ።
- ፍጥነትዎን ይቀንሱ እና የሚከተሉበትትን ርቀት ይጨምሩ። የፊት መብራቶችዎ በሚፈጥሩት የብርሃን አካባቢ ውስጥ ማቆም መቻል አለብዎት።

## መስማት

የጥሩምባ፣ የሳይረን ወይም የሚሰቀጥጥ የጎማ ድምፅ አቅጣጫ ሊጠቁምዎ ወይም አደጋን ሊያስጠነቅቅዎ ይችላል። እንደ እይታ ሁሉ የመስማት ችግርም ቀስ በቀስ ሊከሰት ስለሚችል ብዙውን ጊዜ ለማወቅ አስቸጋሪ ናቸው። የመስማት ችሎታ የሌላቸው ወይም የመስማት ችግር ያለባቸው አሽከርካሪዎች በእይታ ላይ የበለጠ መተማመንን በመማር እና የበለጠ ንቁ በመሆን ማስተካከል ይችላሉ።

ገመድ አልባ የጆሮ ማዳመጫዎችን፣ የጆሮ ማዳመጫዎችን ወይም ድምጽን የሚያሰራጩ ወይም የሚሰርዙ የጆሮ ማዳመጫዎችን አድርጎ ተሽከርካሪ መንዳት በህግ የተከለከለ ነው።

የWashington የአስተዳደር ህግ (Washington Administrative Code) ቁጥር 204-10-045ን የሚያከብር ከሆነ ከእጅ ነጻ የሆነ መሳሪያ በአንድ ጆሮ መጠቀም ይችላሉ።

**ያስታውሱ፦** የተማሪ ፈቃድ ወይም መካከለኛ ፈቃድ ካለዎት፣ ከእጅ-ነጻ ቢሆንም እንኳ ሞባይል ስልክ ወይም ማንኛውንም ተንቀሳቃሽ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ መጠቀም አይችሉም።

ቤት ደርሰዋል!

እኔም! ❤❤❤

ተመሳሳይ። ጥሩ ምሽት አሳልፌያለው

## ወደ ቤት በሰላም ይግቡ። ወደ ውጪ ከመውጣትዎ በፊት ሰካር የሌለበት ጉዞ ያቅዱ።

TOGETHER WE GET THERE

## 3.1 | በተጽዕኖ ስር ሆኖ መንዳት

በተጋላጭ ሁኔታ ማሽከርከር የሚከሰተው ማንኛውም ነገር በትክክል ማሰብን፣ ፈጣን ምላሽ መስጠትን ወይም መኪናዎን መቆጣጠርን አስቸጋሪ በሚያደርግበት ጊዜ ነው። ይህ እንደ አልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅ ወይም ድካም ያሉ ነገሮችን ያካትታል። እነዚህ ሁሉ እርስዎን፣ ተሳፋሪዎችዎን እና በመንገድ ላይ ያሉ ሌሎችን አደጋ ላይ ሊጥሉ ይችላሉ።

በአልኮል ወይም በአደገኛ ዕፆች ምክንያት በተጽዕኖ ስር ሆኖ መንዳት ቅጣቶች በጣም ከባድ ናቸው፦ ከፍተኛ የገንዘብ ቅጣቶች፣ ከፍተኛ የኢንሹራንስ መጠኖች፣ የመንጃ ፈቃድ እገዳ ወይም መነጠቅ እና የእስር ቅጣትንም ያካትታሉ።

ልምድ ያለው አሽከርካሪ እንኳን አልኮል ከጠጡ ወይም አደንዛዥ ዕፅ ከወሰዱ በኋላ በደህና ማሽከርከር አይችሉም። በተፅእኖ ስር ሆኖ በጭራሽ ላለመንዳት መምረጥ ህይወትን ያድናል፦ የእርስዎን እና ሌሎችን።

### አልኮል እና መንዳት

አልኮል በተጽዕኖ ስር ሆኖ የመንዳት አደጋ ውስጥ የሚካተት የተለመደ የሚያሰክር ንጥረ ነገር ነው። ለሌሎች በተጽዕኖ ስር ሆኖ የመንዳት ባህሪ ሲያሳዩ ንቁ ይሁኑ እና ቦታ ይልቀቁላቸው።

**አልኮል የሚከተሉትን በማስከተል አሽከርካሪዎች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፦**

- የመፍታታት እና የእንቅልፍ ስሜቶችን መፍጠር።
- ብዥ ያለ ወይም የተገደበ እይታ።
- ምላሽ መስጫ ጊዜ፣ ትኩረት የመስጠት እና አካባቢን የመቃኘት ችሎታ መቀነስ።
- ምን እየተፈጠረ እንዳለ የመረዳት ችግር።
- እንደ የመንገድ መስመር ውስጥ መቆየት እና ሌሎች ትራፊኮችን ማስወገድ ያሉ ብዙ ተግባራትን በአንድ ጊዜ ለመስራት መቸገር።
- የመንገድ ደንቦችን ማክበር አለመቻል።
- ከመጠን በላይ በራስ መተማመን፣ ይህም ወደ አደገኛ የመንዳት ባህሪ ሊያመራ ይችላል።

**እባክዎ፡-**

- አደንዛዥ ንጥረ ነገሮችን ከወሰዱ ማንኛውንም ተሽከርካሪ አያሽከርክሩ።
- ማንኛውንም ዓይነት ወይም መጠን ያለው አደንዛዥ ንጥረ ነገር ከወሰደ አሽከርካሪ ጋር አይጓዙ።
- ጓደኞች ወይም ቤተሰብ አልኮል እየጠጡ ወይም አደንዛዥ ዕፅ እየወሰዱ ከነበረ እንዲነዱ አይፍቀዱላቸው።
- ጠንቃቃ አሽከርካሪ ያቅዱ።

## ካናቢስ እና መንዳት

ማሪዋና፣ THC (Tetrahydrocannabinol)፣ የቴትራሃይድሮካናቢኖል ካናቢስ መጠን) እና ሌሎች የካናቢስ ምርቶችን (የሚበሉ፣ ተለጣፊዎች፣ ቬፖች፣ ቲንክቸሮች እና ቶፕቲካሎች ለመዝናኛ መጠቀም 21 አመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች ህጋዊ ነው፣ ነገር ግን ማንኛውንም ካናቢስ ከወሰዱ በኋላ ማሽከርከር ለሁሉም እድሜ ህገወጥ ነው።

**ለማሽከርከር አስተማማኝ የካናቢስ መጠን የለም።**

ጥናቶች እንደሚያሳዩት ካናቢስ አሽከርካሪዎችን በተለያዩ መንገዶች ሊያደነዝዝ ይችላል፡-

- ትኩረት መስጠት፣ የምላሽ ጊዜ እና የቅንጅት መቀነስ
- መኪና መቆጣጠር መቀነስ
- ቀርፋፋ የምላሽ ጊዜ
- ርቀቶችን መገመት አለመቻል
- የእንቅልፍ ስሜት መጨመር
- መኪና የመቆጣጠር ችሎታ ማጣት
- ዘገምተኛ የአዕምሮ እና የአካል ተግባራት

# መድሃኒቶች እና መንዳት

**ተጽዕኖ ስር ለመሆን ከአንድ በላይ መንገዶች አሉ።**

በተጽዕኖ ስር ሆኖ መንዳት በአጠቃላይ ከአልኮል፣ ከካናቢስ ወይም ከህገወጥ ዕፅ አጠቃቀም ጋር የተያያዘ ነው። ሆኖም ግን፣ በርካታ በህጋዊ መንገድ የሚገኙ እና በተለምዶ ያለማዘዣ እና በሐኪም የታዘዙ መድሃኒቶች በተጠቃሚውን ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ የማሽከርከር ችሎታ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ።

- አንድ መድሃኒት ህጋዊ ነው ማለት በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ለመጠቀም አስተማማኝ ነው ማለት አይደለም።
- በተጽዕኖ ስር ሆኖ መንዳት በወንጀል የሚያስቀጣ ባህሪ ነው። መድሃኒቱ የታዘዘ፣ ያለ ማዘዣ የተገኘ፣ በችርቻሮ ሁኔታ የተገዛ ወይም እንደ ህገወጥ ንጥረ ነገር ተደርጎ ቢቆጠርም እንኳን ምንም ለውጥ የለውም።

ለራስ ምታት፣ ለጉንፋን ወይም ለአለርጂ የሚወሰዱ ያለሐኪም ትዕዛዝ የሚሰጡ መድኃኒቶች አንድን ሰው እንቅልፍ እንዲጫናቸው ያደርጋሉ፣ ይህ ደግሞ መንዳት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል። እንደ አልኮል፣ በሐኪም የሚታዘዙ መድሐኒቶች ያሉት በቅጽበታዊ ምላሽዎችዎ፣ በአመለካከትዎ፣ በእይታዎ እና በንቃትዎ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ።

ለመጀመሪያ ጊዜ በሐኪም የታዘዙ መድኃኒቶችን መውሰድ ከጀመሩ፣ አዲስ በሐኪም የታዘዘ መድኃኒት መውሰድ ከጀመሩ ወይም አሁን የሚወስዱትን መድኃኒት ከፍተኛ መጠን መውሰድ ከጀመሩ አያሽከርክሩ። በእርስዎ ውሳኔ፣ ቅንጅት እና የምላሽ ጊዜ ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ እንዳለው እስኪያውቁ ድረስ ይጠብቁ። ሐኪምዎን ወይም የፋርማሲ ባለሙያዎን ያነጋግሩ። ከማሽከርከርዎ በፊት ሁሉንም የማስጠንቀቂያ መለያዎች ያንብቡ። “ከባድ ማሽነሪዎችን ማንቀሳቀስ” የሚከለክሉ ማስጠንቀቂያዎች ተሽከርካሪ መንዳትን ያጠቃልላሉ።

አንዳንድ መድሃኒቶች በራሳቸው ተጽዕኖ ላያሳድሩ ይችላሉ፣ ነገር ግን ከሁለተኛው መድሃኒት ጋር ወይም ከአልኮል ጋር ከተወሰዱ ከባድ እክል ሊያስከትሉ ይችላሉ። በርካታ መድሃኒቶች የአልኮል ተጽዕኖን ያባብሳሉ ወይም ሌሎች የጎንዮሽ ጉዳቶች አሏቸው። ከመውሰድዎ በፊት በመድሃኒትዎ ላይ ያሉትን ማስጠንቀቂያዎች ያንብቡ ወይም የፋርማሲ ባለሙያዎ ጋር ይነጋገሩ እንዲሁም በተመሳሳይ መድሃኒቱን ይውሰዱ።

## ብዙ መድሃኒቶችን መጠቀም እና መንዳት

ብዙ መድሃኒቶችን መጠቀም ከአንድ በላይ መድሃኒት መቀላቀል ወይም መውሰድ ነው። አልኮል፣ ካናቢስ ወይም ሌሎች መድሃኒቶችን መቀላቀል አንድ ከማንኛውም መድሃኒት በራሱ ብቻ ካለው የበለጠ ተጽዕኖ ሊያስከትል ይችላል። አልኮል፣ ካናቢስ፣ ሕገወጥ መድኃኒቶች፣ በሐኪም የታዘዙ መድኃኒቶች፣ ያለሐኪም ትዕዛዝ የሚገዙ መድኃኒቶች፣ እና እንደ ቁጥጥር የማይደረግባቸው መድኃኒቶች እና በእስትንፋስ የሚወሰዱ ሌሎች ንጥረ ነገሮችን ሊያካትት ይችላል። ብዙ መድሃኒቶችን መጠቀም ለሞት በሚዳርጉ አደጋዎች ውስጥ በጣም የተለመደ አደንዛዥ ነገር ነው።

ብዙ መድሃኒቶችን የመጠቀም ተጽዕኖዎች ከሰው ወደ ሰው ይለያያሉ እና እንደ የመድኃኒቱ ብዛት፣ የአጠቃቀም ድግግሞሽ እና አወሳሰድ ላይ ይወሰናል። ብዙ መድሃኒቶችን መጠቀም ከልክ በላይ መውሰድን፣ የአእምሮ ጤና ችግሮችን፣ አደገኛ ባህሪን፣ ከባድ ጉዳቶችን እና አደጋ የመከሰት እድል መጨመር ሊያስከትል ይችላል።

## በድካም እና በእንቅልፍ ስሜት ውስጥ ሆነው መንዳት

ድካም የሚከሰተው በአካል ወይም በአእምሮ ውጥረት፣ በተደጋገሙ ስራዎች፣ በህመም ወይም በእንቅልፍ እጦት ነው። ልክ እንደ አልኮል እና አደንዛዥ ዕጾች፣ ድካም እይታዎን እና የማመዛዘን ችሎታዎን ይጎዳል።

በእንቅልፍ ስሜት ውስጥ ሆኖ ማሽከርከር የእርስዎን ንቃት፣ ትኩረት፣ የምላሽ ጊዜ፣ የማመዛዘን ችሎታዎን እና የመወሰን ችሎታዎችዎ ላይ ተጽእኖ ያደርጋል። ደክሞዎት በሚያሽከረክሩበት ጊዜ፣ ከመሪው ጀርባ የመተኛት ስጋት ያስክርትላል እና የአካል ጉዳት ወይም ሞትን የሚያስከትል አደጋ ሊያጋጥምዎት ይችላል።

አንዳንድ የድካም ምልክቶች እነሆ። **የሚከተሉት ካጋጠምዎ መኪናዎን አቁመው እረፍት ያደረጉ፡-**

- ለማተኮር ይቸገራሉ ወይም የነዱትን መጨረሻዎቹን ጥቂት ማይሎች ማስታወስ ካልቻሉ።
- አይንዎ በተደጋጋሚ ከተርገበገበ ወይም የዐይን ሽፋኖችዎ ከከበድዎ።
- ራስዎን ቀና ለማድረግ ከተቸገሩ።
- መውጫዎች ወይም የትራፊክ ምልክቶች ከሳቱ።
- የመቅበጥበጥ፣ የንዴት ወይም የጠበኝነት ስሜት ከተሰማዎ።
- ከመንገድ መስመርዎ ከወጡ፣ ከተወዛወዙ፣ ርቀት ሳይጠብቁ ከነዱ እና/ወይም ወጣገባ መንገድ ከመቱ።




ከሌላ አሽከርካሪ ጋር እየተጓዙ ከሆነ፣ ተራ በተራ ያሽከርክሩ። ብቻዎን እየተጓዙ ከሆነ እና ድካም ከተሰማዎ መኪናዎን መንገድ ዳር አቁመው ለ20 ደቂቃ እረፍት ይውሰዱ። የመኪና አደጋ ከማስከተል ይልቅ አቁሞ መተኛት የተሻለ ነው።

ከጉዞ በፊት፦

- በቂ እንቅልፍ ያግኙ – ብዙ ሰዎች ንቁ ሆነው ለመቆየት ከ7 እስከ 9 ሰዓታት መተኛት ያስፈልጋቸዋል።
- በረጅም ጉዞዎች ጊዜ በየ100 ማይል ወይም በየ2 ሰዓቱ ለማቆም ያቅዱ።
- ይራመዱ፣ ነፋሻማ አየር ያግኙ እና ውሃ ይጠጡ። ለእረፍት ብዙ ጊዜ በመመደብ ጉዞዎን ያቅዱ።
- ንቁ ሆነው እንዲቆዩ፣ ችግሮችን እንዲመለከቱ እና ማሽከርከር ለመጋራት እንዲረዳዎት የጉዞ ጓደኛ ያዘጋጁ።

## የአዕምሮ ጤና

ስሜቶች ማሽከርከርዎ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ። ስሜቶችዎ ባህሪዎ ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ሲረዱ የተሻሉ ውሳኔዎችን ያደርጋሉ።

ለምሳሌ፣ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ጭንቀት ከተሰማዎት፣ ሊዘናጉ እና በእግርዎ የፍጥነቱ መስጫ ፔዳሉ ላይ በጣም ሊጭኑ ይችላሉ። የሚሰማዎት ስሜት (ጭንቀት) ባህሪዎን (በፍጥነት መንዳት) ይቀይራል።

ከዚህ በታች መንገድ ላይ ከመውጣትዎ በፊት ለመረጋጋት እና ጭንቀትን ለማስወገድ የሚረዱ ጥቂት ዘዴዎች አሉ። በቆመ መኪና ውስጥ ተቀምጠው ሊያደርጉዋቸው ይችላሉ።

1. በአፍንጫዎ ወደ ውስጥ ይተንፍሱ እና ትኩስ ሾርባን ለማቀዝቀዝ እንደሚሞክሩት ወደ ወጪ በቀስታ ይተንፍሱ።

2. ከ1 እስከ 20 ይቁጠሩ፣ ወይም ከ100 በሦስት ወደ ኋላ ይቁጠሩ (100፣ 97፣ 94፣ 91፣ 88...)። በአዕምሮ ውስጥ ያለውን ሁሉ ጸጥ ለማድረግ በቁጥሮች ላይ ብቻ ያተኩሩ።

3. ለጉዞዎ ሰፋ ያለ ጊዜ ይመድቡ። ለራስዎ እና ለሌሎች ታጋሽ መሆንን ይምረጡ።

ስሜታዊ ግንዛቤ ትዕግስት እና በመንገድ ላይ ላሉት ሰዎች አክብሮትን ያበረታታል እና ደህንነቱ የተጠበቀ የመንዳት ባህሪን ያዳብራል።

## ግልፍተኛ ማሽከርከር

**ግልፍተኛ ማሽከርከር የትራፊክ ጥፋት ነው።**

ግልፍተኛ ማሽከርከር አሽከርካሪው ሆን ብሎ ሰዎችን ወይም ንብረትን አደጋ ላይ የሚጥል ነገር ሲያደርግ ነው።

**የሚከተሉት ባህሪያት እንደ ግልፍተኛ ማሽከርከር ይቆጠራሉ:-**

- በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ሌሎች ሰዎችን ወይም ንብረቶችን ሊጎዱ የሚችሉ እርምጃዎችን መውሰድ።
- ሌሎች ሰዎች ራሳቸውን እንዲጠብቁ የሚያስገድዱ ሆን ተብለው የሚደረጉ ድርጊቶች።

**ግልፍተኛ ማሽከርከር ጋር የተዛመዱ ባህሪያት የሚከተሉትን ያካትታሉ:-**

- በፍጥነት ማሽከርከር።
- በጣም በቅርበት መከተል።
- ጥንቃቄ የጎደለው የመስመር ለውጦችን ማድረግ።
- ተገቢ ያልሆነ ምልክት መጠቀም።
- የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን ማክበር አለመቻል።
- ከመንገዱ ጎን የሚራመድ ወይም ብስክሌት የሚነዳ ሰው ጋር በጣም ተጠግቶ ማሽከርከር።

በሚሰሩት ነገር ላይ ያተኩሩ። የሌሎችን ግልፍተኛ ማሽከርከር ለእርስዎ እንደሆነ አድርገው ላለመውሰድ ይሞክሩ። ለሌሎች የመንገድ ተጠቃሚዎች ታጋሽ እና ይቅር ባይ ይሁኑ።

## መሽቀዳደም እና የመንገድ ላይ ትዕይንቶች

የጎዳና ላይ እሽቅድምድሞሽ እና ያልተፈቀዱ የጎዳና ላይ ትዕይንቶች በጣም አደገኛ ናቸው፣ ቅጣቶቹም ከባድ ናቸው። ይህም የጎዳና ላይ የእሽቅድምድሞሽ እንቅስቃሴዎችን የሚያነሳሱ አሽከርካሪዎች እና ለሚረዳ ማንኛውም ሰው ተፈጻሚ ይሆናል። ጥፋተኛ የሆኑ ተባባሪዎች የገንዘብ ቅጣት፣ የእስር ጊዜ እና ተሽከርካሪቻቸው የመያዝ አደጋ ሊጠብቃቸው ይችላል።

## የመንገድ ላይ ንዴት

**የመንገድ ላይ ንዴት በወንጀል የሚያስቀጣ ድርጊት ነው።**

የመንገድ ላይ ንዴት በመንገድ ላይ ለተከሰተ ነገር ቁጣዊ ምላሽ መስጠት ሲሆን ይህም በተሽከርካሪ ወይም በሌላ መሣሪያ ጠበኛ ባህሪን የሚያስከትል። የመንገድ ላይ ንዴት በተሽከርካሪ አሽከርካሪ ወይም ተሳፋሪ እና በሌላ አሽከርካሪ፣ ተሳፋሪ ወይም መንገዱን በሚጠቀም ሰው መካከል ሊፈጠር ይችላል።

በርካታ ነገሮች ለመንገድ ላይ ንዴት አስተዋፅዖ ያደርጋሉ፣ ይህም ጭንቀትን፣ የተጣበቡ መርሃግብሮችን፣ ትራፊክን ወይም ከማሽከርከር ጋር ያልተያያዙ ብስጭቶችን ያካትታል። ለመጓዝ ብዙ ጊዜ ይመድቡ፣ በተሽከርካሪዎ አካባቢ ደህንነታቸው የተጠበቁ የቦታ ህዳጎችን ይፍጠሩ እና ለሌሎች ሰዎች ምሕረት ለማሳየት ይሞክሩ።



## የመንገድ ላይ ንዴት እያጋጠምዎት ከሆነ

የሚከተሉት ከሆኑ የመንገድ ላይ ንዴት እየተሰማዎት ሊሆን ይችላል፦

- በመንገድ ላይ በሚገኙ ሌሎች ሰዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የጠላትነት ወይም የጥቃት አስተሳሰብ መያዝ።
- በመንገድ ላይ ያሉ ሌሎች ሰዎችን እና በተሽከርካሪዎ ውስጥ ያሉ ተሳፋሪዎችን በቃላት መቃወም።
- ስለማይስማሙባቸው የትራፊክ ደህንነት ህጎችን አለማክበር።
- በጣም በቅርበት መከተል።
- በፍጥነት ማሽከርከር።
- በመንገድ ላይ መስመሮች መካከል በፍጥነት መንቀሳቀስ።
- የትራፊክ መብራትን ለመቅደም በፍጥነት ማሽከርከር።
- የመንገድ ላይ መስመሮችን ለመለወጥ በተሽከርካሪዎች መካከል መግባት።
- የተሽከርካሪዎን ጥሩምባ ከመጠን በላይ መጠቀም።
- በሚመጣው ትራፊክ ላይ የፊት መብራቶችን ከመጠን በላይ ማብራት ማድረግ።
- ከኋላዎ ያለው አሽከርካሪ በጣም በቅርበት እንዳይከተል ለማስቆም ፍሬን መያዝ።
- ትራፊክን ማለፍ እና ከዚያ ለሌላኛው አሽከርካሪ ትምህርት ለመስጠት ፍጥነት መቀነስ።

## የመንገድ ላይ ንዴቱ ሰለባ ከሆኑ

በዙሪያዎ ያሉ ሌሎች አሽከርካሪዎች በንዴት ሲንቀሳቀሱ ወይም ምላሽ ሲሰጡ ሲመለከቱ ራስዎን በአካል እና በአዕምሮ ከሁኔታው ያርቁ።

- በጥልቀት ይተንፍሱ እና ከመንገዱ ይውጡ።
- ግልፍተኛ ፍጥነት መጨመርን፣ ጡሩምባ ማጮህን ወይም የእጅ ምልክቶችን ያስወግዱ።
- አይኖችዎን በመንገዱ ላይ ያተኩሩ።
- ሌላ አሽከርካሪ እየተከተለዎት ወይም እያስቸገረዎት እንደሆነ ከተሰማዎት ወደ ሌሎች ሰዎች እና ክፍት ንግዶች ወደሚገኙበት አካባቢ ይንዱ። አስፈላጊ ከሆነ ለፖሊስ ይደውሉ።

## የመንገድ ላይ ንዴትን ሪፖርት ማድረግ

በሂደት ላይ ያለ የመንገድ ላይ ንዴትን በፍጥነት ወደ 911 በመደወል ሪፖርት ያድርጉ።

የመንገድ ላይ ንዴትን እና ግልፍተኛ ማሽከርከርን መቀነስ ለWashington ግዛት አውራ ጎዳና (Washington State Patrol) ተልዕኮ ወሳኝ ነው። የትራፊክ ፖሊሶች እና ሌሎች የህግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች ሁልጊዜ ግልፍተኛ ማሽከርከርን እየተጠባበቁ ሳለ፣ Washington ውስጥ የትራፊክ ደህንነትን ለማሻሻል የሚደረጉ እርምጃዎች የሚወሰዱት ነዋሪዎች እርምጃ ሲወስዱ ነው።

ግልፍተኛ ማሽከርከር ድርጊት ካዩ ወይም ሰለባ ከሆኑ፣ እባክዎን ወደ 911 ይደውሉ እና የሚከተለውን መረጃ ያቅርቡ፡-

- ተሽከርካሪዎቹ ለመጨረሻ ጊዜ የታዩበት ቦታ።
- የታርጋ ቁጥር (የሚታወቅ ከሆነ)
- የሚጓዝበት አቅጣጫ (ወደ የት እንደሚሄድ)
- መንገድ ወይም አውራ ጎዳና
- የተሽከርካሪዎቹ ቀለም
- የተሳተፉ መሳሪያዎች (የሚመለከተው ከሆነ)
- የተከሰተው ነገር ማጠቃለያ
- በክስተቱ ውስጥ የነበርዎት ሚና (ተጎጂ ወይም ምስክር)

## 3.2 | በመንገድ ላይ በመረጃ ላይ የተመሰረቱ ውሳኔዎችን መወሰን

ጠንቃቃ እና ኃላፊነት የሚሰማው አሽከርካሪ መሆን የመንገድ ህጎችን ከማወቅ የበለጠ ነገር ይጠይቃል። በሚያሽከረክሩበት ጊዜ በሚያጋጥሙዎት ሁኔታዎች ሁሉ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ማድረግን ያካትታል። በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በየቀኑ በሺዎች የሚቆጠሩ ውሳኔዎችን ያደርጋሉ። ከሚያደርጓቸው በጣም አስፈላጊ ውሳኔዎች መካከል አንዳንዶቹ ከመሪው በስተጀርባ ሲሆኑ ያሉት ናቸው።

## በመንገድ ላይ በመረጃ ላይ የተመሰረቱ ውሳኔዎች አስፈላጊ የሆኑበት ምክንያት

የመንገድ መስመሮችን ከመቀየር አንስቶ እስከ ወደ አውራ ጎዳና መቀላቀል ድረስ ያለ ከመሪው በስተጀርባ የሚወስድ እያንዳንዱ እርምጃ ሁሉ ውሳኔ ነው። በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ማድረግ ማለት እርምጃ ከመውሰድ በፊት ሁሉንም ነገሮች ግምት ውስጥ ማስገባት ማለት ነው። ይህ ለእርስዎ እና ለሌሎች የተመቻቸ እና ደህንነቱ ወደተጠበቀ ማሽከርከርን ያመጣል። በመረጃ የተደገፉ ውሳኔዎች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፦

1. **ግንዛቤን ማሳደግ።** በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ማድረግ ስለ አካባቢዎ የቀጣይነት ያለው ትንተና ያስፈልገዋል። ይህ የእርስዎን አጠቃላይ ሁኔታዊ ግንዛቤን ያሻሽላል።

2. **የኃላፊነት ስሜት ያለው ማሽከርከርን ያበረታታል።** ምርጫዎ የሚያስከትለውን ውጤት መረዳት ኃላፊነት የሚሰማው ባህሪን ያበረታታል። እንዲሁም ለሌሎች የመንገድ ተጠቃሚዎች አክብሮት ያሳያል።

3. **ግጭቶችን መቀነስ**። ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን አስቀድሞ መገመት ግጭቶች የመከሰታቸውን ስጋት ለመቀነስ ይረዳዎታል።

በመረጃ የተደገፉ ውሳኔዎች በሚከተሉት ነገሮችዎ ተጽዕኖ ይደረግባቸዋል፦

- የትራፊክ ህጎች እውቀት።
- በጥንቃቄ የማሽከርከር ልምዶች።
- በእድሜ እና በአእምሮ እድገት ላይ የተመሰረቱ ችሎታዎች።

ታዳጊ አሽከርካሪዎች ለማገናዘብ እና ለውሳኔ አሰጣጥ ተጠያቂ የሆነው የአንጎላቸውን ክፍል አሁንም እየዳበረ መሆኑን ማስታወስ አለባቸው። ይህ ማለት ታዳጊዎች አደጋ የሚያስከትሉ ነገሮችን ለመሞከር ወይም ሁኔታዎችን በተሳሳተ መልኩ ለመረዳት የበለጠ የተጋዝለጡ ሊሆኑ ይችላሉ። ሁሉም አሽከርካሪዎች ከፍጥነት እና ከማህበራዊ ጫና ይልቅ ለደህንነት-ተኮር ውሳኔዎች ቅድሚያ መስጠት አለባቸው። ይህ በተለይ ለታዳጊዎች እውነት ነው።

በእድሜ የገፉ አሽከርካሪዎች የአካል እና የአዕምሮ ችሎታዎች ከእድሜ ጋር እንደሚለዋወጡ ማወቅ ይፈልጋሉ። በእድሜ የገፉ አሽከርካሪዎች በመኪና አደጋዎች በቀላሉ ለከባድ ጉዳቶች ሊጋለጡ ይችላሉ፣ ነገር ግን ብዙዎቹ እስከ እድሜያቸው መጨረሻ ድረስ ደህና እና ብቁ አሽከርካሪዎች ሆነው ይቆያሉ። እድሜያቸው እና ልምዳቸው ምንም ይሁን ምን፣ ሁሉም አሽከርካሪዎች ከመሪው በስተጀርባ በሚሆኑበት ጊዜ ሁሉ በትኩረት ለመከታተል እና ለመሳተፍ ቃል መግባት አለባቸው።

### ጥሩ ውሳኔዎችን ይወስኑ

ጥሩ ውሳኔዎች በመረጃ የተደገፉ ውሳኔዎች ናቸው። ጥሩ ውሳኔዎችን ለመወሰን በአካባቢዎ ያለውን ነገር ማወቅ አለብዎት።

1. ራስዎን በመፈተሽ ለራስዎ ያሳውቁ። በውሳኔዎችዎ ተጽዕኖ ሊያድርባቸው የሚችሉ በዙሪያዎ ያሉትን ሰዎች ጨምሮ ስለ ጠቅላላ ሁኔታው ጥንቃቄ ያድርጉ። ሌሎች ዓላማዎን እንዲያውቁ እና ለእነሱ መዘጋጀት እንዲችሉ ለማድረግ ያሰቡትን ያሳውቁ።

2. በትክክለኛው የመንገድ አቅጣጫ እና በትክክለኛው ፍጥነት ወደ አደጋው ለመድረስ ተሽከርካሪውን ያዘጋጁ።

3. ከማንቀሳቀስዎ በፊት የመጨረሻ ፍተሻ ያድርጉ።

ይህ አቀራረብ እርስዎ ለውጥ እንዲያደርጉ በሚጠይቅ በማንኛውም ሁኔታ ላይ ሊተገበር ይችላል። ሁልጊዜ ንቁ መሆንን፣ ሌሎች ሊገምቱት በሚችሉት መንገድ መንዳትን እና የተረጋጋ መሆንን ኢላማዎ ማድረግ አለብዎት።

## 3.3 | በመንገድ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፍታት

ያልተጠበቁ ሁኔታዎች የማይቀሩ ናቸው እና ለእነዚህ ሁኔታዎች ምላሽ መስጠት ችግሮችን መፍታት ይጠይቃል። በመንገድ ላይ ያሉ ችግሮች ለመፍታት እንደ የሚከተሉት ያሉ የታሰበባቸው ለውጦችን ማድረግ ያስፈልግዎ ይሆናል፦

- ፍጥነትዎን ማስተካከል።
- ስጋትን ለመቀነስ እና አደጋዎችን ለማስወገድ የመንገድ ላይ መስመር ቦታዎን ማስተካከል።
- ሁኔታውን እንደገና ለመገምገም፣ ወደ ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ ለመድረስ አቅጣጫዎን ወይም የጉዞዎን መንገድ መቀየር።

በመንገድ ላይ ያሉ ሌሎች ሰዎችን ላለማስደንገጥ ይሞክሩ። ማናቸውንም ችግሮች ላለመፍጠር ሀሳብዎን ለሌሎች አሽከርካሪዎች ያሳውቁ።

ለአካባቢዎ ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ ዝግጅት የተደረገባቸው ውሳኔዎችን ለመወሰን የተለያዩ መሳሪያዎችን መጠቀም ይችላሉ። አንዱ መሣሪያ OODA (Observe, Orient, Decide, and Act፣ ያስተውሉ፣ ዙሪያዎን ያጢኑ፣ ይወስኑ እና እርምጃ መውሰዱ) ዑደት ነው። እያንዳንዱ ሁኔታ ወደ ሌላ ስለሚያመራ ዑደት ነው።




1. **Observe (ያስተውሉ)።** ሁኔታውን ያስተውሉ። ምን ተለወጠ? የሚወዛወዝ መኪና፣ ድንገተኛ እንቅፋት ወይም የትራፊክ ፍሰት ለውጥ አለ?

2. **Orient (ዙሪያዎን ያጢኑ)።** ያ ለውጥ ምን ማለት እንደሆነ ለመረዳት እውቀትዎን እና ልምድዎን ይጠቀሙ። የእርስዎን እና የሌሎችን ደህንነት ላይ እንዴት ተጽዕኖ ያሳድራል? እርስዎ ካልተቀየሩ ሊሆኑ የሚችሉ አደጋዎች ምን ምንድን ናቸው? ለውጡን ካደረጉ ካደረጉት፣ ምን ዓይነት ዕድሎች እራሳቸውን ይቀርባሉ?

3. **Decide (ይወስኑ)።** በእርስዎ ምልከታ እና ግንዛቤ ላይ በመመስረት፣ በጣም አስተማማኝ የሆነውን የእርምጃ አካሄድ ይምረጡ። ፍጥነትዎን መቀነስ፣ የመንገድ መስመሮችን መቀየር ወይም አላማዎን ማመልከት አለብዎት?

4. **Act (እርምጃ ይውሰዱ)።** የመረጡትን ተግባር በእርጋታ እና በቆራጥነት ይፈጽሙ። ያስታውሱ፣ ግልጽ የሆነ የሐሳብ ልውውጥ ሌሎች ሰዎች ሃሳብዎን እንዲረዱት ወሳኝ ነው።

ልምድ ባካበቱ ቁጥር የOODA ዑደትን በቀላሉ ማሰስ ይችላሉ። ሆኖም ግን፣ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ብዙ ተለዋዋጮች አሉ። ሁልጊዜ ንቁ እና ዝግጁ መሆን ይኖርብዎታል።

# 3.4 | ትኩረትዎ የጎደለው ማሽከርከርን ማስወገድ




ትኩረት የጎደለው ማሽከርከር በመንገዱ ላይ ወይም በአቅራቢያው ላሉት ሰዎች ሁሉ አደጋ የሚፈጥር አሳሳቢ ጉዳይ ነው። ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ለመንዳት የሚያስፈልገውን ግንዛቤ፣ ማስተዋል እና ክህሎት ይረብሸዋል። በተሽከርካሪው ውስጥ እና ውጭ የሚፈጠሩ ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮች ምላሽ የመስጠት እና በአግባቡ የመንቀሳቀስ ችሎታዎ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ።

ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮች በሁሉም ቅርጾች እና መጠኖች ሊመጡ ይችላሉ፦

- **በተሽከርካሪው ውስጥ።** ተንቀሳቃሽ ስልኮች፣ መብላት፣ ሬዲዮ ማስተካከል እና ከተሳፋሪዎች ጋር ያለ መስተጋብር።
- **ከተሽከርካሪው ውጭ።** ቢልቦርዶች፣ ግጭቶች እና የሌሎች ሰዎች ባህሪያት።
- **አካላዊ ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮች።** ድካም፣ ምቾት ማጣት እና የአካል ጉዳቶች።
- **የአዕምሮ ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮች።** የቀን ቅዠት፣ ጭንቀት እና ጠንካራ ስሜቶች።

**ትኩረታቸው የተከፋፈለ አሽከርካሪዎች ለሚከተሉት የበለጠ ተጋላጭ ይሆናሉ፡-**

- ከመንገድ መስመራቸው መውጣት።
- በፍጥነት ወይም በጣም በቀስታ ማሽከርከር።
- የትራፊክ ምልክቶችን፣ የማቆሚያ ምልክቶችን፣ ሞተር ሳይክል ነጂዎችን፣ ብስክሌት ነጂዎችን ወይም እግረኞችን ማየት አለመቻል።
- በመንገድ መስመሩ ውስጥ ያሉ ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ወይም ብስክሌት ነጂዎችን ጋር በጣም በቅርበት መከተል።

**ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮችን ለማስወገድ የሚረዱ ስልቶች፡-**

- አስቀድመው ያቅዱ።
- ስልክዎን አርቀው ያስቀምጡ።
- አስተዋይ ይሁኑ።

**ትኩረትዎን ሙሉ ለሙሉ መንገዱ ላይ በማድረግ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡-**

- በፍጥነት ምላሽ መስጠት።
- የተሻሉ ውሳኔዎችን ማድረግ።
- ሁኔታዊ ግንዛቤን ማሻሻል።
- ውጥረትን እና ድካምን መቀነስ።

## የWASHINGTON ትኩረት የጎደለው ማሽከርከርን የሚቃወሙ ህጎች

ትኩረት የጎደለው ማሽከርከር የአንድን ሰው ትኩረት ዋና ተግባር ከሆነው ማሽከርከር የሚወስድ ማንኛውም እንቅስቃሴ ነው። ሁሉም ትኩረት የሚከፋፍሉ ነገሮች አሽከርካሪውን፣ ተሳፋሪዎችን እና ሌሎች መንገዱን የሚጋሩ እግረኞችን ጨምሮ አደጋ ላይ ይጥላሉ።

የWashington ግዛት ትኩረት የጎደለው ማሽከርከርን የሚከለክሉ ጥብቅ ህጎች አሉት። በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ማንኛውንም የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ (እንደ ተንቀሳቃሽ ስልኮች፣ ጡባዊዎች፣ ወይም የጨዋታ መሳሪያዎች) መያዝ አይችሉም። ይህ እድሜ እና ልምድ ምንም ይሁን ምን፣ ሁሉንም አሽከርካሪዎች ይመለከታል። ከእጅ-ነጻ የሆኑ መሳሪያዎችን መጠቀም ይፈቀዳል፣ ነገር ግን አሁንም አይንዎን እና ትኩረትዎን ከመንገዱ ላይ እንዲያነሱ የሚያደርግ ማንኛውም ነገር አደገኛ ሊሆን

ይችላል። የስልክዎ ማሳወቂያዎቹ፣ ደማቅ መብራቶች፣ እና የእይታ ምልክቶች ሁሉም ጉልህ የሆኑ ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮች ናቸው። ትኩረት የሚከፋፍሉ ነገሮች በማሽከርከርዎ ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ለማወቅ ትንሽ ጊዜ ይውሰዱ።

የህግ አስከባሪ መኮንን ትኩረት የጎደለው ማሽከርከርን የሚቃወመውን ህግ ስለጣሱ ትኬት ሊሰጥዎት ይችላል። ይህ ከባድ ቅጣቶችን ሊያስከትል ይችላል። ከመጀመሪያው ጥሰት በኋላ የሚሰጡ ቅጣቶች በእጥፍ ሊጨመሩ ይችላሉ።

**ማሽከርከር ትልቅ ኃላፊነት ነው።** እባክዎን በመንገዱ ላይ ለማተኮር ይምረጡ እና ትኩረት የጎደለው ማሽከርከርን ለማስቆም የመፍትሄው አካል ይሁኑ። “ሁሉም ሰው የሚያደርገው” ሊመስል ይችላል፤ ነገር ግን ጥናቶች ይህ እውነት እንዳልሆነ ያሳያሉ። ውሳኔዎ የእርስዎን እና የሌሎችን ደህንነት ይጠብቃል።

## 3.5 | ብልህ አሽከርካሪዎች

ብልህ አሽከርካሪዎች የሚከተሉትን ናቸው፦

- በተሽከርካሪው ውስጥ እና ከውጭ ምን እየተከናወነ እንዳለ **የሚያውቁ።**
- የተሽከርካሪዎቻቸውን ፍጥነት፣ ፍሬን፣ መሪውን ማዞር እና ቦታ መቆጣጠር **የሚችሉ።**
- በምልክት እና በተረጋጉ እንቅስቃሴዎች ለሌሎች **ሊተነብዩ** የሚችሉ።
- በውሳኔ አሰጣጣቸው ላይ **አሳቢነት** የሚያሳዩ።
- የማሽከርከር ክህሎቶችን ሲማሩ እና ሲጠቀሙ **ሆን ብለው** የሚያደርጉ።

### ትኩረት ይስጡ

አዲስ አሽከርካሪ በሚሆኑበት ጊዜ ትኩረት መስጠት ያለብዎት የነገሮች በጣም ብዙ እንደሆኑ ሊመስልዎ ይችላል፦ ተሽከርካሪዎ፣ የመንገድ ህጎች፣ አደጋዎች፣ ሌሎች ተሽከርካሪዎች፣ ምልክቶች፣ የመንገድ ላይ ምልክቶች፣ እግረኞች፣ ብስክሌት ነጂዎች... ብልህ አሽከርካሪዎች ትኩረታቸውን ለማመዛዘን መንገድ ያገኛሉ።

- **ትኩረትን መቀየር፡፡** ትኩረትዎን በፍጥነት ከአንድ ነገር ወደ ሌላ ነገር ሲቀይሩ ነው።
- **የተከፋፈለ ትኩረት፡፡** በርካታ ነገሮችን በተመሳሳይ ጊዜ ሲያደርጉ ነው።

- **የተሰበሰበ ትኩረት፡፡** ሙሉ አዕምሮህ በአንድ ተግባር ላይ ሲያተኩር ነው፡፡
- **ቀጣይነት ያለው ትኩረት፡፡** ለረጅም ጊዜ ትኩረት መስጠት ሲኖርብዎት ነው፡፡

**ትኩረት ለመስጠት እንዲረዳዎ ማድረግ የሚችሏቸው ነገሮች፡-**

- በተሽከርካሪዎ ውስጥ ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮችን ማስወገድ፡፡
- በደንብ እረፍት መውሰድ፡፡
- ኤሌክትሮኒክስዎን አርቆ ማስቀመጥ እና ድምጹን ማጥፋት፡፡
- በተሽከርካሪዎ ውስጥ ያሉትን ተሳፋሪዎች እና የቤት እንስሳት ቁጥር መወሰን፡፡
- ከመሪው በስተጀርባ ሆነው ብዙ ስራዎችን ከመስራት መቆጠብ፡፡



## መንገዱን በዕይታ መፈለግ እና መቃኘት

ምስላዊ ፍለጋ ማለት አካባቢዎን በንቃት ለመፈተሽ አይኖችዎን መጠቀም ማለት ነው፡፡ መቃኘት በተሽከርካሪዎ አካባቢ በተቻለ መጠን ማየት እንዲችሉ ጭንቅላትዎን፣ አንገትዎን እና ሰውነትዎን ማንቀሳቀስን ያካትታል፡፡ መፈለግ እና መቃኘት የትኩረት ክህሎቶችዎ በዙሪያዎ ያለውን ሁልጊዜ የሚለዋወጥ አካባቢን እንዲገነዘቡ ያግዛሉ፡- በተሽከርካሪዎ ውስጥ እና ውጭ፡፡ ጥበብ የተሞላባቸው ውሳኔዎችን ለማድረግ መረጃን እንዴት እንደሚሰበስቡ ነው፡፡

የማያቋርጥ የእይታ ፍለጋ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ የማሽከርከር ችሎታዎን ይደግፋል። በትክክል የመፈለግ እና የመቃኘት ችሎታዎን በሚደግፍ ፍጥነት እየተጓዙ እንደሆነ ያረጋግጡ።

**ወደ ፊት ይቃኙ**

በመጨረሻው ደቂቃ ፍሬን መያዝን ወይም በድንገት መታጠፍን ወይም መዞር አስፈላጊነት ለማስቀረት የሚከተሉትን ነገሮች አስቀድመው ይመልከቱ፦

- ዞረው ማለፍ የሚያስፈልግዎ የትራፊክ ሁኔታዎች እና እግረኛን፣ ብስክሌት ነጂን ወይም ሌላ ተሽከርካሪን ሊደብቁ የሚችሉ እገዳዎች።
- በቆሙ ተሽከርካሪዎች ውስጥ፣ በታች እና ዙሪያ እግሮች፣ ጎማዎች፣ ጥላዎች እና እንቅስቃሴዎች።
- ከፊት ለፊትዎ ካለው ተሽከርካሪ አልፎ ምን እየተፈጠረ ነው።

ወደ ፊት መመልከት ሊከሰቱ የሚችሉ ሁኔታዎችን ለመገመት ያስችላል እና አስፈላጊ ከሆነ እንዲያቆሙ ወይም አቅጣጫዎችን እንዲቀይሩ ያዘጋጅዎታል።

**ወደ ጎን ይቃኙ**

- ወደ መስቀለኛ መንገዶች በሚጠጉበት ጊዜ ከግራ እና ከቀኝ ለሚመጡ ተሽከርካሪዎች፣ እግረኞች እና ብስክሌት ነጂዎች ትኩረት ይስጡ።
- መንገዱን ሊያቋርጡ የሚችሉ እግረኞችን እና ብስክሌት ነጂዎችን ይመልከቱ።
- እጽዋቶች ወይም ሌሎች ነገሮች የጎን ዕይታዎን ሲከለክሉ፣ ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን እና መንገዱን ለማቋረጥ እቅድ ያላቸውን ሰዎች ለመለየት እንቅስቃሴን ይመልከቱ።
- ከመታጠፍዎ በፊት የጎን መስታወቶችን ይመልከቱ እና ከጎንዎ ሊሆኑ ወይም መንገዱን ሊያቋርጡ የሚችሉ ብስክሌት ነጂዎችን ወይም እግረኞችን ከትከሻዎ ዞር ብለው ይፈትሹ።

**ወደ ኋላ ይቃኙ**

ከፊትዎ እና ከጎንዎ ያለውን ትራፊክ ከመመልከት በተጨማሪ ከኋላዎ ያለውን ትራፊክ ይፈትሹ። የመንገድ መስመሮችን ሲቀይሩ፣ የብስክሌት መንገድ ሲያቋርጡ፣ ፍጥነትዎን ሲቀንሱ፣ ወደ ኋላ ሲመለሱ፣ ወይም ረጅም ወይም ቁልቁለታማ ኩረባታ ላይ ሲነዱ ተሽከርካሪዎችን እና ብስክሌት ነጂዎች ከኋላዎ መፈለግ በጣም አስፈላጊ ነው።

ትራፊክ በሚበዛበት ጊዜ ብዙ ጊዜ ይፈትሹ። የሆነ ሰው በጣም በቅርበት እየተከተልዎ ወይም በጣም በፍጥነት እየመጣ እንደሆነ ካወቁ፣ ስለ ሁኔታው የሆነ ነገር ለማድረግ ጊዜ ይኖርዎታል (የመንገድ መስመሮችን መቀየር፣ ፍሬን መያዝ፣ ፍጥነት መጨመር ወይም ፍጥነት መቀነስ)።

## 3.6 | አክብሮት እና ኃላፊነት

ደህንነቱ የተጠበቀ፣ አክብሮት እና ኃላፊነት የሚሰማው አሽከርካሪ ባህሪን ለይተው ይወቁ እና ይገዙ።

- በተሽከርካሪው ውስጥ ያሉት ሁሉም ሰዎች የደህንነት ቀበቶዎችን መጠቀማቸውን ያረጋግጡ።
- ለማሽከርከር ጤናማ ይሁኑ።
- ለሌሎች ርኅራኄ ያሳዩ።
- የሌሎች የመንገድ ተጠቃሚዎችን ቦታ ያክብሩ።
- ስህተቱ የማንም ይሁን ግጭትን ያስወግዱ።
- ለመንገድ አካባቢው ጥንቃቄ ያድርጉ።

### የትራፊክ ማስጠንቀቂያዎች

የትራፊክ ማስጠንቀቂያዎች ለአሽከርካሪዎች የሚሰጡ ስለ ወቅታዊ ወይም መጪ የትራፊክ ሁኔታዎች፣ ክስተቶች ወይም የመንገድ መዘጋቶች ያሉማሳወቂያዎች ወይም ማንቂያዎች ናቸው። እነዚህ ማስጠንቀቂያዎች ከትራንስፖርት ባለስልጣናት፣ ከትራፊክ አስተዳደር ማዕከላት ወይም ከአሰሳ መተግበሪያዎች የመጡ ናቸው።

ስለ የጉዞ መስመሮችዎ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ለማድረግ የሚረዱ የትራፊክ ማስጠንቀቂያዎችን ያግኙ። ይህ ሊከሰቱ የሚችሉ መዘግየቶችን ወይም አደጋዎችን ለማስወገድ ይረዳዎታል። የኤሌክትሮኒካዊ የመንገድ ምልክቶችን፣ ማህበራዊ ሚዲያን፣ የሬዲዮ ስርጭቶችን፣ የትራፊክ ድህረ-ገጾችን እና የሞባይል መተግበሪያዎችን ጨምሮ የትራፊክ ማስጠንቀቂያዎች በብዙ መንገዶች ይቀርባሉ።

## ቆሻሻ

ቆሻሻ አስቀያሚ ብቻ አይደለም። መንገዶቹን በሚጠቀሙ ሰዎች ላይ የደህንነት ስጋቶችንም ይፈጥራል። በመንገዶች ላይ ያለው ቆሻሻ አደጋ ሊያስከትል ይችላል። ተቀጣጣይ ወይም የሚያቃጣጠል ቆሻሻ ሰደድ እሳቶችን ሊያስነሳ የሚችል ሲሆን ይህም አካባቢን ሊጎዳ እና ለሞት ሊዳርግ ይችላል። በWashington ውስጥ ቆሻሻ መንገድ ላይ ለመጣል ያሉ ቅጣቶ በጣም ከባድ የሆኑት ለዚህ ነው። እርስዎ እና ተሳፋሪዎችዎ የሚያጓጉዟቸውን እቃዎች የመጠበቅ እና ቆሻሻን በትክክል የማስወገድ ኃላፊነት አለባችሁ።

የWashington ግዛት ህግ በቆሻሻ አወጋገድ እና ለህገ-ወጥ የቆሻሻ መድፋት ዝቅተኛ የቅጣት ገደቦችን ያስቀምጣል። በርካታ ከተሞች እና ካውንቲዎች ከግዛት ህግ የሚለዩ የአካባቢ ህጎች አሏቸው። ስለ የአካባቢው የቆሻሻ ህግ አስፈጻሚ መረጃ እና በአካባቢዎ ምን አይነት ህጎች እንደሚተገበሩ ለማወቅ የአካባቢዎን የፖሊስ መምሪያ፣ የሸሪፍ ቢሮ፣ የከተማ ወይም ካውንቲ ፀሐፊን ያነጋግሩ።

## አካባቢው

**የሚያሽከረክሩበት መንገድ በአካባቢው ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል**
መኪናዎ በቆመበት ጊዜ ሞተር ካላጠፉ፣ በተለይም ጋራዥ ውስጥ፣ እንደ ካርቦን ሞኖክሳይድ ያሉ ጎጂ ጋዞችን ሊለቅ ይችላል፣ ይህም ገዳይ ሊሆን ይችላል። ሞተርዎን ሳያጠፉ መቆየት የአየር ብክለትን ይጨምራል።

እነዚህን ጥቃቅን ለውጦች በማድረግ፣ የተሽከርካሪ ልቀቶችን ለመቀነስ ማገዝ ይችላሉ፦

- ለጥቂት ጊዜ የሚቆሙ ከሆነ ሞተሩን ያጥፉ።
- የበለጠ ነዳጅ ከሚጠቀመው በፍጥነት ማሽከርከር ወይም በከባዱ ፍሬን መያዝ ፈንታ በተረጋጋ ሁኔታ ያሽከርክሩ።
- በተወሰነ ነዳጅ የሚጓዙትን ርቀት ለማሻሻል ጎማዎችዎ በአግባቡ እንዲሞሉ ያድርጉ።
- በመንገድ ላይ ያሉትን ተሽከርካሪዎች ቁጥር ለመቀነስ በጋር ይጓዙ ወይም የህዝብ ማመላለሻ ይጠቀሙ።

**የሚያሽከረክሩት መኪና በአካባቢው ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል**
አብዛኛዎቹ የተሽከርካሪ አምራቾች የትራፊክ ፍሰትን ለማሻሻል በተዘጋጁ ዝቅተኛ የልቀት መጠኖች፣ ነዳጅ ቆጣቢ እና የደህንነት ባህሪያት በኩል የሚለቁትን የካርቦን

መጠን ለመቀነስ ጥረት አድርገዋል። ቀልጣፋ መንገዶችን ለማቀድ እና ከሌሎች ሰዎች ጋር በጋራ ለመጓዝ ማቀድን መምረጥ እነዚህን ጥረቶች (ከኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች በተጨማሪ) ይደግፋል። የWashington የንፁህ መኪና ህግ (Washington's Clean Car Law) በ2009 እና በኋላ ላይ የተሰሩ ተሽከርካሪዎች ከመመዝገባቸው፣ ፍቃድ ከማግኘታቸው ወይም ከመሸጣቸው በፊት ጥብቅ የንፁህ አየር መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ያስገድዳል።

የተሽከርካሪ ወይም የተሽከርካሪ ክፍሎችን መጣል ካስፈለገዎት፣ ይህንን ለአካባቢ ጥበቃ በሚረዳ መንገድ ለማድረግ እንዲረዱዎት የተሽከርካሪ ማስወገጃ መልሶ ጥቅም ላይ ማዋልን ያነጋግሩ።

## ራስን መገምገም

ራስን መገምገም ፈጣን፣ ቀላል እና ኃላፊነት የሚሰማው አሽከርካሪ የመሆን አስፈላጊው ክፍል ነው። በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ወይም በኋላ ላይ ሊከናወን ይችላል። የሚከተሉትን ጥያቄዎች ራስዎን ይጠይቁ፦

- ያስደነገጠኝ ነገር አለ?
- ያስደነገጥኩት ሰው አለ?
- አነዳዴ ህጋዊ፣ ብቃት ያለው እና የተረጋጋ ነበር?
- ለሚቀጥለው ጊዜ ምን ምን ለውጦች ማድረግ ይኖርብኛል?

በእያንዳንዱ ማሽከርከር መጨረሻ ላይ የማሽከርከር ክህሎቶችዎን በመደበኛነት መገምገም ችሎታዎን ለማሻሻል ብቻ ሳይሆን ከዳበሩም በኋላ ችሎታዎችዎን እንዲቀጥሉ ይረዳዎታል። ክህሎቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሱ ይሄዳሉ፤ ስለዚህ በመደበኛነት መገምገም በምርጥ ሁኔታ ማሽከርከርዎን ያቆይልዎታል።

ችሎታዎችዎን አዲስ እንደሆነ አድርገው ለማቆየት የሚከተሉትን ለይተው ይወቁ፦

- የማሽከርከር ክህሎቶችዎዎ ላይ ለውጥ እንዲመጣ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ምክንያቶችን።
- የማሽከርከር ልምዶች ላይ የተከሰቱ ለውጦችን።
- የትራፊክ ህጎች ላይ የተደርጉ ለውጦችን።
- በተሽከርካሪ ቴክኖሎጂ ላይ የተደረጉ ለውጦች እና እድገቶች።
- ከመንዳት ጋር የተያያዙ የዕድሜ ልክ የትምህርት እድሎች።

# ምዕራፍ 4

# መንገዶች



## 4.0 | ግንዛቤ እና ትብብር

ሰዎች የWashington መንገዶችን የሚጠቀሙባቸውን ሁሉንም ምክንያቶች ያስቡ፦ ቤተሰብን ለመጎብኘት፣ የታመሙ ልጆችን ወደ ሐኪም ለመውሰድ ወይም በሥራ ቦታ ከባድ ቀን ካሳለፉ በኋላ ወደ ቤት ለመመለስ። የWashington መንገዶችን የሚጠቀሙት እንደ እርስዎ ያሉ ሰዎች ናቸው እና የመንገዱ ሥርዓት በሚጠቀሙት ሰዎች ትብብር እና የጋራ መረዳት ላይ ይመሰረታል። እርስዎ ሌሎች ሰዎች የመንገዱን ደንቦች እንዲያውቁ እና እንዲከተሉ ይጠብቃሉ። እነሱም ከእርስዎ ተመሳሳይ ነገር ይጠብቃሉ።

አንዳንድ ጊዜ መንገዶች ግራ የሚያጋቡ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ በግንባታ ላይ ሊሆኑ ወይም በተሽከርካሪዎች፣ በጭነት መኪናዎች፣ በሞተር ሳይክሎች፣ በብስክሌት ነጂዎች እና በእግረኞች ሊጨናነቁ ይችላሉ። የእርስዎን ታጋሽነት እና ጠንቃቃነት የሚጠይቁ ጊዜያት ሊኖሩ ይችላሉ። ህይወት አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል እና ብዙ ሰዎች የቻሉትን ያህል እጣሩ እንደሆነ ካስታወሱ በመንገድ ላይ መጓዝን ቀላል ሆኖ ሊያገኙት ይችላሉ።

ዋናው ነገር ጨዋነት፣ አክብሮት እና ሌሎች ሰዎችን መረዳት ነው። የእርስዎ ጥንቃቄ እና ትኩረት መስጠት አንድን ሰው ወይም ራስዎን ከከባድ ጉዳት ወይም ሞት ሊያድን ይችላል።

## 4.1 | ከሰዎች ጋር መጋራት

### ሁልጊዜ ለእግረኞች ቅድሚያ ይስጡ።

እግረኞች እና ብስክሌተኞች በእግረኛ ማቋረጫ እና መገናኛ መንገዶች ላይ **መንገዱ ምልክት የተደረገበት ቢሆንም ባይሆንም** ቅድሚያ የማግኘት መብት አላቸው።

- መጓዝ ከመቀጠልዎ በፊት እግረኛ መስመርዎን እና አንድ ተጨማሪ መስመርን እስኪያልፍ ድረስ **ይጠብቁ**። እግረኛው ተሽከርካሪ ወንበር፣ ምርኩዝ፣ መሪ ውሻ ወይም ሌላ አገልግሎት ሰጪ እንስሳ እየተጠቀመ ከሆነ ከመቀጠልዎ በፊት መንገዱን ሙሉ በሙሉ እስኪያቋርጡ ይጠብቁ።
- እግረኛን ወይም ብስክሌት ነጂውን ለማለፍ ወደ እርስዎ ወደሚመጣ ትራፊክ **አያሽከርክሩ**።

የሚከተሉትን ሰዎች ልብ በሉ፦

- **እርስዎን ማየት የማይችሉ፣** ለምሳሌ ከህንጻ ወይም ከተሽከርካሪ ጀርባ ያሉ ሰዎች፣ ጀርባቸውን ለአርስዎ የሰጡ እግረኞች እና ኮፍያ ያደረጉ ወይም ዣንጥላ የሚጠቀሙ ሰዎች።
- **ትኩረታቸው የተከፋፈለ፣** ለምሳሌ ልጆች፣ ዕቃ የሚያደርሱ ሰዎች፣ የመንገድ ሠራተኞች እና በስልካቸውን የሚጠቀሙ ወይም የጆሮ ማዳመጫዎች ያደረጉ እግረኞች።
- **ግራ ሊጋቡ የሚችሉ ሰዎች፣** ለምሳሌ ካርታ የሚከተሉ ወይም አዲስ ቦታ እየፈለጉ ያሉ ቱሪስቶች እና ሰዎች።
- **ተሽከርካሪ ወንበር፣** ምርኩዝ ወይም አገልግሎት የሚሰጥ እንስሳ የሚጠቀሙትን። አገልግሎት የሚሰጥ እንስሳ ጋር ጣልቃ መግባት ህገወጥ ነው። ክላክስ አያድርጉ። እንስሳውን ወይም እግረኛውን ግራ ሊያጋባ እና ሊያስደነግጥ ይችላል።

## 4.2 | ከትምህርት ቤት አውቶቡሶች ጋር መጋራት



**የትምህርት ቤት አውቶቡስ መጫኛ እና ማውረጃ ቦታ አደገኛ ሊሆን ይችላል።**

እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ልጆች የሚያደርጉት ነገር ሁልጊዜ ቀድሞ ሊታወቅ አይችልም ወይም ስለ አደጋ አያውቁም። ልጆች በትምህርት ቤት አውቶቡስ ላይ ሲወጡ እና ሲወርዱ አስተዋይ እና ጠንቃቃ መሆንዎን ያረጋግጡ። ታጋሽ ይሁኑ እና የፍጥነት ገደቡን እንዲሁም የትምህርት ቤት አውቶቡስ ምልክቶችን ይከተሉ።

የትምህርት ቤት አውቶቡስ መብራቶች ልክ እንደ የትራፊክ ምልክቶች ናቸው፦ ቀይ ማለት ቁም ማለት ሲሆን ቢጫ ማለት ደግሞ ጥንቃቄ ወይም ፍጥነት ቀንስ ማለት ነው።




## ከአውቶቡሱ ኋላ ሲሆኑ

**ቀይ መብራቶች ሲበሩ ማለፍ ህገወጥ ነው።**

ብልጭ ድርግም የሚሉ መብራቶችን እያበራ ያለ የትምህርት ቤት አውቶቡስን በጭራሽ አልፈው አይሂዱ። መብራቶቹ እና ምልክቱ ልጆች ከአውቶቡስ ቅርብ እንደሆኑ እና እየተጫኑ/እየወረዱ እንደሆነ ይነግሩዎታል።

- ከአውቶቡሱ ጋር በተመሳሳይ አቅጣጫ የሚጓዙ ሁሉም አሽከርካሪዎች ቀይ መብራቶች ሲበሩ እና ቁም የሚለው ምልክት ሲዘረጋ መቆም አለባቸው።
- የትምህርት ቤት አውቶቡስ ለማለፍ የመሃል መዞሪያ መስመርን አይጠቀሙ። በሁሉም የመዞሪያ መስመር ላይ ያሉ አሽከርካሪዎች ማቆም አለባቸው።
- መብራቶቹ መብራታቸውን ካቆሙ፣ ምልክቱ ከታጠፈ እና የብረት መያዣው ወደ የአውቶቡሱ የፊት መካለከያ ከተመለሰ በኋላ መሄድ ይችላሉ።
- ቀይ መብራቶች መብራታቸውን ካቆሙ በኋላም ልጆች እንዳሉ ማየትዎ ይቀጥሉ።




## ከአውቶቡሱ ፊት ለፊት ሲሆኑ

**ባለ 2-መስመር መንገድ ላይ**

ቀይ መብራቶች ሲበሩ እና የማቆሚያ ምልክቱ ሲዘረጋ ሁሉም ተሽከርካሪዎች መቆም አለባቸው። መብራቶቹ መብራታቸውን ሲያቆሙ፣ ምልክቱ ሲታጠፍ እና የብረት መያዣው ወደ የአውቶቡሱ የፊት መካለከያ ሲመለስ በተቃራኒ አቅጣጫ ጉዞዎን መቀጠል ይችላሉ።



## ባለብዙ መስመር መንገድ ላይ

- ከአውቶቡሱ ጀርባ የሚጓዙ አሽከርካሪዎች ቀይ መብራቶች ሲበሩ እና ቁም የሚለው ምልክት ሲዘረጋ መቆም አለባቸው።
- **የሚከተሉት ከሆኑ**ከአውቶቡሱ በተቃራኒ አቅጣጫ የሚጓዙ አሽከርካሪዎች ቀይ መብራቶች ሲበሩ እና ቁም የሚለው ምልክት ሲዘረጋ መቆም አይጠበቅባቸውም፡-
    - **ሶስት ወይም ከዛ በላይ መስመሮች ካሉ።**
    - **የመንገድ መስመሮች በመሃል ከፋይ ወይም በመከለያ የተለዩ ከሆነ።**






## 4.3 | ከመጓጓዣ አውቶቡሶች ጋር መጋራት

እርስዎ በሚሄዱበት አቅጣጫ ለሚጓዝ ምልክት አሳይቶ ወደ መንገዱ ለሚገባ ማንኛውም የመጓጓዣ ተሽከርካሪ ቅድሚያ ይስጡ።

## 4.4 | ከትላልቅ ተሽከርካሪዎች ጋር መጋራት

መንገዱን ከትላልቅ የጭነት ተሽከርካሪዎች እና አውቶቡሶች ጋር ደህንነቱ በጠበቀ ሁኔታ መጋራት ልዩ የሆነ ውስንነታቸውን ማወቅን ይጠይቃል። በትላልቅ ተሽከርካሪዎች ባሉበት አካባቢ ሲነዱ ተጨማሪ ጊዜ እና ቦታ ያስፈልግዎታል። በመንገድ ላይ ከትላልቅ ተሽከርካሪዎች አጠገብ ሲሆኑ ለሚከተሉት ነገሮች ልዩ ትኩረት ይስጡ፦

**ታይነት።** ትላልቅ ተሽከርካሪዎችን በሚከተሉበት ጊዜ፣ ከፊት ያለው መንገድ ሰፊ ዕይታ እንዲኖርዎት የሚከተሉበትን ርቀት ያስተካክሉ።

**ለእርስዎ የማይታዩ ዞኖች።** ከትልቅ ተሽከርካሪ አጠገብ ከሆኑ እና የአሽከርካሪውን መስተዋቶች ማየት ካልቻሉ፣ አሽከርካሪው እርስዎን ማየት አይችልም። በትላልቅ ተሽከርካሪዎች በእያንዳንዱ ጎን አሽከርካሪው እርስዎን ማየት የማይችሉባቸው የማይታዩ ቦታዎች አሉ። ከትላልቅ ተሽከርካሪዎች ጎን ለረጅም ጊዜ ከመንዳት ይቆጠቡ።

**ማቆም።** ትላልቅ ተሽከርካሪዎች ልክ እንደ ትናንሽ ተሽከርካሪዎች በፍጥነት ማቆም አይችሉም። በአግባቡ የተስተካከለ ፍሬን ያለው፣ 55 ማይል በሰዓት የሚጓዝ ጭነት የጫነ የጭነት መኪና ሙሉ በሙሉ ለማቆም 450 ጫማ ይወስድበታል። ያለ በቂ ቦታ ከፊታቸው በመቅደም መስመር መቀየር ለሁሉም ሰው አደገኛ ነው።

**መቀላቀል።** ከትልቅ ተሽከርካሪ ቀድመው ወደ ትራፊክ ሲገቡ ከፊት ለፊታቸው ከመቀላቀልዎ በፊት ሁለቱንም የፊት መብራቶቻቸውን በኋለኛው መስታወትዎ ላይ በግልፅ ማየት እስኪችሉ ድረስ ይጠብቁ። ከተቀላቀሉ በኋላ፣ በሌሎች አሽከርካሪዎች ላይ የሚደርሱትን ተፅዕኖዎች ለመቀነስ የትራፊክ ፍሰትን ይጠብቁ።

**መታጠፊያ ቦታ።** የሆነ ነገር እንዳይመቱ ለመከላከል ትላልቅ ተሽከርካሪዎች ሙሉ በሙሉ ለመታጠፍ ከአንድ በላይ መስመር ሊፈልጉ ይችላሉ። እንዲሁም አደባባይ ላይ 2 የመንገድ መስመሮች የሚያህል ቦታ ያስፈልጋቸዋል። አሽከርካሪው በሚታጠፉበት ወቅት ትልቅ ተሽከርካሪን አይለፉ። ይህ ከትላልቅ ተሽከርካሪዎች ጋር ለሚኖሩ ግጭቶች ተደጋጋሚ መንስኤ ነው። ይታገሱ እና ወደፊት ከመሄድዎ በፊት ሙሉ በሙሉ እንስኪታጠፉ ድረስ ይጠብቁ።

**አደገኛ ቁሳቁሶች።** በሚያሽከረክሩበት ጊዜ፣ አደገኛ ቁሳቁሶችን እንደያዙ የሚጠቁሙ ምልክቶች ያሉባቸው ተሽከርካሪዎችን ይጠንቀቁ። የሚቻል ከሆነ በእነሱ አቅራቢ ከመንዳት ይቆጠቡ።

**ረጅም፣ ገደላማ ቁልቁለቶች።** ገደላማ ቁልቁለቶች ላይ ወደ ላይ ወይም ወደ ታች ሲጓዙ ትላልቅ ተሽከርካሪዎች በዝግታ ይጓዛሉ። በዝግታ የሚሄዱ ተሽከርካሪዎችን በቀኝ በኩል ያለው መስመር ላይ ለመገናኘት ዝግጁ ይሁኑ።



## የበረዶ ማረሻዎች

ከበረዶ መጥረጊያ መሣሪያ አቅራቢያ ሲያሽከረክሩ ጥንቃቄ ያድርጉ። የበረዶ ማረሻዎች በረዶውን ከመንገድ ላይ ወደ ላይ እና ከመንገዱ ውጭ ሊገፉ ስለሚችሉ የበረዶ ብናኝ አውሎ ንፋስ የሚመስል ሁኔታ ሊፈጥሩ ይችላሉ። ይህ በጣም በቅርበት የሚከተሉ አሽከርካሪዎች ታይነትን ሊቀንስ ይችላል።

# 4.5 | ከሞተር ብስክሌቶች ጋር መጋራት

የሞተር ሳይክል ነጂዎች እንደ ሌሎች የመንገድ ተጠቃሚዎች ሁሉ ተመሳሳይ መብቶች እና ሀላፊነቶች አሏቸው። ተመሳሳይ የትራፊክ ህጎችን ያከብራሉ። ሆኖም ግን፣ ሞተር ሳይክሎች ትናንሽ ተሽከርካሪዎች በመሆናቸው ለጥቃት የተጋለጡ እና ለማየት የሚከብዱ ናቸው። ሞተር ሳይክሎችን መቃኘት ልማድ ያድርጉ እና በእነሱ አካባቢ ሲሆኑ ይጠንቀቁ።




## መከተል

ሞተር ሳይክልን በሚከተሉበት ጊዜ ከፊት ለፊትዎ ለማቆም የሚሆን ሰፊ ቦታ ይተዉ። በአደጋ ጊዜ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ለማቆም በቂ ጊዜ እንዲኖርዎት ያስፈልጋል። የአየር ሁኔታዎች እና የሚያንሸራትቱ ወለሎች ለሞተር ሳይክል ነጂዎች ከባድ ችግሮች ሊሆኑ ይችላሉ። ዝናብ በሚዘንብበት ጊዜ ወይም መንገዱ የሚያንሸራትት በሚሆንበት ጊዜ ሰፊ የመከተያ ክፍተቶች እንዲኖሩ ያድርጉ።



## የመንገድ መስመሮች

ማየት እና መታየት እንዲሁም በመንገድ ላይ ካሉ ነገሮች ለመራቅ እንዲችሉ፣ ሞተር ሳይክል ነጂዎች በመንገድ መስመራቸው ውስጥ በየጊዜው ቦታ ይቀያይራሉ። ልክ እንደ ሌሎች ተሽከርካሪዎች ተመሳሳይ የመንገድ መስመር ስፋት የማግኘት መብት አላቸው። ምንም እንኳን የመንገድ መስመሩ ሰፊ ቢሆንም እና ሞተር ሳይክል ነጂው ወደ አንድ ጎን ርቆ የሚነዳ ቢሆንም፣ ከሞተር ሳይክል ነጂ ጋር ወደ ተመሳሳይ የመንገድ መስመር በጭራሽ አይሂዱ።



## መታጠፍ

ሞተር ሳይክል ነጂዎች ብዙውን ጊዜ በማይታዩ ዞኖች ውስጥ ይደበቃሉ ወይም ከዕይታ ያመልጣሉ። ለእርስዎ የማይታይ ዞን ግልጽ መሆኑን ለማረጋገጥ ከትከሻዎ ዞር በማለት ይፈትሹ። ለምሳሌ፣ ወደ ቀኝ እየታጠፉ ከሆነ፣ ወደ ግራ ይመልከቱ፣ ወደ ቀኝ ይመልከቱ፣ ከዚያም ወደ ግራ በድጋሚ ይመልከቱ። ሁለት ጊዜ መመልከት ህይወትን ሊያድን ይችላል። ከሞተር ሳይክል ፊት ለፊት ወደሚገኝ የመንገድ መስመር የሚገቡ ወይም ከሚመጣው ሞተር ሳይክል ፊት ለፊት የሚታጠፉ አሽከርካሪዎች ሞተር ሳይክሉን ላያዩ ይችላሉ። እንዲሁም ወደ እነሱ የሚመጣውን የሞተር ሳይክል ፍጥነት ሲገምቱ ሊሳሳቱ ይችላሉ።

## የመንገድ ንጣፍ

እንደ ጠጠር፣ ፍርስራሾች፣ የእግረኛ መንገድ መጋጠሚያዎች፣ ትናንሽ እንስሳት፣ የተቦረቦሩ የአስፋልት ክፍሎች እና የጉድጓድ ሽፋኖች ያሉ ሌሎች አሽከርካሪዎች ላይ ተጽዕኖ የማያሳድሩ ጎድጓዳማ የአስፋልት መንገዶች እና ብልሽቶች የሞተር ሳይክል ነጂው ፍጥነት ወይም የመንገድ መስመር ቦታ እንዲቀይር ሊያስገድዱ ይችላሉ። አንድ ሞተር ሳይክል ነጂ ሊያደርጋቸው የሚችላቸውን ለውጦች አስቀድመው ይገምቱ።

## መብራቶች

**የእርስዎ መብራቶች፡፡** የሞተር ሳይክል ነጂዎች የእርስዎን የፍሬቻ መብራቶች (አቅጣጫን የሚያመለክቱ መብራቶች) እና የፍሬን መብራቶች እንዲያስተውሉ ብዙ ጊዜ ይስጧቸው፡፡

**የሞተር ሳይክል ነጂዎች መብራቶች፡፡** ፍጥነት በሚቀንሱበት ጊዜ፣ ሞተር ሳይክል ነጂዎች የእጅ ፍሬን እንጂ ፍሬኖችን ላይጠቀሙ ይችላሉ፣ ስለዚህ የፍሬን መብራቶች አይታዩም፡፡ በተጨማሪም፣ አንዳንድ ሞተር ሳይክሎች በራስ-ሰር የሚጠፉ የፍሬቻ መብራቶች (አቅጣጫን የሚያመለክቱ መብራቶች) የሏቸውም፡፡ ከሞተር ሳይክል አቅራቢያ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ንቁ መሆንዎን እና በጥንቃቄ ትኩረት መስጠትዎን ያረጋግጡ፡፡ ሞተር ብስክሌቶችን ስለመንዳት የበለጠ መረጃ ለማግኘት dol.wa.gov በመጎብኘት **motorcycle operator manual** (የሞተር ብስክሌት ነጂ መመሪያ) ብለው ይፈልጉ፡፡

## 4.6 | ከብስክሌት ነጂዎች ጋር መጋራት

ብስክሌት ነጂዎች እንደ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ሁሉ ተመሳሳይ መብቶች፣ ግዴታዎች እና ኃላፊነቶች አሏቸው፡፡ እንደ ሞተር ሳይክሎች፣ ብስክሌቶች ትንሽ እና ብዙም የማይታዩ ሲሆኑ፣ ይህም ነጂዎች በአሽከርካሪ የመገጨት እና ለከባድ ጉዳት ወይም ለሞት የመዳረግ እድላቸውን ይጨምራል፡፡



## አጠቃላይ መመሪያ

- ጥግ ጋር ሲታጠፉ ወይም ወደ የግል ተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታ ሲሄዱ በእግረኛ ማቋረጫ ላይ ወይም በእግረኛ መንገድ ላይ ያሉ ብስክሌት ነጂዎችን ይመልከቱ።
- መገናኛ መንገድ ላይ፣ ለተሽከርካሪ እንደሚያደርጉት ለብስክሌት ነጂዎች ቅድሚያ ይስጡ።
- ከብስክሌት ነጂ ጋር መስመርን መጋራት አይችሉም። በህጋዊ መንገድ፣ ብስክሌት ነጂዎች ሙሉውን መስመር ተጠቅመው ለእርስዎ እና ለሌሎች አሽከርካሪዎች በጣም በሚታዩበት ቦታ መንዳት ይችላሉ። ከብስክሌት ነጂ ኋላ ሆነው በሚያሽከረክሩበት ጊዜ፣ ቢያንስ 3 ጫማ ክፍተት ይተው።
- በእግረኛ ማቋረጫዎች ላይ ያሉ ብስክሌት ነጂዎች እንደ እግረኞች ይቆጠራሉ። በሁለቱም ምልክት በተደረገባቸው እና ምልክት በሌላቸው የእግረኛ ማቋረጫዎች እና መገናኛ መንገዶች ላይ ለእነሱ ቅድሚያ መስጠት አለብዎት።

## ብስክሌት ነጂን ማለፍ

- ለእርስዎ እና ለብስክሌት ነጂው ደህንነቱ የተጠበቀ እስኪሆን ድረስ አይለፉ።
- በተመሳሳይ አቅጣጫ ሁለት የመንገድ መስመሮች ካሉ ወደ አንድ ሙሉ መስመር ዞር ይበሉ። በእያንዳንዱ አቅጣጫ 1 መስመር ብቻ ካለ፣ ወደ እርስዎ የሚመጣ ትራፊክ በማይኖርበት ጊዜ ወደ ሌላኛው መስመር ዞር ይበሉ። በብስክሌት ነጂው እና በተሽከርካሪዎ ሰፊው ክፍል መካከል ቢያንስ 3 ጫማ ክፍተት ይተዉ። (ብስክሌት ነጂው እርስዎ ሊያዩት የማይችሉትን አደጋ ለማስቀረት ቦታቸውን መቀየር ሊኖርባቸው እንደሚችል ልብ ይበሉ።)
- ብስክሌት ነጂን ለማለፍ ብለው ወደ እርስዎ የሚመጣ ትራፊክን በጭራሽ አያቋርጡ።
- በብስክሌት ነጂው ግራ በኩል በዝግታ ይለፉ እንጂ ወደ እርስዎ ወደሚመጣ ትራፊክ በጭራሽ አይለፉ።
- ወደ መስመሩ ከመመለስዎ በፊት ከብስክሌት ነጂው ነጻ መሆንዎን ያረጋግጡ። ቶሎ መስመር መቀየር ብስክሌት ነጂውን አደጋ ላይ ሊጥል ይችላል።
- ከመታጠፍዎ በፊት ብስክሌት ነጂው መገናኛ መንገዱን ጨርሶ እንዲያልፍ ያድርጉ። ወደ ቀኝ መታጠፍ ከፈለጉ፣ ከመታጠፊያው በፊት ብስክሌት ነጂን አይለፉ።

## የብስክሌት መስመሮች

- በተለምዶ አረንጓዴ ቀለም የተቀቡ፣ ጠንካራ ነጭ መስመሮችን የሚጠቀሙ እና የብስክሌት ምልክት የተደረገባቸው የብስክሌት መስመሮችን ይመልከቱ። የብስክሌት መስመር የተሳሉ ምልክቶች በርዝመታቸው ቢለያዩም ምልክቶቹ እስከሚቀጥሉበት ድረስ መንዳት አለብዎት።
- ከመንገድ ጠርዝ አጠገብ ለማቆም በሚታጠፉበት ወይም መስመር በሚያቋርጡበት ጊዜ ብቻ በብስክሌት መስመሮች ውስጥ ያሽከርክሩ።
- ከቆሙ በኋላ እና በርዎን ከመክፈትዎ በፊት ብስክሌት ነጂ መኖሩን በሁሉም አቅጣጫዎች በጥንቃቄ ይመልከቱ።

ስለ ብስክሌት መንዳት የበለጠ መረጃ ለማግኘት wsdot.wa.gov በመጎብኘት **bicycling and walking** (ብስክሌት መንዳት እና መራመድ) ብለው ይፈልጉ።

## 4.7 | መንገድን ከባቡሮች ጋር መጋራት

**የባቡር ሀዲዶች ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።**




በባቡር ሀዲዶች ላይ በተሰየሙ መሻገሪያ ቦታዎች ላይ ብቻ ያሽከርክሩ። የደህንነት ምልክቶችን፣ የሚበሩ መብራቶችን እና ማቋረጫ በሮችን ይፈልጉ። በባቡር መንገድ ማቋረጫ ላይ ቀይ መብራቶች በሩ ማለት ባቡር እየቀረበ ነው እና ከበሩ ውጭ መቆየት ያስፈልግዎታል ማለት ነው።

ባቡሮች ሁልጊዜ ቅድሚያ የማግኘት መብት አላቸው። ከባድ በመሆናቸው በዝቅተኛ ፍጥነት ቢጓዙም እንኳን በፍጥነት ማቆም አይችሉም። አንድ ባቡር ሙሉ በሙሉ እስኪቆም ድረስ አንድ ማይል ሊወስድበት ይችላል።

**በባቡር ማቋረጫ ላይ መብራቶች ሲበሩ እና ደወሎች ሲጮሁ በሩ ዝግ ቢሆንም ባይሆንም — ማቆም አለብዎ። በበሩ ዙሪያ በጭራሽ አያሽከርክሩ።**

የሚከተሉት ሲሆኑ በአቅራቢያው ካለው የባቡር ማቋረጫ በ15 እና 50 መካከል ያለ የጫማ ርቀት ላይ ያቁሙ፦

- ምልክቱ በሚበራበት ጊዜ።
- ማቋረጫ በሩ ዝቅ እያለ ወይም አስቀድሞ ዝቅ ያለ በሚሆንበት ጊዜ።
- ምልክት ሰጪው የማቆም ምልክት እየሰጠ ሲሆን።
- ወዲያውኑ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ባቡር በጣም በቅርብ እየመጣ በሚሆንበት ጊዜ።
- የባቡርን የማስጠንቀቂያ ክላክስ በሚሰሙበት ጊዜ።
- የአቁም ምልክት ልጥፍ በሚያዩበት ጊዜ።

ቀይ መብራቶች መብራታቸውን ሲያቆሙ እና ሁሉም ሌሎች የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ሲጠፉ መሄድ ይችላሉ።

## አስፈላጊ የደህንነት አስታዋሾች

**በሃዲዶቹ ላይ ባቡር ለመቅደም አይሞክሩ።**

ማስጠንቀቂያዎቹ እንደበሩ፦ ያቁሙ።

**በሃዲዶቹ ላይ አይቁሙ።**

ተሽከርካሪዎ ማቋረጫ ላይ ከተቀረቀረ ወዲያውኑ ሁሉንም ሰው ያስወጡ።

**የማስጠንቀቂያ ምልክቶቹን ችላ አይበሉ።**

ባቡር ባያዩም እንኳን ምልክቶቹን ይመኗቸው። ባቡሮች ከሚታዩት የበለጠ ቅርብ፣ ዝግ ያሉ እና በፍጥነት የሚንቀሳቀሱ ሊሆኑ ይችላሉ። ባቡሮች ከየትኛውም አቅጣጫ ሊመጡ እና በማንኛውም ሃዲድ ላይ ሊሄዱ ይችላሉ።

## ለእርዳታ መቼ እንደሚደውሉ




በባቡር ሀዲድ ላይ ወይም በቅርበት የሆነ ነገር ካለ፣ በሰማያዊ እና በነጭ የአደጋ ጊዜ ማሳወቂያ ሥርዓት (Emergency Notification System) ምልክት ላይ ላለው ቁጥር ይደውሉ። የማቋረጫ መታወቂያ ቁጥሩን ለመረጃ ላኪ እና ተቀባዩ ይስጡ። አካባቢዎን እና የሁኔታውን ዝርዝር ነገሮች ያሳውቋቸው። ምንም ምልክት የለም? 911 ይደውሉ።

## ቀላል የባቡር ሃዲድ

የSound Transit Link ቀላል የባቡር ሃዲድ መስመር የWashington የረጅም ጊዜ የመጓጓዣ አውታር ወሳኝ አካል ነው። በባቡር ጣቢያዎች እና መስመሮች አቅራቢያ ለማሽከርከር አንዳንድ መመሪያዎች እነሆ፦

- ለሁሉም ምልክቶች እና በመንገድ ላይ የተሳሉ ምልክቶች ትኩረት ይስጡ።
- ንቁ ይሁኑ እና እየቀረቡ ያሉ የቀላል የባቡር ሃዲድ ባቡሮችን ይመልከቱ።
- በተሽከርካሪዎ እና በቀላል የባቡር ሃዲድ ባቡሮች መካከል ቢያንስ የአንድ መኪና ርዝመት (ወይም ከዚያ በላይ) ይተዉ።
- በሃዲዶቹ ላይ አይቁሙ፣ መኪናዎን አያቁሙ ወይም አይተዉ! የባቡር ሐዲድ ባቡሮች በዙሪያዎ እንዲያልፉ የሚያስችል በቂ ቦታ ሰጥተው ያቁሙ።

## 4.8 | ከግብርና ተሽከርካሪዎች ጋር መጋራት

በሰዓት 25 ማይል ወይም ከዚያ በታች እንዲሄዱ የተነደፉ የግብርና እና የእርሻ ተሽከርካሪዎች በጀርባቸው ላይ የሶስት ማዕዘን ምልክት ወይም አርማ ይኖራቸዋል። በዝግታ የሚንቀሳቀስ ተሽከርካሪ ሲያዩ፣ የሚከተሉትን ለማድረግ ያስታውሱ፦

- ለመተገስ እና ፍጥነት ለመቀነስ።
- በሚያልፉበት ጊዜ ሰፋ ያለ ቦታ መስጠት እና መጠንቀቅ።

የግብርና ተሽከርካሪን ማለፍ ከፈለጉ እና በተመሳሳይ አቅጣጫ ሁለት መስመሮች ካሉ ወደ አንድ ሙሉ መስመር ይለፉ። በእያንዳንዱ አቅጣጫ አንድ መስመር ብቻ ካለ፣ ወደ እርስዎ የሚመጣውን ትራፊክ ይመልከቱ እና በጥንቃቄ መሄድዎን ይቀጥሉ። በሚያልፉበት ጊዜ፣ በተሽከርካሪዎ ሰፊው ክፍል እና በግብርና ተሽከርካሪው መካከል ቢያንስ 3 ጫማ ርቀት መኖር አለበት።

## 4.9 | ከድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች ጋር መጋራት

**መብራቶችን እና/ወይም የማስጠንቀቂያ ድምፆችን የሚጠቀሙ የእሳት አደጋ ተሽከርካሪዎች፣ አምቡላንሶች እና የፖሊስ ተሽከርካሪዎች ሁልጊዜ ቅድሚያ የማግኘት መብት አላቸው።**

ምልክቶቹን እንዳዩ ወይም እንደሰሙ፣ ወዲያውኑ ተሽከርካሪዎን ወደ መንገዱ ቀኝ ዳር በማይስያዝ ያቁሙ። ምልክት ከማሳየትዎ እና ወደ ትራፊክ ከመግባትዎ በፊት የድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪው እስኪያልፍ ድረስ ይጠብቁ። ከዚህ ቀደም እየተጓዙ በነበረው መሰረት ወደ ትራፊክ እንደገና መግባት አለብዎት። ምልክት ከማሳየትዎ እና ወደ ትራፊክ ከመግባትዎ በፊት የድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪው እስኪያልፍ ድረስ ይጠብቁ። ከዚህ ቀደም እየተጓዙ በነበረው መሰረት ወደ ትራፊክ እንደገና መግባት አለብዎት። ወደ ቀኝ በመንቀሳቀስዎ፣ የአደጋ ጊዜ ተሽከርካሪ አሽከርካሪዎች ስራቸውን እንዲሰሩ እና ህይወትን ማዳን እንዲችሉ ያግዛሉ!

# የመንገድ ደንቦች

## 4.10 | የትራፊክ ህጎች

የመንገድ ደንቦች የሰዎችን ደህንነት ለመጠበቅ የተነደፉ ናቸው። ሁሉም ሰው መንገዱን በሚጠቀሙበት ጊዜ ለመከተል የሚስማሙበትን ህግ በማውጣት የትራፊክ አደጋዎችን ይከላከላሉ። ህጎቹ ያሉት የመንገድ ሥርዓቶች በተሳለጠ ሁኔታ እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ ነው።

በአብዛኛው የመንገድ መሰረታዊ ደንቦች ተመሳሳይ ናቸው። ሆኖም ግን፣ የትራፊክ ህጎች ሊለወጡ ይችላሉ። በመስመር ላይ **RCW 46.61** (Revised Code of Washington 46.61፣ የተሻሻለ የWashington ሕግ 46.61) በመፈለግ በጣም ወቅታዊ የሆኑ የመንገድ ደንቦች ማግኘት ይችላሉ። በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ሁሉ፣ በጣም ወቅታዊ ስለሆኑት የመንገድ ደንቦች መረጃ የማወቅ ኃላፊነት የእርስዎ ነው።

### አጠቃላይ የማሽከርከር መመሪያ

በWashington ግዛት ውስጥ አሽከርካሪ እንደመሆንዎ፣ ይህን አጠቃላይ የማሽከርከር መመሪያን ከግምት ውስጥ ማስገባት ጥሩ ሀሳብ ነው፦

- በመንገዱ ቀኝ በኩል ያሽከርክሩ። በግራ በኩል በጊዜያዊነት የሚጓዙበት ብቸኛው ጊዜ በባለ ሁለት መስመር መንገድ ላይ ሌላ ተሽከርካሪን ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ እና በህጋዊ መንገድ ካለፉ ነው።
- **ለማለፍ ካልሆነ በስተቀር በቀኝ በኩል ይቆዩ።** በተመሳሳይ አቅጣጫ የሚጓዙ ብዙ መስመሮች ሲኖሩ፣ በትክክለኛው የመንገድ መስመር ውስጥ ያሽከርክሩ። በዝግታ የሚሄድ ትራፊክ ለማለፍ የግራ መስመርን ይጠቀሙ።
- ለማለፍ የግራ መስመርን በሚጠቀሙበት ጊዜ እንኳን የፍጥነት ገደብ ህጎችን ይከተሉ።
- ያስታውሱ፣ የካርፑል መስመሮች ማለፊያ መስመሮች አይደሉም።
- ለማለፍ የመንገድ ዳር ድንገተኛ ማቆሚያዎችን አይጠቀሙ። በሃላፊዎች ወይም በምልክቶች ካልታዘዙ በስተቀር የመንገድ ዳር ድንገተኛ ማቆሚያዎች ላይ ማሽከርከር የለብዎትም።
- የጉዞ መስመሮችን ከመዝጋት ይቆጠቡ። ማቆም ካስፈለገዎት ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ማቆም እስኪችሉ ድረስ መንቀሳቀስዎን ይቀጥሉ።

- ወደፊት መጓዝዎን ይቀጥሉ። ምንም እንኳን መታጠፊያዎን ወይም መውጫዎን ቢስቱም በመንገዱ ላይ በተቃራኒ አቅጣጫ አያሽከርክሩ። የመንገድ ዳር ድንገተኛ ማቆሚያ ወይም አውራ ጎዳና ላይ ወደኋላ መንዳት ህገወጥ ነው።
- በWashington አውራ ጎዳናዎች ላይ ሊፍት አይጠይቁ ወይም ሊፍት የሚጠይቁትን አይጫኑ። ህገወጥ እና አደገኛ ነው።

## የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሣሪያዎች

የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሣሪያዎች የትራፊክ ፍሰቱን የሚቆጣጠሩ ምልክቶች እና በመንገድ ላይ የተሳሉ ምልክቶች ሲሆኑ ጎዳናዎች እና አውራ ጎዳናዎችን ለሞተር ነጂዎች፣ ለብስክሌት ነጂዎች እና ለእግረኞች ደህንነታቸው የተጠበቀ ያደርጋሉ። ሁሉንም ምልክቶች እና በመንገድ ላይ የተሳሉ ምልክቶችን መመልከት እና ማክበር የእርስዎ ኃላፊነት ነው።

በልዩ ሁኔታዎች የህግ አስከባሪዎች፣ የግንባታ ሰራተኞች፣ የጥገና ሰራተኞች እና የትምህርት ቤት መሻገሪያ ጠባቂዎች ትራፊክን ሊመሩ ይችላሉ። እነዚህ ሰዎች ከትራፊክ ምልክቶች ውጭ መሆን ይችላሉ እና ትዕዛዞቻቸው ወይም መመሪያዎቻቸው መከተል አለብዎት።

## የማይሰሩ መብራቶች ወይም ምልክቶች

የትራፊክ ምልክት የማይሰራ ከሆነ መገናኛ መንገዱን እንደ ባለአራት መንገድ ማቆሚያ ይጠቀሙት። ሙሉ በሙሉ ያቁሙ። በቀኝዎ ላለ ትራፊክ ቅድሚያ ይስጡ። ደህንነቱ የተጠበቀ ሲሆን በጥንቃቄ መጓዝ ይቀጥሉ።

## 4.11 | የትራፊክ መብራት ምልክቶች



**ደማቅ ቀይ**
ቁም። ወደ ፊት ከመሄድዎ በፊት የትራፊክ መብራቱ አረንጓዴ እስኪሆን እና በመገናኛ መንገዱ ላይ ምንም አይነት ተሽከርካሪዎች ወይም እግረኞች እስከማይኖሩ ድረስ ይጠብቁ።

ቀይ መብራት ላይ ሙሉ በሙሉ ካቆሙ በኋላ፣ "ቀይ ላይ መዞር አይቻልም (no turn on red)" የሚል ምልክት ካላዩ እና ወደ ትራፊክ ለመግባት ሰፊ ቦታ ካለዎት ወደ ቀኝ መታጠፍ ይችላሉ።

ቀይ መብራት ላይ ሙሉ በሙሉ ካቆሙ በኋላ፣ "ቀይ ላይ መዞር አይቻልም" የሚል ምልክት ካላዩ እና ወደ ትራፊክ ለመግባት ሰፊ ቦታ ካለዎት በባለ አንድ አቅጣጫ ጎዳና ላይ ወደ ግራ መዞር ይችላሉ።



**ብልጭ ድርግም የሚል ቀይ**
ቁም። ብልጭ ድርግም የሚል ቀይ የትራፊክ መብራት እንደ ቁም ምልክት ሆኖ ያገለግላል። ወደ ሙሉ ያቁሙ እና ተራዎ ሲደርስ ይሂዱ።



**ቀይ ቀስት**
ቁም። ቀይ ቀስት ማለት ወደ ቀስቱ አቅጣጫ መሄድ አይችሉም ማለት ነው።



**ደማቅ ቢጫ**

ፍጥነት ቀንስ። ይህ ማለት መብራቱ ወደ ቀይ ሊቀየር ነው ማለት ነው። ቢጫ መብራት ሲያዩ፣ ፍጥነት ይቀንሱ እና ለመቆም ይዘጋጁ። ቢጫ መብራቱ ሲበራ መስቀለኛ መንገድ ላይ ከሆኑ በተለጠፈው ፍጥነት መሰረት መስቀለኛ መንገዱን ማለፍ ይቀጥሉ።

መብራቱ ቢጫ ሲሆን ወደ መስቀለኛ መንገዱ ለመግባት ወይም ከዛ ለመውጣት ከተለጠፈው የፍጥነት ገደብ በላይ ማፋጠን አይፈቀድልዎትም።



**ብልጭ ድርግም የሚል ቢጫ**

ፍጥነት ቀንስ። ብልጭ ድርግም የሚል ቢጫ መብራት ከቅድሚያ መስጠት ምልክት ተመሳሳይ ትርጉም አለው። መገናኛ መንገዱን ቁጥጥር እንደማይደረግበት መስቀለኛ መንገድ ይቁጠሩት። ቅድሚያ የማግኘት መብት ሲኖርዎት ጉዞ ይቀጥሉ።



**ቢጫ ቀስት**

ፍጥነት ቀንስ። ቢጫ ቀስት ማለት መብራቱ በቅርቡ ወደ ቀይ ይቀየራል ማለት ነው። ለመቆም ይዘጋጁ እና ወደ እርስዎ ለሚመጣ ትራፊክ ቅድሚያ ይስጡ።



**ደማቅ አረንጓዴ**
ጉዞ ይቀጥሉ፣ ነገር ግን የሚከተሉትን ማድረግዎን ያረጋግጡ፦

- መስቀለኛ መንገዱ ባዶ እስኪሆን መጠበቅ።
- በህጉ በተጠየቀው መሰረት ለድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት።
- ለእግረኞች ቅድሚያ መስጠት።

አረንጓዴ መብራት ላይ ወደ ግራ ሲታጠፉ፣ እየተቃረቡ ላሉ ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ ይስጡ። ወደ እርስዎ የሚመጣ ትራፊክ ቅድሚያ የማግኘት መብት አለው። እየተቃረበ ስላለ ትራፊክ ግልፅ ዕይታ በሚሰጥዎት ቦታ ላይ ቆም ይበሉ እና የትራፊክ መቋረጥ በሚኖርበት ጊዜ በጥንቃቄ ዞረው ይጨርሱ።



**ብልጭ ድርግም የሚል አረንጓዴ**
በWashington ግዛት ውስጥ ብልጭ ድርግም የሚል አረንጓዴ መብራት አይመለከቱም። ሆኖም ግን፣ በBritish Columbia፣ Canada ውስጥ እግረኞች ለመሻገር እየጠበቁ መሆናቸውን ለማሳየት እንደ ማስጠንቀቂያ ሊያዩዋቸው ይችላሉ።



**አረንጓዴ ቀስት**
በቀስቱ አቅጣጫ ይጓዙ። አረንጓዴ ቀስት ወደዚያ አቅጣጫ ለመጓዝ ቅድሚያ የማግኘት መብት ይሰጥዎታል። ቀስቱ አረንጓዴ ሲሆን ወደ እረስዎ የሚመጡ ተሽከርካሪዎች፣ የሚሻገር ትራፊክ ወይም እግረኞች ሊኖሩ አይገባም።

# የፍጥነት መንገድ መግቢያ መቆጣጠሪያ መብራቶች

ፍጥነት መለኪያዎች እንደ መደበኛ የትራፊክ ምልክቶች ይሰራሉ። ቀይ መብራት ሲበራ፣ ነጭ የመቆሚያ መስመር ላይ ይቁሙ። ምልክቱ ወደ አረንጓዴ ሲቀየር፣ በመንገዱ ላይ ጉዞዎን መቀጠል ይችላሉ።

## 4.12 | ምልክቶች

የትራፊክ ምልክቶች ስለ የትራፊክ ደንቦች፣ አደጋዎች፣ የመንገድ አቅጣጫዎች እና የመንገድ አገልግሎቶች አካባቢ ይነግሩዎታል። የእነዚህ ምልክቶች ቅርፅ እና ቀለም፣ ምልክቶቻቸው እና ቃሎቻቸው ለሚያቀርቡት የመረጃ ዓይነት ፍንጮችን ይሰጣሉ።

| | | |
|---|---|---|
| **ቀይ** | የተከለከለ ወይም የተገደበ እርምጃ |   |
| **ቡርትካናማ** | የግንባታ እና የጥገና ማስጠንቀቂያ |  |
| **ቢጫ** | አጠቃላይ እና የማይጠበቁ የመንገድ ሁኔታዎች ማስጠንቀቂያ |  |
| **የፍሎረሰንት ቢጫ አረንጓዴ** | የትምህርት ቤት፣ የእግረኛ እና የብስክሌት ነጂ እንቅስቃሴ ማስጠንቀቂያ |  |
| **ነጭ** | አስገዳጅ |   |
| **አረንጓዴ** | መመሪያ ወይም አቅጣጫ ጠቋሚ መረጃ |   |
| **ሰማያዊ** | የሞተር ሳይክል ነጂ አገለግሎቶች መመሪያ |   |
| **ቡናማ** | የህዝብ መዝናኛ፣ የባህላዊ እና ታሪካዊ አካባቢ መለያ |  |

## የተለመዱ ምልክቶች




**ቁም**
የቁም ምልክት ማለት በመስመሩ፣ በእግረኛ ማቋረጫው ወይም ጥግ ላይ ማቆም አለብዎ ማለት ነው። የሚያቋርጡ ተሽከርካሪዎችን እና እግረኞችን በሁሉም አቅጣጫዎች ይመልከቱ እና ቅድሚያ ለሚገባቸው ቅድሚያ ይስጡ።




**ቅድሚያ ይስጡ**
ቅድሚያ የመስጠት ምልክት ማለት ፍጥነት መቀነስ እና ቅድሚያ የማግኘት መብት ላለው ትራፊክ መጀመሪያ እንዲያቋርጥ መፍቀድ አለብዎት ማለት ነው።




**የፍጥነት ገደብ**
እነዚህ ምልክቶች የሚፈቀደውን ከፍተኛ አስተማማኝ ፍጥነት ወይም የሚጠየቀውን አነስተኛውን አስተማማኝ ፍጥነት ይነግሩዎታል።

- ከፍተኛው የፍጥነት ገደብ ተስማሚ ለሆኑ ሁኔታዎች ነው። የመንገድ ሁኔታዎች ሲፈልጉ ፍጥነትዎን ይቀንሱ – ለምሳሌ መንገዱ የሚያዳልጥ ወይም ጭጋጋማ እና ለማየት አስቸጋሪ ከሆነ። በተለጠፈው የፍጥነት ገደብ መሠረት እያሽከረከሩ ቢሆንም እንኳን ለመንገድ ሁኔታዎች በፍጥነት በመጓዝዎ ቲኬት ሊያገኙ ይችላሉ።
- አንዳንድ መንገዶች ዝቅተኛ የፍጥነት ገደቦች አሏቸው። በሌሎች አሽከርካሪዎች ላይ አደጋ እንዳያደርሱ ቢያንስ በዚህ ፍጥነት መጓዝ ይጠበቅብዎታል።



**ቀኝዎን ይዘው ይቆዩ**
ይህ ምልክት፣ ሌላ ተሽከርካሪ እያለፉ ካልሆነ በስተቀር በትክክለኛው መስመር ላይ እንዲቆዩ ያስታውሰዎታል።




## ራስ-ሰር የትራፊክ ደህንነት ካሜራዎች

እርስዎ የሚከተሉትን ካደረጉ እነዚህ ካሜራዎች በራስ ሰር ምስሎችን ይቀርጻሉ፡-

- ቀይ መብራት ላይ ማቆም ካልቻሉ።
- የባቡር ሃዲድ መሻገሪያ ምልክት ላይ ማቆም ካልቻሉ።
- በትምህርት ቤት ዞን የፍጥነት ገደብን ካለፉ።

የትራፊክ ካሜራ ያላቸው ሁሉም ቦታዎች በግልጽ ምልክት ተደርጎባቸዋል። ከእነዚህ ቦታዎች የሆኑ የፍጥነት ቲኬቶች ለተሽከርካሪው ባለቤት በፖስታ ይላካሉ።




## የፍጥነት ማስጠንቀቂያ

እነዚህ ምልክቶች አደጋ ወይም የመንገድ ሁኔታ (ብዙውን ጊዜ ጥምዝ ወይም መታጠፊያ) ስለሚኖር የፍጥነት ለውጥ እንደሚመከር ያመለክታሉ። ሁሉንም ሁኔታዎች (መንገድ፣ የአየር ሁኔታ፣ ትራፊክ፣ ወዘተ) ግምት ውስጥ በማስገባት ፍጥነትዎን በአግባቡ ያስተካክሉ እና የፍጥነት ማስጠንቀቂያ ገደቡን ይከተሉ።




## ተለዋዋጭ የፍጥነት ገደብ እና የተሻሻለ ማሳወቂያ

እነዚህ ዲጂታል ምልክቶች የፍጥነት ገደቦች ለውጥን በመለጠፍ የትራፊክ ፍሰትን ለማሰራጨት ይሞክራሉ። እንዲሁም ዲጂታል የላቁ የማሳወቂያ ምልክቶች አሽከርካሪዎች በዝግታ የሚጓዝ ትራፊክ ጋር ከመድረሳቸው በፊት በፍጥነት ሁሉንም መስመሮችን መዝጋት እና የማስጠንቀቂያ መረጃ መስጠት ይችላሉ።







## አንድ አቅጣጫ

እነዚህ ምልክቶች ትራፊክ ወደ ቀስቱ አቅጣጫ ብቻ የሚሄድበትን ቦታ ይለያሉ። በባለ አንድ-አቅጣጫ መንገድ ላይ በጭራሽ በተሳሳተ አቅጣጫ አያሽከርክሩ።



**አይፈቀድም**

አንዳንድ የአስገዳጅ ምልክቶች በምልክቱ ላይ ቀይ አግድም መስመር ያለበት ቀይ ክብ አሏቸው። እነዚህ ምልክቶች እንደ ወደ ግራ መታጠፎች፣ ወደ ቀኝ መታጠፎች ወይም መዞሮች የመሳሰሉ የተወሰኑ ድርጊቶች እንደማይፈቀዱ ያመለክታሉ።




**አይግቡ**

በክብ ውስጥ ነጭ አግድም መስመር ያለው የካሬ ምልክት ማለት ከዚያ አቅጣጫ ወደ መንገዱ መግባት አይችሉም ማለት ነው።




**የተሳሳተ አቅጣጫ**

ይህ በተሳሳተ አቅጣጫ እየነዱ መሆንዎን የሚያስውቅዎ ሲሆን የፊት ለፊት ግጭቶችን ለመከላከል የታሰበ ነው። ያቁሙ እና ወዲያውኑ ያዙሩ።







**ማለፍ እና በጥንቃቄ ማለፍ አይቻልም**

እነዚህ ምልክቶች ማለፍ የማይፈቀድበትን ቦታ ይነግሩዎታል። እንደ ዳገት፣ ኩርባዎች፣ እና መገናኛ መንገዶች እንዲሁም ሌተሽከርካሪ ወደ መንገዱ ሊገባ የሚችልባቸው ሌሎች ቦታዎች ያሉ አደጋዎች ሊከሰቱ የሚችሉባቸው ቦታዎች ላይ እነዚህን ምልክቶች ሊያዩ ይችላሉ። እንዲሁም ለማለፍ ደህንነቱ የተጠበቀ የሚሆነው መቼ እንደሆነ የሚነግሩ ምልክቶች እና የመስመር የተሳሉ ምልክቶችም አሉ።




**የተጋራው የመሀል መስመር ወደ ግራ መታጠፊያ ብቻ**

ይህ ምልክት የሚያመለክተው ከየትኛውም አቅጣጫ ወደ ግራ ለሚታጠፉ ተሽከርካሪዎች የተያዘ መስመር እንደሆነ እና ለትራፊክ ወይም ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ለማሳለፍ ጥቅም ላይ የማይውል መሆኑን ነው። ብዙውን ጊዜ በመንገዱ ላይ ቀስቶች ይሳላሉ።



**አደባባይ**

እነዚህ ምልክቶች ወደ አደባባዩ መግቢያ ምልክት ያመለክታሉ። አደባባዩች ቅድሚያ የመስጠት፣ የእግረኛ ማስጠንቀቂያ እና የአቅጣጫ ጠቋሚ ቀስት ምልክቶች ሊኖሯቸው ይችላል።

## የሥራ ዞን ምልክቶች




እነዚህ የግንባታ፣ የጥገና ወይም የድንገተኛ አደጋ ክንውኖች ምልክቶች ሰዎች በመንገድ አጠገብ እየሰሩ እንደሆነ ያስጠነቅቁዎታል። ሞተር ነጂዎች፣ እግረኞች እና ብስክሌት ነጂዎች ለማንኛውም የአውራ ጎዳና ግንባታ ባለሙያዎች፣ ቢጫ መብራቶችን ብልጭ ድርግም ለሚያደርጉ ተሽከርካሪዎች ወይም በአወራ ጎዳና ግንባታ ወይም የጥገና ሥራ ዞን ውስጥ ላሉት ቅድሚያ መስጠት አለባቸው። ሰራተኞች ባሉባቸው የግንባታ ቦታዎች ላይ በሚያሽከረክሩበት ወቅት ለሚፈጸሙ ጥሰቶች የገንዘብ ቅጣቶች በእጥፍ ይጨምራሉ።

## የአገልግሎት ምልክቶች




የአገልግሎት ምልክቶች እንደ ሆስፒታሎች፣ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ሃይል መሙያ ጣቢያዎች እና የእረፍት ቦታዎች ያሉ የተለያዩ አገልግሎቶች የሚገኙበትን ቦታ ያሳያሉ።

## የመዝናኛ ምልክቶች



የመዝናኛ ምልክቶች እንደ የእግር ጉዞ መንገዶች፣ የሽርሽር ቦታዎች እና የበረዶ መንሸራተቻ ቦታዎች ያሉ አካባቢያዊ መስህቦችን ያሳያሉ።

## የመድረሻ ምልክቶች

የመድረሻ ምልክቶች ለተለያዩ አካባቢዎች አቅጣጫዎችን እና ርቀቶችን ያሳያሉ፣ ለምሳሌ ከተማዎች፣ አየር ማረፊያዎች፣ ወይም የግዛት መስመሮች ወይም እንደ ብሔራዊ ፓርኮች፣ ታሪካዊ ቦታዎች ወይም ሙዚየሞች ያሉ ልዩ ቦታዎች።

የመንገድ ቁጥር ምልክቶች ቅርፅ እና ቀለም የመንገዱን ዓይነት ያመለክታሉ – በግዛት ውስጥ፣ U.S.፣ ግዛት፣ ከተማ ወይም የካውንቲ መንገድ።




የከተማ ማይል




አማራጭ መውጫ እና መውጫ ብቻ




የአውራ ጎዳና ምልክቶች

## ሌሎች የትራፊክ ምልክቶች

ሁሉም ሳይሆኑ የተወሰኑት የWashington ግዛት ምልክቶች ከዚህ በታች ይታያሉ። የከተማ እና የካውንቲ ምልክቶችን ጨምሮ ሁሉንም ምልክቶች የማወቅ ኃላፊነት አለብዎት።




ቀይ ላይ መዞር
አይቻልም




የመስመር
አጠቃቀም ቁጥጥር




የማይል አመልካች




የትምህርት ቤት ዞን
የፍጥነት ገደብ




የተቀነሰ ፍጥነት
ከፊት ያለ ገደብ




የባቡር ሃዲድ
መስቀለኛ መንገድ



የእግረኛ መሻገሪያ



ኩርባ



አጋዘን ሊሻገር ይችላል



ዳገት




የከፍታ ገደብ አለ



መቀላቀል



ትራፊክን መቀላቀል




ማለፍ የማይቻልበት ዞን



የእግረኛ ማቋረጫ



በተቃራኒ አቅጣጫ
መታጠፊያዎች



የትምህርት ቤት ማቋረጫ



የጎን መንገድ



ከፊት ያለ ምልክት



በእርጥበት ጊዜ የሚያንሸራትት




የመንገድ ጎን ጫፍ



ከፊት የቁም ምልክት አለ



በፍጥነት ይዙሩ



የሁለት-አቅጣጫ ትራፊክ



የታከለ መስመር (ከቀኝ በኩል፣ ምንም መቀላቀል አያስፈልግም)



ለብስክሌት ነጂ የቅድሚያ እንዲሰጡ ማስጠንቀቂያ



ከፊት ለፊት ጠባብ መንገድ ወይም ድልድይ አለ



ክብ መስቀለኛ መንገድ




በግራ በኩል ጥምዝ አለ በሰዓት 35 ማይል ይመከራል



የተከፋፈለ አውራ ጎዳና (መንገድ) ይጀምራል



የተከፋፈለ አውራ ጎዳና (መንገድ) ያበቃል




በዝግታ የሚጓዝ ተሽከርካሪ



ጠመዝማዛ መንገድ




የሚመከር ፍጥነት




ሰንሰለት ማድረግ ይመከራል



ቀላል የባቡር ሃዲድ



ከፊት ለፊት ሃይለኛ መታጠፊያ አለ




የባቡር ሃዲድ ማቋረጫ



የትራፊክ አቅጣጫ




የሱናሚ አደጋ ዞን




ብሄራዊ ደን




እሳተ ገሞራ በሚኖር ጊዜ የመውጫ መንገድ

## 4.13 | የተለመዱ መስቀለኛ መንገዶች

መስቀለኛ መንገድ ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ መንገዶች የሚገናኙበት ማንኛውም ቦታ ነው። ብዙ አይነት መስቀለኛ መንገዶች አሉ፡- አቋራጭ መንገዶች፣ አደባባዮች፣ የሚያረጋጉ ክቦች፣ የጎን ጎዳናዎች፣ የተሽከርካሪ መንገዶች፣ የገበያ ማዕከሎች እና የተሽከርካሪ ማቆሚያ መግቢያዎች። ምልክት የተደረገበትም ይሁን ምልክት የሌለው ማንኛውም መስቀለኛ መንገድ በህጋዊ መንገድ ማቋረጫ ነው። እያንዳንዱ የመገናኛ መንገድ ዓይነት ማስተዋል የተሞላበት ውሳኔ፣ ጥንቃቄ የተሞላበት ባህሪ እና ስለራስዎ እና ስለሌሎች ግንዛቤን ይፈልጋል።

መስቀለኛ መንገድ ላይ ከመግባትዎ በፊት፡-

- በመስቀለኛ መንገዱ ውስጥ ላሉ እግረኞች እና ትራፊክ ቆመው ቅድሚያ ይስጡ።
- በእያንዳንዱ አቅጣጫ በርካታ ጊዜያት ይመልከቱ።
- ብስክሌት ነጂ፣ ሞተር ሳይክል ነጂ ወይም እግረኛ ወደ መንገድዎ እንደማይመጣ እርግጠኛ ለመሆን የጎን መስተዋቶችዎን እና ከትከሻዎ ዞር ብለው ይመልከቱ።
- ወደ አዲስ መስመር ወይም መንገድ ሲገቡ የሚከተሏቸውን በመንገድ ላይ የተሳሉ ምልክቶች ይፈልጉ።

- ወደ መገናኛ መንገድ ከመግባትዎ በፊት የማቋረጫ ትራፊክን በግልፅ ማየት መቻልዎን ያረጋግጡ። በማቆሚያው መስመር ላይ ከቆሙ፣ ነገር ግን የማቋረጫ መንገድ ዕይታዎ ከተጋረደ፣ ማየት እስኪችሉ ድረስ በቀስታ ወደ ፊት መሄድዎን ይቀጥሉ። ይህ የሚያቋርጡ አሽከርካሪዎች እነሱን ከማየትዎ በፊት የተሽከርካሪዎን የፊት ክፍል እንዲያዩ ያስችላቸዋል። ይህ ፍጥነት እንዲቀንሱ እና አስፈላጊ ከሆነ እርስዎን ለማስጠንቀቅ እድል ይሰጣቸዋል።
- መስቀለኛ መንገዱን ሳይከልሉ ለማቋረጥ ወይም ለመታጠፍ የሚያስችል በቂ ቦታ እንዳለ ያረጋግጡ።

በተለይም የገበያ ማዕከላት፣ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታዎች፣ የግንባታ ቦታዎች፣ በተጨናነቁ የእግረኛ መንገዶች፣ የመጫወቻ ሜዳዎች፣ መናፈሻዎች እና የትምህርት ቤት ግቢዎች አቅራቢያ በሚሆኑበት ጊዜ በመገናኛ መንገዶች ዙሪያ ያለውን አካባቢ በሙሉ መቃኘት በጣም አስፈላጊ ነው።

**ቅድሚያ የማግኘት መብት**

ቅድሚያ የማግኘት መብት ደንቦች ተሽከርካሪዎች በመገናኛ መንገድ ውስጥ የሚንቀሳቀሱበትን ቅደም ተከተል ይወስናሉ። ህጉ ማን ቅድሚያ መስጠት እንዳለበት ይወስናል።

**ባለ አራት-አቅጣጫ መቆሚያ**

በማቆሚያ ምልክቶች ቁጥጥር ወደሚደረግበት መገናኛ መንገድ ሲቃረቡ፣ የሚከተሉት ደንቦች ተፈጻሚ ይሆናሉ፦

- መጀመሪያ የሚደርሰው ተሽከርካሪ መጀመሪያ ይሄዳል።
- ሁለተኛ የሚደርሰው ተሽከርካሪ ሁለተኛ ይሄዳል፣ ወዘተ.
- ሁለት ተሽከርካሪዎች በግምት በተመሳሳይ ጊዜ ከደረሱ በቀኝ በኩል ላለው ቅድሚያ ይስጡ።
- ወደ ግራ የሚታጠፍ ማንኛውም ተሽከርካሪ ቀጥታ ወይም ወደ ቀኝ ለሚታጠፉ ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ የማግኘት መብትን መስጠት አለበት።

**ባለ ሁለት-አቅጣጫ መቆሚያ**

የሚታጠፉ ተሽከርካሪዎች ቀጥታ ለሚሄደው ተሽከርካሪ ቅድሚያ መስጠት አለባቸው። ቀጥታ የሚሄደው ተሽከርካሪ ቅድሚያ የማግኘት መብት አለው።

## 4.14 | መታጠፍ

በመገናኛ መንገድ ላይ ወደ ግራ ወይም ቀኝ ሲታጠፉ፣ እርስዎ ከሚመጡበት አቅጣጫ በጣም ቅርብ በሆነ መስመር ላይ እንዲታጠፉ የግዛት ህግ ያስገድድዎታል።

ከአንድ በላይ የመዞሪያ መስመር ካለ፣ በሚዞሩበት ጊዜ በመጀመሪያ መስመርዎ ላይ ይቆዩ። በሚዞሩበት ጊዜ ወደ ሌላ መስመር እንዳይገቡ መዞሪያዎችዎን በጥንቃቄ ማቀድዎን ያረጋግጡ።

አንዴ ሙሉ በሙሉ ከዞሩ በኋላ ከፈለጉ ወደ ሌላ መስመር መቀየር ይችላሉ።






ወደ እርስዎ በሚመጣው ትራፊክ ላይ ወደ ግራ ወይም ቀኝ ከመታጠፍዎ በፊት ቢያንስ 100 ጫማ የመታጠፍ ምልክት ያሳዩ። ከዚያ በትራፊክ ውስጥ ደህንነቱ የተጠበቀ ክፍተት ይፈልጉ። ምንም አይነት ተሽከርካሪ፣ እግረኞች፣ ወይም ብስክሌት ነጂዎች መንገድዎ ላይ እንዳልሆኑ ወይም እየተቃረቡ እንዳልሆነ ለማረጋገጥ የሚታጠፉበትን መንገድ ያረጋግጡ።

**ከኋላዎ ብስክሌት ነጂዎች ካሉ ያረጋግጡ እና**
**ከመታጠፍዎ በፊት ለእነሱ ቅድሚያ ይስጡ።**

ብስክሌት ነጂዎች እርስዎ ከሚያስቡት በላይ በፍጥነት ወደ እርስዎ እየመጡ ሊሆን ይችላል። ደህንነትዎ ተጠብቆ ለማዞር ጊዜ እንዳለዎት እርግጠኛ ይሁኑ።

## ዞሮ መመለሻዎች

ዞሮ መመለስ ከፈለጉ፣ ዞሮ መመለስ መፈቀዱን ወይም አለመፈቀዱን የሚያሳዩ ምልክቶችን ይፈልጉ። ዞረው ከመመለስዎ በፊት በሁሉም አቅጣጫዎች ግልጽ ዕይታ ሊኖርዎት ይገባል። በዚህ ምክንያት፣ ኩርባ ላይ ወይም ወደ ዳገት ጫፍ በሚጠጉበት ጊዜ ዞረው አይመለሱ። በWashington ውስጥ፣ ዞሮ መመለስ እንደማይፈቀድ የሚገልጽ ምልክት ካልተለጠፈ በስተቀር በአጠቃላይ ዞሮ መመለስ ይፈቀዳል።




### መገናኛ መንገድ

መስቀለኛ መንገድ በእያንዳንዱ አቅጣጫ የሚጓዙ አንድ ወይም ከዚያ በላይ መስመሮች ያሉት ባለ አራት መንገድ መገናኛ ነው። በትራፊክ መብራቶች፣ የመንገድ ዳር ምልክቶች እና/ወይም በመንገድ ላይ የተሳሉ ምልክቶች ምልክት ሊደረግበት ይችላል። በመገናኛ መንገድ ላይ ቅድሚያ የማግኘት መብት ህጎችን ይወቁ እና ይተግብሩ።




### T-መገናኛ መንገድ

T-መገናኛ መንገድ የሶስት አቅጣጫ መገጣጠሚያ ሲሆን መንገዱ ያበቃና ከአንድ ሙሉ መንገድ ጋር ይዋሃዳል። T-መገናኛ መንገዶች የሚያልፍ ትራፊክ ቅድሚያ የማግኘት መብት እንዳለው ለማሳወቅ ቅድሚያ የመስጠት ወይም የቁም ምልክት ይኖራቸዋል።




### Y-መገናኛ መንገድ

Y-መገናኛ መንገድ አንድ ትንሽ መንገድ ከተጨማሪ ዋና መስመሮች ጋር ሲገናኝ ነው። ትንሹ መንገድ ከዋናው መንገድ ጋር የሚገናኝበት ቦታ ላይ ቁም የሚል ምልክት ሊኖር ይችላል። በዋና መንገዶች ላይ ያሉት መኪናዎች ቅድሚያ የማግኘት መብት አላቸው።

### መሃል ላይ ያለ ማቋረጫ



እነዚህ በመንገዱ መሃል ላይ ያሉ የእግረኛ ማቋረጫዎች ናቸው። እግረኞች ምልክት በተደረገበት የእግረኛ ማቋረጫ ላይ **ሁልጊዜ** ቅድሚያ የማግኘት መብት አላቸው።

የእግረኛ ማቋረጫው የማቆሚያ ምልክት ቢኖረውም ባይኖረውም አሽከርካሪዎች እግረኞችን እና ብስክሌት ነጂዎች እንዲሻገሩ ለማድረግ ማቆም አለባቸው።

## 4.15 | ሌሎች መገናኛ መንገዶች

### ትራፊክ የሚያረጋጉ አደባባዮች



ትራፊክ የሚያረጋጋ አደባባይ ማለት ቀለም የተቀባ ወይም ከፍ ያለ የመሃል ደሴት ያለው መገናኛ ሲሆን ትራፊክ በሰዓት ተቃራኒ አቅጣጫ የሚኬድበት ቦታ ነው። የዚህ አይነት መገናኛ መንገድ በሁሉም፣ በተወሰኑ ወይም በማናቸውም አቀራረቦቹ ላይ የቁም ወይም ቅድሚያ ስጥ ምልክቶች ሊኖሩት ይችላል። በባለ 4-መንገድ፣ ባለ 3-መንገድ ወይም ባለ 2-መንገድ መገናኛዎች ላይ ሊገኙ ይችላሉ። በማንኛውም መገናኛ መንገድ ላይ የሚተገበሯቸውን ተመሳሳይ ቅድሚያ የመስጠት ደንቦች ይተግብሩ።

ትራፊክ ማረጋጊያ አደባባዮች መንገደኞች ለያዙ ተሽከርካሪዎች የታሰቡ ሲሆን እንደ የእሳት አደጋ ተሽከርካሪዎች ፣ አውቶቡሶች ወይም የጭነት ተሽከርካሪዎች ያሉ ትላልቅ ተሽከርካሪዎችን በቀላሉ ማስተናገድ አይችሉም። ለትላልቅ ተሽከርካሪዎች ሰፊ ቦታ ይስጡ እና አደባባዩን ለማለፍ በሰዓት አቅጣጫ መሄድ እንዳለብዎ ይወቁ።

## ዋና አደባባዮች

ዋና አደባባይ ሁሉም እየተቃረቡ ያሉ ተሽከርካሪዎች ሲገቡ እና በሰዓት አቅጣጫ ሲጓዙ ቅድሚያ የሚያገኙበት ክብ መገናኛ መንገድ ነው።

ዋና አደባባዮች ተሽከርካሪዎች፣ የእሳት አደጋ ተሽከርካሪዎች፣ አውቶቡሶች፣ ማድረሻ ተሽከርካሪዎች፣ የጭነት ተሽከርካሪዎች፣ ብስክሌት ነጂዎች እና እግረኞችን ጨምሮ ለተለያዩ ተጠቃሚዎች የተነደፉ ናቸው።



ዋና አደባባዩች በማዕከላዊ ደሴት ዙሪያ የጭነት ተሽከርካሪዎች በደህንነት እንዲዞሩ መከለያ ሊኖራቸው ይችላል። የከባድ ተሽከርካሪ መከለያዎች ለትላልቅ ተሽከርካሪዎች የተነደፉ ናቸው። ወደ መገናኛው ሲጠጉ እና በዛ ላይ ሲያሽከረክሩ የጭነት ተሽከርካሪዎች መከለያዎችን እና ሁለቱንም መስመሮች እንዲያቋርጡ ስለሚፈቀድላቸው ለትላልቅ ተሽከርካሪዎች ሰፋ ያለ ቦታ ይስጡ።

ብስክሌት ነጂዎች አደባባዩን እንደ እግረኛ ወይም እንደ ተሽከርካሪ ለመዞር መምረጥ ይችላሉ። እንደ ተሽከርካሪ ሲጓዙ፣ ብስክሌት ነጂዎች ለአሽከርካሪዎች ያላቸውን ታይነት ለመጨመር በመስመሩ መሃል ላይ መንዳት አለባቸው።

**በዋና አደባባይ ላይ እንዴት መንዳት እንዳለብዎት**

1. ወደ አደባባዩ ሲቃረቡ ፍጥነትዎን ይቀንሱ። ዋና አደባባዮች በሰዓት በ15 እና 25 ማይል መካከል ለሚሆኑ ፍጥነቶች የተነደፉ ናቸው።
2. ወደ ዋና አደባባዩ ሲቃረቡ መስመር ይምረጡ። የመንገድ መስመር ምርጫ ምልክቱ የትኛዎቹ መስመሮች ወደ ቀኝ ለመታጠፍ፣ በቀጥታ ለመጓዝ እና ወደ ግራ ለመታጠፍ እንደሚጠቅሙ ያሳያል። አንዴ መስመር ከመረጡ በኋላ፣ ዋና አደባባዩን ጨርሰው እስኪወጡ ድረስ በዚያ መስመር ላይ ይቆዩ።
3. ወደ ዋና አደባባዩ ሲገቡ እና ሲወጡ በማቋረጫ መንገዶች ላይ ለእግረኞች እና ለብስክሌት ነጂዎች ያቁሙ።
4. ዋና አደባባዩ ውስጥ ላሉ ትራፊክ ሁሉ ቅድሚያ ይስጡ። ወደ ግራ ይመልከቱ እና ቀድሞውኑ አደባባዩ ውስጥ ያሉት ሁሉም ትራፊክ ቅድሚያ የማግኘት መብት ስላላቸው ያስቀድሟቸው። አንዴ በትራፊክ ውስጥ ክፍተት ካዩ፣ ወደ አደባባዩ ውስጥ ይግቡ እና ወደ መውጫ መጓዝዎን ይቀጥሉ። ከጭነት መኪናዎች በስተጀርባ ደህንነቱ የተጠበቀ ርቀት መጠበቅ ያስታውሱ ምክንያቱም ብዙ ቦታ ስለሚያስፈልጋቸው እና ሁለቱንም መስመሮች እንዲጠቀሙ ይፈቀድላቸዋል።
5. ከቀኝ በኩል በተቃራኒ የሰዓት አቅጣጫ በመጓዝ ወደ ዋና አደባባዩ ይግቡ እና መስመርዎ ላይ ይቆዩ።
6. የሚፈልጉት መንገድ ላይ ይውጡ።
7. በአደባባዩ ላይ ሲያሽከረክሩ የድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪ ከመጣ ልክ በማንኛውም መስቀለኛ መንገድ ላይ እንደሚያደርጉት ሁሉ ያቁሙ።




## አቅጣጫ የሚያስቀይሩ ዳይመንዶች

አቅጣጫ የሚያስቀይር ዳይመንድ በWashington ውስጥ አዲስ የመገናኛ መንገድ ዓይነት ነው። የተነደፈው ትራፊክ ወደ ሌላኛው የመንገዱ ክፍል እንዲሻገር ለማድረግ ነው። እርስዎ ወደ ተቃራኒው አቅጣጫ የሚሄዱ ትራፊክ መስመሮችን ስለሚያቋርጡ ይህ ምናልባት ምክንያታዊ ላይመስል ይችላል። መገናኛ መንገዱ ተሽከርካሪዎች ወደ ግራ (ወደ ክፍት መንገድ ሲገቡ ወይም ከዛ ሲወጡ) ያለችግር እንዲታጠፉ ያስችላቸዋል። እነዚህ መገናኛ መንገዶች ተሽከርካሪዎች የሚያቋርጡባቸውን ቦታዎች ቁጥር ይቀንሳሉ፣ ይህም ደግሞ የግጭት ስጋትን ይቀንሳል። አቅጣጫ የሚያስቀይሩ ዳይመንድ መገናኛ መንገዶች የግራ መታጠፊያዎችን ከመጪው ትራፊክ በማስወጣት የትራፊክ ፍሰትን ያሻሽላሉ እና መጨናነቅን ይቀንሳሉ።

**ምን እንደሚጠብቁ**

- የመስመር ቅየራ። ወደ ማሳለጫ ሲቃረቡ፣ ወደ የመንገዱ ግራ እንዲያቋርጡ ይመራሉ። ከመንገዱ በተቃራኒ አቅጣጫ ስለሚነዱ ይህ መጀመሪያ ላይ እንግዳ ነገር ሆኖ ሊሰማዎ ይችላል፣ ነገር ግን ግልጽ የተሳሉ ምልክቶች ይመሩዎታል።
- የነፃ-ፍሰት መንገድ ወደ ግራ መታጠፍያዎች። ዋናው ጥቅሙ እርስዎ ሳይቆሙ ወይም ለሚመጣው ትራፊክ ቅድሚያ ሳይሰጡ ወደ ነፃ መንገዱ ወደ ግራ እንዲታጠፉ ማስቻሉ ነው።
- ወደ መደበኛው ይመለሱ። መሻገሪያውን ወይም የስር መተላለፊያውን ካቋረጡ በኋላ፣ ወደ የመንገዱ ቀኝ በኩል ተመልሰው እንዲሻገሩ ይመራሉ።

**ምን ማድረግ እንዳለብዎ**

- ለምልክቶች እና በመንገድ ላይ ለተሳሉ የመንገድምልክቶች ትኩረት ይስጡ። በመስመር ቅየራ እና መዞሪያዎች ይመሩዎታል።
- ወደ ነፃ መንገዱ ወደ ግራ ሲታጠፉ ወደ እርስዎ ለሚመጣው ትራፊክ አይጨነቁ። ንድፉ ከሚመጡ ተሽከርካሪዎች ጋር ግጭቶችን ያስወግዳል።
- ንቁ ሆነው ይቆዩ እና በአስተማማኝ ፍጥነት ያሽከርክሩ። ምንም እንኳን የትራፊክ ፍሰቱ የተሻሻለ ቢሆንም፣ አካባቢዎን ማወቅ አስፈላጊ ነው።

## ቁጥጥር የማይደረግበት መገናኛ መንገድ

ቁጥጥር የማይደረግባቸው መገናኛ መንገዶች ምልክቶች የሏቸውም፣ ነገር ግን መደበኛው ቅድሚያ የማግኘት መብት ደንቦች ተፈጻሚ ይሆናሉ። እነዚህ መገናኛ መንገዶች በአብዛኛው በአካባቢው መንገዶች እና ጎዳናዎች ላይ ይገኛሉ። ከቁጥጥር ውጭ ወደ ሆነ መገናኛ መንገድ ሲገቡ፣ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የሚተገበር ከሆነ ቅድሚያ የማግኘት መብትን መስጠት አለብዎት፦

- አንድ ተሽከርካሪ አስቀድሞ በመገናኛ መንገድ ላይ ከሆነ።
- እርስዎ የግዛት አውራ ጎዳና ላይ የገቡት ወይም ያቋረጡት ከሁለተኛ መንገድ ከሆነ።
- ካልተነጠፈ መንገድ ወደ የአስፋልት ንጣፍ ወዳለው መንገድ ከገቡ።
- ወደ ግራ ለመታጠፍ ካቀዱ እና ተሽከርካሪ ከተቃራኒው አቅጣጫ እየተቃረበ ከሆነ።

# 4.16 | በመንገድ ላይ የተሳሉ ምልክቶች

በመንገድ ላይ የተሳሉ ምልክቶች አቅጣጫዎችን ወይም ማስጠንቀቂያዎችን ለእርስዎ ለመስጠት በመንገድ ላይ የተሳሉ መስመሮች፣ ቀስቶች፣ ቃላት ወይም ምልክቶች ናቸው። መስመሮችን ለመከፋፈል ያገለግላሉ። በመንገድ ላይ የተሳሉ ምልክቶች ሌሎች ተሽከርካሪዎችን መቼ ማለፍ ወይም መቼ መስመሮችን መቀየር እንደሚችሉ ያሳያሉ። የትኞቹን መስመሮች ለመታጠፍ እንደሚጠቀሙ ያሳያሉ፣ የእግረኛ መንገዶችን ይገልፃሉ እና ለምልክቶች ወይም ለትራፊክ ምልክቶች የት ጋር ማቆም እንዳለብዎት ያሳያሉ።

## የመንገድ መስመሮች



ደማቅ ነጭ መስመሮች የመንገዱን ጠርዝ ያሳያሉ እንዲሁም የብስክሌት መስመሮችን ከሌሎች ትራፊክ ይለያሉ።



በመንገድ ላይ ምንም የተሳሉ ምልክቶች ከሌሉ በተቻለ መጠን ደህንነትዎን ጠብቀው በቀኝ በኩል ይቆዩ።



ነጭ እና ቢጫ መስመሮች የጉዞ መስመሮችን ይለያሉ ወይም የመንገዱን መሃል ላይ ምልክት በማድረግ ትራፊክ በአንድ ወይም በሁለት አቅጣጫዎች የሚጓዝ መሆኑን ይነግሩዎታል።

ቢጫ መስመሮች በተቃራኒ አቅጣጫዎች የሚንቀሳቀስ ትራፊክን ይለያሉ። ነጭ መስመሮች በአንድ አቅጣጫ የሚንቀሳቀሱ የትራፊክ መስመሮችን ይለያሉ።



አጠር ያሉ የተቆራረጡ ነጭ መስመሮች ማለት መስመሩ እያበቃ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው። መቀላቀል ወይም መውጣት ይኖርብዎታል። ደህንነቱ የተጠበቀ ከሆነ የተቆራረጡ መስመሮችን መሻገር ይችላሉ።



መሃል ከፋዮች ሁለት ወይም ከዚያ በላይ መንገዶችን ይከፍላሉ። ክፍት ቦታዎች፣ የሲሚንቶ መከፋፈያዎች ወይም ቡራቡሬ መስመር ያላቸው 18-ኢንች ደማቅ ቢጫ በመንገድ ላይ የተሳሉ ምልክቶች ሊሆኑ ይችላሉ። መሃል ከፋዮች ውስጥ፣ ላይ ወይም እነሱን በመሻገር ማሽከርከር ህገወጥ ነው።



በትራፊክ መስመሮች መካከል የተቆራረጠ ነጭ መስመር ማለት ደህንነቱ የተጠበቀ ከሆነ መስመሮችን ለመቀየር ማቋረጥ ይችላሉ ማለት ነው።

ደማቅ ነጭ መስመር ማለት ልዩ ሁኔታ መስመሮችን እንዲቀይሩ ካላስገደደዎት በስተቀር መስመርዎ ላይ መቆየት አለብዎት ማለት ነው።

ድርብ ደማቅ ነጭ መስመሮች በመስመሮች መካከል እንዳይታለፉ የሚከለክሉ ናቸው። ድርብ ደማቅ ነጭ መስመሮችን መሻገር ህገወጥ ነው።



የተቆራረጠ ቢጫ መስመር የባለ ሁለት መንገድ፣ የባለ ሁለት መስመር መንገድ መሃልን ያሳያል። ደህንነቱ የተጠበቀ ከሆነ፣ ሌላ ተሽከርካሪን ለማለፍ ወደ እርስዎ መምጫውን መስመር መጠቀም ይችላሉ።

ደማቅ ቢጫ መስመር የመንገዱን ወይም ማለፍ የማይቻልበትን ዞን-ጠርዝ ሊያመለክት ይችላል። ሌላ ተሽከርካሪ ለማለፍ ደማቅ ቢጫ መስመር አያቋርጡ።

ድርብ ደማቅ ቢጫ የመሃል መስመሮች የባለ ሁለት አቅጣጫ መንገድ መሃልን ያሳያሉ። በሁለቱም አቅጣጫ፣ ድርብ ቢጫ መስመሮች ባላቸው መንገዶች ላይ ማለፍ አይፈቀድልዎም።



እንዲሁም ደማቅ ቢጫ እና የተቆራረጠ ቢጫ መስመር የባለ ሁለት አቅጣጫ መንገድ መሃልን ያሳያል። ደማቅ ቢጫ መስመር በእርስዎ ጎን በኩል ያለ መንገድ ላይ በሚሆንበት ጊዜ ማለፍ አይፈቀድልዎትም። የተቆራረጠው መስመር በእርስዎ ጎን በኩል ያለ መንገድ ላይ ከሆነ፣ ይህን ለማድረግ ደህንነቱ የተጠበቀ ከሆነ ማለፍ ይችላሉ።



ብዙውን ጊዜ መዞሪያ መስመሮች የሚኖሩት በዋና መገናኛ መንገዶች ላይ ነው። እነዚህን መስመሮች የሚያመለክቱ ምልክቶች እና መንገድ ላይ የተሳሉ ምልክቶች አሉ። አንዳንድ ጊዜ የቀስት ምልክት እነዚህ የመንገድ መስመሮችን ለመቆጣጠር ያግዛል። አንዴ የመታጠፊያ መስመር ላይ ከገቡ በኋላ መታጠፊያውን መከተል **አለብዎት**።



ወደ መሃል መስመር ለመግባት በመንገዱ በእርስዎ ጎን በኩል ድፍን ቢጫ መስመርን ማለፍ ይችላሉ። ይህ መስመር ወደ ግራ በመታጠፊያ ቀስቶች ምልክት ተደርጎበታል።

እነዚህ የጋራ መሃል የመንገድ መስመሮች ከመንገዱ ወይም ወደ መንገዱ ወደ ግራ ለሚታጠፉ (ወይም በሚፈቀድበት ጊዜ U-መታጠፎችን ለሚያደርጉ) ተሽከርካሪዎች የተያዙ ናቸው።

ዓይኖችዎን ከሌላኛው አቅጣጫ በሚመጣው ትራፊክ ላይ ያድርጉ ምክንያቱም እነዚህ ተሽከርካሪዎችም ተመሳሳይ መዞሪያ መስመር የመጠቀም መብት አላቸው።

እነዚህ መስመሮች ለማለፍ ጥቅም ላይ መዋል የለባቸውም። በመሃል የመንገድ መስመር ከ300 ጫማ ርቀት በላይ መጓዝ የለብዎትም።

## HOV / ካርፑል






የHOV (High occupancy vehicle፣ ከፍተኛ የተሳፋሪዎች ቁጥር የመያዝ አቅም ያለው ተሽከርካሪ) መስመሮች ለካርፑል፣ ብዙ መንገደኞችን ለጫነ ተሽከርካሪ እና ለአውቶቡሶች የተያዙ ናቸው። የHOV መስመሮች የሚታወቁት በምልክቶች እና በመንገዱ ላይ ባለው የዳይመንድ ምልክት ነው። እነዚህ መስመሮች አውራ ጎዳና ላይ ካሉት ሌሎች መስመሮች በደማቅ ነጭ መስመር ይለያያሉ። በHOV መስመር ላይ ለመጓዝ ተሽከርካሪ በምልክቶቹ ላይ የተለጠፉትን ሰው የመያዝ መስፈርቶች ማሟላት አለበት። እንዲሁም ሞተር ሳይክሎች HOV መስመሮችን እንዲጠቀሙ ተፈቅዶላቸዋል።



## ሊለወጡ የሚችሉ መስመሮች

እንደ የፍጥነት መስመሮች ያሉ ሊለወጡ የሚችሉ መስመሮች ተጨማሪ አቅም በሚያስፈልግበት ጊዜ የአንድ ወይም ከዚያ በላይ መስመሮችን የጉዞ አቅጣጫ በመቀየር የትራፊክ መጨናነቅን ለመፍታት ያግዛሉ። ሊለወጡ የሚችሉ መስመሮች በተለምዶ ዕለታዊ የጉዞ ዘይቤዎችን በሚያንፀባርቁ ቋሚ መርሃ ግብሮች ላይ ይተገበራሉ። እንዲሁም ለዋና ክስተቶች ወይም አጋጣሚዎች ስራ ላይ ሊውሉ ይችላሉ።

እነዚህ የመንገድ መስመሮች አብዛኛውን ጊዜ በድርብ የተቆራረጡ ነጭ መስመሮች ምልክት ይደረግባቸዋል። ሊለወጡ የሚችሉ መስመር ላይ ማሽከርከር ከመጀመርዎ በፊት ከላይ ያሉትን ምልክቶች ይመልከቱ። አረንጓዴ ቀስት ማለት መስመሩን መጠቀም ይችላሉ ማለት ሲሆን ቀይ X ማለት መጠቀም አይችሉም ማለት ነው። ቋሚ ቢጫ X ማለት መስመሩ አቅጣጫውን እየቀየረ ነው ማለት ነው እና ደህንነቱ የተጠበቀ ሲሆን ወዲያውኑ ከመስመሩ መውጣት አለብዎት።

## የተመደቡ የመንገድ መስመሮች

የተመደቡ የመንገድ መስመሮች መስመሩ ለልዩ ዓላመዎች መያዙን በሚያመላክቱ ምልክቶች እና/ወይም በመንገድ ላይ የተሳሉ ምልክቶች ሊታወቁ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ የጉዞ መስመሮች ለአውቶቡስ አገልግሎት ብቻ ናቸው።

## የክፍያ መስመሮች

ፈጣን የክፍያ መስመሮች እና ብዙ ቁጥር ያለው ተሽከርካሪ መያዝ የሚችሉ የክፍያ መስመሮች ለአውቶቡሶች፣ ብዙ ተሳፋሪዎችን ለጫነ ተሽከርካሪ፣ ለካርፑሎች እና ለሞተር ሳይክሎች ከክፍያ ነጻ የሆነ ፈጣን ጉዞዎችን ይሰጣሉ፣ ነገር ግን ለፈጣን ጉዞ መስመሮቹን ለመጠቀም ለግለሰብ አሽከርካሪዎች ክፍያ የመክፈል አማራጮችን ይሰጣሉ።

ለበለጠ መረጃ፣ wsdot.wa.gov ላይ **toll roads** (የክፍያ መንገዶችን) ብለው ይፈልጉ።

Good To Go! መለያን መጠቀም በWashington ውስጥ ክፍያዎችን ለመክፈል ምርጡ መንገድ ነው። Good To Go! መለያዎች በግዛቱ ውስጥ በእያንዳንዱ የክፍያ መንገድ ገንዘብ ይቆጥቡልዎታል እንዲሁም ለራስ-ሰር ክፍያዎች ምቾት ይሰጡዎታል።

Good To Go! መለያዎችን በተመለከተ ለተጨማሪ መረጃ mygoodtogo.com ይጎብኙ።

## ሌሎች በመንገድ ላይ የተሳሉ ምልክቶች



**የእግረኛ ማቋረጫዎች** ለእግረኞች እና ለብስክሌት ነጂዎች መንገዱን የሚያቋርጡበት አስተማማኝ መንገድ ያቀርባሉ። የእግረኛ ማቋረጫዎች ላይ ላሉ ወይም እየገቡ ላሉ ሰዎች ቅድሚያ መስጠት አለብዎት።

መስቀለኛ መንገድን ሲያቋርጡ ወይም ሲታጠፉ እግረኞችን እና ብስክሌት ነጂዎችን በንቃት የማየት ልማድ ይኑርዎ።

እንዲሁም አንዳንድ የእግረኛ ማቋረጫዎች በሚሻገሩ እግረኞች የሚበሩ የመንገድ መብራቶች ሊኖሯቸው ይችላሉ። እነዚህ መብራቶች በሚበሩበት ጊዜ ቅድሚያ መስጠት አለብዎት።

**ሁሉም የእግረኛ ማቋረጫዎች ምልክት የተደረገባቸው አይደሉም! በመንገድ ላይ የተሳለ ምልክት የእግረኛ ማቋረጫ ቢኖርም ባይኖርም ማንኛውም መገናኛ መንገድ በህጉ እንደ የእግረኛ ማቋረጫ ይገለጻል።**



**የብስክሌት መስመሮች** በደማቅ ነጭ መስመሮች እና የብስክሌት ምልክቶች ምልክት ይደረግባቸዋል።

አንዳንድ የብስክሌት መስመሮች ከጎን ካለው የጉዞ መስመር ጋር መሃል ላይ ሰያፍ መስመር ባላቸው ሁለት ደማቅ ነጭ መስመሮች እንዲለዩ ይደረጋሉ። ይህ ለዩ ምልክት የብስክሌት መስመር አካል ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን ይህን ማድረግ ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ ህጋዊ መታጠፍ ለማድረግ ካልሆነ በስተቀር መግባት የለብዎትም።

አንዳንድ የብስክሌት መስመሮች ከሚያልፈው ትራፊክ በአካል የሚለዩት እንደ መሰናክል፣ ማስታወቂያዎች ወይም የአበባ መትከያዎች ባሉ ዘዴዎች ነው።




**የማቆሚያ መስመሮች** ቁም የሚለው ምልክት ያለበት ላይ ይታያሉ። ተሽከርካሪዎ ወደ ማቆሚያው መስመር ወይም የእግረኛ ማቋረጫ (ካለ) ከመድረሱ በፊት ማቆም አለብዎት።




**የእሳት አደጋ መኪና መስመሮች** ብዙውን ጊዜ በቀይ መስመሮች ወይም በቀይ ኩርባ ምልክት ይደረግባቸዋል። ለእሳት አደጋ መኪና የሚሆኑ መስመሮች ውስጥ ተሽከርካሪዎን አያቁሙ ወይም አይቁሙ። በአንዳንድ ማህበረሰቦች ውስጥ፣ ለእርዳታ ሰጪ ተሽከርካሪዎች መንገዱን ነፃ ለማድረግ ከእሳት አደጋ ጣቢያ ፊት ለፊት ያለው መንገድ እንደ ለእሳት አደጋ መኪና የሚሆን መስመር ምልክት ተደርጎበታል።



**ቢጫ ሰያፍ መስመሮች** መንዳት የማይፈቀድልዎትን ቦታ ያሳያሉ።



**ከላይ ሁለት ቀስት ያላቸው የብስክሌት ስዕሎች (Sharrows)** የተሽከርካሪ መስመር ከብስክሌት ትራፊክ ጋር መጋራቱን ለማመልከት የሚያገለግሉ በመንገድ ላይ የሚሳሉ ምልክቶች ናቸው።

የብስክሌት ስዕሎች ምልክቶችን ካዩ፣ ብስክሌት የሚነዱ ሰዎች መኖራቸውን ይመልከቱ። በዝግታ ያሽከርክሩ እና በሚያልፉበት ጊዜ ቢያንስ 3 ጫማ ክፍተት ይስጡ።

ብስክሌቶች ራሳቸውን የብስክሌት ስዕል ምልክቶች ባለበት መስመር ላይ መሆን እና ቀስቱ ወደሚያመለክተው አቅጣጫ መንዳት አለባቸው።




**የትራፊክ መብራት ላይ የብስክሌት ማቆሚያ ቦታዎች**

መብራቱ አረንጓዴ ሲሆን ብስክሌተኞች መጀመሪያ መገናኛ መንገዱን ያቋርጣሉ እና በመገናኛ መንገዱ ሌላኛው ጎን ባለው የብስክሌት መስመር ውስጥ ይገባሉ። የትራፊክ መብራት ላይ በብስክሌት ማቆሚያ ቦታዎች ላይ ቀይ ሲበራ ወደ ቀኝ መታጠፍ አይችሉም። የትራፊክ መብራት ላይ የብስክሌት ማቆሚያ ቦታ ነፃ እስኪሆን ድረስ ከነጩ መስመር ኋላ ይቆዩ።

ብስክሌቶች በመገናኛ መንገድ ላይ ካለ ተሽከርካሪዎች ፊት ለፊት መሆን አለባቸው።

## 4.17 | ዞኖች




### የትምህርት ቤት ዞን

የትምህርት ቤት ዞን የሚያመለክተው በትምህርት ቤት ህንፃ ወይም በመጫወቻ ስፍራ ዙሪያ ያሉትን መንገዶች ነው። እነዚህ ቦታዎች በምልክቶች፣ በመንገድ ላይ የተሳሉ ምልክቶች እና በሚበሩ መብራቶች ምልክት ሊደረግባቸው ይችላሉ።

ከፍተኛ ፍጥነቶች ለሞት የሚዳርጉ አደጋዎችን ስለሚጨምሩ የትምህርት ቤት ዞን የፍጥነት ገደብ በሰዓት 20 ማይል ነው። በሰዓት 20 ማይል የፍጥነት ገደብ ሲተገበር የሚያብራሩ ምልክቶች ሊታዩ ይችላሉ።

ልብ ይበሉ፦ ተማሪዎች ከትምህርት በኋላ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች፣ በስፖርት ቡድኖች፣ ወይም ከት/ቤት መዝጊያ ሰዓታት በኋላ የመጫወቻ ስፍራው ላይ ሊሆኑ ይችላሉ። ትምህርት ቤት አጠገብ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ፍጥነትዎን ይቀንሱ እና ይጠንቀቁ። በልጆች ላይ የሚደርሰውን አደጋ ለመቀነስ የሚደረግ ማንኛውም ጥረት ጊዜዎን እና ትኩረትዎን የሚጠይቅ ነው።




## የሥራ ዞን

የሥራ ዞን የመንገድ ሥራ ወይም ግንባታ የሚካሄድበት ቦታ ነው። የመስመር መዘጋትን፣ ዙሪያ ጥምጥም መንገዶች እና ተንቀሳቃሽ መሣሪያዎችን ሊያካትት ይችላል።

ተሽከርካሪዎቹ በፍጥነት በሚያልፉበት ጊዜ ተጓዦችን ደህንነታቸውን ለመጠበቅ የሚሰሩትን የቡድን አባላትን ልብ ይበሉ። በሥራ ዞኖች ውስጥ ያሉ ሰራተኞች ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ አካባቢ የሚያስፈልጋቸው ወላጆች፣ አጋሮች፣ ወንድም/እህት እና ጓደኞች ናቸው።




**እባክዎ የእነዚህን ሰራተኞች ደህንነት ለመጠበቅ የድርሻዎን ይወጡ።**

- ወደ የሥራ ዞኖች ሲቃረቡ ምልክቶችን፣ ኮኖችን፣ በርሜሎችን፣ ትላልቅ ተሽከርካሪዎችን እና ሰራተኞችን ይመልከቱ።
- ትኩረት ማድረግን ለማሻሻል ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮችን ያስወግዱ። የሙዚቃን ድምጽ ይቀንሱ እና ንግግሮችን ለአፍታ ያቁሙ።
- ሁልጊዜ ምንም እንኳን ሰራተኞች ባይኖሩም በስራ ቀጠና ውስጥ ፍጥነትዎን ይቀንሱ። ጠባብ የመንገድ መስመሮች እና ጎርበጥባጣ አስፋልት አደገኛ ሁኔታን ይፈጥራሉ።
- የሚከተሉበትን ርቀት ይጨምሩ፣ በዙሪያዎ ያለውን ትራፊክ ይመልከቱ እና ለማቆም ይዘጋጁ።

- ሰራተኞችን ቢመለከቱ ወይም ባይመለከቱ በምሽት በሥራ ዞን ውስጥ በሚያሽከረክሩበት ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ያድርጉ።
- ለሠራተኞች እና ለግንባታ ተሽከርካሪዎች ቦታ ለመስጠት በሚቻልበት ጊዜ ሁሉ ዞር ይበሉ።
- End Road Work (የመጨረሻው የመንገድ ሥራ ምልክት) እስኪያዩ ድረስ የተለጠፉትን የሥራ ዞን ምልክቶችን ይመልከቱ።
- መዘግየቶችን ይጠብቁ፣ በእነሱ ላይ ያቅዱ እና ወደ መድረሻዎ በሰዓቱ ለመድረስ አስቀድመው ይውጡ።
- በሚቻልበት ጊዜ የሥራ ዞንኖች ውስጥ ላለመግባት የተለየ መንገድ ይጠቀሙ።




## የድንገተኛ አደጋ ቀጠና

የድንገተኛ አደጋ ቀጠና የሚፈጠረው አስቸኳይ ትኩረት ለሚያስፈልገው የመንገድ ዳር ጉዳይ ምላሽ ለመስጠት ነው። ግጭት፣ የተሰበረ ተሽከርካሪ ወይም በችግር ውስጥ ያለ ግለሰብ ሊሆን ይችላል። እነዚህ ማንም ሊያቅዳቸው የማይችላቸው ሁኔታዎች እና ከሁሉም የመንገድ ተጠቃሚዎች ጥንቃቄ እና ትዕግስት የሚሹ ናቸው።

የድንገተኛ አደጋ ቀጠናዎች የመንገድ ችቦዎች ወይም ምልክቶችን ሊያካትቱ ይችላሉ ነገር ግን ምላሽ ሰጪ ተሽከርካሪዎች ብልጭ ድርግም የሚሉ መብራቶችን ይጠቀማሉ። ብልጭ ድርግም የሚሉ መብራቶች ያሉት የመንገድ ዳር ምላሽ ሰጪ ተሽከርካሪ እንደተመለከቱ ከሚከተሉት አንዱን ማድረግ አለብዎት፦

ራቅ ወዳለ መስመር **ዞር ማለት**።
ከተለጠፈው የፍጥነት ገደብ ቢያንስ በሰዓት 10 ማይል ያህል **ፍጥነት መቀነስ**።
በድንገተኛ አደጋ ቀጠና ውስጥ መቼም በሰዓት ከ50 ማይል በላይ አያሽከርክሩ።

የመንገድ ዳር ምላሽ ሰጪ ተሽከርካሪዎች ጎታች መኪናዎች፣ የደረቅ ቆሻሻ የጭነት ተሽከርካሪዎች፣ የአደጋ ምላሽ፣ የአውራ ጎዳና ጥገና፣ የግልጋሎት ተሽከርካሪዎች፣ የህግ አስከባሪዎች፣ የእሳት አደጋ መኪናዎች እና አምቡላንሶችን ሊያካትቱ ይችላሉ።

በተቻለ ፍጥነት ለመንገድ ዳር ሠራተኞች ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ ይፍጠሩ። እነሱ ሌሎችን እያገዙ ሳለ እርስዎ ሊያግዟቸው ይችላሉ።

## 4.18 | ተሽከርካሪ ማቆሚያ

### አጠቃላይ የተሽከርካሪ የማቆም ህጎች

የቆመ ተሽከርካሪዎ ለሌሎች አደጋ የማይፈጥር መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለብዎት።

በተሰየሙ አካባቢዎች ውስጥ ብቻ ማቆምዎን ያረጋግጡ። ተሽከርካሪ ማቆምን የሚከለክሉ ወይም የሚገድቡ ምልክቶች ካሉ ይፍትሹ። ባለ ቀለም ምልክት የተደረገባቸው ኩርባዎች የተሽከርካሪ ማቆም ገደቦችን ሊያመላክቱ ይችላሉ። የቆመ ተሽከርካሪዎ ለሌሎች አደጋ የማይፈጥር መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለብዎት።

**በሚከተሉት ቦታዎች ላይ ተሽከርካሪ አያቁሙ፦**

- መገናኛ መንገድ ላይ።
- በእግረኛ መሻገሪያ፣ በእግረኛ መንገድ ወይም የብስክሌት መስመር ላይ።
- ከትራፊክ ምልክት፣ ከቁም ምልክት ወይም ከቅድሚያ መስጠት ምልክት በ30 ጫማ ርቀት ውስጥ።
- ከተሽከርካሪ መግቢያ፣ ከአገናኝ መንገድ ወይም ከግል መንገድ በ5 ጫማ ርቀት ውስጥ።
- ከእሳት አደጋ ጣቢያ የተሽከርካሪ መግቢያ መንገዱ ተሻግሮ በ75 ጫማ ርቀት ውስጥ።

- ከእግረኛ መንገድ የደህንነት ዞኖች በ20 ጫማ ርቀት ውስጥ።
- በባቡር ሃዲዶች ላይ።
- ከባቡር ሃዲድ ማቋረጫ በ50 ጫማ ርቀት ውስጥ።
- በግንባታ ዞን ውስጥ።
- ቀድሞውኑ የቆመ ተሽከርካሪ አጠገብ (ደርቦ ተሽከርካሪ ማቆም)።
- በነፃ መንገዱ ጫፍ ላይ (ድንገተኛ አደጋ ካላጋጠመዎት በስተቀር)።
- በድልድይ፣ ከላይ መሻገሪያ ላይ ወይም መተላለፊያ ወይም በታች መተላለፊያ ውስጥ።
- ወደ እርስዎ የሚመጣ ትራፊክ ፊት ለፊት።
- ከኩርባው ከ12 ኢንች በላይ ርቀው።
- ተሽከርካሪ ማቆም የተከለከለ የሚል ምልክት ባለበት ማንኛውም ቦታ።
- ከእሳት አደጋ ውሃ መርጫ በ15 ጫማ ርቀት ውስጥ።

ምልክቶች ወይም የተቀቡ የመንገድ ኩርባዎች ሌሎች የተሽከርካሪ ማቆሚያ ገደቦችን ሊያመላክቱ ይችላሉ።

- ነጭ ማለት የአጭር ጊዜ ማቆሞች ብቻ ይፈቀዳሉ ማለት ነው።
- ቢጫ ወይም ቀይ ጭነት የመጫኛ ዞን ወይም ሌላ ገደብ ያመላክታሉ።

**የተሽከርካሪ ማቆሚያ ፍሬንዎን ያዘጋጁ**

ሁልጊዜ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ፍሬንዎን ያዘጋጁ፣ በተለይ ዳገት ላይ።

**በርዎን ከመክፈትዎ በፊት ትራፊኩን ይፈትሹ**

- የኋላ እና የጎን ዕይታ መስታወትዎን ይፈትሹ።
- ከበሩ ርቆ ባለው እጅዎ በሩን ይክፈቱ። ይህ “የደች መድረስ (Dutch Reach)” ዘዴ ይባላል። ይህ ሰውነትዎ እንዲዞር ያስገድድዎታል፣ ይህም እየመጡ ያሉ ብስክሌት ነጂዎችን እንዲያዩ ያስችልዎታል። እንዲሁም የተሽከርካሪው በር በጣም በፍጥነት እንድዳይከፈት ይከላከላል። ይህ የብስክሌት ነጂዎችን ሊጠብቅ ይችላል እና የተሽከርካሪዎ በር እየመጣ ባለ ተሽከርካሪ እንዳይጎዳ ይከላከላል።

**በቆመ ተሽከርካሪ ውስጥ ልጆችን ወይም እንስሳትን በጭራሽ አይተዉ።**

**አዋቂዎች፣ ልጆች እና እንስሳት በአግባቡ ከተሽከርካሪው መውጣታቸውን ያረጋግጡ**

- ሞተሩ በርቶ ሳለ ከ16 ዓመት ዕድሜ በታች የሆኑ ልጅን ያለክትትል በቆመ ተሽከርካሪ ውስጥ መተው ወንጀል ነው።
- ከ12 ዓመት ዕድሜ በታች የሆኑ ልጅን በቆመ ተሽከርካሪ ውስጥ ያለ ክትትል መተው ወንጀል ነው።
- አንድ እንስሳ በከፍተኛ ሙቀት፣ ቅዝቃዜ፣ በአየር እጦት ወይም በአስፈላጊ ውሃ እጦት ምክንያት ጉዳት ሊደርስበት ወይም ለሞት ሊዳረግ የሚችል ከሆነ እንስሳውን በተሽከርካሪ ውስጥ ለብቻው መተው ወንጀል ነው።
- በአቅራቢያው ያለ ማንም ሰው ወደ ተሽከርካሪው መድረስ ካልቻለ የህግ አስከባሪዎች አካላት ጤናቸውን እና ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ ምክንያታዊ በሆኑ ማናቸውም መንገዶች ልጆቹን ወይም እንስሳቱን ለማስወጣት ፈቃድ አላቸው። መኮንኑ ወይም መኮንን የሚቀጥረው ኤጀንሲ በሕጋዊ ወይም በደህንነት ምክንያቶች ልጆቹን ወይም እንስሳቱን ማስወጣት ካስፈለጋቸው በተሽከርካሪው ላይ ለሚያደርሱት ጉዳት ተጠያቂ አይሆኑም።

**ቁልፎችዎን ይውሰዱ እና በርዎን ይቆልፉ**

በርዎን መቆለፍ ስርቆትን ይከላከላል እና ተሽከርካሪዎን ካልተፈለጉ ሰርጎ ገቦች ይከላከላል።



## ቀጥ ያለ እና ማዕዘናዊ የተሽከርካሪ ማቆም

**ቀጥ ያለ ወይም ማዕዘናዊ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታ ውስጥ መግባት**

1. ተሽከርካሪ ማቆም የሚፈልጉበትን ቦታ ይለዩ እና ትራፊክን ይመልከቱ።
2. የመታጠፍ ሐሳብዎን በምልክት ያሳውቁ።
3. ተሽከርካሪው ወደ ቦታው መሃል እስኪደርስ ድረስ እንደ አስፈላጊነቱ መሪውን ወደ ግራ ወይም ቀኝ በማዞር በዝግታ ወደ ፊት ይሂዱ።
4. ተሽከርካሪውን በተቀቡት መስመሮች መካከል መሃል ላይ ያቁሙ።
5. ወደ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታው ወደፊት ይሂዱ፣ ያቁሙ እና ተሽከርካሪውን ቦታ ያስይዙት።

**ቀጥ ካለ ወይም ከማዕዘናዊ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታ መውጣት**

1. በሁሉም አቅጣጫዎች ያለ ትራፊክን ይፈትሹ።
2. ትራፊክን መፈተሽዎን ይቀጥሉ እና የመኪናዎ መከላከያ ከጎንዎ የቆመውን ተሽከርካሪ እስከሚያልፍ ድረስ በቀጥታ ወደ ኋላ ይሂዱ።
3. ተሽከርካሪዎ እንዲቀሳቀስ ወደሚፈልጉት አቅጣጫ መሪውን በፍጥነት ያዙሩ።
4. ከተሽከርካሪ ማቆሚያው ይውጡ እና ያቁሙ። ወደ ፊት ይሂዱ፣ በቀስታ ፍጥነት ይጨምሩ እና ጎማዎቹን ቀጥ ለማድረግ እንደ አስፈላጊነቱ ያሽከርክሩ።



## ትይዩ የተሽከርካሪ ማቆም

### ትይዩ ተሽከርካሪ ማቆሚያ ውስጥ መግባት

1. ተሽከርካሪ የሚያቆሙበትን ቦታ ይለዩ፣ ትራፊክ ይመልከቱ እና ምልክት ያሳዩ።
2. ወደ ኋላ ይምጡ እና ተሽከርካሪው ወደሚንቀሳቀስበት አቅጣጫ ይመልከቱ።
3. የፊት መከላከያዎ ከኋላው ከሚያቆሙት ተሽከርካሪ የኋላ መከላከያ ጋር ትይይዩ እስኪሆን ድረስ በቀስታ ወደ ኋላ ያሽከርክሩ።
4. መሪዎን በፍጥነት ያዙሩ እና በቀስታ ወደ ቦታው ወደ ኋላ ያሽከርክሩ።
5. ተሽከርካሪዎን ወደ ቦታው መሃል ለማስያዝ መሪዎን በፍጥነት ያዙሩ።
6. ከኋላዎ ያለውን ተሽከርካሪ መከላከያ ከመንካትዎ በፊት ያቁሙ።
7. በተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታው ላይ ተሽከርካሪዎን ለማስተካከል ወደፊት ይሂዱ። ተሽከርካሪው ከኩርባው ከ12 ኢንች በላይ አለመራቁን ያረጋግጡ።

### ከትይዩ ተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታ መውጣት

1. በሁሉም አቅጣጫዎች ያለ ትራፊክን ይመልከቱ፣ እግርዎን ፍሬኑ ላይ ያድርጉ፣ የኋላ ማርሽ ያስገቡ እና በተቻለ መጠን ከኋላዎ ወዳለው ተሽከርካሪ ወደኋላ ይሂዱ።
2. ትራፊክን እና ምልክትን ይመልከቱ።
3. ወደ መስመሩ መሪዎን እያዞሩ በቀስታ ወደፊት ይሂዱ።

4. የእርስዎ ተሽከርካሪ የፊት መከላከያ ከፊት ካለው ተሽከርካሪ እንደሚያልፍ ያረጋግጡ፤ ይህ ካልሆነ ወደ ኋላ ይሂዱ እና መሪውን ያስተካክሉ።
5. የፊት በርዎ ከፊት ለፊትዎ የቆመውን ተሽከርካሪ የኋላ መከላከያ ሲያልፍ በቅርብ ወዳለው የትራፊክ መስመር ወደ ፊት ይሂዱ።




## ዳገት ላይ ተሽከርካሪ ማቆም

**ምንጊዜም ዳገት ላይ ተሽከርካሪ ሲያቆሙ የመኪና ማቆሚያ ፍሬንዎን ይያዙ** ተሽከርካሪዎ ወደ መንገዱ እየተሽከረከረ አለመውረዱን ማረጋገጥ ይኖርብዎታል። የተሽከርካሪ ማቆሚያ ፍሬን መያዝ ካልተቻለ ጎማዎችዎን ወደ የመንገዱ ጥግ ማዞር ተጨማሪ ደህንነት ይሰጣል።

**ፊትን ወደ ዳገቱ ማዞር**

ረጃጅም ኩርባዎች ባሏቸው ዳገቶች ላይ የፊት ጎማዎ ጀርባ ኩርባውን እስከሚነካ ድረስ መሪዎን ከመንገድ ዳርቻው በተቃራኒ ያዙሩ። ተሽከርካሪዎ መሽከርከር ከጀመረ ወደ ኋላ ወደ ኩርባው ይንሸራተታል። ዝቅ ያሉ ወይም ክብ የሆኑ ኩርባዎች ያሏቸው ዳገቶች ላይ መሪዎን ወደ ኩርባው ማዞር ይበልጥ አስተማማኝ ሊሆን ይችላል ምክንያቱም የተሽከርካሪ ማቆሚያ ፍሬን መያዝ ካልተቻለ ተሽከርካሪዎ ከመንገዱ ርቆ ይንሸራተታል።

**ፊትን ከዳገቱ ወደታች ማዞር**
የፊት ጎማዎ ፊት ኩርባውን እስከሚነካ ድረስ መሪዎን ወደ ኩርባው ያዙሩ። ተሽከርካሪዎ መሽከርከር ከጀመረ ወደፊት ወደ ኩርባው ይንሸራተታል።

**ምንም ኩርባ ከሌለ።**
የእርስዎን መሪ እና ጎማዎች ወደ የመንገዱ ጫፍ ያዙሩ። በዚህ መንገድ ተሽከርካሪዎ መንሸራተት ከጀመረ ከትራፊክ ርቆ ይንሸራተታል።

## ለአካል ጉዳተኞች ተሽከርካሪ ማቆሚያ የተያዘ




አንዳንድ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታዎች የአካል ጉደተኛ ታርጋ ላላቸው ወይም የአካል ጉዳተኛ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ማሳወቂያ ካርድ ላላቸው ተሽከርካሪዎች የተያዙ ናቸው። የመዳረሻ መንገድ የሚባሉት ከተያዘ ቦታ አጠገብ ያሉ ነጭ መስመሮች ነፃ ሆነው መቆየት አለባቸው። የሚጠየቀውን ማሳወቂያ ካርድ ሳያሳዩ በቦታዎች ውስጥ እና/ወይም የመዳረሻ መንገዱን በመከለል ተሽከርካሪ ካቆሙ የገንዘብ ቅጣት እንዲከፍሉ ሊደረጉ ይችላሉ።

የመራመድ አቅምዎን የሚገድብ ወይም የሚከለክል አካል ጉዳት ካለብዎት ለጊዜያዊ ወይም ቋሚ የአካል ጉዳተኛ የተሽከርካሪ ማቆሚያ መብቶች ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ።

በሚያሽከረከሩበት ወቅት የተሽከርካሪ ማቆሚያ ማሳወቂያ ካርድዎን ከኋላ መስታወትዎ ላይ ማንጠልጠል ዕይታዎን ሊገድብ ስለሚችል ይህን አያድርጉ።

ለማመልከት፣ እርስዎ እና ሐኪምዎ **የግለሰቦች የአካል ጉዳተኛ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታ ማመልከቻ** (Disabled Parking Application for Individuals) ቅጽ መሙላት አለባቹ፣ ይህም dol.wa.gov ላይ ይገኛል።

## የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የኃይል መሙያ ጣቢያ ማቆሚያ




ተሽከርካሪው ከኃይል መሙያ መሣሪያው ጋር ካልተገናኘ አንድን ተሽከርካሪ በማንኛውም የኤሌክትሪክ የኃይል መሙያ ጣቢያ ውስጥ ማቆም ህገወጥ ነው።

## 4.19 | ማጓጓዝ

### መጎተት

እንደ ጀልባ፣ ተሳቢ ወይም የጉዞ ላይ መኖሪያ ያለ ማንኛውንም ነገር እየጎተቱ ከሆነ ሁሉንም የአምራቾች ስምምነቶች፣ የግዛት ሕጎች እና የፌደራል ደንቦች መከተል የእርስዎ ኃላፊነት ነው። የሚከተሉትን በተመለከተ ያሉ ሁሉንም መመሪያዎች ማወቅ እና መከተል ይኖርብዎታል፦

- የክብደት ገደቦች።
- የተሽከርካሪ ገደቦች።
- የመጎተቻ ገመዶች እና የኋላ መብራት ተገጣሚዎች።
- የአገልግሎት ፍሬኖች።
- የፈቃድ አሰጣጥ እና የሰነድ አያያዝ።

## ጭነትዎን ያጥብቁ

ያልታሰረ ጭነት ማንቀሳቀስ ሕግ የሚጻረር እና በጣም አደገኛ ነው። ያልጠበቁ ንጥሎች ወደ አየር እንዳይወሰዱ፣ እንዳይንሸራተቱ፣ ቦታ እንዳይስቱ ወይም ወደ መንገድ ወድቀው ግጭት እንዳይፈጥሩ ጭነትዎን ያጥብቁ።

በእርስዎ ተሽከርካሪ ወይም ተሳቢ ውስጥ ያለውን ጭነት ለማጥበቅ፦

- ሁሉንም ነገር በገመድ፣ በመረብ ወይም ቀበቶዎች ይሰሩ።
- ትላልቅ እቃዎችን በቀጥታ ከተሽከርካሪዎ ወይም ከተሳቢዎ ጋር ይሰሩ።
- ተሽከርካሪዎን ወይም ተሳቢዎን ደህንነቱ እና አስተማማኝነቱ በተጠበቀ መንገድ መያዝ በሚችሏቸው እቃዎች ብቻ ይሙሉ።

## እንስሳት

- ማንኛውም ሰው እንስሳው መዝለል ወይም መውደቅ እንዳይችል በገመድ ወይም በሣጥን ውስጥ ሳያደርጉ እንስሳትን ከተሽከርካሪው ውጭ (እንደ የጭነት ተሽከርካሪ ላይ ያለ ቦታ ላይ) አድርጎ ማጓጓዝ ሕገወጥ ነው።
- በWashington በእንስሳት ላይ የሚፈጸም ጭካኔን መከላከል ሕጎች (Prevention of Cruelty to Animals laws) መሠረት እንስሳውን ወይም የሕዝብ ደህንነትን ስጋት ላይ በሚጥል መንገድ እንስሳትን ማጓጓዝ ወንጀል ነው። በማንኛውም ምክንያት ወደ እስር ከተወሰዱ ኋላፊ በተሽከርካሪ ውስጥ የሚገኝ (የሚገኙ) ማንኛውም (ማናቸውም) እንስሳ(ት) መንከባከብ ይችላሉ። የእርስዎ እንስሳ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ከሆነ እንስሳውን መቀበል ከመቻልዎ በፊት ክፍያ ይከፍላሉ።
- ተሽከርካሪዎን በደህንነት ከማሽከርከር ትኩረትዎን በሚወስድ ማንኛውም እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ ሕገወጥ ነው። በተሽከርካሪ ላይ ያልታሰሩ ወይም በአሽከርካሪው ታፋ ላይ እየሄዱ ያሉ እንስሳት ሊያዘናጉ የሚችሉ ነገሮች ናቸው።

### ማጓጓዣ ጀልባዎች

አንዳንዴ የግዛቱ የባህር ፈጣን መንገድ ሥርዓት የሚባሉት የWashington ግዛት ጀልባዎች (Washington State Ferries) የWashington አውራ ጎዳና አውታር አካል ናቸው። የዚህ አውታረ መረብ አካል እንደመሆናቸው ሁሉም የመንገድ ደንቦች ተግባራዊ ይሆናሉ።

ወደ ጀልባው ማቆሚያው ሲጠጉ ወደ የተሰየመ የጀልባ መስመር የሚመሩዎ ምልክቶች ሊመለከቱ ይችላሉ። ቀድሞውኑ በመስመር ላይ ከሚገኙ ሌሎች ተሽከርካሪዎች ጀርባ ያቁሙ። የጀልባ ሰልፍ መጣስ ወደ የገንዘብ ቅጣት ሊያመራ የሚችል የትራፊክ ጥፋት ነው። በመኖሪያ አካባቢ ውስጥ የመርከብ መያዣ መስመር ውስጥ ከሆኑ እባክዎ የመኖሪያ ተሽከርካሪ መግቢያዎች ወይም መገናኛ መንገዶችን አይሸፍኑ።

በአብዛኞቹ የማጓጓዣ ጀልባዎች ላይ ብስክሌቶች የቅድሚያ ጭነት ያገኛሉ እና ከሞተር ተሽከርካሪዎች ፊት የብስክሌት መቆያ አካባቢ ይኖራቸዋል። ብስክሌት ነጂዎች በጀልባ መያዣ መስመር ላይ የሚጠብቁ ተሽከርካሪዎችን አልፈው መሄድ ይችላሉ። ስለ የWashington የግዛት የማጓጓዣ ጀልባዎች ሥርዓት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ወይም ለክፍያዎች እና መርሐግብሮች፣ እባክዎ wsdot.wa.gov በመጎብኘት **ferries** (የማጓጓዣ ጀልባዎች) ብለው ይፈልጉ።

### የባህር ዳርቻዎች

በGrays Harbor እና Pacific ካውንቲዎች ውስጥ ብቻ የውቂያኖስ ዳርቻዎን ላይ ማሽከርከር ይፈቀዳል። የባህር ዳርቻው እንደ የግዛት አውራ ጎደና ይቆጠራል፣ ስለዚህ ሁሉም የማሽከርከር ሕጎች ተግባራዊ ይሆናሉ። የፍጥነት ገደቡ በሰዓት 25 ማይል ነው እና በሁሉም ጊዜያት እግረኞች እና ብስክሌት ነጂዎች ቅድሚያ የማግኘት መብት አላቸው።

ምልክት በተደረገባቸው የባህር ዳርቻ መቅረቢያዎች ብቻ በተሽከርካሪዎ ወደ የባህር ዳርቻው መግባት እና በጠንካራው በተጠቀጠቀ አሸዋ ላይ ብቻ ማሽከርከር ይችላሉ። በአንዳንድ አካባቢዎች እና ሁኔታዎች ውስጥ የባህር ዳርቻ ማሽከርከርን ሊከለክሉ የሚችሉ ምልክቶችን ይመልከቱ።

# ምዕራፍ 5
## ስጋቶች



# 5.0 | የመንዳት አደጋዎች

መኪና ማሽከርከር ከባድ ስጋቶች እና መዘዞች እንዳሉት ያውቃሉ። እርስዎ ስህተቶችን ይሰራሉ፣ እና በዙሪያዎ ያሉ ሰዎች ስህተቶችን ይሰራሉ። ምንም እንኳን ስጋት ሁልጊዜ ቢኖርም፣ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ማሽከርከር አደጋ የመከሰት እድሉን ሊቀንስ ይችላል።

ስጋትን ማሰስ ከመሪው በስተጀርባ ንቁ መሆንን፣ መተንበይን፣ መረጋጋትን እና ጎበዝ መሆንን ያካትታል። በጥሩ ሁኔታ እና ያለችግር ለማሽከርከር፣ ሆን ብለው ደህንነታቸው የተጠበቁ የማሽከርከር ልማዶችን እንደ ነባሪ የማሽከርከር ዘይቤ ማዳበር እና መጠቀም አለብዎት።

**ሞት የሚያስከትሉ አደጋዎች የተለመዱ ምክንያቶች**

- ፍጥነት
- እክል
- ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮች
- የደህንነት ቀበቶ ያላሰሩ ተሳፋሪዎች
- የልምድ ማነስ*

*በWashington የተሽከርካሪ ግጭቶች እድሜያቸው ከ16 እስከ 25 ዓመት ለሆኑ ሰዎች ሞት ዋነኛ መንስኤ ናቸው። ይህ የዕድሜ ክልል ለሞት የሚዳርጉ እና ከባድ የአካል ጉዳት ለሚያደርሱ ግጭቶች ተጋላጭ ነው።

## የስጋት ግንዛቤ

የስጋት ግንዛቤ በመንገድ ላይ ያሉትን እና ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን የመለየት ችሎታዎ ነው። ግጭትን ለማስወገድ ባህሪዎን እንዲቀይሩ ሊጠይቁ የሚችሉ ነገሮችን እንዲያውቁ ያግዝዎታል። የስጋት ግንዛቤ ሌሎች የመንገድ ተጠቃሚዎችን፣ የአየር ሁኔታዎችን እና ትኩረትዎን ሊከፋፍሉ የሚችሉ ነገሮችን መገንዘብን ያካትታል።

የስጋት ግንዛቤ በአካባቢዎ ያለውን እና ቀጣይ ምን ሊከሰት እንደሚችል በመረዳት ላይ የተመሰረተ ነው።

- ጭንቅላትዎ ያለማቋረጥ ይቃኝ። ከፊትዎ፣ ከጎንዎ እና ከኋላዎ እየሆነ ያለውን ነገር ያስተውሉ። የእርስዎን የዳር እይታ እና መስታወቶች በመጠቀም ይህንን ማድረግ ይችላሉ።

- ከፊት ለፊት ባለው መንገድ ላይ ምን እየተፈጠረ እንዳለ ለማየት ከተሽከርካሪዎ ፊት ለፊት በቂ ቦታ ይተዉ።
- ለውጥ እንዲያደርጉ የሚጠይቅዎትን አደጋ ካዩ በኋላ ከኋላዎ ያለውን ሁኔታ ይፈትሹ። ከኋላዎ እየተከሰተ ያለው ነገር በውሳኔ አሰጣጥዎ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል

ስጋትን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ የማይቻል ነው። ሆኖም፣ ስጋቶችን በመለየት እና ማሽከርከርዎን በተገቢው መንገድ በማስተካከል እንዴት ማስወገድ ወይም መቀነስ እንደሚችሉ መማር ይችላሉ።

## የአደጋ ግንዛቤ

የአደጋ ግንዛቤ በመንገድ ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶችን የመቃኘት እና ችግር ከመከሰታቸው በፊት የመለየት ችሎታዎ ነው። ይህ ችሎታ ደህንነቱ ለተጠበቀ ማሽከርከር አስፈላጊ ነው እና አደጋዎችን ለመከላከል ይረዳል። የአደጋ ግንዛቤ የሚከተሉትን ይጠይቃል፦

- ትኩረት መስጠት።
- ፈጣን ውሳኔ መስጠት።
- ለተለዋዋጭ ሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽ የመስጠት ችሎታ።

**አደጋ እርስዎ ለውጥ እንዲያደርጉ የሚጠይቅ ማንኛውም ነገር ነው። ከመሪው በስተጀርባ ሲሆኑ ሁልጊዜ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮችን መፈለግ ወይም ለእነሱ ምላሽ መስጠት አለብዎት።**

አደጋ ፍጥነትዎን ወይም አቅጣጫዎን እንዲቀይሩ ሊጠይቅዎት ይችላል።

- አደጋ እንደ አንድ ልጅ ወደ መንገዱ እየሮጠ ሲገባ ወይም እንደ በመንገድ ላይ ያለ የቆሻሻ መጣያ፣ የፍጥነት ገደብ ምልክት ላይ መድረስ ወይም ወደ የቤትዎ መኪና ማቆሚያ መታጠፊያ እንደመቅረብ ያለ ትንሽ ከበድ ያለ ነገር ሊሆን ይችላል።
- አደጋ የማይንቀሳቀስ ወይም የሚንቀሳቀስ ሊሆን ይችላል።
- በተመሳሳይ ጊዜ ከአንድ በላይ አደጋዎች ሊኖሩ ይችላሉ። የትኛው አደጋ አስቸኳይ ምላሽ እንደሚያስፈልገው መወሰን እንደ ሹፌር የእርስዎ ሃላፊነት ነው።

ደህንነታቸው የተጠበቁ ውሳኔዎችን ለማድረግ ለራስዎ ተጨማሪ ቦታ ለመስጠት ወደ አደጋዎች ሲጠጉ በዝግታ ያሽከርክሩ።

## ሁኔታዊ ግንዛቤ

ሁኔታዊ ግንዛቤ በዙሪያዎ ያለውን ነገር ማስተዋል እና ለቀጣይ ምን መዘጋጀት እንዳለበት መተንበይ ነው። ይህንን ያለማቋረጥ ማድረግ አለብዎት።

በድርጊትዎ ማን ተጽእኖ ሊያድርበት እንደሚችል እና ማን አላማዎን ማወቅ እንዳለበት ማወቅ አለብዎ። ከጀርባዎ ያሉት አሽከርካሪዎች በውሳኔዎችዎ ተጽእኖ የሚደርስባቸው ሊሆኑ ይችላሉ።

## አደጋን መቆጣጠር

በመንገድ ላይ ገደብ የሌላቸው ብዛት ያላቸው ሁኔታዎች ያጋጥሙዎታል። ለእያንዳንዱ መተንበይ ወይም እቅድ ማውጣት አስቸጋሪ ነው። በምትኩ፣ የሚከተሉትን ማድረግ የሚጠይቁ ለአደጋዎች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አስተማማኝ አሠራር ማዳበር አለብዎት፦

- **ያቅዱ።** በዙሪያዎ ምን እየተፈጠረ እንዳለ ለማወቅ አካባቢዎን ይቃኙ። ከኋላዎ ምን እየተፈጠረ እንዳለ ለማየት ወደኋላ መመልከቻ መስታወት መመልከትዎን ያረጋግጡ። ማድረግ የሚፈልጉት ለውጥ ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ይወስኑ።
- **ይግባቡ።** ምን ለማድረግ እንዳሰቡ ለሌሎች ያሳውቁ። ፍሬቻዎችዎን ይጠቀሙ እና ሁሉም ሰው ሃሳብዎን በሚገባ ማወቁን ያረጋግጡ።
- **ይፈትሹ።** ከመካከለኛ ፍሬን መያዝ በማይበልጥ ለውጡን ለማድረግ በቂ ቦታ እንዲኖርዎ የተሽከርካሪዎን ቦታ እና ፍጥነት ያዘጋጁ። መስታወቶችዎን እንደገና ይፈትሹ እና እግረኞችን እና ብስክሌት ነጂዎችን ከትከሻዎ ዞር ብለው ይመልከቱ። ሌሎች አሽከርካሪዎች ወደ ተመሳሳይ ቦታ ለመሄድ እየሞከሩ አለመሆናቸውን ያረጋግጡ።
- **ያድርጉ።** ለውጡን ያለችግር በእርጋታ ይፈጽሙ። ማንንም ላለመስደንገጥ ይሞክሩ። አስፈላጊ ከሆነ እቅድዎን ለመቀየር ዝግጁ ይሁኑ።
- **ይገምግሙ።** እንዴት እንደተፈጸመ ያስቡ። ለሚቀጥለው ጊዜ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎን ማስተካከል እንደሚያስፈልግዎ ይመልከቱ።

## 5.1 | ፍጥነት

ቸኩለው ቢሆኑም እንኳን በፍጥነት የማሽከርከር ስጋቶች ዋጋቸው ያነሰ ነው። በፍጥነት ማሽከርከር በመንገዱ ላይ ያሉትን ሁሉ አደጋ ላይ ይጥላል። ራስዎን፣ ስለእርስዎ የሚያስቡ ሰዎችን እና ከእርስዎ ጋር መንገዱን የሚጋሩ ሌሎች ግለሰቦችን እና ቤተሰቦችን ደህንነት ለመጠበቅ የተለጠፈውን የፍጥነት ገደብ ያክብሩ።

የተለጠፈውን የፍጥነት ገደብ መከተል ህጉን ከመከተል ያለፈ ነው። ቸኩለው ቢሆኑም እንኳን በፍጥነት የማሽከርከር ስጋቶች ዋጋቸው ያነሰ ነው። በፍጥነት ማሽከርከር በመንገዱ ላይ ያሉትን ሁሉ አደጋ ላይ ይጥላል። ለደህንነት ቅድሚያ ይስጡ እና ቁጥጥርን ለመጠበቅ እና ለአደጋዎች ምላሽ ለመስጠት በሚያስችል ፍጥነት ያሽከርክሩ።

### ከልክ ያለፉ ከፍተኛ ፍጥነቶች

ከፍጥነት ገደቡ በላይ ማሽከርከር መኪናዎን፣ ሌሎች ሰዎችን እና እርስዎን ሊጎዳ ይችላል። ከልክ ያለፉ ከፍተኛ ፍጥነቶች የሚከተሉትን ያስከትላሉ፦

- **የደህንነት ቀበቶዎችን ውጤታማነት ይቀንሳሉ።** የደህንነት ቀበቶዎች በአደጋ ጊዜ እርስዎን ለመጠበቅ የተሰሩ ናቸው፤ ነገር ግን በከፍተኛ ፍጥነቶች ላይ ውጤታማነታቸው ይቀንሳል።
- **አደጋዎችን በዕይታ የመቃኘት ችሎታዎን ይገድባሉ።** በፍጥነት ባሽከረከሩ ቁጥር፣ እንደ እግረኛ፣ ብስክሌት ነጂዎች ወይም ሌሎች ተሽከርካሪዎች ያሉ የአደጋ ተጋላጭነቶችን ከፊት ለፊት ባለው መንገድ ላይ ለመቃኘት የሚያስፈልግዎት ጊዜ ይቀንሳል።
- **የተሽከርካሪ እና መሬት የመቆንጠጥ ቁጥጥርን ይቀንሳሉ።** ከፍተኛ ፍጥነት ተሽከርካሪዎን ለመቆጣጠር አስቸጋሪ ያደርገዋል፣ በተለይ እንደ ዝናብ ወይም በረዶ ባሉ መጥፎ ሁኔታዎች። ይህ መኪናው እንዲንሸራተት ወይም ሙሉ በሙሉ ቁጥጥርን እንዲያጣ ሊያደርግ ይችላል።
- **ረጅም የማቆሚያ ርቀቶችን ይፍጠሩ።** በከፍተኛ ፍጥነት የሚጓዝ ተሽከርካሪን ለማቆም ረጅም ጊዜ ይወስዳል። ይህ በድንገት ፍሬን መያዝ ካስፈለግዎ ግጭት የመከሰት እድሉን ይጨምራል።
- **የጉዞዎን መንገድ ለመገምገም እና አስፈላጊ ለውጦችን ለማድረግ ያነሰ ጊዜ ይሰጥዎታል።** በፍጥነት ማሽከርከር እንደ ኩርባዎች፣ መገናኛ መንገዶች ወይም መሰናክሎች ባሉ የመንገድ ለውጦች ላይ ምላሽ ለመስጠት ያነሰ ጊዜ ይሰጥዎታል።

- **በአደጋ ጊዜ የአካል ጉዳቶችን አስከፊነት ይጨምራል።** አደጋ በሚፈጠርበት ጊዜ ያለው የግጭቱ ኃይል ከፍጥነት ጋር አብሮ ይጨምራል፤ ይህም ከባድ የአካል ጉዳቶችን ወይም ሞቶችን ያስከትላል።

## የፍጥነት ገደቦች

የፍጥነት ገደቦች ተስማሚ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ በህግ የሚፈቀደውን ከፍተኛ ፍጥነት ያመለክታሉ። የWashington ሕግ በአሁን የመንገድ ሁኔታዎች ላይ ደህንነታቸው በተጠበቁ ፍጥነቶች እንዲያሽከረክሩ ያስገድድዎታል። ይህ ማለት ሁኔታዎች ተስማሚ በማይሆኑበት ጊዜ ፍጥነትዎን መቀነስ ማለት ነው። ከፍጥነት ገደቡ በታች ማሽከርከር ይችላሉ፤ ነገር ግን ከእሱ መብለጥ ህገወጥ ነው።

**የተለጠፈው ገደብ ምንም ይሁን ምን ሁልጊዜ ደህንነቱ በተጠበቀ ፍጥነት የማሽከርከር ሃላፊነት አለብዎት።**

## ለሁኔታዎች ፍጥነትን ማስተካከል

ፍጥነት መጨመር አደገኛ እና አላስፈላጊ ስጋት ያለው ነው። ዘግይቶ መድረስ፣ ጭራሽ ካለመምጣት ይሻላል። እንደሚከተሉት ባሉ ሁኔታዎች ፍጥነትዎን ይቀንሱ፦

- ታይነት የተገደበባቸው ሹል ኩርባዎች ወይም ዳገቶች
- በዝናብ፣ በጥጥ በረዶ ወይም በድንጋይ በረዶ ምክንያት የሚያንሸራትቱ መንገዶች
- እግረኞች፣ ህጻናት፣ ብስክሌት ነጂዎች ወይም እንስሳት ያሉባቸው ቦታዎች
- የገበያ ማዕከሎች፣ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች እና እግረኛ የሚበዛባቸው አካባቢዎች
- ከባድ የትራፊክ መጨናነቅ
- ጠባብ ድልድዮች እና ዋሻዎች
- የመኖሪያ አካባቢዎች

## 5.2 | ቦታ

በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ቦታን መገምገም ጠቃሚ ችሎታ ነው። ኀበዝ ከመሆንዎ በፊት ጊዜ እና ልምምድ ሊወስድ ይችላል፤ ለዚህም ነው ጀማሪ አሽከርካሪዎች የበለጠ ለአደጋ የተጋለጡ የሆኑት። ቦታን በርቀት ወይም በጊዜ መገመት ይችላሉ፤ ነገር ግን በመንገድ ላይ ያለዎትን ቦታ ያለማቋረጥ መገምገም ያስፈልግዎታል። በሚያሽከረክሩበት ጊዜ በዙሪያዎ ብዙ ቦታ ለመተው ይሞክሩ።

ለተሽከርካሪዎ በቂ ቦታ በመተው ስጋትዎን መቀነስ እና አስፈላጊ ከሆነ አማራጭ መንገድ ለመወሰን ለእራስዎ ጊዜ መስጠት ይችላሉ። በሚጓዙበት መንገድ ላይ ችግር ካለ እርምጃ ለመውሰድ ተጨማሪ ቦታ ይሰጣል።

ከሌሎች ተሽከርካሪዎች አጠገብ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ፣ በእርስዎ እና ከፊት ባለው ተሽከርካሪ መካከል ቢያንስ ከተሽከርካሪዎ ርዝመት ሁለት እጥፍ የሚበልጥ ርቀት መተው አስፈላጊ ነው። ወደ ትራፊክ ፍሰት በሚቀላቀሉበት ጊዜ፣ **ለማቀድ**፣ **ለመግባባት**፣ **ለመፈተሽ**፣ **ለመፈጸም** እና **ለመገምገም** አደጋን የመቆጣጠር ስራዎን ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ እንዲተገብሩ ለራስዎ በቂ ቦታ ይስጡ።



## 5.3 | ወደ ትራፊክ ፍሰት መቀላልቀል

ወደ ትራፊክ ፍሰት በሚቀላቀሉበት ጊዜ፣ በዙሪያዎ ያሉ ሰዎች በድንገት እንዳይዞሩ፣ እንዳይዘገዩ ወይም እንዳያቆሙ ለማድረግ ከበቂ ቦታ ጋር ፍሰቱን ይቀላቀሉ። በጣም ትንሽ ወደሆነ ቦታ ለመቀላቀል መሞከር፣ በተለይም ከፊት ያለው አሽከርካሪ ማቆም ወይም ፍጥነት መቀነስ ካለባቸው፣ አደገኛ ሊሆን ይችላል።



ቀድሞውንም በግዛት ውስጥ ያሉ አሽከርካሪዎች ቅድሚያ የማግኘት መብት አላቸው፣ ስለዚህ መንገዱን ለመቀላቀል ቦታ መፍጠር ፍጥነትዎን በፍጥነት ወይም በዝግታ እንዲያስተካክሉ ሊጠይቅ ይችላል። በግዛት ውስጥ ወደ ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ ለመቀላቀል ሙሉውን የቀለበት መንገድ መቀላቀያውን፣ የመታጠፊያ ምልክትዎን እና መስታወቶችዎን ይጠቀሙ።

### ወደ አነስ ያለ የመንገድ መስመሮች መግባት

ትራፊክ በቀስታ ሲንቀሳቀስ ወይም መስመሩ በመዘጋቱ ምክንያት ሲቆም፣ በተቀላጠፈ ሁኔታ እና በብቃት መቀላቀል አስፈላጊ ነው። ወደ አነስ ያለ የመንገድ መስመሮች የትራፊክ ፍሰት መግባት፦

- የትራፊክ ፍሰትን በ60 በመቶ የሚያሻሽል ዘዴ ነው።
- ሊገመት የሚችል የትራፊክ ፍሰት መቀላቀያ ንድፍ የሚፈጥር ዘዴ ሲሆን ይህም በድንገተኛ የመንገድ መስመር ለውጦች ምክንያት የግጭቶች ስጋትን ይቀንሳል።
- የረጅም መስመሮችን ብስጭት እና መስመር የመቁረጥ ፈተናን ለማስወገድ የሚረዳ ዘዴ ነው።

**ወደ አነስ ያሉ የመንገድ መስመሮች መቀላቀል እንዴት እንደሚቻል፦**

- **በመንገድ መስመርዎ ውስጥ ይቆዩ።** የተመደበው የመቀላቀያ ቦታ ጋር እስኪደርሱ ድረስ ሁለቱንም መስመሮች መጠቀም ይቀጥሉ።

- **በየተራ ይሂዱ።** ልክ እንደ ዚፕ ጥርሶች አንድ ላይ እንደሚቀላቀሉ ሁሉ፣ ከሌላው የመንገድ መስመር ከመጡ ተሽከርካሪዎች ጋር በየተራ መቀላቀል።
- **ትሑት ይሁኑ።** ከመጨረሻው የመንገድ መስመር አንድ ተሽከርካሪ ከፊት ለፊትዎ እንዲቀላቀል ይፍቀዱ እና ወደ ክፍት የመንገድ መስመር ይቀላቀሉ።
- **ፍጥነት ይጠብቁ።** በክፍት የመንገድ መስመር ላይ ካለው የትራፊክ ፍጥነት ጋር በማዛመድ በተረጋጋ ፍጥነት መቀላቀልዎን ይቀጥሉ።

## 5.4 | ጊዜ

ስጋትን ለመቀነስ፣ ለመገምገም እና በትራፊክ ውስጥ ለመንቀሳቀስ በቂ ጊዜ ለራስዎ ይስጡ። እንደ በአይን የሚመራ ጊዜ ያለ ዘዴን መጠቀም ይችላሉ፣ ይህም ሊከሰቱ ለሚችሉ አደጋዎች ከፊት ለፊት ያለውን መንገድ እንዲቃኙ ያስችልዎታል። በአይን የሚመራ ጊዜ የተከላካይ ማሽከርከር አስፈላጊ አካል ነው። አደጋዎችን ለማየት፣ ለመተንተን እና ምላሽ ለመስጠት ጊዜ ይሰጥዎታል። ወደፊት እና ወደ ጎን ማየት እስከሚችሉት ድረስ ይቃኙ። ከኋላ ለመቃኘት መስታወቶችዎን ይጠቀሙ። አደጋን ቀደም ብለው ለይተው ባወቁ ቁጥር ለዚያ ለመዘጋጀት ብዙ ጊዜ ይኖርዎታል እና በዙሪያዎ ያሉ ሰዎች ከለውጦችዎ ጋር ለመላመድ ብዙ ጊዜ ይኖራቸዋል። ይህ ለማሽከርከር ንቁ የሆነ አቀራረብ ነው። አደጋን ለማስወገድ በምላሾችዎ ላይ ከመተማመን ያነሰ አደገኛ ነው።

### ሰከንዶችን ይቁጠሩ

ይህንን ቀላል መልመጃ በመጠቀም ተሽከርካሪዎ የሚጓዝበትን ቦታ በአጭር ጊዜ ውስጥ መገመትን ይለማመዱ፦

1. ከተሽከርካሪዎ 15 ሰከንድ ርቀት ላይ ነው ብለው የሚያስቡትን እንደ የመንገድ ምልክት ወይም የመገልገያ ምሰሶ ያለ ምልክት ይምረጡ።
2. ጠቋሚው ጋር እስኪደርሱ ድረስ ይቁጠሩ።

ከመቁጠርዎ በፊት መገመት ተሽከርካሪዎ በሰከንዶች ውስጥ የሚጓዝበትን ርቀት በትክክል የመገመት ችሎታን እንዲያዳብሩ ይረዳዎታል። ይህንን ዘዴ መለማመድ በሚቀጥሉበት ጊዜ ትክክለኛነትዎ ይሻሻላል።

በእንቅፋቶች እና በማይታወቁ የትራፊክ ሁኔታዎች ውስጥ ለማቆም ወይም ለመንቀሳቀስ ለራስዎ በቂ ጊዜ መስጠት በጣም አስፈላጊ ነው። ከበቂ ጊዜ ጋር፣

በትራፊክ ፍሰት ውስጥ የሚያደርጓቸውን ውሳኔዎች መገምገም እና ቅድሚያ መስጠት ይችላሉ። ይህ ድንጋጤ እና ስሜት ቀስቃሽ ምላሾችን ለመቀነስ ይረዳል።

## እየተቃረቡ ካሉ ተሽከርካሪዎች ፊት መታጠፍ

ከልምድ ጋር ይሻሻላል፣ ነገር ግን እየመጣ ያለ ትራፊክ ሲያጋጥም ለመታጠፍ ምን ያህል ጊዜ እንዳለዎት ለመወሰን ፈታኝ ሊሆን ይችላል። ለራስዎ በቂ ጊዜ ካለመስጠት ይልቅ ብዙ ጊዜ መስጠቱ ይሻላል።




እየቀረበ ያለው ትራፊክ ቅድሚያ የማግኘት መብት እንዳለው ያስታውሱ። መጪ ተሽከርካሪዎች ልክ እንደ ዛፍ ያሉ የመንገዱ ዳር ምልክቶችን ሲያልፉ ማየት እና መታጠፍ የሚፈልጉትን መንገድ እስኪለቁ ድረስ ምን ያህል ሰከንዶች እንደሚወስድ መቁጠር ይችላሉ።

የሚቀጥለው ተሽከርካሪ ተመሳሳይ ርቀት ለመጓዝ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ ለመገመት ያንን የጊዜ ገደብ መጠቀም ይችላሉ። ከዚያ በደህና ለመታጠፍ በቂ ጊዜ ሲኖርዎት ያውቃሉ።




ወደ የትራፊክ ፍሰት መታጠፍ ተመሳሳይ ነገር ይጠይቃል። በሚገቡበት የትራፊክ ፍሰት ላይ ተጽዕኖ ሳያደርጉ ተራዎን ለማጠናቀቅ ጊዜ ያስፈልግዎታል። ለመታጠፍ እና የሚመጣው የትራፊክ ፍጥነት ጋር ለመድረስ በቂ ጊዜ ያስፈልግዎታል።

## 5.5 | ትኩረት

ጥንቃቄ ማድረግ በመንገድ ላይ ለደህንነት እና ግንዛቤ ቅድሚያ እንዲሰጡ ይረዳዎታል።

- **ሀሳብዎ የሚያደርጉት ነገር ላይ ይሁን።** ሙሉ በሙሉ ተሳትፎ ማድረግና ማሽከርከር ላይ ለማተኮር ቁርጠኛ ይሁኑ። እንደ ስልክዎ እና በመኪና ውስጥ መዝናኛ ስርዓቶች ያሉ ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮችን ያጥፉ።
- **ዝግጁ ይሁኑ።** ከፊት ያለውን መንገድ በመቃኘት አደጋዎችን ይገምቱ። በአካባቢዎ ያለውን ነገር በጥንቃቄ ይከታተሉ።
- **ንቁ ይሁኑ።** በመንገድ ሁኔታ፣ በአየር ሁኔታ እና በትራፊክ ላይ በመመስረት ፍጥነትዎን እና የማሽከርከር ባህሪዎን ያስተካክሉ።

### ትኩረት ይስጡ

ደህንነቱ ለተጠበቀ ማሽከርከር ሙሉ ትኩረት መስጠትዎ አስፈላጊ ነው። አእምሮዎ በአንድ ጊዜ አንድ ነገር ላይ ብቻ ማተኮር ይችላል። ከመሪው በስተጀርባ ሲሆኑ በንቃት ትኩረት ለመስጠት ይምረጡ። የአዕምሮ ትኩረትዎን እና የዕይታ ትኩረትዎን ያስተካክሉ። የእርስዎ ትኩረት መስጠት በመንገድ ላይ በጣም ዋጋ ያለው ንብረት ነው።

ውስጣዊ እና ውጫዊ ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮችን ያስወግዱ። ለጥቂት ሰከንዶችም ቢሆን ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮች፣ አስከፊ መዘዞችን ሊያስከትሉ ይችላሉ። በትኩረት እየተከታተሉ በመቆየት እና ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮችን በማስወገድ በመኪና አደጋ ውስጥ የመሳተፍ እድልዎን በእጅጉ መቀነስ ይችላሉ።

## የእይታ መስክ

በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ሶስት ዓይነት ዕይታዎችን ይጠቀማሉ። ከፍተኛ ፍጥነት የእያንዳንዱን ዕይታ አይነት ጥራት ይቀንሳል።

1. **ማዕከላዊ ዕይታ** ዝርዝሩ መረጃ ከፊት ለፊትዎ በቀጥታ እንዲያዩ ያስችልዎታል። እነዚህን ቃላቶች ለማንበብ የሚጠቀሙበት ዕይታ ነው።
2. **የዙሪያ ዕይታ** የአሽከርካሪ መመሪያ ገጽ ጠርዞችን ለማየት የሚጠቀሙበት ነው። ሊያዩት ይችላሉ፣ ነገር ግን ብዙ ትኩረት ላይኖረው ይችላል።
3. **የዳር እይታ** በቃሉ ላይ ትኩረት ሳያጡ ከጎንዎ ማየት የሚችሉት ነገር ነው። እርስዎ ያሉበት ክፍል ግድግዳዎች ወይም ከእርስዎ አጠገብ የሚሄድ አንድ ሰው ሊሆን ይችላል።



## የጉዞ መንገድ

የጉዞ መንገድዎ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመድረስ የሚያሽከረክሩት መንገድ ወይም አቅጣጫ ነው።

የሆነ ጊዜ ላይ መንገድዎን መቀየር ያስፈልግዎ ይሆናል። በአደጋ፣ በአየር ሁኔታዎች፣ ወይም በአዲስ አቅጣጫ መጓዝ ስላለብዎት ማስተካከል ሊያስፈልግዎ ይችላል። አዲሱን የዒላማ ቦታዎን እና የታሰበውን የጉዞ መንገድ በዓይነ ሕሊናዎ መሳል ያስፈልግዎታል።

የማሽከርከር ትልቁ አካል የዕይታ ትኩረትዎን እና የአዕምሮ ትኩረትዎን ባሉበት ቦታ እና መሄድ በሚፈልጉበት ቦታ መካከል በየጊዜው ማዘዋወር ነው።




## የእይታ መስመር

እንዴ መሄድ የሚፈልጉበትን ቦታ ከመረጡ፣ የእይታ መስመርዎ በእርስዎ እና በዒላማው መካከል ያለው ነው። የዕይታ እና የአዕምሮ ትኩረትዎን በጉዞዎ እና በእይታ መስመርዎ መካከል በፍጥነት እና በተደጋጋሚ ይቀያይራሉ። የእይታ ትኩረትን እና የአዕምሮ ትኩረትን በሚከተሉት መካከል እንደሚከፋፈሉ ይወቁ፦

- የእርስዎ የጉዞ መንገድ
- የእርስዎ የእይታ መስመር
- የእርስዎ የታሰበው ዒላማ የተደረገ አካባቢ
- አሁን ያሉ እና ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎች
- ተሽከርካሪዎ (ውስጣዊ እና ውጫዊ)
- ሌሎች የመንገድ ተጠቃሚዎች
- ራስዎ

### መረጃ መሰብሰብ

ሆን ብለው ትኩረት መስጠት እና ንቁ ትኩረት መስጠት ከተሽከርካሪው በስተጀርባ ጥበብ የተሞላባቸው ውሳኔዎችን ለማድረግ የሚያስፈልግዎትን መረጃ ለመሰብሰብ ያግዝዎታል። በተለይም ለመጀመሪያ ጊዜ ማሽከርከር ሲማሩ የጉዞዎን መንገድ እና የእይታ መስመርዎን መቃኘት አንዳንድ ጊዜ ከባድ ሊመስልዎ የሚችል ቀጣይነት ያለው ሂደት ነው። የማያቋርጥ ንቃት እና አነስተኛ ትኩረትን የሚከፋፍሉ ልምዶችን እና የተለመዱ ተግባራትን በመፍጠር ራስዎን ለስኬት ያዘጋጁ።

## 5.6 | የመንገድ እና የመንግስት ሁኔታዎች

የማሽከርከር አካል ማለት የፍጥነት ገደቦችን መከተል እና ለመንገድ ላይ ሁኔታዎች ማስተካከል ማለት ነው። ለምሳሌ፣ ከሹል ኩርባ በፊት፣ መንገዱ የሚያዳልጥ ሲሆን ወይም መንገዱ ላይ ውሃ በሚኖርበት ጊዜ ተሽከርካሪዎን ለመቆጣጠር እንዲረዳዎት ፍጥነትዎን ይቀንሳሉ። የእርስዎ የአደጋ ግንዛቤ፣ የውሳኔ አሰጣጥ እና ጥበብ የተሞላባቸው ምርጫዎች በተለያዩ ሁኔታዎች ምን ያህል ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንደሚጓዙ ማድረግ ላይ ትልቅ ተጽእኖ አላቸው።

### በምሽት መንዳት

በምሽት ለማየት በጣም ከባድ ነው፣ እና እርስዎ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፦

- የግንባር መብራቶች (ብዙውን ጊዜ 400 ጫማ) ውስጥ እንዲያቆሙ በሚያስችል ፍጥነት ይንዱ።
- ከፊት የሚመጡ ተሽከርካሪዎች በሌሉበት ጊዜ ረጅም ጨረሮችን ይጠቀሙ። ትራፊክ ሲቃረብ ወደ መደበኛ የግንባር መብራቶችዎ ይመልሱ።

- ሌላ ተሽከርካሪ ሲከተሉ መደበኛ የግንባር መብራቶችዎን ይጠቀሙ።
- የሚመጡትን የግንባር መብራቶች በቀጥታ ከመመልከት ይቆጠቡ። ዓይኖችዎ ከተሽከርካሪዎ ፊት ለፊት ያለውን መንገድ እንዲፈልጉ ያድርጉ።
- ከእርስዎ የግንባር መብራት ጨረሮች አልፈው ለመፈለግ ይሞክሩ። በመንገድ ላይ ጥቁር ቅርጾችን ወይም ጥላዎችን ይፈልጉ።
- የእግረኛ መንገዱን ጠርዝ ለማግኘት እና ከጎኖቹ ሊመጡ የሚችሉ አደጋዎችን ለመለየት አልፎ አልፎ ወደ ጎን ይመልከቱ።
- በምሽት ወይም ደመናማ በሆኑ ቀናት በሚያሽከረክሩበት ጊዜ የፀሐይ መነፅር ወይም ባለቀለም ሌንሶች አያድርጉ። ቲንትድ ወይም ባለቀለም ሌንሶች ዕይታዎን ይቀንሳሉ።
- በምሽት መንዳት ሁኔታዎች እና ማታ ላይ በማያውቋቸው መንገዶች ላይ ለማሽከርከር ሌሎችን የሚከተሉበትን ርቀት ይጨምሩ።

**አንድ ተሽከርካሪ ረጅም ጨረሮችን አብርቶ ወደ እርስዎ ቢመጣ፣ የግንባር መብራቶቹ እንዳይረብሹዎት የመንገዱን ቀኝ ጎን ይመልከቱ።**

## ኩርባዎች




ኩርባዎች ዙሪያ መንዳት የመንገድ ግንዛቤ እና የተሽከርካሪዎን ቁጥጥር ይጠይቃል። ረጋ ያለ መሪ ማዞር እና ብልህ የማሽከርከር ልማዶች በመንገድ አቀማመጥዎ እና ሚዛን ላይ የተወሰነ ቁጥጥር ይሰጡዎታል። ከእርስዎ ቁጥጥር ውጭ የሆኑት የእንቅስቃሴ ህጎች የመንገድ አቀማመጥ እና ሚዛን ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ።

**ወደ ኩርባ መቅረብ**

- **ፍጥነትዎን ይከታተሉ።** ወደ ኩርባው ከመግባትዎ በፊት ፍጥነትዎን ይቀንሱ። ይህ መሬት የመቆንጠጥ ችሎታን ለመጠበቅ ይረዳል እና ተሽከርካሪዎ ከመንገድ ላይ እንዳይንሸራተት ወይም አቅጣጫውን እንዳይስት ይከላከላል። የዳገት ኩርባዎች የበለጠ መፋጠን ሊያስፈልጋቸው ይችላል፤ የቁልቁለት ኩርባዎች ደግሞ ተጨማሪ ፍሬን መያዝ ሊያስፈልጋቸው ይችላል።
- **ወደፊት ይመልከቱ።** የኩርባውን ሹልነት እና ርዝመት ለመገመት ከፊት ያለውን መንገድ ይቃኙ። ይህ ተገቢውን ፍጥነት እና የመሪ ማዞር ማስተካከያዎችን ለመወሰን ይረዳዎታል።
- **በጣም ጥሩውን የመስመር ቦታ ይምረጡ።** ወደ ኩርባው ሲቃረቡ ተሽከርካሪዎን በትንሹ ከመስመሩ ውጭ ያውጡት። ይህ ለመንቀሳቀስ ተጨማሪ ቦታ ይሰጥዎታል እና በኩርባው ዙሪያ ዕይታዎን ያሻሽልልዎታል።

**ኩርባው ውስጥ**

- **የተረጋጋ ፍጥነት ይኑርዎት።** ኩርባው ውስጥ እያሉ በድንገት ፍሬን መያዝን ወይም ማፋጠንን ያስወግዱ። ይህ የተሽከርካሪዎን ሚዛን ሊያበላሽ እና ወደ ቁጥጥር ማጣት ሊያመራ ይችላል።
- **ረጋ ያለ መሪ ማዞር።** በእርጋታ እና ቀስ በቀስ በኩርባው በኩል መሪ ያዙሩ። ተሽከርካሪዎ እንዲንሸራተት ሊያደርጉ የሚችሉትን ከመጠን በላይ መሪ ማዞር ወይም ድንገተኛ እንቅስቃሴዎችን ከማድረግ ይቆጠቡ።
- **ለማስተካከል ዝግጁ ይሁኑ።** በመንገድ ሁኔታ፣ ታይነት እና በሌሎች አሽከርካሪዎች ባህሪ ላይ በመመስረት ፍጥነትዎን ወይም መሪ ማዞርዎን ለማስተካከል ዝግጁ ይሁኑ።

**ከኩርባው መውጣት**

- **ቀስ በቀስ ያፍጥኑ።** ከኩርባው ሲወጡ በእርጋታ ወደሚፈልጉት ፍጥነት በቀስታ ያፍጥኑ። ይህ መረጋጋትን ለመጠበቅ እና ያለችግር ቀጥታ ወደመጓዝ ለመመለስ ይረዳዎታል።
- **መስታወቶችዎን ይፈትሹ።** አስፈላጊ ከሆነ መስመሮችን ለመቀላቀል ወይም ለመቀየር በቂ ቦታ እንዳለዎት ለማረጋገጥ መስታወቶችዎን ይቃኙ።

**የእንቅስቃሴ ህጎች**

በኩርባ መንገዶች ላይ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ፣ ተሽከርካሪዎ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩትን ኃይሎች መረዳት እና በቁጥጥር ውስጥ ለመቆየት መንዳትዎን ማስተካከል አስፈላጊ ነው።

- **ተሽከርካሪ ወደ ጎን ማዘንበል እና ዮ'ው።** ተሽከርካሪ ወደ ጎን ማዘንበል ተሽከርካሪዎ በሚታጠፍበት ጊዜ ምን ያህል እንደሚያዘነብል ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፣ ዮ'ው ከጎን ወደ ጎን እንቅስቃሴ ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፣ እና ሁለቱም ቁጥጥርን ለመጠበቅ አስፈላጊ ናቸው። ፍጥነትዎን እና መሪውን ማዞር በኩርባዎች ላይ በሚነዱበት ጊዜ ተሽከርካሪ ወደ ጎን ማዘንበልዎን እና ዮ'ው የተመጣጠነ ለማድረግ ይረዳል።
- **ሞመንተም።** ቀጥታ መስመር ላይ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ፣ ተሽከርካሪዎ ወደዚያ አቅጣጫ ሞመንተም አለው። ሆኖም ግን፣ ወደ ኩርባ ሲገቡ፣ የተሽከርካሪዎን አቅጣጫ እና ፍጥነት መቀየር አለብዎት።
- **ኢነርሺያ።** ኩርባ ውስጥ፣ ተሽከርካሪዎ ቀጥታ መስመር ላይ መጓዝ እንዲቀጥሉ ለማድረግ ትንሽ መጎተት ይፈልጋል። በድንገት መሪውን ካዞሩ ኢነርሺያ መኪናው ቀጥ ብሎ እንዲጓዝ ለማድረግ ይሞክራል። ለዚህም ነው መታጠፉን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማድረግ በጥንቃቄ ማሽከርከር ያለብዎት።
- **የካይኔቲክ ጉልበት።** ከፍተኛ ፍጥነቶች የበለጠ ጉልበት የሚፈጥሩ ሲሆን ይህም ለማቆም ወይም አቅጣጫ ለመቀየር ተጨማሪ ጊዜ እና ቦታ ይፈልጋል። ለኩርባዎች ፍጥነትዎን መቀነስ የተሽከርካሪዎን ካይኔቲክ ጉልበት ይቀንሳል እና መሬቱን የመቆንጠጥ ችሎታ ወይም ቁጥጥር ሳያጡ እንዲታጠፉ ያግዝዎታል።
- **ሰበቃ።** ሰበቃ በጎማዎቹ እና በመንገዱ መካከል ያለው ኃይል ነው። ተሽከርካሪዎ መሬቱን ቆንጥጦ እንዲይዝ ያስችለዋል። ሰበቃ በጨመረ ቁጥር ጎማዎችዎ መንገዱን በተሻለ ሁኔታ መቆንጠጥ ይችላሉ። ይህ ፍጥነትዎን እንዲቀንሱ፣ ፍጥነትዎን እንዲጨምሩ ወይም በደህና እንዲታጠፉ ይረዳዎታል። በዝናብ፣ በጥጥ በረዶ ወይም በበረዶ ምክንያት የሚያንሸራትቱ መንገዶች በኩርባዎች ላይ ያለውን ሰበቃ በእጅጉ ሊቀንሱ ይችላሉ። ይበልጥ ፍጥነት ይቀንሱ እና በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ድንገተኛ እንቅስቃሴዎችን ያስወግዱ።

## የሚያንሸራትቱ መንገዶች



የWashington አየር ሁኔታ የሚያንሸራትቱ መንገዶችን ሊያስከትል ይችላል። ዝናብ፣ ጥጥ በረዶ እና በረዶ በመንገድ ላይ አደጋዎችን ይፈጥራሉ። መንገዱ የሚያዳልጥ ሲሆን ማሽከርከርዎን ለሁኔታዎቹ ማስተካከል አለብዎት፣ ይህም ከተለጠፈው የፍጥነት ገደብ በታች መንዳት ሊያስፈልግዎ ይችላል።

በሞቃትማ ቀን ላይ ዝናብ መዝነብ ከጀመረ በመጀመሪያዎቹ ደቂቃዎች መንገዱ በጣም ሊያንሸራተት ይችላል። ሙቀት በአስፓልት ውስጥ ያለው ዘይት ወደ ላይ እንዲመጣ ያደርገዋል። ዘይቱ እስኪታጠብ ድረስ መንገዱ ያንሸራትታል።



በጥጥ በረዶ የተሸፈኑ መንገዶች ሰፋ ያለ የመከተያ ርቀት እና በከፍተኛ ሁኔታ የተቀነሰ ፍጥነት ይፈልጋሉ።

- በሚያስፈልግበት ጊዜ የበረዶ ጎማዎችን ወይም ሰንሰለቶችን ይጠቀሙ።
- በክረምት ወራት፣ በጎማዎ ላይ ሰንሰለቶችን በማከል ወይም ወደ ጉጥ ያላችው ጎማዎች በመቀየር መሬቱን የመቆንጠጥ ችሎታ ማሻሻል ይችላሉ።

በተቻለ መጠን በረዷማ መንገዶችን ያስወግዱ። በበረዷማ መንገዶች ላይ መንዳት ካለብዎት ፍጥነትዎን ይቀንሱ እና በተሽከርካሪዎ ዙሪያ ተጨማሪ ቦታ ይተዉ።

- በቀዝቃዛ እና እርጥበታማ ቀናት ጥላ ያለባቸው ቦታዎች በረዷማ ሊሆኑ ይችላሉ።
- ተደራራቢ ድልድዮች እና ሌሎች የድልድይ ዓይነቶች ቀሪው መንገድ ባይኖረውም እንኳ በረዷማ ቦታዎች ሊኖራቸው ይችላል።
- ከበረዶነት በታች ያለው የሙቀት መጠን ወደ በረዶነት ቅርብ የሆነ የሙቀት መጠን ሲሞቅ በረዶው ሊቀልጥ እና እርጥብ ሊሆን ይችላል። ይህም መንገዱን የበለጠ የሚያዳልጥ ያደርገዋል።
- *ጥቁር በረዶ*ለአሽከርካሪዎች ለማየት የሚከብድ ቀጭን የበረዶ ሽፋን ያመለክታል። በረዶ ባይታይዎትም እንኳ ለበረዶነት ቅርብ የሆኑ ወይም ከበረዶነት በታች ባለው የሙቀት መጠን ሲያሽከረክሩ ትኩረት ይስጡ። ብዙ አሽከርካሪዎች ጥቁር በረዶ ላይ ተሽከርካሪዎቻቸውን መቆጣጠር ሲያቅታቸው ይጋጫሉ።

## መንሸራተት

ጎማዎቹ መንገዱን ቆንጥጠው መያዝ በማይችሉበት ጊዜ መንሸራተቶች ይከሰታሉ። ከፍተኛ ፍጥነት እና የሚያንሸራትቱ መንገዶች በድንገት ከታጠፉ ወይም ካቆሙ የመንሸራተት እድልን ይጨምራሉ። ተሽከርካሪው በሚንሸራተትበት ጊዜ መቆጣጠር ስለማይችሉ ገና ከመጀመሪያው መንሸራተትን ማስቀረት የተሻለ ነው።

እየተንሸራተቱ ከሆነ የሚከተሉትን ያድርጉ፦

1. **እግርዎን ከማፍጠኛ ፔዳሉ ላይ ያንሱ።**
2. **ፍሬንዎን ይጫኑ ወይም ፓምፕ ያድርጉ።** አንቲሎክ ፍሬኖች በፍጥነት ፍጥነትዎን ለመቀነስ የጎማዎችን እሽክርክሪት ለመቆጣጠር ይረዳል። እንዲሁም ተሽከርካሪውን ማዞር እንዲቀጥሉ ያስችሉዎታል። አንቲሎክ ፍሬኖች ከሌለዎት የፍሬን ፔዳሉን በፍጥነት መጫን የበለጠ እንዲንሸራተቱ ሊያደርግዎት ይችላል።

3. **ተሽከርካሪዎ በሚንቀሳቀስበት ተመሳሳይ አቅጣጫ መሪውን ያዙሩ።**
4. **መሪውን ማስተካከል ይቀጥሉ።** ጎማዎችዎ እንደገና የመቆንጠጥ ችሎታቸውን እስኪያገኙ እና መሪ ወደሚያዞሩበት አቅጣጫ እስኪሄዱ ድረስ መሪውን ያስተካክሉ።
5. **ሁኔታውን ይገምግሙ።** ከተቆጣጠሩ በኋላ የመንገዱን ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገቡ እና እንደ አስፈላጊነቱ የማሽከርከር ባህሪዎን ያስተካክሉ።

## በውሃ ላይ መንሳፈፍ

በውሃ ላይ መንሳፈፍ የሚከሰተው በጎማዎ እና በመንገድ ወለል መካከል ውሃ ሲከማች ነው። ይህ ጎማዎቹ የመቆንጠጥ ችሎታቸውን እንዲያጡ እና እንዲሸራተቱ ያደርጋል። ተሽከርካሪው የሚንሳፈፍ ወይም የሚንሸራተት ሆኖ ሊሰማ ይችላል፣ ይህም ለመቆጣጠር ከባድ ያደርገዋል። በውሃ ላይ ከመንሳፈፍ ራስን ለመጠበቅ ምርጡ መንገድ መንገዱ እርጥብ በሚሆንበት ጊዜ ፍጥነት መቀነስ ነው።

በውሃ ላይ እየተንሳፈፉ ከሆነ የሚከተሉትን ማድረግ አስፈላጊ ነው፦

1. **እግርዎን ከማፍጠኛ ፔዳሉ ላይ ያንሱ።**
2. **ፍሬኑን በቀስታ ይጫኑ።** አንቲሎክ ፍሬኖች ተሽከርካሪው ከመንገዱ ጋር እንደገና እንዲገናኝ ይረዳሉ። አንቲሎክ ፍሬኖች ከሌለዎት የፍሬን ፔዳሉን በኃይል መጫን ይበልጥ ውሃ ላይ እንዲንሳፈፉ ሊያደርግዎት ይችላል።
3. **መሪውን አረጋግተው ይያዙት።** መሪውን ከመጠን በላይ ማስተካከል ወይም ማወዛወዝ ያስወግዱ።
4. **መሄድ ወደሚፈልጉበት ይመልከቱ።** ጎማዎችዎ መሬት የመቆንጠጥ ችሎታቸውን መልሰው እስኪያገኙ በእርጋታ እየጠበቁ ሳለ በመንገዱ ላይ ያተኩሩ።
5. **ሁኔታውን ይገምግሙ።** ከተቆጣጠሩ በኋላ የመንገዱን ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገቡ እና እንደ አስፈላጊነቱ የማሽከርከር ባህሪዎን ያስተካክሉ።

## 5.7 | የተሽከርካሪ ብልሽቶች

በመንገድ ላይ የተሽከርካሪ ብልሽቶች ካጋጠሙዎት እነዚህን ምክሮች ያስታውሱ፦

- ከተቻለ ተሽከርካሪዎን ከመንገድ ያስወጡ እና ከትራፊክ ያርቁ።
- ሌሎች አሽከርካሪዎች የተሽከርካሪዎ ግልጽ ዕይታ በሚኖራቸው ቦታ ያቁሙ፣ በተለይ ተሽከርካሪዎን ከመንገድ ማስውጣት ካልቻሉ። ዳገት አፋፍ ላይ ወይም በኩርባ ዙሪያ ማቆምን ያስወግዱ።
- የአደጋ ጊዜ ብልጭታዎችን እና የፊት መብራቶችን ያብሩ።
- ከተሽከርካሪው ጀርባ ከ200 እስከ 300 ጫማ ርቀት ላይ የአደጋ ጊዜ እሳቶችን በማድረግ ሌሎች የመንገድ ተጠቃሚዎችን ያስጠንቅቁ።
- የአደጋ ጊዜ እሳቶች ወይም ሌላ የማስጠንቀቂያ መሣሪያ ከሌለዎት ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ይቁሙ እና በተሽከርካሪዎ ዙሪያ ላለው ትራፊክ እጅዎን ያወዛውዙ።
- የአደጋ ጊዜ ምልክት ለመስጠት ኮፈኑን ይከፈቱት ወይም አንቴናው፣ የጎን መስታወት ወይም የበር እጀታው ላይ ነጭ ጨርቅ ይሰሩ።

### ጎማዎች

ጎማ ከፈነዳ ውይም በድንገት ከተነፈሰ፦

- መሪውን አጥብቀው ይያዙ እና ተሽከርካሪው ቀጥታ እንዲሄድ ያድርጉ።
- ቀስ በቀስ ፍጥነት ይቀንሱ። እግርዎን ከማፍጠኛ ፔዳሉ ላይ ያንሱ።
- ፍሬን አይጫኑ። ተሽከርካሪው በራሱ ፍጥነት እንዲቀንስ ያድርጉ ወይም አስፈላጊ ከሆነ በቀስታ ፍሬን ይያዙ።
- ከተቻለ ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ከመንገዱ ይውጡ እና የአደጋ ጊዜ ብልጭታዎችን ያብሩ። ጎማዎን ለመቀየር ወደ አስተማማኝ ቦታ መድረስ ካልቻሉ፣ የአደጋ ግዜ ማስጠንቀቂያ መብራቶችን ያብሩ፣ በተሽከርካሪዎ ውስጥ ይቆዩ እና ለእርዳታ ይደውሉ።
- ጎማው እንዲጠግን ወይም እንዲተካ ያድርጉ።

## ኃይል

በሚነዱበት ጊዜ ሞተሩ፦

- መሪውን አጥብቀው ይያዙት። መሪው ለመዞር አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል ይገንዘቡ፣ ነገር ግን ሊያዞሩት ይችላሉ።
- የማምለጫ መንገድ ይፈልጉ። የፍሬ ፔዳሉን በኃይል አይጫኑት። በምትኩ፣ ፔዳሉ ላይ የተረጋጋ ግፊት በማድረግ ፍሬን ይያዙ፣ ፍጥነትዎን ይቀንሱ፣ እና ከዛ ከመንገዱ ይውጡ።
- ያቁሙ እና ሞተሩን እንደገና ለማስጀመር ይሞክሩ። ካልተሳካ፣ ኮፈኑን ይክፈቱት እና የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያ መብራቶችን ያብሩ። እርዳታ ለማግኘት ይደውሉ።

## የፊት መብራቶች

የፊት መብራቶችዎ በድንገት ከጠፉ፦

- የአደጋ ግዜ ማስጠንቀቂያ መብራቶችዎን፣ የፍሬቻ መብራቶችን (አቅጣጫን የሚያመለክቱ መብራቶች) ወይም ከያዟቸው የጭጋግ መብራቶችን ያብሩ።
- በተቻለ ፍጥነት ከመንገዱ ያውጡ።

## ማፍጠኛ

ተሽከርካሪው ፍጥነቱን እየጨመረ መሄዱን ከቀጠለ፦

- አይኖችዎን በመንገዱ ላይ ያድርጉ።
- ማርሽዎን በፍጥነት ወደ ዜሮ ወይም ኒውትራል ይቀይሩ።
- ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ ማድረግ በሚችሉበት ጊዜ፣ ከመንገዱ ለቀው ያውጡ።
- ሞተሩን ያጥፉት።

## 5.8 | ስጋቶችን ማሳወቅ

ስጋት በሁሉም ቦታ አለ፦ በከተማ እና በክፍለ ሀገር ከተሞች፣ በአውራ ጎዳናዎች፣ በገጠር መንገዶች፣ በመኪና ማቆሚያዎች እና በመግቢያ መንገዶች። አሁን ስላሉት እና ሊከሰቱ ስለሚችሉ ስጋቶች ራስዎን ያሳውቁ። ስጋት እንዳለ ለሌሎች መነጋገር የሚያስፈልግዎ ጊዜያት ሊኖሩ ይችላሉ። የእርስዎን መብራቶች፣ ክላክስ እና የእጅ ምልክቶች በጥንቃቄ አጠቃቀምዎ እንደየሁኔታው ሊለያዩ ይችላሉ – ነገር ግን ከሌሎች የመንገድ ተጠቃሚዎች ጋር ለመነጋገር ውጤታማ መንገዶች ሊሆኑ ይችላሉ።



## 5.9 | ግጭቶች

ሁሉም አሽከርካሪዎች በመጨረሻ ድንገተኛ ሁኔታ ውስጥ ይገባሉ። ምንም ያክል ጠንቃቃ ቢሆኑ እንኳን፣ ችግር ሊፈጥሩብዎ የሚችሉ ሁኔታዎች አሉ። ሁሉም አሽከርካሪዎች የመኪና አደጋዎችን የመከላከል ኃላፊነት አለባቸው። አንዳንድ ጊዜ ይህ የማምለጫ ዘዴዎችን እንዲጠቀሙ ያስገድድዎታል፣ ነገር ግን መሠረታዊ የፊዚክስ ሕጎች ግንዛቤን መያዝ ግጭትን ለማስወገድ ይረዳል። ምንም ያህል በጥሩ ሁኔታ ቢነዱም፣ አሁንም በግጭት ውስጥ ሊሳተፉ ይችላሉ።

ግጭቶች በተለምዶ ሦስት ምክንያቶች አሏቸው፡-

1. ከመጠን በላይ ፍጥነት
2. በጣም ትንሽ ቦታ
3. በቂ ያልሆነ ሁኔታዊ ግንዛቤ።

### ተሽከርካሪን መግጨት

- ቦታውን ለቅቀው አይሂዱ። ማንኛውሰው ሰው ከተጎዳ ወይም ከሞተ፣ ወደ 911 ይደውሉ። ሕግ አስከባሪ አካላት ማወቅ አለባቸው።
- ተሽከርካሪውን በተቻለ ፍጥነት ወደ መንገዱ ዳር ያንቀሳቅሱት፣ ነገር ግን ከግጭቱ ቦታ አጠገብ መሆን አለበት።
- በመስመሮች ውስጥ አይቁሙ ወይም አይራመዱ። በሌላ ተሽከርካሪ ሊገጩ ይችላል።

- ስለ ግጭቱ ሌሎች አሽከርካሪዎችን ለማስጠንቀቅ የአደጋ ጊዜ እሳቶች ወይም ሌሎች የማስጠንቀቂያ መሣሪያዎችን ይጠቀሙ።
- የተበላሹ ተሽከርካሪዎችን ሞተር ያጥፉ።
- በተበላሹ ተሽከርካሪዎች አካባቢ አያጨሱ። ነዳጅ ፈሶ ሊሆን ይችላል እና እሳት ትክክለኛ አደጋ ነው።
- ግጭቱ የቆመ ተሽከርካሪን የሚያካትት ከሆነ ባለቤቱን ለማግኘት መሞከር አለብዎት። ማግኘት ካልቻሉ፣ በቀላሉ ሊያዩት በሚችሉበት ቦታ ላይ ማስታወሻ ይተዉ። ግጭቱ የተከሰተበትን ቀን እና ሰዓት እንዲሁም አድራሻዎን ያካትቱ።

## የትራፊክ አደጋን ሪፖርት ማድረግ

ከግጭት በኋላ፣ አደጋውን ሪፖርት ለማድረግ የሚረዳዎትን መረጃ ይሰብስቡ።

- ከተሳተፉት ሌሎች ሰዎች መረጃ ይሰብስቡ። እንዲሁም የእርስዎን መረጃ ማጋራት አለብዎት። የሚከተሉትን መለዋወጥ ያስፈልግዎታል፦
    - ስም፣ የእውቂያ መረጃ እና የመንጃ ፈቃድ (driver license) ቁጥር
    - የኢንሹራንስ ኩባንያ እና የፖሊሲ ቁጥር
- በተሽከርካሪዎቹ ላይ የደረሰውን ማንኛውንም ጉዳት ፎቶዎችን ያንሱ ወይም ቪዲዮዎችን ይቅዱ።
- ከተጠየቁ፣ ለፖሊስ ወይም ለሌላ የአደጋ ጊዜ ባለስልጣናት መረጃ ያቅርቡ።
- የሕግ አስከባሪ መኮንን ይህንን ካላደረገልዎ በ4 ቀናት ውስጥ የግጭት ሪፖርት ቅጽ ያስገቡ። ቅጹ በግዛቱ ሕግ መሰረት ያስፈልጋል። ወደ dol.wa.gov ይሂዱ እና **collision report form (የግጭት ሪፖርት ቅጽ)** ብለው ይፈልጉ።

## ጉዳትን ሪፖርት ማድረግ

ጉዳቶች ግጭት ከተከሰተ በኋላ ተጨማሪ ጭንቀት ሊጨምሩ ይችላሉ። በተቻለ መጠን ለመረጋጋት ይሞክሩ፣ ራስዎን ይገምግሙ እና ከዛ ሌሎችን ይርዱ።

- ወደ 911 ይደውሉ።
- እየተቃጠለ ባለ ተሽከርካሪ ውስጥ ወይም ድንገተኛ አደጋ ውስጥ ካልሆኑ በስተቀር የተጎዱ ሰዎችን አያንቀሳቅሱ።
- አስቀድሞ የማይራመድ እና የማይናገር ማንኛውንም ሰው ይርዱ። እየተነፈሱ መሆናቸውን ይፈትሹ፣ ከዚያም የደም መፍሰስ ካለ ይፈትሹ።

- የደም መፍሰስ ካዩ እነዚህን እርምጃዎች ይከተሉ፦
    - በእጆችዎ ግፊትን ይተግብሩ።
    - ማሰሪያ/መጠቅለያ ይተግብሩ።
    - ተርንኬት ይተግብሩ።
- ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ምንም የሚጠጣ ነገር አይስጧቸው – ውሃ እንኳን ቢሆን።
- ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች እንዲሞቁ እና ወደ ድንጋጤ እንዳይገቡ ለማገዝ በብርድ ልብስ ወይም ኮት ይሸፍኑ።

## 911 መደወል

የመኪና አደጋ ሲያጋጥም የአደጋ ጊዜ እርዳታ ለማግኘት ወደ 911 መደወል አስፈላጊ ነው። የሚከተሉትን ልብ ይበሉ፦

1. **ይረጋጉ።** በተረጋጋ መንፈስ ለመቆየት ይሞክሩ። ይህ ለጥሪ አስተላላፊው ግልጽ እና ትክክለኛ መረጃ እንዲሰጡ ይረዳዎታል።
2. **ሁኔታውን ይገምግሙ።** አደጋው ምን ያህል ከባድ እንደሆነ እና በእርስዎ ወይም በሌሎች ላይ የደረሰውን ጉዳት በፍጥነት ይገምግሙ።

ከ911 ጥሪ አስተላላፊ ጋር ሲነጋገሩ፦

1. **አካባቢዎን መናገር አለብዎት።** ማናቸውንም የሚታወቁ ምልክቶችን ወይም የማይል ምልክቶችን ጨምሮ አካባቢዎን ለጥሪ አስተላላፊው በግልፅ ይግለጹ። ስለ አካባቢዎ እርግጠኛ ካልሆኑ፣ የድንገተኛ አደጋ ምላሽ ሰጭዎች እርስዎን እንዲያገኙ ለማገዝ የተቻለውን ያህል ዝርዝር ለማቅረብ ይሞክሩ።
2. **ሁኔታውን ይግለጹ።** የተጎዱትን ተሽከርካሪዎች ብዛት፣ የደረሰውን ጉዳት እና ማናቸውንም ጉዳቶች ጨምሮ ስለግጭቱ አጭር መግለጫ ይስጡ።
3. **የጥሪ አስተላላፊውን መመሪያዎችን ይከተሉ።** ሁኔታውን ለመገምገም እና መመሪያዎችን ለመስጠት የጥሪ አስተላላፊው ጥያቄዎችን ሊጠይቅ ይችላል።

4. **ዝርዝሮችን ያቅርቡ።** አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ ዝርዝሮችን ለመስጠት ዝግጁ ይሁኑ። እነዚህ ዝርዝሮች የተሽከርካሪ ዓይነቶችን፣ የታርጋ ቁጥሮችን እና ማናቸውንም አደጋዎች ሊያካትቱ ይችላሉ።
5. **የስልክ ጥሪው ላይ ይቆዩ።** እርዳታ እስኪያገኙ ድረስ ከጥሪ አስተላላፊው ጋር በስልክ ይቆዩ።

## የኃይል መስመሮች ሲያጋጥሙ

**የኤሌክትሪክ መስመር ከተሽከርካሪዎ ጋር ከተገናኘ ከተሽከርካሪው አይውጡ።**

ግጭት የኤሌክትሪክ መስመሮችን የሚያካትት ከሆነ ልዩ ጥንቃቄዎችን ማድረግ ያስፈልግዎታል። የድንገተኛ አደጋ ምላሽ ሰጪዎች እስኪመጡ ድረስ ሞተርዎን ያጥፉ፣ ወደ 911 ይደውሉ እና በተሽከርካሪዎ ውስጥ ይቆዩ። የኤሌትሪክ መስመር እንዴት፣ መቼ እና ኃይል ይኑረው አይኑረው አያውቁም፣ ነገር ግን ሁሉም ኃይል እንዳላቸው አድርገው ይውሰዷቸው።

በድንገት በኤሌክትሪክ መስመር ላይ ከነዱ ወዲያውኑ ያቁሙ። ወደ ፊት ወይም ወደ ኋላ መሄድ በኤሌክትሪክ የመያዝ አደጋ ላይ ይጥልዎታል። ለመውጣት ደህና እንደሆነ እስኪነገርዎት ድረስ ወደ 911 ይደውሉ እና በተሽከርካሪዎ ውስጥ ይቆዩ።

የኤሌክትሪክ መስመሮች በተሽከርካሪዎ ላይ ከወደቁ፣ ወይም የትራንስፎርመር ሳጥን ከገጩ፣ በተሽከርካሪዎ ውስጥ ይቆዩ እና ወደ 911 ይደውሉ። በተሽከርካሪዎ ዙሪያ ያለው መሬትም የኤሌክትሪክ ኃይል ሊኖረው ይችላል። በሚቻል ጊዜ፣ ሰዎች ቢያንስ በ35 ጫማ ርቀት ላይ እንዲቆዩ ያበረታቱ።

ተሽከርካሪዎ ከኤሌክትሪክ መስመሮች ጋር ከተገናኘ እና የእሳት ቃጠሎ ከተነሳ፣ ተሽከርካሪውን ለቀው መውጣት ይኖርብዎታል። ከተሽከርካሪው ዘልለው መወጣትዎ በጣም አስፈላጊ ነው። በርዎን ይክፈቱ፣ እና በበሩ ጫፍ ላይ ይቀመጡ። ክንዶችዎ ከጎንዎ እንዳሉ ከተሽከርካሪዎ በተቃራኒ ይዝለሉ። ተሽከርካሪውን ላለመንካት ይጠንቀቁ። ሁለቱም እግሮችዎ አንድ ላይ ማረፋቸውን ያረጋግጡ። በኤሌትሪክ መያዝን ለማስወገድ፣ ለደህንነት 35 ጫማ ርቀት ያህል ይንቀሳቀሱ። ይህን ለማድረግ ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን እስካልተነገርዎ ድረስ ለማንኛውም ዕቃዎ ወደ ተሽከርካሪው አይመለሱ።

## ስለግጭት ምስክር መሆን

- የአደጋ ጊዜ ምላሽ ሰጪዎችን አያግዱ።
- በፖሊስ፣ በእሳት አደጋ ተከላካዮች እና ሌሎች በቦታው ላይ ትራፊክ እንዲመሩ ስልጣን በተሰጣቸውን ሰዎች የተሰጡ መመሪያዎችን ይከተሉ።
- በሚያልፉበት ጊዜ በማሽከርከርዎ ላይ በማተኮር የድንገተኛ አደጋ ምላሽ ሰጪዎችን እና በግጭት ቦታ ላይ የተሳተፉ ሰዎችን ደህንነት ይጠብቁ። ክስተቱን ለማየት ፍጥነት መቀነስ የትራፊክ መጨናነቅ ይፈጥራል።

## የአደጋ ጊዜ መሣሪያ ስብስብ

በተሽከርካሪዎ ውስጥ የአደጋ ጊዜ መሣሪያ ስብስብ ማስቀመጥ ጥሩ ሀሳብ ነው። በድንገተኛ አደጋ ጊዜ እንዲኖርዎ የሚፈልጓቸው አንዳንድ ነገሮች እዚህ አሉ፦

- ☐ **የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ መሣሪያ ስብስብ**
- ☐ **የእጅ ባትሪ**
- ☐ **ብርድ ልብስ**
- ☐ **ውሃ**
- ☐ **ጃምፐር ኬብሎች**
- ☐ **የመሣሪያ ስብስብ ወይም ሁለገብ የመገልገያ መሣሪያ**
- ☐ **የመጠባበቂያ ስልክ ቻርጀር ወይም የኃይል ምንጭ**
- ☐ **ተለዋጭ ጎማ፣ የጎማ መፍቻ፣ ጃክ (ክሪክ)**
- ☐ **አንጸባራቂ ሶስት ማዕዘን ወይም የእሳት ነበልባሎች**

የጠቃሚ ስልክ ቁጥሮች (የቤተሰብ አባላት፣ የኢንሹራንስ አቅራቢዎች) የወረቀት ቅጂ መያዝ ጥሩ ሀሳብ ነው። የስልክዎ ባትሪ ካለቀ እና በሌላ ስልክ መደወል ካለብዎት የወረቀት ቅጂው ጠቃሚ ይሆናል።

## 5.10 | የህግ አስከባሪዎች

የWashington መንገዶች የሚተዳደሩት በፖሊስ እና በግዛት ኤጀንሲዎች ነው። በጉዞዎችዎ ወቅት፣ የግዛት፣ ካውንቲ ወይም የአካባቢ ሕግ አስከባሪዎች፣ እንዲሁም የድንገተኛ አደጋ ምላሽ ሰጪዎች ሊያጋጥሙዎ ይችላሉ።




### የህግ አስከባሪዎች ሲያስቆምዎት

አሽከርካሪዎችን ለማቆም የሚሞክሩ የፖሊስ ተሽከርካሪዎች ብልጭ ድርግም የሚሉ መብራቶችን እና/ወይም ሳይረን ድምጽ ያበራሉ። አንድ የሕግ አስከባሪ መኮንን ካስቆሙዎ የሚከተሉትን ያስታውሱ፦



1. የመታጠፊያ ምልክትዎን ይጠቀሙ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ሲሆን ከመንገዱን ወደ ቀኝ መኪናዎን ያቁሙ።



2. ሞተሩን እና እንደ ሬዲዮ ያሉ ማናቸውንም የድምጽ መሣሪያዎች ያጥፉ።



3. እንዲወጡ በመኮንኑ ካልታዘዙ በስተቀር በተሽከርካሪዎ ውስጥ ይቆዩ።



4. በምሽት ከሆነ የቆሙት የውስጥ መብራቶችን ያብሩ። መኮንኖች ለተጨማሪ ታይነት ስፖትላይት ሊጠቀሙ ይችላሉ።



5. እጆችዎን በመሪው ላይ ያቆዩ።



6. መኮንኑ ለእርስዎ ወይም ለተሳፋሪዎችዎ የሚሰጡዎትን ሁሉንም መመሪያዎች ይከተሉ።

**መኮንኑ ወደ ተሽከርካሪው ከሁለት በአንዱ በኩል ሊጠጋ ይችላል። መኮንኑ ወደ ተሽከርካሪው ሲቀርብ፣ የሚከተሉትን ያስታውሱ፦**

1. እርስዎ እና መኮንኑ መነጋገር እንዲችሉ ተዛማጅ መስኮቱን ዝቅ ያድርጉ።
2. በተሽከርካሪው ውስጥ የጦር መሣሪያ ከያዙ ወዲያውኑ ለመኮንኑ ያሳውቁ።
3. የመንጃ ፈቃድዎን ወይም የተሽከርካሪ ሰነዶችን ለመፈለግ እጅዎን ከመዘርጋትዎ በፊት የኃላፊው መመሪያዎችን ይጠብቁ።

**የሕግ አስከባሪዎች ካስቆሙዎት፣ አንድ መኮንን በተለምዶ የሚከተሉትን ያደርጋል፦**

- ለምን እንዳስቆምዎ ያብራራል።
- የሚከተሉትን ይጠይቅዎታል፦
    - የመንጃ ፈቃድ (Driver license)
    - የኢንሹራንስ ማረጋገጫ (Proof of insurance)
    - የተሽከርካሪ ምዝገባ (Vehicle registration)

**እነዚህን ሰነዶች ለመፈለግ እጅዎን ከመዘርጋትዎ በፊት የት እንደሚገኙ ለመኮንኑ ይናገሩ።**

- ምን እርምጃ እየወሰዱ እንደሆነ ያብራራሉ (ማስጠንቀቂያ ወይም ትኬት መስጠት ወይም በቁጥጥር ስር ማዋል)። መኮንኑ የሚወስዱትን እርምጃ ካላብራሩ፣ እንዲያብራሩልዎ መጠየቅ ይችላሉ።

ለመኮንኑ በአክብሮት ጥያቄዎቹን መጠየቅ ይችላሉ። በመኮንኑ ውሳኔ ወይም በድርጊቱ ካልተስማሙ ከመኮንኑ ጋር በመጨቃጨቅ ንግግርን አያራዝሙ። በፍርድ ቤት ውሳኔውን ለመቃወም መጠየቅ ይችላሉ።

መኮንኑ ተገቢ ያልሆነ ተግባር ፈጽመዋል ብለው ካመኑ ወይም በሥነ ምግባራቸው ላይ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ወደ መኮንኑ ኤጀንሲ መደወል ወይም ማነጋገር እና የበላይ ተቆጣጣሪ እንዲያናግርዎ መጠየቅ ይችላሉ። ይህ የሕግ አስከባሪዎች ካስቆሙዎት በኋላ በተቻለ ፍጥነት ቢከናወን ጥሩ ነው።

## የቅጣት ትኬት ማግኘት

የቅጣት ትኬት ከተሰጥዎ ለእሱ መፈረም ያስፈልግዎታል። የእርስዎ ተቀባይነት እና ፊርማ ጥፋተኝነትን መቀበል ማለት አይደለም። ሆኖም ግን፣ የትራፊክ ትኬት ለመፈረም አለመቀበል እስር ሊያስከትል ይችላል።

የማሽከርከር መብቶችዎ እንዳይታገዱ በ15 ቀናት ውስጥ በትኬቱ ጀርባ ላይ ያሉትን መመሪያዎች መከተል ያስፈልግዎታል። በታገደ መንጃ ፈቃድ ማሽከርከር ተሽከርካሪዎን ሊያሳጣዎ እና/ወይም መታሰርን ሊያስከትል ይችላል።

# ማጠቃለያ

የWashington መንገዶች በግዛታችን ውስጥ ያሉ ሁሉንም ማህበረሰብ ያገናኛሉ። ወደ ስራ ለመሄድ፣ እቃዎችን ለማድረስ እና የሰሜን ምዕራብ ፓሲፊክን ውበት ለመቃኘት እንጠቀምባቸዋለን።

ልብ ይበሉ፣ ብልህ የማሽከርከር ልማዶች ደህንነቱ የተጠበቀ እና አስደሳች የማሽከርከር ልምድ መሰረት ናቸው።

ጥሩ አሽከርካሪዎች የሚከተሉት ናቸው፦

- **ንቁ።** ሁል ጊዜ አካባቢያቸውን እና ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን ያውቃሉ።
- **የደህንነት ቀበቶ ያሰሩ።** ለእያንዳንዱ ጉዞ በትክክል በደህንነት ቀበቶዎች ያስራሉ።
- **የተረጋጉ።** ግልፍተኛ ባህሪን የሚያስወግዱ እና ከመሪው በስተጀርባ ስሜቶችን የሚቆጣጠሩ።
- **ትኩረት ያላቸው።** ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮችን የሚያስወግዱ እና በማሽከርከር ላይ ያተኮሩ።
- **ያልሰከሩ።** በአልኮል ወይም በአደንዛዥ ዕፅ ተጽዕኖ ስር በጭራሽ የማያሽከረክሩ።

ልምድ በራስ መተማመንን ያዳብራል፤ ይሁን እንጂ ቸልተኝነትን ለማስወገድ ይጠንቀቁ። ማሽከርከር ህጎች፣ ተሽከርካሪዎች እና የማሽከርከር ሁኔታዎች ሲቀያየሩ ቀጣይነት ያለው ትምህርት እና መላመድን ይጠይቃል።

**ወደ Washington የጋራ የማሽከርከር ማህበረሰብ እንኳን በደህና መጡ። የመንገዶቹን ደህንነት ለሁሉም ሰው ለማስጠበቅ በጋራ እንስራ።**

## ሙዳየ ቃላት

**መደበኛ የምልክት ቀለሞች፡-** የተወሰኑ ትርጉሞችን ለማስተላለፍ ለተዘጋጁ የትራፊክ ምልክቶች የሚያገለግሉ ቀለሞች።

**መንሸራተት፡-** ተሽከርካሪው ከቁጥጥር ውጭ እንዲንሸራተት የሚያደርገውን መሬትን የመቆንጠጥ ችሎታ ማጣት።

**መታወቂያ፡-** እንደ ስምዎ፣ የልደት ቀንዎ ወይም ፎቶግራፍዎ ያሉ የግል መረጃዎችን የያዘ ሰነድ።

**መዞር፡-** በሚያሽከረክሩበት ጊዜ አቅጣጫ መቀየር።

**ሚዛኑን የጠበቀ ክብደት፡-** መረጋጋትን ለመጠበቅ በተሽከርካሪ ውስጥ የክብደት እኩል መከፋፈል።

**ማለፍ ወይም መተላለፍ፡-** ሌላ ተሽከርካሪ ማለፍ።

**ማሳለጫ፡-** 2 ወይም ከዚያ በላይ መንገዶች የሚገናኙበት ቦታ።

**ማንነት፡-** ስማቸውን፣ የልደት ቀናቸውን እና ሌሎች የግል መረጃዎችን ጨምሮ የአንድ ሰው ማንነት።

**ማዕዘናዊ የመኪና ማቆም፡-** ከኩርባው አንጻር ቀጤ ዘዌ ማቆም።

**ምላሽ ሰጪ፡-** እየተመለከቱት ላለ ሁኔታ ምላሽ መስጠት።

**ምልክት መስጠት፡-** ለሌሎች አሽከርካሪዎች ዓላማዎችን ለማመልከት የማዞሪያ ምልክቶችን መጠቀም።

**ምስላዊ ፍለጋ፡-** ሆን ብሎ አሁናዊ ወይም ሊሆኑ የሚችሉ አደጋዎችን መፈለግ።

**ርቀት ሳይጠብቁ መንዳት፡-** ከፊትዎ ያለውን ተሽከርካሪ በጣም በቅርበት መከተል።

**ስጋት፡-** የሆነ መጥፎ ነገር ሊከሰት የሚችልበት እድል።

**ቅድሚያ የማግኘት መብት፡-** ትራፊክ ውስጥ መጀመሪያ የመሄድ ህጋዊ መብት፤ ለምሳሌ፣ በመስቀለኛ መንገድ ላይ የሚቆም የመጀመሪያው ተሽከርካሪ ቅድሚያ የመሄድ መብት አለው።

**በስህተት መጋጨት፡-** ግጭት ሲከሰት እና በአብዛኛው ለጉዳቱ ተጠያቂው አንድ አሽከርካሪ መሆኑ ሲረጋገጥ።

**በተጽዕኖ ሥር ሆኖ መንዳት፡-** በአልኮል፣ በአደንዛዥ ዕጾች፣ ወይም በሌሎች ውሳኔ እና ቅንጅት ላይ ተጽዕኖ በሚያሳድሩ ነገሮች ተጽዕኖ ስር ተሽከርካሪን ማንቀሳቀስ።

**በትንሹ መዞር፦** ተሽከርካሪው አሽከርካሪው ያሰበውን ያህል ሳይዞር ሲቀር።

**በአንድ እጅ ማሽከርከር፦** መሪ በአንድ እጅ ማሽከርከር።

**በውሃ ላይ መንሳፈፍ፦** አንድ ተሽከርካሪ እርጥብ በሆነ መንገድ ላይ የመቆንጠጥ ችሎታ ሲያጣ እና ሲንሸራተት።

**ባህላዊ መገናኛ፦** መንገዶች በቀጤ ዘዌዎች የሚገናኙበት መደበኛ መስቀለኛ መንገድ።

**ብዙ አደንዛዥ ዕፅ መጠቀም፦** በተመሳሳይ ጊዜ ከ1 ዓይነት በላይ አደንዛዥ ዕፅ መውሰድ ወይም መጠቀም።

**ተርንኬት፦** የደም መፍሰስን ለመቆጣጠር የሚረዳ ጥብቅ መጠቅለያ።

**ተቀባይነት ያለው ስምምነት ሕግ (Implied consent law)፦** አሽከርካሪዎች በተፅዕኖ ስር ማሽከርከር ከተጠረጠሩ እንደ የአልኮል መጠጥ መመርመር የመሳሰሉ የተወሰኑ ምርመራዎችን እንዲያደርጉ የሚጠይቁ ሕጎች።

**ታርጋ፦** ተሽከርካሪውን ለህግ አስከባሪዎች እና ለሌሎች ለመለየት ጥቅም ላይ የሚውል፣ ቁጥሮች እና ፊደሎች ያሉት፣ ከተሽከርካሪው ፊት እና ጀርባ ላይ የሚገጠም የብረት ወይም የፕላስቲክ ሰሌዳ።

**ታዳጊ፦** በህግ እንደ አዋቂ የማይቆጠር ሰው ሲሆን በተለምዶ ከ18 አመት በታች የሆነ።

**ታይነት፦** በዙሪያው ያሉትን ነገሮች ምን ያህል ማየት እንደሚችሉ።

**ትራፊክ፦** በመንገዶች ላይ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች።

**ትራፊክ መቀላቀል፦** ወደ የሚንቀሳቀስ ትራፊክ መቀላቀል።

**ትኩረት የጎደለው ማሽከርከር፦** እንደ ስልክዎ ወይም ከመሪ በስተጀርባ ብዙ ተግባራትን ማማከናወን ያለ፣ ትኩረትዎን ከማሽከርከር የሚወስድ ማንኛውም ነገር።

**ትይዩ የመኪና ማቆም፦** ከመንገዱ ትይዩ በሁለት ተሽከርካሪዎች መካከል መኪና ማቆም።

**ነዋሪ ያልሆነ፦** እንደ ከተማ ወይም ግዛት ባለ አንድ የተወሰነ ቦታ ላይ በቋሚነት የማይኖር ሰው።

**ንቁነት፦** እርስዎ ይከሰታል ብለው ለገመቱት ሁኔታ ምላሽ መስጠት።

**አንግል ፓርኪንግ፦** ትይዩ ከመሆን ይልቅ መኪናን ከኩርባው አንጻር በሰያፍ ማቆም።

**እግረኛ፦** መንገድ ላይ ወይም በአቅራቢያው የሚሄድ ሰው።

**ከእጅ ወደ-እጅ መሪን ማሽከርከር፦** እጆችን ሳያጣምሩ በመሪው ዙሪያ የማንቀሳቀስ ዘዴ።

**ካርፑል፦** ተሽከርካሪው በሚንቀሳቀስበት ጊዜ በውስጡ 2 ወይም ከዚያ በላይ ሰዎች ሲኖሩ።

**ክፍት በሆነ እቃ መጠጥ መያዝን የሚከለክል ህግ (Open container law)፦** ጠጥቶ መንዳትን ለመከላከል የተዘጋጀ ህግ ሲሆን አሽከርካሪዎች እና ተሳፋሪዎች ክፍት የአልኮል መጠጦች መያዣዎችን በተሽከርካሪ ውስጥ እንዳይያዙ የሚከለክል ነው።

**ክብ አደባባይ፦** በመስቀለኛ መንገድ ላይ ያለውን ትራፊክ የሚቆጣጠር ክብ ማገጃ፤ የትራፊክ ክብ በመባልም ይታወቃል።

**ወላጅ ወይም አሳዳጊ፦**ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅን የመንከባከብ ኃላፊነት ያለው ሕጋዊ አዋቂ ሰው።

**ወደ ፊት የሚመለከት መቀመጫ፦** ወደ ተሽከርካሪው ፊት ለፊት የሚመለከት የመኪና መቀመጫ ዓይነት ሲሆን ወደ ኋላ የሚመለከቱ መቀመጫዎች ስላደጉ ለማይበቃቸው ልጆች ተስማሚ ነው።

**ወደ ኋላ ማሽከርከር፦** ተሽከርካሪን ወደ ኋላ ማሽከርከር።

**ዋቢ ማድረጊያ ነጥቦች፦** በመንገድ ላይ ያሉበትን ቦታ ለማወቅ የሚረዱ በመንገድ ላይ ያሉ መስመሮች ወይም ከተሽከርካሪዎ አጠገብ ያሉ ነገሮች።

**ውስብስብ መገናኛ/መስቀለኛ መንገዶች፦** ብዙ የመኪና መስመሮች ወይም ያልተለመዱ የትራፊክ ቅጦች ያላቸው መስቀለኛ መንገዶች።

**የሁኔታ ግንዛቤ፦** በሚያሽከረክሩበት ጊዜ አካባቢዎን ሙሉ በሙሉ የማወቅ ችሎታዎ ሲሆን ደህንነቱ የተጠበቀ የማሽከርከር ውሳኔዎችን እንዲወስኑ ይረዳዎታል።

**የልጆች የመኪና ወንበር፦** ስላደጉ የመኪና ወንበራቸው የማይበቃቸው፣ ነገር ግን አሁንም መደበኛ ቀበቶ በትክክል ለማድረግ በጣም ትንሽ ለሆኑ ልጆች የተነደፈ ልዩ መቀመጫ።

**የልጅ ደህንነት የተጠበቀ መቀመጫ ወይም የልጅ መያዣ፦** በተሽከርካሪ ውስጥ ያሉ ልጆች አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ ደህንነታቸውን ለመጠበቅ የተዘጋጀ ልዩ መቀመጫ።

**የመንጃ ፈቃድ መስጫ ጽ/ቤት (Driver licensing office)፦** ከፍቃድ አሰጣጥ ጋር የተዛመደ የደንበኞች አገልግሎት የሚሰጥበት ቦታ።

**የመንገድ መስመር መቀየር፦** ከአንድ የመኪና መንገድ መስመር ወደ ሌላ መንቀሳቀስ።

**የመራጭ ምዝገባ (Voter Registration)፦** አንድ ነዋሪ በአካባቢያዊ እና በብሔራዊ ምርጫዎች ላይ ድምጽ መስጠት እንዲችል የተመዘገበበትን ጊዜ የሚያሳይ ሰነድ።

**የመንጃ ፍቃድ፣** የተሽከርካሪ ትሮች፣ የንግድ ፍቃድ፣ ወይም ተሽከርካሪ ሲሸጡ ሪፖርት የሚያደርጉበት የመስመር ላይ አገልግሎት። License Expressን እዚህ security.dol.wa.gov ላይ ማግኘት ይችላሉ።

**የመንትዮች መዝገብ (Twin Registry)፦** ብዙውን ጊዜ ለምርምር የሚያገለግሉ የመንትዮች ስም ዝርዝር እና ስለእነሱ ያሉ አንዳንድ መረጃዎች።

**የመቆንጠጥ ችሎታ መጥፋት፦** በጎማዎች እና በመንገዱ መካከል ያለው የመቆንጠጥ ችሎታ መቀነስ።

**የመቆንጠጥ ችሎታ፦** በጎማዎች እና በመንገዱ መካከል ያለው የመቆንጠጥ ችሎታ።

**የማሽከርከር መዝገብ፦** ማናቸውንም ጥሰቶች ወይም ግጭቶችን ጨምሮ የአንድ ሰው የማሽከርከር ታሪክ መዝገብ።

**የማቆሚያ ርቀት፦** አሽከርካሪው ፍሬኑን ከተጫነበት ጊዜ አንስቶ ተሽከርካሪው እስኪቆም ድረስ የተጓዘው ርቀት።

**የማቆሚያ ቦታ፦** ተሽከርካሪ የሚቆምበት ቦታ።

**የማይታይ አካባቢ፣** ቦታ ወይም ዞን፦ በአሽከርካሪው ዙሪያ ያሉ የአሽከርካሪው እይታ የተከለለበት እና ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ማየት የማይችሉባቸው አካባቢዎች።

**የባለቤትነት የምስክር ወረቀት (Certificate of ownership)፦** የተሽከርካሪው ወይም መንቀሳቀሻው ባለቤት ማን እንደሆነ የሚያሳይ ሰነድ።

**የተሽከርካሪ ፍቃድ መስጫ ጽህፈት ቤት፦** ለተሽከርካሪ የምስክር ወረቀቶች፣ መለያዎች እና የምዝገባ እገዛ ለማግኘት የሚሄዱበት ቦታ።

**የተሳፋሪዎች ደህንነት ጥበቃ ስርዓቶች (Occupant protection systems)፦** እንደ ኤርባግ እና የመቀመጫ ቀበቶዎች ያሉ በተሽከርካሪዎች ውስጥ የሚገኙ የደህንነት ባህሪያት።

**የተሽከርካሪ አቀማመጥ፦** የተሽከርካሪው የፊት ወይም የኋላ ዘዌ።

**የተሽከርካሪ ማዘንበል፦** የተሽከርካሪ ከጎን ወደ ጎን እንቅስቃሴ።

**የተመረጠ የወታደራዊ አገልግሎት ምዝገባ (Selective Service registration)፦** ለዚህም መመዝገብ ከ18 እስከ 25 ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ የተወለደ ወንድ የሆነ ሰው ብሔራዊ ድንገተኛ ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ ለውትድርና ምልመላ ብቁ ያደርገዋል።

**የተሽከርካሪ ኢንሹራንስ፦** በግጭቶች ምክንያት ለተከሰቱ አደጋዎች ወይም ጉዳቶች ለመክፈል የሚረዳ የኢንሹራንስ ሽፋን።

**የተሽከርካሪ እንቅስቃሴዎች፦** እንደ መዞር ወይም ማቆም ያሉ በመንዳት ወቅት የሚከናወኑ ተግባራት።

**የተሽከርካሪ ምዝገባ (Vehicle registration)፦** የተሽከርካሪ ባለቤትነትን የሚያረጋግጡ ፈቃድ ያላቸው ሰነዶች።

**የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች፦** ትራፊክን ለመቆጣጠር የሚያገለግሉ ምልክቶች፣ ጠቋሚዎች እና አመልካቾች።

**የትራፊክ ፍሰት፦** ተሽከርካሪዎች በመንገድ ላይ እንዴት እንደሚንቀሳቀሱ።

**የትራፊክ ህጎች፦** ተሽከርካሪዎች በመንገድ ላይ እንዴት መንቀሳቀስ እንዳለባቸው የሚቆጣጠሩ ደንቦች።

**የትራፊክ ምልክት ቅርጾች፦** ልዩ ትርጉም ያላቸው የምልክቶች የተለያዩ ቅርጾች።

**የትራፊክ ምልክት፦** መስቀለኛ መንገድ ላይ የትራፊክ ፍሰትን የሚቆጣጠር መብራት።

**የትራፊክ ይዘት፦** በመንገድ ላይ ያለው ትራፊክ መጠን።

**የትርፊክ መቆጣጠርያ መሳሪያዎች የሌለው መገናኛ፦** የትራፊክ ምልክቶች ወይም ጠቋሚዎች የሌሉበት መስቀለኛ መንገድ።

**የአደጋ መብራቶች፦** ሌሎች አሽከርካሪዎች እና እግረኞች ወደ ተሽከርካሪው በሚጠጉበት ጊዜ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ የሚያመለክቱ በመኪናው ፊት እና ጀርባ ላይ ያሉት ጠቋሚ መብራቶች።

**የአደጋ ግንዛቤ፦** በሚያሽከርክሩበት ጊዜ ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን የመለየት እና ምላሽ የመስጠት ችሎታ።

**የአካል ክፍል ለጋሽ፦** ንቅለ ተከላ የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች ህይወት ለመታደግ ከሞቱ በኋላ የአካል ክፍሎቻቸውን ለመለገስ የተስማሙ ግለሰብ።

**የአቁም ምልክት፦** አሽከርካሪዎች ሙሉ በሙሉ ማቆም እንዳለባቸው የሚጠቁም ምልክት።

**የእንቅስቃሴ ጥሰት፡-** ተሽከርካሪው በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ህግ ከተጣሰ የሚሰጥ ቲኬት።

**የአየር ሁኔታዎች፡-** የአየር ሁኔታው ምን እንደሚመስል።

**የእውቀት መመዘኛ ፈተና፡-** አንድ ሰው ስለ ማሽከርከር ህጎች፣ ምልክቶች እና ሌሎች ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ለማሽከርከር አስፈላጊ ስለሆኑ መረጃዎች ያለውን ግንዛቤ የሚገመግም ፈተና።

**የእግረኛ ደህንነቱ የተጠበቀ ዞን፡-** ሰዎች ከትራፊክ ርቀው ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ እንዲኖራቸው ለማድረግ አሽከርካሪዎች መሄድ የማይችሉበት ቦታ።

**የክህሎት መመዘኛ ፈተና፡-** አንድ ሰው እንደ መኪና ማቆም እና ማንቀሳቀስ ያሉ ተግባራዊ የማሽከርከር ተግባራትን ለማከናወን ያላቸውን ችሎታ የሚወስን ግምገማ።

**የክሩዝ ወይም ፍጥነት መቆጣጠሪያ፡-** አሽከርካሪው የፍጥነት መስጫ ፔዳል መጫን ሳያስፈልገው የተወሰነ ፍጥነትን የሚያስተካክል መኪና ውስጥ ያለ ስርዓት።

**የገንዘብ ኃላፊነት፡-** ጉዳት ከደረሰ ለአንድ ነገር የመክፈል ተጠያቂ መሆን።

**የግብርና ፈቃድ፡-** እድሜው ከ18 ዓመት በታች ለሆነ ግለሰብ ለእርሻ ስራ የሚውሉ ትራክተሮችን እና ሌሎች ተሽከርካሪዎችን እንዲያሽከረክሩ ፈቃድ መስጠት።

**የግጭት ተሳትፎ፡-** የተሽከርካሪ ግጭት ወይም መከስከስ አካል መሆን።

**የጎን እይታ፡-** ወደ ፊት ቀጥ ብለው እየተመለከቱ ዕቃዎችን ወደ ጎን ማየት።

**የጎማ መፈንዳት፡-** በሚነዱበት ጊዜ ድንገተኛ የጎማ አየር ግፊት መቀነስ።

**የዓይን ምርመራ፡-** ምን ያህል በደንብ ማየት እንደሚችሉ እና ዓይኖችዎ ጤናማ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚደረግ ምርመራ።

**የፊት መብራቶች፡-** አሽከርካሪው ዝቅተኛ ብርሃን ባለባቸው ሁኔታዎች ወይም በሌሊት እንዲያዩ እና እንዲታዩ የሚያስችሉ ከፊት ለፊት ያለውን መንገድ የሚያበሩ በተሽከርካሪ ፊት ለፊት ያሉ መብራቶች።

**የፍሬን መበላሸት፡-** የተሽከርካሪ ፍሬኑ በትክክል መስራት ሲያቆም።

**የፍሬን መብራቶች፡-** አሽከርካሪው የፍሬን ፔዳሉን ሲጫን የሚበሩት በተሽከርካሪው ከኋላ በኩል ያሉ ቀይ መብራቶች ተሽከርካሪው ፍጥነት እየቀነሰ ወይም እየቆመ መሆኑን ለሌሎች አሽከርካሪዎች ምልክት ይሰጣል።

**የፍሬቻ መብራቶች፡-** አሽከርካሪው ወደ ግራ ወይም ቀኝ ለመታጠፍ ወይም መስመሮችን ለመለወጥ ያለውን ፍላጎት የሚያሳዩ በተሽከርካሪው ፊት እና ኋላ ላይ ያሉ ብልጭ ድርግም የሚሉ መብራቶች።

**የፍጥነት ገደቦች፦** በመንገዶች ላይ የሚፈቀደው ከፍተኛው ህጋዊ ፍጥነት።

**ዮ'ው፦** የተሽከርካሪ ከጎን ወደ ጎን እንቅስቃሴ።

**ድካም፦** በጣም የመድከም ስሜት።

**ጉጥ ያላቸው ጎማዎች፦** 'ስተዶች' የተባሉ የብረት ቁርጥራጮች ያላቸው በበረዶ ሁኔታ ውስጥ ለመንዳት የሚያገለግሉ የክረምት ጎማዎች።

**ጉዞ ወይም መንገድን ማቀድ፦** ለጉዞ የሚወስዱትን መንገድ እቅድ ማውጣት።

**ግልፍተኛ ማሽከርከር፦** እንደ በፍጥነት ማሽከርከር ወይም ርቀትን ሳይጠብቁ ማሽከርከር ያለ ንዴት የተሞላበት፣ አደገኛ ወይም ትዕግስት የሌለው የማሽከርከር ባህሪ።

**ግጭት ወይም መከስከስ፦** ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ተሽከርካሪዎች ወይም ነገሮች እርስ በርስ ሲጋጩ።

**ጎብኚ፦** ለአጭር ወይም ለተወሰነ ጊዜ በአንድ ቦታ ላይ የሚገኝ ሰው።

**ABS (Anti-lock Braking System፣ የጸረ-መቆለፊያ የፍሬን ስርዓት)፦** በእርስዎ ቁጥጥር ስር እንዲቆይ እና ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንዲያቆሙ የሚረዳዎት የተሽከርካሪ ደህንነት ባህሪ ነው።

**ADAS (Advanced Driver Assistance Systems፣ የላቁ የአሽከርካሪ አጋዥ ስርዓቶች)፦** ጣልቃ የሚገባ፣ የሚያስጠነቅቅ ወይም አሽከርካሪዎችን የሚረዳ የተሽከርካሪ ደህንነት ቴክኖሎጂ ነው።

**Department of Licensing (DOL)፦**የመንጃ ፍቃድ፣ መታወቂያ ካርዶች፣ ታርጋዎች እና የተሽከርካሪ እና የጀልባ ምዝገባዎችን የሚሰጥ የግዛት ኤጀንሲ።

**DUI (Driving under the influence፣ በተፅዕኖ ስር ማሽከርከር)፦** በአልኮሆል ወይም በአደንዛዥ ዕጾች እክል ስር እያሉ ተሽከርካሪን ማንቀሳቀስ።

**HOV (High occupancy vehicle፣** ከፍተኛ የተሳፋሪዎች ቁጥር የመያዝ አቅም ያለው ተሽከርካሪ)፦ ከውስጥ 2 ወይም ከዚያ በላይ ሰዎችን የያዙ ተሽከርካሪዎች ለማጓጓዝ የተዘጋጀ የመኪና መስመር።

**VST (Vehicle Safety Technology፣ የተሽከርካሪ ደህንነት ቴክኖሎጂ)፦** ዳሳሾችን ወይም ካሜራዎችን በመጠቀም ጣልቃ ለመግባት፣ ለማስጠንቀቅ ወይም ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ ለማሽከርከር የሚረዱዎ የተሽከርካሪ ባህሪያት።

## ተደራሽነት እና መስተንግዶዎች

DOL ተቋሞቻችንን እና አገልግሎቶቻችንን ለመጠቀም ለሚፈልጉ ደንበኞች በተጠየቀ ቁጥር ሁሉ ተገቢ የሆነ መስተንግዶ ያቀርባል።

- የእኛን ፕሮግራሞች፣ ተቋሞች ወይም አገልግሎቶችን ለማግኘት መስተንግዶ ከፈለጉ ወደ 360-902-3900 ይደውሉ ወይም በማህበረሰብ ላይ የተመሰረተ የፍቃድ መስጫ ጽ/ቤት ውስጥ ያሉ ሰራተኞች ሊረዱዎት ይችላሉ። መስተንግዶ ማግኘት ካልቻሉ ወይም የADA (Americans with Disabilities Act፣ የአሜሪካውያን አካል ጉዳተኞች ህግ) ቅሬታ ካለዎት፣ የእኛን ADA ቅሬታ አስተዳዳሪ (ADA Compliance Manager) በada@dol.wa.gov ያግኙ።
- ከእንግሊዝኛ ውጭ በሌላ ቋንቋ እርዳታ ከፈለጉ የቋንቋ ተደራሽነት ቡድናችንን በLanguageaccess@dol.wa.gov ያግኙ።
- በ1964 የሲቪል መብቶች ህግ (Civil Rights Act of 1964) ርዕስ VI ላይ በተገለፀው ጥበቃ በሚደረግለት ቡድንዎ ላይ በመመርኮዝ ከDOL አገልግሎቶችን ሲያገኙ አድልዎ ደርሶብኛል ብለው ካመኑ፣ እባክዎን ወደ እኛ የሲቪል መብቶች ተገዢነት አስተባባሪ (Civil Rights Compliance Coordinator) በCivilRtsCoord@dol.wa.gov ያግኙ።

## ማስተባበያ

የWashington ግዛት የአሽከርካሪ መመሪያ (The Washington State Driver Guide) ሕጋዊ ስልጣን የሌለው እና በፍርድ ቤት ለመጠቀም የታሰበ አይደለም። መመሪያው ለህጋዊ የይገባኛል ጥያቄዎች ወይም ድርጊቶች መሰረት ሆኖ ሊያገለግል አይችልም። በከተሞች፣ በመንደሮች እና በአገሮች ውስጥ ያሉ የትራፊክ ደንቦች ከግዛት ሕጎች ውጪ ሊሆኑ ይችላሉ፣ ነገር ግን ከእነሱ ጋር ሊጋጩ አይችሉም። ከሞተር ተሽከርካሪ ማሽከርከር እና የመንጃ ፈቃድ አሰጣጥ ጋር በተያያዙ የተወሰኑ ሕጎች ላይ ፍላጎት ካለዎት፣ RCW (Revised Code of Washington፣ የተሻሻለው የWashington ኮድ) ርዕስ 46፣ Motor Vehiclesን (የሞተር ተሽከርካሪዎች)ይመልከቱ።

በዚህ መመሪያ ውስጥ ያለው ቁሳቁስ ለትምህርት ወይም ለምርምር ዓላማዎች የታሰበ ነው። በሌላ መልኩ ካልተገለጸ በስተቀር፣ ሁሉም ይዘቶች የWashington ግዛት Department of Licensing (DOL) የቅጂ መብት ያለው ንብረት ነው። ከDOL የጽሁፍ ፈቃድ ከሌለ የዚህን ቁሳቁስ ለንግድ ወይም ፖለቲካዊ ዓላማ መጠቀም የተከለከለ ነው። በዚህ መመሪያ ውስጥ ስላለው መረጃ ጥቆማ ወይም ጥያቄ ወይም ያልተሸፈነ ሁኔታ ካለ፣ እባክዎን tse@dol.wa.gov ላይ ኢሜይል ያድርጉ።

ይህ ስራ በU.S. የቅጂ መብት ህግ (U.S. Copyright Law) የተጠበቀ ነው። የWashington ግዛት Department of Licensing (DOL) የዚህ ሥራ የቅጂ መብት ባለቤት ነው።

© የቅጂ መብት 2025፣ የWashington ግዛት Department of Licensing ሁሉም መብቶች የተጠበቁ ናቸው።